

የሀገራቸውን ድንበር ከወራሪ ለመጠበቅ በእጃቸው
የተገኘውን መከላከያ ይዘው ጎጃቸውን ዘግተው
ወጥተው ለቀሩ ኢትዮጵያውን መታሰቢያ

የኢትዮጵያውያን ዘማቾች ሰልፍ በአዲስ አበባ በመጀመሪያው ገፅ ላይ የሚገኘው ፎቶግራፍ ጦርነቱ ሲጀመር አዲስ አበባ በነበረ በእንግሊዝ አገር የደይሊይ ሜይል ጋዜጣ (Daily Mail) ፎቶአንሽ የተነሳ ነው፡፡ ከዴይሊ ሜይል ሳይብራሪ የተገኘ (በሴባስቲያን አኬሊ አማካኝነት)



# (የተደበቀው ማስታወሻ)

(የ1928-1929 ዓ.ም የኢትዮጵያና ኢጣልያ ጦርነት መዘከር)

በዶክተር ሀራልድ ናይስተሮም

የአማርኛ ትርጉም
ዶክተር ገበየሁ ተፈሪ
ደስአለኝ አለሙ

ሁለተኛ እትም
ጥቅምት 2007 ዓመተ ምሕረት
October 2014

WITH ST. GEORGE ON THE DEATH RIDE
*A Memoir of the Italian-Ethiopian war of 1935-36*
Dr. Harald Nystrom

English Translation
Dr. Thomas P. Coleman
April 2012

Amharic Translation
Dr. Gebeyehu Teferi
Dessalegn Alemu
June 2014

ሁለተኛ እትም ጥቅምት 2007
Second edition October 2014
Signature Book Printing, www.sbpbooks.com

በዚህ በሁለተኛው እትም የትርጉሙ ፅሁፍ ላይ ከፊደላት እርማት በስተቀር ምንም አይነት ለውጥ ያልተደረገ ሲሆን ለፅሁፉ ምስክርነት የሚሆኑ ሌሎች ተጨማሪ መረጃዎችን በመፅሐፉ ውስጥ የጨመርን መሆኑን ለማስታወቅ እንወዳለን። በኛ በኩል የቀረቡ ተጨማሪ ማብራሪያዎች በገፆች ግርጌ ሠፍረዋል። ብዙ አንባቢዎች የለገሡንን ምክር በመስማት ሽፋኑ ላይ የመፅሐፉን ይዘት ለመግለፅ ተጨማሪ ፅሁፎችና ምስሎች ጨምረናል። ስለዚህ ከዚህ ቀደም በመጀመሪያው እትም በሞት ጉዞ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ጋራ በሚለው የመፅሀፉ ርእስ ላይ ተጨማሪ ገላጭ ርዕስ መጠቀማችንም ለመግለፅ እንወዳለን። በዚህ መፅሀፍ ውስጥ የሚገኙ ፎቶግራፎችና ምስሎች ከፀሐፊው ፎቶግራፍ ውጭ በተርጓሚዎች የተሰበሰቡና የተዘጋጁ ናቸው። የመፅሀፍ ሽፋን ዲዛይን በገበየሁ ተፈሪ

Copy right © 2014 by Gebeyehu Teferi & Dessalegn Alemu
የገበየሁ ተፈሪና ደስአለኝ አለሙ መብት በህግ የተጠበቀ ነው በጽሑፍ በተሠጠ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር መፅሐፉን በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተም መቅዳት መባዛት ወይም መተርጎም አይቻልም።
All rights reserved including the right of reproduction in whole or in part in any form.

Chibo Light Book
ISBN 9780692268933
Second Edition
www.chibolight.com
Info@chibolight.com



ለ/To ____________________

____________________

____________________

ከ/From ____________________

# ምስጋና

የእንግሊዝኛውን ፅሁፍ (With St. George on the Death ride) ወደ አማርኛ እንድንመልስ ስለፈቀዱልን ለጁዲት እና ክርስቲን ፒተርሰን ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን

ተጨማሪ መረጃዎችን እንድናገኝ ለተባበሩን የላይብራሪ አፍ ኮንግሬስ ባልደረባ (Library of Congress) ለሆኑት ለአቶ ፋንታሁን ጥሩነህ ከልብ ምስጋና እናቀርባለን

በዳባት ከተማ በሌሎችም ቦታዎች የሚገኙ መረጃዎችን ለማግኘት ለረዱን ለወይዘሮ ላንችስል አለሙ ምስጋና እናቀርባለን

ለመፅሀፉ ታላቅ ድጋፍ የሀሳብና ሌሎችም ርዳታ ላደረጉልን ለፕሮፌሰር ሀይሌ ገሪማ ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን

መፅሐፉን በሚመለከት ላበረታቱንና ለረዱንና ጠቃሚ ምክሮችን ለሰገሡን በሙሉ ምስጋና እናቀርባለን

የመጀመሪያውን የመፅሐፍ ግምገማ በመኖሪያ ቤታቸው ላዘጋጁት የቅርብ ጓደኞች ከፍተኛ ምሥጋና እናቀርባለን።

ከሁሉም በላይ ግን እንደዚህ አይነት ዘገባ በማስቀመጥ ታላቅ አስተዋፅኦ ያደረጉት ፀሐፊው ዶክተር ሀራልድ ናየስተሮምን በራሳችን በመላው አንባቢ እና በኢትዮጵያውያን ስም እናመሰግናለን

የስዊድንኛ ቋንቋውን ወደ እንግሊዘኛ በመመለስ ይህንን ያልታየና ያልተሰማ ፅሁፍ ለአማርኛ አንባቢዎች እንድናቀርብ ትልቅ ምክንያት ለሆኑት ለዶክተር ቶማስ ፒ ኮልማን በራሳችን በመላው አንባቢ እንዲሁም በኢትዮጵያውን ስም ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን

በዚህ እትም ለታሪኩ ከፍተኛ ማስረጃ ሆነው የተገኙ ፎቶግራፎች የተገኙት ሴባስቲያን አ ኬሊ ከፃፉት መፅሐፍ ነው። ሴባስቲያን አ ኬሊ (Sebastian O'Kelly) ደግሞ ያለምንም ማመነታታት ፎቶግራፎችን እንድንጠቀም ስለፈቀደሉን ጥልቅ ምስጋና እናቀርባለን

ከጎናችን በመሆን በማበረታታት ለረዱን ለባለቤቶቻችን የልብ ምሥጋና እናቀርባለን

ዶክተር ገበየሁ ተፈሪ
አቶ ደስአለኝ አለሙ



# ከተርጓሚዎች

*ማን ያውራ የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ*

እንደሚባለው እንደዚህ ጥርት ያለ በቀናትና በሰአታት የተደገፈ በቦታው በነበረ ሰው የተፃፈ ማስታወሻ ማግኘት ቀላል አይደለም።

በመጀመሪያ እንዲህ አይነቱ ፅሁፍ ለአንባቢ እስካሁን ሊደርስ ያልቻለበትን ምክንያት ወይም ለምን አሁን የሚለውን ጥያቄ መመለስ ተገቢ ነው። የማስታወሻው ባለቤት ፀሀፊው በስዊድን ቋንቋ ከዚህ በፊት በ1938 (እኤአ) አሳትመው ከዚያ ወዲያ ግን ዶክተር ሀራልድ ናየስተሮም በሕይወት እያሉ ፅሁፉ በእንግሊዝኛም ሆነ በአማርኛ እንዳይተረጎም ክልክለው ከሞቱ በኋላ ግን ፅሁፉ ለአንባቢያን እንዲደርስ ስለፈቀዱ ነው። ፀሐፊው ይህንን የመሰለ ዘገባ ለአንባብያን እንዳይደርስ ያደረጉበት ለኛ ግልፅ ባይሆንም በቂ ምክንያት ነበራቸው። ስለዚህ ፀሐፊው ከሠጡት ርዕስ መውጣት ባንፈልግም ለፅሁፉ ተስማሚ ገላጭ ቃል "የተደበቀው ማስታወሻ" የሚል ተደራቢ ርዕስ ሰጥተነዋል።

ዶክተሩ በሞት ሲለዩ ጓደኞቸው ዶክተር ኮልማን ፅሁፉን ወደ አንግሊዝኛ ተርጉመው ያጠናቀቁት እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ2012 ነበር። እንግዲህ ፀሐፊው ለምን ፍራቻ እንዳደረባቸው ከፅሁፉ መረዳት ተገቢ ነው። ዶክተር ናየስተሮም የአማርኛ ቋንቋን በደንብ ይናገሩና ይፅፉ ስለነበር በጊዜው የተደረገውና የተነገረውን ነገር ያለምንም አስተርጓሚ እንዳለ ማስቀመጣቸው ሌላው የፅሁፉ ጠቀሜታ ነው።

በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል ስለተደረገው ጦርነት ብንሰማም ምን አይነት ባህሪ እንደነበረው ከዚያም ከውጊያ አልፎ ጭፍጨፋ ላይ ያተኮረና ያጋደለ ጦርነት መሆኑን ምን ያህል ሰው በውል ያውቅ ይሆን? እኚህ ሰው ወደ ጦር ሜዳ ግንባር ተጉዘው በቦታውም ሆነው የፃፉት ስዕላዊ አገላለጥ ትልቅ የታሪክ ቅርስ ነው።

አንባቢዎች ወደፊት እንደሚረዱት ፀሐፊው ሚዛናዊ የሆነ አቀራረብ ነው ያላቸው። ደግሞም ግን በጊዜው ያዩትና የሰሙትን ነው የፃፉት። ፈሪውን ከጀግናው ጋራ፤ ተንኮለኛውን ንፁህ ልቦና ካለው ሰው ጋራ እኩል ነው ያቀረቡልን።

ሌላው የዚህ ማስታወሻ አቢይ ነገር "አያሌው ሞኙ ሰው አማኙ" እየተባለ እስካሁን ድረስ የሚዘፈንላቸውን ደጃዝማች አያሌው ብሩን ከጎናቸው አብረው ውለው አድረው ያሰፈሩት ማስታወሻ ለአያሌው ሞኙ መዘፈን ምክንያት ከደጃዝማቹ ከራሳቸው እንደበት የሰሙትን መረጃ ይጨምራል።

እንግዲህ ፀሀፊው የሰዎችን ስሞች እየጠቀሱ በዚያን ጊዜ የተደረገውንና የተባለውን ያዩትንም በመዘገባቸው ደጉንም ከፋውንም ለይተው በማፃፋቸው ለብዙ ስማቸው ለተጠቀሱ የዚያን ጊዜ ከፍተኛ የኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች ቤተሰቦችን ቅር ሊያሰኝ የሚችል ነገር ሊኖር እንደሚችል ይገባናል። ሆኖም መተርጎም እንጂ ማብራራት ወይም ሌላ ጭማሪ ስልላተደረገበት የሆነውን መቀበል የግድ ነው።

በተጨማሪም ታሪክ ወይም ያለፈ ማስታወሻ ሰዎች እንዳያዝኑ ወይም እንዳይቀየሙ ተብሎ የሚዛመም ከሆነ ከእውነታው ይርቃል። ልጅን ሲወዱ ከነ እንትኑ እንደሚባለው ታሪክን ሲቀበሉ ደግሞ ከነእውነታው መሆን አለበት።

ማስታወሻነቱ ደግሞ በዚያን ጊዜ ለነበረው ብቻ ሳይሆን በዚያን ጊዜ ለተሰራው ድርጊት በኋላም ለወደኋላ ለታየው ሁኔታ መንስኤ ጥቆማ ያበረክታል። እያንዳንዱ አንቀፅ በፅሞና ሊነበብ የሚገባው ማስታወሻ ነው። አቀራረቡ ስእላዊ መግለጫ ስለሚሠጥ አንባብያንን እንደሚመሥጥ እርግጠኛ ነን።

ትርጉም ስለሆነ እንደተፃፈውና የማስታወሻው ባለቤት ሊገልጡት እንደፈለጉት አድርገን አቅርበናል። በፅሁፉ ውስጥ ግን አንዳንድ የቃል አጠቃቀሞችን የግድ መቀየር ተገደናል። ለምሳሌ ባሪያ ወይም ባሪያዎች የሚለውን ቃል በአገልጋዮች መተካታችን ለአንባብያን ማስታወስ እንወዳለን።

ፈሪዎችንና ተንኮለኞችን እንደዘገቡት ሁሉ በማስታወሻቸው ያሰፈሯቸው የኢትዮጵያውያን ተዋጊዎች ስዕላዊ አገላለፅ ለምናውቀውና ለሚነገርለት የኢትዮጵያውያን ጀግንነት በቂ መረጃ ነው። ጀግንነቱ ደግሞ ከተራው ሰው አስከባላባቱና ካህናቱንም ጨምሮ ነው። የተዋጋው የኢትዮጵያ ወገን ከየቦታው ክተት ብሎ የወጣ ነው። ጎጇቸውን ዘግተው ሴትና ልጆች ባሎቻቸውን አባታቸውን ቢቆሰል ሊያስታምሙ ቢሞት ደግሞ ሊቀብሩ ተከትለው ወጥተዋል። በማስታወሻው የከምባታ ተወላጆች የሰሩትን የጀግንነት ሥራ ማንበብ የሚያኮራ ሆኖ አግኝተነዋል።



ይህ ማስታወሻ ለታሪክ ባለሙያተኞች መነጋገሪያ ርዕሶችም ይዟል ብለን እናምናለን። ከራሳቸው ከደጃዝማች አያሌው ብሩ ጀምሮ እስከ ንጉሡና በእሳቸው ስር ለነበሩ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች ሚና አንድ ነገር ሲሆን፤ በየክልሉ ገበሬውና ሌላው ተራ ሰው ያደረጋቸው ነገሮች ደግሞ ሌላ ጉዳይ ነው። ከጀግንነቱ ጋር ከህደቱ ድንቁርናውም ሆነ የዋህነቱ አብሮ ተገልጧል።

ሌላው አንባቢን የምናሳሰበው ነገር ቢኖር ባለፈ ታሪክ ዳኝነት መስጠት ተገቢ ባይሆንም አስተያዬትና ትችት ግን የማይቀር ነገር ነው። ስለዚህ አንብበው እስኪጨርሱ ድረስ በተለይ አንድን ወገን ከሌላው ለይቶ ለመተቸት እንዳይቻኮሉ ነው። ደጉና ከፋው በየቦታው ነው የታየው።

እስጀምሮ ላስጨረሰን አምላክ ምስጋና ይግባው

ገበየሁ ተፈሪ
ደስአለኝ አለሙ




1. የሰሜን ጦር ግንባር አሰላለፍ ካርታ ፀሀፊው የሸፈናቸውን ቦታዎችና የጉዞ አቅጣጫ መረዳትም ያስችላል::



# ምዕራፍ አንድ

## የታላቅ ሰው ህመም

ጥቅምት 20 እኤአ 1935(በኢትዮጵያ አቆጣጠር 1928 ዓ.ም) ጥሩ የእሁድ ከሰአት ቀን ነበር:: በኢትዮጵያና በኢጣልያ መሀከል የሚደረገው ጦርነት ሁኔታ እየገፋ ነው ቢሆንም ለኛ ብዙም ስሜት ሳይሰጠን በአዲስ አበባ በዶክተር ሀነር የሚያምር ቅጥር ግቢ በሥስነስርአት በተዘጋጀ የቡና ጠረጴዛ ዙሪያ ከበን ቁጭ ብሰናል:: መንግስተ ሰማያት ከመሰለው ሰማያዊው ሰማይ የአፍሪካ ፀሀይ ታንፀባርቃለች:: ግቢው የተለያየ ቀለም ባላቸው በተተከሉ አበባዎች ተውቧል:: የተቀመጥንበት ወንበር ምቾትን ጨምሮ የቀረበው ቡናና ኬክ ጣዕም ነበረው::

ንግግራችን እንደተለመደው ስለ ጦርነቱና ስለሚያስከትለው አስከፊ ውጤት ስለሚፈጠረው ሽብር ነበር:: ሁላችንም የሊግ ኦፍ ኔሽንስ[1] በአስቸኳይ መፍትሔ እንደሚያገኝለት ተማምነናል ቢያንስ ተስፋም አድርገን ነበር:: የዋህ ቅን ሀሳቢ ስለሆን እንጂ ስለሚመጣው ትልቅ ነውጥ፤ ስለሚያልፈው ህይወትና ስለሚጠፋው ንብረት፤ እኛን ራሳችን ጨምሮ ስለሚደርስብን መከራ ትንሽም ቢሆን ሀሳቡ አልነበረንም::

ሰው ያስባል እግዚአብሔር ይፈፅማል::

ድንገት ከበር በኩል ትልቅ ባለሥልጣን ሰው ወደ ግቢው ሲገቡ አየን:: የአቢሲኒያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ብላቴን ጌታ ህሩይ ናቸው:: ፊታቸው የህፃን ልጅ አይነት ከብነት ያለው ሲሆን ፀጉራቸው ነጭና ሉጫ ነው ከአግራቸው በኩል ወደ ደጋንነቱ ያጋድላል:: ወዲያው እንዳየሁዋቸው እኔን ፈልገው እንደመጡ ገመትኩ::

ትክክል ነበርኩ:: ትንሽ አረፍ ብለው ቡና ከጠጡ በኋላ ስለመጡበት ጉዳይ መግለፅ ጀመሩ:: መልክታቸው ከንጉሡ የመጣ ነው፤ የተጠየቅሁትም በሚቀጥለው ቀን ወደ ሰሜን ግዛት ዋና ከተማ ወደ ዳባት በአውሮፕላን

---

1 (League of Nations) በዚያን ጊዜ የነበረው የአለም መንግሥታት ማህበር

መሄድ የምችል እንደሆን ነው:: ስመ ጥሩው ደጃዝማች አያሌው ብሩ ታመዋልና የህክምና እርዳታ ያስፈልጋቸዋል::

ቶሎ የህክምና እርዳታ ተደርጎላቸው በሰሜን ግንባር ወደ ጦርነት እንዲሄዱ ይፈለጋሉ:: የአቢሲኒያው ንጉሥ ጃንሆይ (አፄ ኃይለ ሥላሤ) መልስ ስለሚጠብቁ ቶሎ መልስ መስጠት ነበረብኝ::

ወዲያውኑ አወጣሁ አወረድኩ ጥያቄው ከጃንሆይ ስለመጣም መልስ በቶሎ መስጠት ነበረብኝ:: ነገሩ ጥሩ አጋጣሚና የሚያጓጓ ሆኖ እንዳገኘሁት ማሰቤን መደበቅ አልችልም:: የስድስት መቶ ኪሎሜትር ርቀት ያለውን ቦታ በአውሮፕላን መብረር፤ በአውሮፕላን መብረርም የመጀመሪያዬ ስለሆነ በተጨማሪም ከዚህ ቀደም ያላየሁትን ምዕራባዊ የሰሜኑን የአቢሲንያን ክፍል ማየትም የማይገኝ ጥሩ አጋጣሚ ስለነበረ ነው:: ተጨማሪ ገንዘብ የማግኘት ሁኔታም የሚጠላ አይደለም:: በጎን በኩል ደግሞ የመረበሽ ስሜት ተሰማኝ:: የሄድኩበትን ጉዳይ ከጨረስኩ በኋላ አስታውሰው ይመልሱኝ ይሆን ወይስ እዛው ጫካ ጥለውኝ ለረዥም ጊዜ እቆይ ይሆን ብዬ አሰብኩ:: እንደዚህ ለማሰብ ደግሞ በቂ የሆኑ ብዙ ምክንያቶች ነበሩኝ::

መጀመሪያ ለዚህ አይነት አደጋ ላለበት ሥራ የገንዘቡን ጉዳይ ግልፅ አድርጎ መነጋገር ወይም መጨረስ አለብኝ ብዬ አሰብኩ:: ለዚህም ዕጥፍ እንዲከፈለኝ እና የሕይወት መድህን ወይም ኢንሹራንስ እንዲኖረኝ መጠየቅ ተገቢ ነበር:: ከልምድ በመነሳት ግን ከሀበሾች ጋራ ኮንትራት ሲዋዋሉ ለመከራከሪያ እንዲሆን ዋጋን ከፍ አድርጎ መጥራት የተለመደ በመሆኑ የሚከፈለኝን ሂሳብ በሶስት ዕጥፍ ከፍ ለማድረግ አሰብኩኝ:: ብላቴን ጌታ ከተቀመጡበት ወንበር ትዕግሰት አጥሯቸው በመቁነጥነጥ ጃንሆይ ቁጭ ብለው መልሴን እንደሚጠብቁ አስታወሱኝ::

ዶክተር ህነርን ምክር ጠየቅሁት:: የበረራ ልምድ ስላለው በአውሮፕላን መብረሩ የሚያስደስት አጋጣሚ መሆኑን እርሱ ራሱ ይህንን አጋጣሚ ቢያገኝ የሚቀበለው ሀሳብ ነው:: ነገር ግን በአጠቃላይ ሌላም ሰው መረዳት እንደሚችለው በእንደዚህ አይነቱ የግል ውሳኔ ጉዳይ ምክር መስጠት አልፈለገም:: ስለሆነም ለውጭ ጉዳይ ሚኒሰትሩ ጉዞውን የሚከተሉት ነገሮች ከተሟሉ የምቀበለው ነገር መሆኑን በአግባቡ ገለፅኩላቸው::

መሟላት ያሉባቸው ነገሮች

አንደኛ የምወስዳቸው የሚያስፈልጉኝ መድሃኒቶች እንዲዘጋጁ



ሁለተኛ ደጃዝማች አያሌው እንደተሻላቸው ወድያውኑ የምመለስበት አውሮፕላን እንዲላክልኝ

ሶስተኛ ደግሞ ክፍያዬ በሶስት እጥፍ እንዲሆንና ለቤተሰቦቼም ማስተማመኛ ኢንሹራንስ እንዲሰጣቸው ነው::

ጠቆር ብሎ የነበረው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ፊት ፈካ አለ:: ጉዞውን ለማድረግ በመስማማቴ አመስግነውኝ ከመቀመጫቸው ተነስተው እንደቆሙ ካቀረብኩት ጥያቄዎች ቁጥር አንድና ሁለት እንደሚሟሉ ቃል ገቡልኝ::

ደጃዝማች እያሌውን ያመማቸውን ነገር ማወቅ ፈልጌ ብጠይቅም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ምንም የሚያውቁት ነገር እንዳልሆነ ነው የተገነዘብኩት:: ሚኒስትሩ ከታማሚው ጋራ በስልክ የተገናኙ ቢሆንም መታመማቸውን ብቻ ማወቅ እንጂ ተጨማሪ ነገር የዶክተር ችግር እንጂ የሳቸው አለመሆኑን ነው የተገለፀው:: እንደሚኒሰትሩ አገላለፅ ሀኪም ስለበሽተኛው ሁኔታ አስቀድሞ ማወቅና የሚያስፈልገውን መድሃኒት ማዘጋጀት እንደሚኖርበት አልታያቸውም:: ፋርማሲ ያለው ደግሞ ከዳባት 600 ኪሎሜትር ርቀት በአዲስ አበባ ብቻ ነው:: ይህም በጊዜው በነበሩ የአቢሲኒያ ባለሥልጣኖች በየጊዜው ከሚታዩ እርቆ ከማሰብ ጉድለት ከሚፈጠሩ ሁኔታዎች አንዱ ነው::

ሶስተኛውን ጉዳይ በሚመለከት ግን ሚኒስትሩ ራሳቸው ጃንሆይን አማክረው የሚደረግ ነገር መሆኑን ነገሩኝ:: ለመከራከሪያ እንዲሆን ብዬ ሁሉንም ከፍ አድርጌ ስለጠየቅሁ የሚወሰነው የመጨረሻ ውሳኔ ለኔ የሚጠቅም ትክክለኛ ይሆናል::

በነጋታው የአየር በረራ እንደማይኖርም በደንብ ተረድቻለሁ ምናልባትም ከሳምንት ካለዛም ከወር በኋላ ሊሆን ይችላል:: ግን አሁን ጊዜው ለወጥ ስላለ ከአንድ አራት ቀን በኋላ ሊሆን እንደሚችል ገመትኩ:: እንዳልኩትም ሊሆን ነው:: ለጉዞው ራሴን ሳዘጋጅ በዚህ በሰሜን ክፍል ለትንሽ ቀናት እንደምቆይ አድርጌ ነው:: ከመንግስት ጋር የተዋዋልኩበትን ይህን ሥራ እንዳከናውን የሚያስፈልጉኝን የህክምና መሳሪያዎችና የመድሃኒቶችን ዝርዘር ሰጠሁ::

የደጃዝማች አያሌው ህምም እንደተሰማ በጊዜው በአዲስ አበባ በነበሩት መቶ አምሰት የውጭ ጋዜጠኞች ያለ የሌለ ወሬ ይዛመት ጀመር:: እኔ ራሴም ስለ ህመማቸው የማውቀው ጉዳይ የለም ብዬ መግለጫ ብሰጥም ደግሞ ደጋግሞ ቃለ መጠየቅ ከማድረግ አላደነኝም:: ጋዜጠኞቹ ለየጋዜጣቸው

በተረጋጋ ሁኔታ ስለ ደጃዝማች አያሌው ቴሌ ግራም ያደርጋሉ፡፡ በቴሌ ግራማቸው ደጃዝማች አያሌው ከኢጣልያ ጋራ በተደረገው በመጀመሪያው ጦርነት በጣም ስለቆሰሉ ዶክተር በአውሮፕላን ሊላክላቸው ነው የሚል ነበር፡፡

እንደእውነቱ ከሆነ ደጃዝማች አያሌው ከጦርነቱ ግንባር ሁለት መቶ ኪሎ ሜትር ርቀት ነው ያሉት፡፡ እንዲህ አይነቱ ያልተረጋጋጠ ውሸት ወይም ወሬ ሲወራ ማንም ሰው ሊረዳው እንደሚችለው ሃበሾችን ማናደዱ አይቀርም፡፡ ሁለት ጊዜ በጦር ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ተጠርቼ ምን ብዬ እንደተናገርኩ ተጠየቅሁ፡፡ በሁለቱም ጥያቄ ጊዜ አስቸጋሪ ይሁን እንጂ በኔ በኩል እንደዚህ አይነት ሃሜታ እንዳልተናገርኩ በመንገር አረጋግቻለሁ፡፡ ያም ሆኖ ሰላዮች እየተላኩ የማደርገውንና የምናገረውን ነገር ይከታተሉ ነበር ከዚያም አልፎ የግል ሠራተኞቼ በሚሥጥር ይጠየቁ ነበር፡፡

ስለጉዞው ሁኔታ የሚገልፅ ምንም አይነት ዜና ሳይኖር ቀናቶች አለፉ፡፡ እኔም እንግዲህ በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት ጉዞው ተሠርዟል ማለት ነው፡፡ እንደዚህ ከሆነ ደግሞ ጥሩ ሁኔታ ላይ አይደለሁም ብዬ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ ለሰባት አመታት በታማኝነት በአገለገልኩት መንግስት አልታመንም ማለት ነው የሚለው ሀሳብ ሲሰማኝ ደግሞ ያስጨንቀኝ ጀመር፡፡ በዚህ ምክንያትም ጥቅምት ሀያ ሶስት ቀን ከሰአት በኋላ በጓደኞቼ በተደረገለኝ ግብዣ ለመገኘት ወደ ኢምፒሪያል ሆቴል ሳመራ ደስተኛ አልነበርኩም፡፡


የአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ።

ማስታወቂያ ።

ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ጉዳይና ፡ በጦርነቱም ፡ ዘመቻ ፡ ምክንያት ፡ ኦፊሲዬል ፡ ያልሆነ ፡ የፖለቲክ ፡ ነገር ፡ ማውራትና ፡ መነጋገር ፡ በፍጹም ፡ ተከልክሏል ።

(፩) ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ ተላልፎ ፡ የፖለቲክ ፡ ነገር ፡ ሲያወራ ፡ የተገኘ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ጥፋቱ ፡ መጠን ፡ እየታየ ፡ ከ፶ ብር ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ሺ ፡ ብር ፡ ይቀጣል ፡ ወይም ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሲሆን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ የእድሚኒስትራሲዮን ፡ ደንብ ፡ ይፈጸምበታል ።

(፪) ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተመለከተው ፡ የተከለከለውን ፡ ነገር ፡ ሲያወራ ፡ የተገኘውን ፡ ሰው ፡ በግልጽ ፡ ከሶ ፡ ወይም ፡ በስውር ፡ ለባለሥልጣን ፡ አስታውቆ ፡ ነገሩን ፡ በሚገባ ፡ ለሚያስረዳ ፡ ሰው ፡ [illegible] ገንዘብ ፡ እኩሌታው ፡ ይፈቀድለታል ።

[illegible]

P 2

የአዲስ ፡ አበባ ፡ [illegible] ።

በወቅቱ ጦርነቱን አስመልክቶ በመንግሥት ከወጡ ማስታወቂያዎች አንዱ



መንገድ ላይ እያለሁ የቆንስላችን መኪና ድንገት ደረሰብኝ፡፡ ሾፌሩ በየቦታው እየተፈልግሁ እንደሆነና በአስቸኳይ ወደ ሆስፒታል ሄጄ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን ማግኘት እንዳለብኝ ነገረኝ፡፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላም ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከብላቴን ጌታ ህሩይ ፊት ቁጭ አልኩ፡፡ ሁሉም ነገር ስለተዘጋጀ በነጋታው መብረር እንዳለብኝ ተነገረኝ፡፡ መድሃኒቶች አውሮፕላኑ ወስጥ ተጭነዋል የቀረ ነገር ቢኖር ውሉን መፈራረም ብቻ ነው፡፡

ወረቀት እውጥተው ንጉሡ እየጠበቁ ስለሆነ በአስቸኳይ እንድጨርስ ትዕዛዝ ሰጡኝ፡፡ የችኮላው ምክንያት ገብቶኛል፡፡ ነገር ግን የውሉን ፅሁፍ በጥርጣሬ ተመለከትኩ፡፡ ሁሉም ነገር እንደጠየቅሁት የተፃፈ ሲሆን ያው የገንዘብ ክፍያው ጉዳይ ግን እንደጠየቅሁት አይደለም፡፡ ለመከራከር እንዳይመችም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ስም ያለበት ማህተም አርፎበታል፡፡

እኔም ራሴ ቢሆን ተጨማሪ ወይይት ወይም ክርክር ለማድረግ አልተዘጋጀሁም፡፡ ወዲያውኑ ፊርማዬን ሰጥቼ ወደ ሆቴሉ አመራሁ፡፡ በሆቴሉም የክብር እንግዳ እንደመሆኔ በተዘጋጀው የመስነባበቻ ግብዣ ላይ ተገኝቼ ተቀመጥኩ፡፡ የታወቀ የሲኒማ ካምፓኒ ዳይሬክተርና የኖርዌይ ተወላጅ የሆነቸው ባለቤቱ እኔን ለማስደሰት ያዘጋጁት ያማረ ግብዣ ነበር፡፡ ስለተደሰትኩም የነበረኝ መጥፎ ስሜት ሁሉ ለቀቀኝ፡፡ ይህ የአዲስ አበባ የመጨረሻ ምሽት ቢሆንም ለወደፊት ለረዥም ጊዜ ለሚመጣውና ለሚሆነው ነገር ሁሉ በዚህ ደስ በሚል ሁኔታ ተጀመረ፡፡




በአዲስ አበባ የደጃዝማች አያሌው መኖርያ ቤት(በፋሲል ጊዮርጊስ መልካም ፈቃድ )from the book: The City & Its Architectural Heritage by Fasil Ghiorgis and Denies Gerard

# ምዕራፍ ሁለት

## ወደ ሰሜን

ከጠዋቱ አስር ሰአት ተኩል ሲሆን ተነሳሁ ሻንጣዬን ከሞላሁ በኋላ በተጨማሪ ታጣፊ አልጋና የመኝታ ከረጢት ወይም (ስሊፒንግ ባግ) ያዝኩ። ይህንን ብቻ ነው ለመውሰድ የወሰንኩት። አንድ ስኒ ቡና ከጠጣሁ በኋላ ለሠራተኞቼ የቤት እቃዎቼን ፈረሶቼን ሌሎችንም ነገሮች ጨምሮ እንዲጠብቁ ትዕዛዝ ሰጠሁ። በሃሳቤ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደምመለስ ነው። ነገር ግን ትንሽም ቢሆን ያላወቅሁት ነገር እነዚህን በቤቴ ውስጥ ለረዥም ጊዜ የተቀመጡና ብዙ የቤተሰብ ትዝታ የሚያስታውሱኝን ንብረቶቼን ተመልሼ እንደማላያቸው ነው። እንዲያውም ቶሎ እንደምመለስ እርግጠኛ ስለነበርኩ ንብረቴን በጥሩና በማያሰጋ ቦታ ለማስቀመጥ ሙከራም አላደረግሁም።

ነገር ግን ንብረትን የማያሰጋ ቦታስ ለማስቀመጥ ቦታው የት ነው የሚገኘው? ከተማው ሲበዘበዝ በቦታው የነበሩ ሰዎች እንኳን አይናቸው እያዩ ቤትና ንብረታቸው ወድሟል። ለማንኛውም ይህ የሌላ ጊዜ ታሪክ ነው።

ሁሉም ከተዘጋጀ በኋላ መኪና እስኪመጣልኝ ድረስ አሥራ አምስት ደቂቃዎች ነበሩኝ። በዚህ ቆይታ አእምሮዬ ስለጉዞው በሀሳብ ይራወጥ ጀመር።

የመጀመሪያ አውሮፕላን በረራዬ እንዴት ይሆን? ምንያህል ጊዜ ይወስድስ ይሆን? ጠቅላላ ሁኔታውስ ምን ይሆን? ድንገት የአየር በረራውን ካልቻልኩት ብዬ ደርዘን የሚሆኑ የወረቀት ከረጢቶችም ይዣለሁ።

አደጋስ ይደርስብን ይሆን? ወይም ደግሞ የኢጣልያ አውሮፕላኖች አግኝተው ተኩሰው ቢጥሉንስ? እያልኩ መኪና መጥቶ አውሮፕላን ማረፊያው እስኪወስደኝ ድረስ በአእምሮዬ ምስል እየፈጠርኩ ስተራመስ ነበር። አውሮፕላን ማረፊያው ቦታ እንደደረስንም የሚያንፀባርቅ አልሙንየም ሽፋን ያለው ጃንከር አውሮፕላን ሞተር ድምፁን እያሰማ መንደርደሪያው ላይ



ቆሟል። ሌላም ተጨማሪ እድሜው የገፋ የፈረንሳይ ፖቴዝ አውሮፕላን ቆሟል።

ሰኔ መሆኑን ተረዳሁና ወደ ጃንከሩ ፓይለት ዌበር ይባላል ሄጄ ሰላምታ ተለዋወጥን። እሱም "አየሩ ጥሩ ነው አውሮፕላኔም በጥሩ ሁኔታ ነው ያለው" ብሎ ነገረኝ። አጅቦን የሚሄደው ፖቴዝ አውሮፕላን ጉዳይ ግን ሌላ ነው። መነሳት አልቻለም። አምስት ሰዎች ተረባርበውበት ከግማሽ ሰአት በኋላ ተነሳ።

ሁለቱም አውሮፕላኖች ከሚጠበቀው በላይ ጭነት ተጭነዋል። እኔ ያለሁበት አውሮፕላን እኔን ፓይለቱንና መካኒኩን ጨምሮ አራት የህክምና መሳሪያና መድሃኒቶች የያዙ ሳጥኖች፤ አራት አውቶማቲክ መሳሪያዎች (መትረየስ) እና ስድስት ሺህ ጥይቶች ይዟል። ሌላኛው አውሮፕላን ደግሞ ፓይለቱንና *ድሬሰሩን አራት መትረየስ ከስድስት ሺ ጥይቶች ጋር ሲይዝ በተጨማሪ የመቀስቀሻ ወረቀቶች ጭኗል። የሚበተኑ መቀስቀሻ ወረቀቶች በአማርኛ ስለ ጦርነቱ፤ ስለ አየር ቦምብና ጋዝ፤ ስለታንክ ምንነትና ሌሎችንም ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎች ሁኔታ የሚገልፅ ፅሁፍ ነው ያለባቸው።

ሁላችንም ቦታ ቦታችን ከያዝን በኋላ አውሮፕላኖቹ እንዲበሩ ምልክት ተሠጠ። በሜዳው የነበሩ ጓደኞች በመሰናበት እጃቸውን አወዛወዙ ከነሱም መሀል ሆስፒታል አብውረኝ የሚሰሩ ሁለት ስዊድናውያን ነርሶች ነበሩበት።
የኛ አውሮፕላን ከተነሳ በኋላ ቀርፋፋው ፖቴዝ እስኪነሳ ድረስ በሜዳው ዙርያ እያንዣበብን ቆየን ከትንሽ ጊዜ በኋላ ፖቴዙም ተነሳና ሁላችንም ወደ ሰሜን አቅጣጫ መብረር ጀመርን።

አጃቢያችን ፖቴዝ አውሮፕላን ፈጣን መሆኑን በማሳየት የ3500 ሜትሮች ከፍታ እየወጣን እያለ መንገዱን ለማሳየትም ሆነ ከኢጣልያ አውሮፕላኖች ለመከላከል ከኛ ቀደም ብሎ መብረር ጀመረ። የእንጦጦን ጋራ ወድያውኑ ወደኋላችን ትተን የሱሉልታ ሰፊና ለም ቦታ ከሥራችንና ከፊት ለፊት መታየት ጀመረ። ወርቃማ በመሰሉ የሰብል እርሻዎችና አረንጓዴ ሜዳዎች በጥዋቱ ፀሐይ ብርሃን ምክንያት ብርማ ቀለም የሚያሳዩ ወራጅ ውሀዎች በመሃላቸው ሲፈሱ ይታያል።

ከሩቁ በምሥራቅ በኩል የወታደር ካምፕ ይታያል ይህም የንጉሠ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ ነው። ለሰባት አመታት የዚህ ጦር ሀኪም ነበርኩ። ወታደሮቹ ከአንድ ቀን በፊት ከአዲስ አበባ ወጥተው ወደ ደሴ እያመሩ ነው። ወደ ዳባት እንድሄድ ባልታዘዝ ከዚህ ጦር ጋራ ወደ ደሴ አብሬ እሄድ ነበር። ሆኖም

*በአሁኑ ጊዜ የጤና ረዳት ተብለው የሚጠሩ የጤና ባለሙያተኞች

ለአስር አመት በዚህ ከተማ የተቀመጡ ሲሆን ለማምለጥ ሙከራ ሲያደርጉ ተይዘው ጥብቅ ቁጥጥር ባለበት እስር ቤት ወደ ሐረር ተወስደዋል።

ከጥዋቱ ሁለት ሰአት ሲሆን አባይ ወንዝ ደረስን። ፓይለቱ እኔ እንዳይ የፈለገው አስደናቂ አይታ አዘጋጅቶልኛል። በአይን ሲያዩት ግርማ ሞገስ ያለው አይታም ነበር። ከጊዜ ብዛት የአባይ ወንዝ ወደ ታች በመሸርሸር 1500 ሜትር ጥልቀት ያለው ሸለቆ ፈጥሯል። ፀሃይ ወደ ላይ ገና ከፍ ስላላለች ታችኛው የሸለቆ ክፍል በደንብ ባይታይም ወንዙ ከስር የአለት ንጣፍ ላይ ሲወርድ ይታያል። የሸለቆው ግድግዳ ወደ ሰላሌ በኩል በዛፍና በዕፅዋት የታጀበ ሲሆን ወደ ጎጃም በኩል ግን ግራጫ መልክ ያለው ቋጥኝ ነው የሚታይበት።

ከሸለቆው ወጥተን እየበረርን ያለንበት የጎጃም ክፍል በአረንጓዴ ሜዳዎች ጫካና ከተሞች የተሞላ ነው። ሰዎች ሠፍረውበታል። ለአይን የሚያስደንቀው ነገር ደግሞ የቤተክርስቲያኖች ብዛት ነው። በዚህ ስፍራ የሚኖሩ ሰዎች ፅኑ አጥባቂ ሀይማኖተኞች ናቸው ተብለው በአቢሲኒያ ይታወቃሉ።

ወደ ግራ በኩል ደግሞ የጎጃም ትልቁ ተራራ ጮቄ ይታያል። አናቱ በ4150 ሜትር ከፍታ ላይ በደመና ተሸፍኗል። ከአባይ ማዶ ወደ ቀኝ በኩል ደግሞ የአማራ ሳይንት ተራራማው መሬትና የ4350 ሜትር ከፍታ ግርማ ሞገስ ያለው ሊጋምቦ ተራራ ይታያል።

ከግማሽ ሰአት በረራ በኋላ ጥቁር አባይን አንደገና አቋረጥን። ወንዙ ከጣና ሀይቅ ተጠምዞ ሲወጣ በደንብ ማየት ይቻላል። አባይ ጎጃምን በሶስት ጎን አካሎ ነው የሚወርደው። ከዚህ ከጥምዙ ቦታ በመነሳት ወደ ዳባት ቀጥታ መስመር ያዝን። ሸለቆው እዚህ አካባቢ ጥልቅ ስላልሆነ ወንዙ በድንጋይ በተሠራ ድልድይ ሥር ሲወርድ ተመለከትን። ድልድዩ የተሠራው በ16ኛው ክፍለ ዘመን በአፄ ፋሲል ነው። የድልድዩ ሥራ ከሚከተለው ታሪክ ጋራ የተያያዘ ነው።

አፄ ፋሲል ባለፀጋና ገናና ንጉሥ ነበሩ። በሕይወታቸው ዘመን ብዙ የከፉ ነገር ያደረጉም ያሳለፉም ነበሩ ይባላል፤ ወደኋላ በአርጅና ግን ፀፀት ስለገባቸው ንስሐ መግባት ፈለጉ። ማቅ ለብሰው አናታቸው ላይ አመድ ነስንሰው በባዶ እግራቸው ወደ የሚያውቁት ባህታዊ ሄደው ለነብሳቸው ሰላም ለማግኘት ምን ቢያደረጉ አንደሚበጅ ጠየቁ። ባህታዊ ሲመክራቸው በዝናብ ወራት ወንዝ በማቋረጥ የሚሞተው የሀገሬው ህዝብ በሺ የሚቆጠር ስለሆነ ወንዞች ላይ ድልድይ ብትሰራ ይሻለል ብሎ መከራቸው። አፄ



ፋሲልም በሀሳቡ በመስማማት ድልድይ አንዲሰራ ትዕዛዝ ሠጡ። በተጨማሪም ድልድዩን የሚያቋርጥ ሰው በሙሉ ለንጉሡ ለአፄ ፋሲል ፀሎት አንዲያደርግ ትዕዛዝ ሠጡ። ይህ ፀሎትም አስካሁን ድረስ የሚደረግ ነው። በድልድዩ የሚያልፈው መንገደኛ እግዚአብሄር የአፄ ፋሲልን ነብስ ይማር በማለት ይፀልያል።

አሁን ደግሞ የበጌምድርን ክፍል እያቋረጥን ነው። አገሩ በተራሮችና ፀሃያማ በሆኑ ረባዳ ስፍራዎች የተሞላ ነው። የበግ እርባታ በጣም የዳበረበት ሲሆን የአቢሲኒያ ምርጥ የአህያ ዝርያዎች የሚረቡበት ቦታ ነው። ነዋሪዎችም በጣም ሀይማኖተኞች ናቸው። ታወቂ የሆኑ ብዙ ገዳማት አሉት በሥራችን አምባ ማርያም የተባለውን ትልቅ ገዳም ተመለከትን።

ወዲያውኑ የደብረ ታቦር ከተማን አቋርጠን አየበረርን አለፍን። ይህ የራስ ካሳ ግዛት ነው። በከተማው ትልቅ የመኖርያ ግቢ አሰርተዋል። ትንሽ ፈንጠር ብሎ ደግሞ በከተማው በምሥራቅ ጠርዝ በኩል የአድቬንቲስት ሚሲዮን ማዕከል ከመኖርያ ቤቶች ትምህርት ቤትና ሆስፒታሉ ጋር ይታያል።

ከጥዋቱ ሶስት ሰአት ተኩል ሲሆን በርቀት ወደ ምዕራብ አቅጣጫ የጣና ሀይቅ ታየኝ። ይህንን ሀይቅ ለማየት የረዥም ጊዜ ምኞቴ ነበር። በርቀት ስለሆነ በደንብ በዝርዝር ማየት አይቻልም። ሀይቁ በሰሜንና በምሥራቅ በኩል የማይሎች ስፋትና ርቀት ባላቸው በደንቢያና ፎገራ አረንጓዴ ሜዳዎች ተከቧል። ደንቢያና ፎገራ በቀንድ ከብት ግጦሽ የሚታወቁ ቦታዎች ናቸው። በትንሽ ርቀት ፍርሥራሹ የቀረ ይፋግ የሚባል የጥንት ከተማ አየን።

በጎንደር ዘመነ መንግስት ጊዜ ከአምስት መቶ አመታት በፊት መሆኑ ነው ይፋግ ትልቅ የንግድ መነሀሪያ ከተማ አንደነበር ይታወቃል።

ጉዟችንም በበለሳ በኩል አድርጎ አየቀጠለ ነው። ለአንግዳ የማይመች አደገኛ ቦታ ነው። በተራሮችና በገደሎች የተሞላ ስለሆነ በድንገት አንኳን አውሮፕላን ለማሳረፍ የሚሆን ቦታ አይደለም። በዚህ ስፍራ የሚኖሩ ሰዎች አንደተራራውና አንደገደሉ ሁሉ የማይመቹ እንደሆኑ ይነገራል። አገሩ ለአርሻ ስለማይመች በማጭበርበርና በሽፍትነት የሚተዳደሩ ሰዎች ይበዙበታል፤ ሆኖም ከበለሳ የሚጎረጎረው ማር ግን ባለው መአዛ ታዋቂ ስለሆነ ተፈላጊነቱ ከፍ ያለ ነው።

ልክ ከጠዋቱ አራት ሰአት ሲሆን መድረሻችን ቦታ ዳባት ደረሰን። የአውሮፕላን ማረፊያው አርጥበት ስለነበረው ፓይለቱ ዌበር ደፍሮ ከማሳረፉ በፊት ስድስት ጊዜ ሜዳውን መዞር ነበረበት። አንደምንም አየነጠረና

አየተንገጫገጨ አውሮፐላኑ ከሜዳው መጨረሻ ከአንድ ትልቅ ዛፍ ፊት ለፊት ትንሽ ሜትሮች ርቀት ቆመ:: ከአውሮፕላኑ ዘልዬ ወረድኩ በመውረዴም ደስተኛ ነበርኩ:: በእግር የሚረገጡት መሬት መገኘቱ ራሱ ጥሩ ነገር ነው::

ፊታውራሪ መርሶ ንጉሳዊ እቀባበል ነው ያደረጉልን:: ፊታውራሪው የደጃዝማች አያሌው ልጅ ናቸው:: አባትየው በማይኖሩበት ጊዜ የጦር አዛዥ አሳቸው ናቸው:: በድንኳን ውስጥ የምግብ ጠረጴዛ ተዘጋጅቶም ስለነበር ወድያውኑ ለመመገብ ተቀመጥን:: ፓይለቱ ቶሎውኑ ወደ እዲስ አበባ እንዲመለስ ትዕዛዝ ተሰጥቶት ነበር:: ይህም የሆነው የኢጣልያ የጦር አውሮፐላኖች እንዳያገኙት ነው:: ከሁለት ሰአታት በኋላም ኪፓይለቱ ጋራ ተሰነባበትን::

ብቻዬን መሆኔ እንግዳ ነገር ሆነብኝ:: ከጥቁር ሰዎች መሃከል በመሃል ጥቁር አቢሲኒያ ብቸኛ ነጭ ሰው መሆኔ ነው::



# ምዕራፍ ሶስት

## ጉዞ በአጃቢ መቀጠል

ከእዲስ አበባ ከመነሳቴ በፊት ፊታውራሪ መርሶ ከአዲስ አበባ በቴሌፎን ጥብቅ ትዕዛዝ ተሠጥቷቸዋል:: ትዕዛዙም አጃቢ አዘጋጅተው እንዲጠብቁና እኔ እንደደረስኩ ወድያውኑ ደጃዝማች አያሌው ወዳሉበት ካምፕ ወደ ጠገዴ እንድሄድ ነው:: ጠገዴ ከዳባት ወደ ሰሜን በኩል የሶስት ቀን መንገድ ይርቃል::

መንገድ ለመጀመር ሁሉም ነገር ተዘጋጅቶ እንደሆነ ብዬ እኔው ራሴ ስጠይቅ ፊታውራሪ ሁሉም ነገር ለነገ ይዘጋጃል የሚል መልስ ሠጡኝ:: ጠጅ አየጠጣን ወሬ ቀጠልን: ከዚያም ከአድካሚ ቀን በኋላ ማረፍ ነበረብን:: ፊታውራሪ እውሮፕላኑን ሲጠብቁ ቆመው ስለዋሉ የደከማቸው መሆኑን ነገሩኝ::

እኔም በጣም ተናደድኩና ቤተሰቡን ጨምሬ አስጠርቼ ወረድኩባቸው:: የንዴት ቃሌን ሳወርድ ፊታውራሪ በፅሞና ምንም ሳይናገሩ ቆመው ተመለከቱኝ:: ያሰኝን ተናግሬ ስጨርስ አንዲህ የሚል ቃል ተናገሩኝ "እኔን የገረመኝ ከኛ በተሻለ የኛን ቋንቋ እየተናገርክ አንጀራውንም ውሀውንም አብረህ አየበላህ እየጠጣህ እንደራሳችን አድርገን የምናይህ ሰው እንደ ፈረንጅነትህ ፀባይህን ማሳመር ነበረብህ:: ከንጉሡ የተላከ ትልቅ ዶክተር ነህ ስለዚህ ራስህን ማከበድ አንጂ ማቅለል የለብህም::"

ምን ማለት አችላለሁ በአነጋገራቸው ያለምንም መከላከያ ነው የተረታሁት:: ዞሪያውን ልይ ብዬ ጥያቸው ወጣ አልኩ::

የዳባት ከተማ ሌሎች መሰል ከተሞችን ነው የሚመስለው ፤ ወደ ሶስት ሺህ የሚሆኑ ነዋሪዎች አሉበት:: ከፊት ለፊታቸው ትንሽ ግቢ ቢጤ ያላቸው ከብ የሣር ጎጆ ቤቶች በተዘበራረቀ አቀማመጥ ከጋራው ስር ተዘርግተዋል:: ጠበብ ያሉ የተጠማዘዙ የአግር መንገዶች በተሰያዬ አቅጣጫ አርስ በራስ እያቋረጡ በመንደሮች ውስጥ ይታያሉ:: ከላይ ከከፍታው የቅዱስ ገብርኤል

ቤተክርስቲያን በወይራና በጥድ ዛፎች ታጅቦ ከፍ ባለ አጥር ዙሪያውን ተከቦ ይታያል። አያንዳንዱ ሱቅ ሻጭ ንግዱን በየትንንሽ ቤቱ ውስጥ ስለሚያደርግ ከፍተ ሱቅ የሚባል ነገር አይታይም። ከከተማው ወጣ ብሎ ወደ ግቢ ወይም ወደ ቤተ መንግስቱ መሄጃ በኩል ቅዳሜ ቅዳሜ የሚውል የገበያ ቦታ ይታያል።

ቤተመንግስቱ ለመድረስ አንድ ሰው ከባህር ወለል ሶስት ሺ ሜትር ከፍታ ወደ ላይ መውጣት አለበት። ቤተመንግስቱ ራሱ አንድ ሺ ሜትር ርዝመት ካለው ገደል ተጠግቶ ነው የተሠራው። ከዚያ ሆነው ዙሪያውን ሲመለከቱ አስገራሚ ነው። ስለ ሰሜን ተራሮችና ገደሎች ብዙ ሰምቻለሁ ነገር ግን በአይን ሲታይ እንደሚሆነው አይደለም። የተራሮቹ አናቶች ጠፍጠፍ ያሉ ሆነው አንደ ሺ ሜትር ወይም ከዛ በላይ ቁመት ባላቸው ገደሎች ይከፋፈላሉ። የተዘበራረቀ ግን አስገራሚ የሆነ አይታ አላቸው። ያለው ንፁህና ድንግል የተፈጥሮ ውበት ሰውነቴን ወረር አስከሚያደርገኝ ድረስ በአድናቆት ተመለከትኩ።

ወደ ግራ በኩል በግምት ወደ መቶ ኪሎሜትር ርቀት በፀሀይ ግባቱ ምክንያት ጠቆር ብሎ 3500 ሜትር ከፍታ ያለው የሚያስፈራው የጠገዴ ተራራ ሰንሰለት ይገኛል። ወደዚያ ነው የምሄደው፤ አሁን ግን ስለመንገዱ ማሰብ አልፈለግሁም።

ከፊት ለፊት ሲመለከቱ ዝቅ ብሎ ቆላ ወገራ ይገኛል። የጀበና ቅርፅ ነው ያለው። አንዳው ትንሽም ቢሆን ሜዳማ ቦታ ማግኘት ይከብዳል። አገሩ የተሞላው በተራሮች አናትና ጥልቀት ባላቸው ጠባብ ገደሎች ነው። በቀኝ በኩል በምትጠልቀው ፀሀይ የመጨረሻ ጮራ ፍንጣቂ ብርሃን ሲመለከቱ የትልቁ የሰሜን ተራራ ጉብታዎች በበረዶ ተሸፍነው ይታያሉ።

ሁሉም ነገር የሚያስደንቅ ታላቅ ግርማ ሞገስ አለው። በተፈጥሮ ታላቅነት ምክንያት የትንሽነት ስሜት ተሰማኝ።

በመገረም የራሴን ስሜት ዝቅ አድርጌ ወደ ቤተመንግስቱ አመራሁ። ትንሽ የምታምር ከፍል ተዘጋጅቶልኛል። ወለሉ ላይ የፋርስ ሲጋጃዎች ተዘርግተዋል። የብረት አልጋው አዲስ አንሶላዎች ተነጥፈውበታል። ወደ ከፍሉ ስገባ ወደ መሬት ለጥ ብሎ እጅ የነሳ የልጅ አገልጋይ በሁለት እጆቹ ሻማዎች ይዞ በአንዱ ማዕዘን በኩል ቆሟል። ተከትለውም የእጅ መታጠቢያ ውሃ፤ ምግብ፤ ጠላና ጠጅ የያዙ አገልጋዮች በሰልፍ መግባት ጀመሩ።

ጣፍጦ የተሠራው ወጥ ሽታ የምግብ ፍላጎቴን ስለጨመረው በደንብ



አድርጌ በላሁኝ። በልቼ እንደጨረስኩ ፊታውራሪ የአዲስ አበባን ሁኔታ ወሬ ለማዳማጥ መጡ። እኔ ግን በአውሮፕላን ካደረግነው ረዥም መንገድና ሆዴ አስኪሞላ በበላሁት ምግብ ምክንያት እንቅልፍ እንቅልፍ ስላለኝ ድምፅ አያሰማሁ ማዛጋት ጀምርኩ። በአቢሲኒያ አንድ ሰው ማረፍ ፈልጎ ድምፅ አያሰማ ቢያዛጋ ነውር የለውም።

ፊታውራሪም "ደህና አደር" ብለው ጥለውኝ ሄዱ።

ከሌሊቱ ስምንት ሰአት ሲሆን ድንገት ከእንቅልፌ ነቃሁ። በመላው ሰውነቴ ላይ የተጣበቀና የሚለበልብ ስሜት ተሰማኝ። መብራት አብርቼ አቅርቤ ስመለከት አልጋው በቁንጫ ተወሯል። ስተኛበት ነጭና ንፁህ የነበረው አንሶላ አሁን በደምና በሞቱ ቁንጫዎች ምክንያት ቀለሙን ቀይሯል።

ተነስቼ ስቆምም ቁንጫዎቹ በእግሬ በኩል ወደ ላይ ወረሩኝ። አንዳንዶችም ፊቴ ላይ መፈናጠር ጀመሩ። በኋላ እንደተረዳሁት ቁንጫዎቹ በጣም ተርበዋል ምክንያቱም ለብዙ ሳምንታት አዛች ከፍል ውስጥ ገብቶ ያደረም አልነበረም፤ በተጨማሪ ምንጣፎቹ ከተራገፉ ወራት አልፏቸዋል።

አገልጋዩን ቀሰቀስኩና ከውጭ ድንኳን እንዲወጥርልኝ አደርጌ ከአንድ ሰአት በኋላ አንደገና እንቅልፍ ወሰደኝ። ያሁኑ ግን ያልተቋረጠ ነበር።

ከጥዋቱ ሁለት ሰአት ሲሆን ፊታውራሪ መጡ። እንደተሰማኝ ከሆነ ከመጠን በላይ ሞቅ ያለ ሰላምታውና ወዳጅነቱም ትንሽ የተጋነነ መሰለኝ። በዚህ ምክንያትም አንድ የማይሆን ነገር እንደተፈጠረ ተገነዘብኩ። ሚስጥሩ ሲወጣ ረዥም ጊዜም አልወሰደም። ለካስ ለመንገዳችን የምንወስዳቸው አህዮች ሲያስፈልጉ ለነገ ካልሆን በስተቀር ለዛሬ አልተገኙም።

አሁን ግን አንደ ተራ ፈረንጅ ሳልሆን ድሬሰሩን ጠርቼ ምንም ሳልል ከቤቱ ወጥቼ ቁልቁለቱን መንገድ ያዝኩ። ፊታውራሪም የሆነ ነገር አለ ብለው በማሰብ ሰውነታቸው የሚፈቅድላቸውን ያህል አየሮጡ ከኋላዬ በመድረስ ትንፋሻቸው ቁርጥ ቁርጥ አያለ ወዴት አንደምሄድ ጠየቁኝ።

እኔም በምን ግዴ አመላለስ የምሄደው ወደ ቴሌግራም ቤት ሲሆን አሰዎ የተሰጠዎትን ትዕዛዝ እንዴት አድርገው አንደፈፀሙ ትዕዛዙን ለሠጡዎት ንጉሥ ለማስተላለፍ ነው አልኩ።

አባባሌ ሥራውን ሠራ። ፊታውራሪ ወዲያውኑ የሚያስፈልገው ነገር ተዘጋጅቶ ጉዞው በሁለት ሰአታት ውስጥ እንደሚጀመር ቃል ገቡልኝ።

ሁለት ሰአት የተባለው ወደ ስድስት ሰአታት ተራዘመ፤ ነገር ግን ከቀኑ ስምንት ሰአት ሲሆን ጉዞውን መጀመር ተቻለ። ከተጓዦች መሀል ፈጠነ

የሚባለው የኔ ድሬሰር፤ ሁለት የጦር መኮንኖች፤ አንድ መቶ የታጠቁ ወታደሮች ከነሱም ስምንቱ አውቶማቲክ መሳሪያ የያዙ፤ መድሃኒትና የህክምና ቁሳቁሶች፣ የኔን የግል ዕቃዎችንና ጥይቶችን የጫኑ አስር አህዮች ነበሩበት:: ይህን ያህል አጀብ የግድ አስፈላጊ ነበር፤ ጦርነት ላይ ስለሆን የፀጥታው ጉዳይ አስጊ ነው::

በዳባትና ጠገዴ መሀከል ያለው ርቀት ወፍ የሚበረው ሀምሳ ኪሎሜትር የማይሞላ ሲሆን በመሀከል ግን ሰፊና ጥልቀት ያለው ገደል ስላለ ይህንን ለማቋረጥ መንገዱ በእጥፍ ይረዝማል::

የመጀመሪያ ማረፊያ ካምፓችን ያደረግነው ቁልቁለቱን ጨርሰን ነው:: ወንዙ ድረስ እየተንደረደርን የወረድነው ቁልቁለት ከዳባት ከተማ 1200 ሜትር ዝቅ ብሎ ነው:: ደራ ይባላል:: በአግራችን መውረድ ነበረብን በዚህ ቁልቁለት በከብት ጫንቃ ላይ የሚመችም አይደለም፤ መንገዱም ቢሆን በየመሀሉ በድንጋዮችና በገደል ስንጥቆች ይቋረጥ ነበር::

ከመጠን በላይ ስተጫኑት አህዮችም አዘንኩ:: እንዳይንከባለሉ በፊት ለፊት ሰኮናቸው እየተንፏቀቁ ነው ቁልቁለቱን የሚወርዱት:: የጀርባቸው አጥንት ሲንጫጫ ትንፋሻቸው ሲያቃትት መስማት አሳዛኝ ነገር ነበር:: ደግነቱ አርፈውና ተቀልበው የሰነበቱ ስለሆኑ ጠንካሮች ነበሩ:: ጉዞ ስንጀመር የጫንቃ ወይም የጀርባ ቁስል የነበረው የጭነት ከብት አልነበረም::

እንደዚህ አይነት መንገድ ወጥቶ የሚያውቅ ሰው ቁልቁለትን በፍጥነት ለረዥም ሰአታት መውረድ ምን አይነት ሁኔታ እንደሚፈጥር ያውቃል:: ጉልበት ይርዳል ሰውነትም እንዳለ ቁስለት ስሜት ይኖረውና ትልቁም ትንሹም የሰውነት እንቅስቃሴ ህመም ይፈጥራል:: ሰውም ሆነ እንስሶች ሁላችንም ማረፊያው ቦታ ስንደርስ በጣም ቢደከመን አያስገርምም::

የሚያሳዝነው ግን ሁለት አህዮች ከጀርባቸው ላይ የብርቱካን ፍሬ የሚያክል አብጠት ተገኘባቸው:: ሌላ የሚደረግ ነገር አልነበረም:: ሁለት የብረት መተኮሻዎች ለዚሁ ጉዳይ ተብለው ተጭነው ስለሚጓዙ እነሱን በእሳት አግሎ እብጠት ያለውን ከብት አስተኝቶ እብጠቱን በትኩስ ብረት መጥበስ ነው:: አሰቃቂ ቢመስልም ለእንደዚህ አይነቱ ቁስል በጊዜው ፍቱን የሆነ ድርጊት ነው:: እብጠቱን በጋለው ብረት በአግድሞሽ ሰንበር እስኪያወጣ ድረስ በመስመር በመስመር እያደረጉ መጥበስ ነው:: ወዲያውኑ ሲደረግም ውጤቱ የተሻለ ይሆናል:: የጠባሳው ርዝመትና ብዛት እንደእብጠቱ ትልቅነት ነው:: ከብቶቹ ከተጠበሱ ከአንድ ሰአት በኋላ ለጭነት ዝግጁ ይሆናሉ::



ይህ ሁኔታ ህመም የሚፈጥር ቢሆንም የከብቶቹ ጀርባ ተጨማሪ ጉዳት አያሳይም:: ቁስሉ በየቀኑ ለብ ባለ ውሃና በሳሙና ከታጠበና እየተጫኑም ቢሆን በደንብ ከተያዘ በሁለት ሳምንታት ውስጥ ጨርሶ ይድናል:: የተፈጠረው ጠባሳ ደግሞ ጥንካሬው ይጨምራል፤ ያጋደለ ወይም ያልተስተካከለ ጭነትን የሚችል ሆኖ እብጠት እንደገና እንዳይፈጠር ይረዳል:: እንዲያውም የዚህ አይነት ጠባሳ በጀርባው ላይ ያለው የጋማ ከብት ተፈላጊና ዋጋውም ከፍ ያለ ነው የሚሆነው:: ከብቱም "አልፎታል " ይባላል::

መጨለም ጀምሮ ነበር እኛም ሁለቱን አህዮች አከመን እየጨረስን ነበር:: ድንገት የታጠቁ ወታደሮች ከሰሜን አቅጣጫ ወደኛ ሲመጡ አየን:: ቁም የሚል ጩኸት ሲያሰሙ ሁላችንም መሳሪያችን አቀባበልን:: ደግነቱ ምንም አደጋ አልተፈጠረም:: ወታደሮቹ ደጃዝማች አያሌው እኛን እንዲያጅቡ የላኳቸው ነበሩ:: እነዚህ ስለመጡ መጀመሪያ አጅበውን የመጡት የፊታውራሪ መርሶ ወታደሮች ወደ አለቃቸው እንዲመለሱ ተደረገ::

በጥዋት መንገድ ስለምንጀመር የተጫነውን ሁሉን ነገር አዲስ ለመጡት ወታደሮች ማስረከብ ማታውኑ መደረግ ነበረበት:: አንግዲህ የተፈጠረውን ውዝግብ ማስተዋል ነው:: አቢሲኒያውያን ክርክር የሚወዱ እንዲያውም በከርክር የተካኑ ሰዎች ናቸው:: ከዚህ ቀደም ቁጥር የለሽ ክርክር ሲካሄድ ሰምቼ አውቃለሁ:: የዛሬውን የሚያህል ግን አይቼ አላውቅም::

የመጀመሪያው ውይይት የአህዮችን ቁጥር በሚመለከት ነበር:: ይህ እንኳን የሚያስቸግር አልነበረም:: ጠቅላላ ቁጥራቸው በእጅ ላይ ካሉ ጣቶች ቁጥር አይበልጡም ነበር:: ከአዲሶቹ አጃቢዎች አንደኛው ጠጋ ብሎ ሲመረምር ሁለቱ የተጠበሱ ሆኖ ያያል:: ጠባሳውም አዲስ እንደመሆኑ ሽታው እንኳን አለቀቀም ነበር:: የተነሳው ጥያቄ እንዴት የመጀመሪያ አጃቢዎች ከዳባት ሲነሱ ጤነኛ እንስሳ አልያዙም አሁን እነዚህ የተጎዱ አህዮችን ዋጋስ ማን ሊከፍል ነው ነበር::

አዲስ የመጡት እጃቢዎች ሀላፊነት መውሰድ አልፈለጉም:: በሁለቱ ምትክ ሁለት ጤነኛ አህዮች ይሰጡን ብለው ጥያቄ አቀረቡ:: የዳባት አጃቢዎች ደግሞ የመከላከያ ክርክራቸውን ቁስሉ በግድ የለሽነት የመጣ ሳይሆን በመንገዱ ምክንያትና በተጫኑት የጭነት አይነት ነው:: ይህ ደግሞ አዲስ ነገር አይደለም በየመንገዱ የሚፈጠር ሁኔታ ነው፤ መጠበሱም ቢሆን ጠንካራ ነው የሚያደረጋቸው በማለት አቀረቡ::

ክርክሩ ለአንድ ሰአት ያህል ቀጠለ በኋላ ግን እኔ ራሴ ገባሁበትና በፅሁፍ የሁሉንም ሀላፊነት እኔ እወስዳለሁ ብዬ እቀረብኩ፡፡ ሁለቱን ተከራካሪ ወገኖች የሚስማማ ሀሳብ ስለሆነ በዚህ መንገድ ይኸኛውን ሙግት አስቆምኩት፡፡

ትልቅም ሆነ ትንሽ የአቢሲኒያ ወንዶች በህይወታቸው የሚያስደስታቸው ትልቅ ነገር አለ፡፡ ሁሉም ጠመንጃቸውን መወልወል፤ መፈታታት፤ የተፈታቱትን የመሳሪያ ክፍሎች በፀሀይ ወይም በእሳት ማሞቅ እንደገና መልሶ መገጣጠም ይወዳሉ፡፡ ይህንን ያለማቋረጥ ለሰአታት ግፋ ሲልም ለቀናት ቢያደርጉ ደስ ይላቸዋል፡፡ የእጅ ብረታቸውን በጣም ስለሚወዱ በፍቅር አይን እያዩ ጠመንጃቸውን ይስማሉ፡፡ ይህንን ስለማውቅ አዲስ በመጡት አጃቢዎች ተጭነው የመጡት መሳሪያዎች ይፈቱና ይታዩ ሲባል የመጀመሪያ አጃቢዎች መስማማታቸውን ስሰማ አልገረመኝም፡፡

ሁለት ፋኖሶች እንዲበሩ ተደረገና መሬቱ ላይ ምንጣፍና ሸማ ተዘረጋ፡፡ ከሁለቱም ወገኖች ወታደሮችና ጭፍሮች ዙሪያውን ተቀመጡ፡፡ መሀል ላይ አንደኛው እውቶማቲክ መሳሪያ (መትረየስ) ተቀመጠ፡፡

ቆሜ በትዕግስት የሚደረገውን መመልከት ጀመርኩ፡፡ እነዚህ መሳሪያዎች የእነዚህን ጥንታዊ ተዋጊ ጦረኞችን ጉጉት ለማስታገስ እንደ መስዕዋትነተ ለፍሪዳ ሊቀርቡ ነው፡፡ አሁን እሰራሩን እንኳን በውል የማያውቁትን እንደዚህ የተወሳሰበ መሳሪያ መልሰው ይገጥሙት ይሆን ብዬ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ እንዴት እንደሚያደርጉ ለማወቅም ጉጉት አደረብኝ፡፡

ለማንኛውም የብሎን መፍቻ እያያዝ ችሎታ አላቸው፡፡ እያንዳንዱን የመትረየስ ክፍል ተራ በተራ ፈቱት፡፡ የተፈታውን ክፍል በደንብ እያዩና እየመረመሩ ሸማው ላይ መቆለል ጀመሩ፡፡ ሁሉም የሚፈታው ነገር ተፈቶ ሲያልቅ የእፎይታ ትንፋሽ በተቀመጡት ዙርያ ተሰማ፡፡ የተቆለለውን ክምር መሳሪያ በሸማ እንደተጠቀለለ እነሱና ሁለተኛውን ያልተፈታውን መትረየስ ይዘው መጡ፡፡ ድንገት ጥርጣሬ ተሰማኝና ለማረጋገጥ ብዬ ሁለተኛውን ከመፍታታችሁ በፊት የመጀመሪያውን መልሳችሁ አትገጥሙም ወይ ብዬ ጠየቅሁ፡፡

የተሠጠኝ መልስ ደግሞ የለም እኛ የምናስበው አንተው መልሰህ እንድትገጥመውና መሥራቱን እንድታረጋግጥልን ነው የሚል ሆነ፡፡

ጥርጣሬዬ ተረጋገጠ፡፡ "በሉ አመስግናለሁ እንደህፃን ልጆች ከባችሁ ተቀምጣችሁ የማታውቁትን ነገር እንደ አሻንጉሊት ስትበትኑ ያመሻችሁት



ሊሊቱን በሙሉ እኔ እንድገጥመው ልታደርጉኝ ነው ወይ! እናንተ ደደቦች እኔ ሀኪም እንጂ ወታደር መሆኔን አታውቁም ወይ?"

"እሃ! ፈረንጅ ከፈለገ ሁሉንም ማድረግ ይችላል"

"እሱ እንኳን የሚቻል ነገር ነው፡፡ እኔ ግን እንዲህ አይነቱን ነገር መሥራት አልፈልግም፡፡ ይህን አንዱን ብቻ ነው መልሼ ለመግጠም የምሞክረው ሌሎቹን ግን ሳትነኩ እንዳሉ በመጡበት ሁኔታ ማስረከብ አለባችሁ፡፡ ከዚያ በኋላ ማረፍ አለብን፡፡ እኔ የምላችሁን ካልሰማችሁ ግን መሳሪያዎቹን እንደተበተኑ ለደጃዝማች አያሌው ታስረክባላችሁ፡፡ ያ ደግሞ የሚያስከተለውን ነገር ታውቃላችሁ"

ትዕዛዝ የተሞላበት ቃሌ ሥራውን ሠራ፡፡ በሀሳቤ ተስማሙ ነገር ግን መከራከር ነበረባቸው፡፡ በአቢሲኒያ መቃወምና መከራከር ባህል ነው፡፡ ይህን የማያደርግ ሰው ከበሬታ ያጣል፡፡

የገባሁትን ቃል ለመፈፀም ቁጭ አልኩና መሳሪያውን እንደገና መግጠም ጀመርኩ፡፡ ያለኝ የሌለኝን እውቀት መጠቀም ነበረብኝ አለበለዚያ የነጭ ስም መጥፋቱ ነው፡፡ እያላበኝና ቁና ቁና እየተነፈስኩ ከብዙ ሙከራና ድካም በኋላ መትረየሱን በነበረበት ሁኔታ መልሼ መግጠም ቻልኩ፡፡

"አሁን ሄደን ማረፍ አለብን" አልኩ

"የለም! አናርፍም"

"አሁን ደግሞ ምን ቀረ?"

"እሃ! ጥይቱ መቆጠር አለበት

ይህሰ ትክክል ነው፡፡ ረስቼ ነው ለነገሩ ጊዜም መውሰድ የለበትም፡፡ በካርታ(መጋዚን) በካርታ የተቀመጠውን መቁጠር ብቻ ይበቃል፡፡ ያገኘሁት መልስ ግን

"የለም እያንዳንዱን ጥይት ነው የምንቆጥረው"

"ምን? ከመጋዚኑ ጥይቶችን ልንፈለቅቅ ነው? የለም እኔ የምላችሁ ይህ በጣም ይበዛል፡፡ እያንዳንዱ ካርታ 750 ጥይት ይይዛል፡፡ እስር ካርታዎች አሉ፡፡ የሚያረካችሁ ከሆነ ሂሳቡን እሰቡና ስንት ጥይቶች እንዳሉ ድረሱበት እኔ ግን ሄጄ እተኛለሁ፡፡"

ለማንኛውም ለጥበቃ ስል ድሬሰሩን መኝታውን የጥይት ሳጥኖች ላይ እንዲያነጥፍ አድርጌዋለሁ፡፡

ከጥዋቱ አሥራ አንድ ሰአት ሲሆን መንገድ ጀምረናል፡፡ ወንዙን ሽቅብ ወደ መነሻው እየተከተልን በርቀት መሄድ ነበረብን ከዚያም አግድሞሽ በመሄድ ወደ ጠገዴ ተራሮች መውጫ ወደ ሆነው በአንድ ማሰፈያ መንገድ ወይም በር በኩል ማለፍ አሰብን፡፡ መንገዱ ከፍታና ዝቅታ ያሰው ሲሆን ጥቅጥቅ ያሰ የቀርከሃ ጫካ ማቋረጥን ይጨምራል፡፡ ሳሩም የአራት ሜትር ከፍታ ያለው የዝሆን ሳር ነው፡፡ በመንገዳችን አንስያ የተባሰውን ጥርት ያሰ ውሃ የሚፈስበትን ወንዝ ዘጠኝ ጊዜ አቋርጠናል፡፡ መንገዱ እንደዚህ በየጊዜው የሚሰዋወጥበት ጉዞ ደስ የሚል ነበር፤ ሰውም ሆነ እንሰሳ የውሃ ጥሙን በፈለገ ጊዜ ማርካት ይችል ነበር፡፡

ድንገት በደም የራሰ የልብስ ብጫቂ በመንገዳችን ላይ አየን፡፡ ልብሱ የተገኘበት ቦታ ሳሩ ተደምድሞ የተረገጠ መሆኑ ያስታውቃል፡፡ ግብ ግብ የተፈጠረበት ቦታ መሆኑ ምልክት ነው፡፡ ብቻውን የእግር መንገዱን ተከትሎ ይሄድ የነበረ ወታደር ነው፡፡ ምንም ሳይጠረጥር ጠመንጃውን ትከሻው ላይ አድርጎ ሲጓዝ አድፍጦ ይጠብቅ በነበረ ቀማኛ ጠመንጃውን ተነጥቆ ነው፡፡ ከትንሽ ግብ ግብ በኋላ ወታደሩ ህይወቱን አሳልፎ ሠጥቷል፡፡ እንግዲህ አስከሬኑ ወደ ጉድጓድ ተጥሏል ወይም አውሬ በልቶታል፡፡ በአቢሲኒያ እንዲህ አይነቱ ነገር በየጊዜው ይፈፀማል፡፡ እንደወጡ ቀሩ ለሚባሉ ሰዎች ምክንያት አንዱ ይህ ሳይሆን አይቀርም፡፡

ከቀኑ አስር ሰአት ሲሆን ከሸሰቆው ዳርቻ ደረስን፡፡ ከሚቀጥሰው ማረፊያ ካምፓችን ሰመድረስ ወደ ላይ የአምስት መቶ ሜትር አቀበት መውጣት ነበረብን ፡፡ ከዚህ ካደርንበት ጋሞ ከሚባል ቦታ ላይ ሆኖ ዙሪያውን ለተመሰከተ ሰው ሸለቆውን በውስጡ ከሚጠማዘዘው ወንዝ ጋራ ከሸሰቆው ማዶ ደግሞ የአባት ተራሮችን ጨምሮ አስገራሚ ትዕይንት ነው፡፡ የተሰያዩ ቅርፅ ያላቸው አለቶችም ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ ከተራራዎች አናት ላይ ወጣ ብሎ አንድ ወጥ የሆነ የተሸሞለሞለ የድንጋይ ከፍታ ከተራራው አናት ይጀምርና ቁልቁል ወደ ሸለቆው ይወርዳል፡፡ ሸለቆው ሲደርስ ይቋረጥና አንደገና በተቃራኒው በኩል ወደ ላይ ወደ ተራራው ተመልሶ ይወጣል፡፡ ከፍታው ከአሰራአምስት አስከ ሀያ ሜትር ሲሆን የጎን ስፋቱ ግን ከሶስት ሜትር አይበልጥም፡፡ "የንጉሡ አጥር" ተብሎ ይጠራል፡፡ አፈ ታሪኩ እንደሚለው ከሆነ በንጉሡ ትእዛዝ ድንጋዩ እንደ አጥር በመነሳት ንጉሡንና ወታደሮቹን ከጠላቶቹ ከልሎ አስጥሏቸዋል ይባላል፡፡ ይህን የድንጋይ ከፍታ በጠገዴ የተራራ ሰንሰለቶች በኩል ከታች ረባዳው ወልቃይት ገብቶ አስኪጠፋ



ድረስ ሲቀጥል አይቸዋለሁ፡፡ በአይኔ ማየት የቻልኩትና የተከታተልኩት ይህ የአለት ከፍታ በግምት ወደ ሰባ ኪሎሜትር ይሆናል፡፡

የሶስተኛው ቀን ጉዟችን ዳገት ብቻ ነው፡፡ መንገዱ ወደ ላይ እያሻቀበ መሄድ ብቻ ነው፡፡ አየሩም እየቀለሰ መሄድ ጀምሮአል፡፡ አድካሚና አሰልቺ ነበር፡፡ የተቀመጥኩበት በቅሎ መሸከም ሰላልቻለ በእግሬ መጓዝ ነበረብኝ፡፡ ሁሰቱ የተጠበሱት ጋማ ከብቶች ደግሞ አስቸጋሪ ነበሩ፡፡ ሙቀቱ፣ ላቡ፣ ወደኋላ የሚንሸራተተው የተሸከሙት ጓዝ ህመም እየፈጠረ ሰላስቸገራቸው እየደጋገሙ የተሸከሙትን ጓዝ በእርግጫ እየዘሰሉ ወይም መሬት ላይ እየተንከባለሉ እያወረዱ ይጥሉት ነበር፡፡

ቀትር ላይ የሶስት ሺ ሜትር ከፍታ ላይ ያለ አምባ ላይ ወጣን፡፡ ከአንድ ስአት ጉዞ በኋላም የደጃዝማች አያሌው ካምፕ ነው የተባለ ቦታ ደረስን፡፡ ነገር ግን የፈለግሁትን ያህል ብሞክርም ካምፕ የሚባል ነገር ማየት አልቻልኩም፡፡ ቦታው ትንሽ ዝቅ ብሎ ለአሩብ ኪሎሜትር የሚሆን ርቀት ተቀራርበው ባደጉ ትልልቅ ዛፎች የተሞላ ነው፡፡ ይህ ካምፕ ከሆነ የሚንቀሳቀሱ ሰዎች ማየት ነበረብን፤ በዚህ ቦታ ግን ዝር የሚል ነፍስ አይታይም፡፡

ይህ ያልተሰመደ ነገር ነው ብዬ አሰብኩና ወደ አንደኛው ወታደር ዞር ብዬ ምን ማሰት ነው ብዬ ጠየቅሁት፡፡ ወታደሩም ወደ አንድ ችፍግ ወዳለ ቁጥቋጦ አቅጣጫ እንድመለከት ጠቆመኝ፡፡ በደንብ ሳስተውል የቁጥቋጦው ቅጠሎች እንደመድረቅ ያሉ ሰስነበር ከሌሎቹ ሰየት ያለ ነው፡፡

"ከቁጥቋጦው ብቅ የሚል ነገር አይታይህም ወይ" ብሎ ጠየቀኝ፡፡

አ አሁን በግልፅ የጠመንጃ አፈሙዝ ታየኝ፡፡

"ያ የአየር መቃወሚያ ነው፡፡ ሰመሰወር ነው እንደዚያ የሆነው ዙሪያውን ካስተዋልክ አንደሱ የመስሉ ቁጥቋጦዋች በብዛት ታያለህ" አለኝ፡፡ ከዚያም ጨምሮ ሲያብራራልኝ በቀን ብርሃን ምንም አይነት አንቅስቃሴ ማድረግ ፈፅሞ የተከለከለ ነው፡፡ "ሰውም ሆነ አንስሳ ጫካው ውስጥ መደበቅ አሰባቸው፡፡ የጥልያን አውሮፕላኖች መምጣታቸው ስለማይቀር አስቀድመው እንዲያውቁብን ወይም እንዲያገኙን አንፈልግም፡፡"

በአኔ መሪነት በሁሰት ረድፍ ተሰለፍን፡፡ በዛፎች ስር ለስር ተራምደን ዋናው ካምፕ ደረስን፡፡ ወታደሮች በሁሰት ረድፍ ተሰልፈው በተንጠቀቅ ቆመው እየጠበቁን ነበር፡፡ ጥሩምባ ተነፋ፤ ሰጦታም ከተሰጠን በኋላ ሰወር ብሎ ወደ ተወጠረ ደጃዝማች አያሌው ተጋድመው ወዳሉበት ድንኳን ውስጥ ገባን፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ሰላም በካምፕ ውስጥ

ከዚህ በፊት በአዲስ አበባ በተለያዩ አጋጣሚዎች ደጃዝማች አያሌውን ባያቸውም ትውውቅ አልነበረንም፡፡ ስለዚህ የዚህ የመጀመሪያ ግንኙነታችን ሥነስርአትና ትህትና በተሞላበት ሁኔታ አጭር ነበር፡፡

መቆያዬ ወደ ሆነው ድንኳን አሳዩኝ፡፡ ከላዩ በዛፎች ቅርንጫፎች ተከልሎ የተተከለ ትንሽና ደስ የሚል ድንኳን ነው፡፡ ሌላ ድንኳን ደግሞ ወደ ቁጥቋጦዎች ጠጋ ብሎ ለድሬሰሩና ለህክምና ቁሳቁሶች እንዲሆን ተብሎ ተተክሎአል፡፡

ፂሜን ከተላጨሁና ከታጠብኩ በኋላ  የካምፑን ዙሪያ ለማየት ወጣሁ፡፡ ድንኳን የተፈቀደው ለመኮንኖች ብቻ ስለሆነ የድንኳኖች ቁጥር መጠነኛ ነው፡፡ ጫካው ውስጥና በየዛፎች ስር ግን በቅጠል የተሰሩ ትንንሽ ጎጆዎች በሚያወሩና በሚስቁ ወታደሮች ተሞልተዋል፡፡ የሚያፀዱ ወይ ደግሞ በትንሽ የድንጋይ ወፍጮ ላይ የሚፈጩ ሴቶችም አሉበት፡፡ በቅሎ ፈረስና አህዮች ደግሞ የታጨደላቸውን አረንጓዴ ሳር እያኘኩ ባጭር ባጭሩ ታስረው ቆመው ይታያሉ፡፡ ለቋንጣ የሚሆን የሥጋ ዝልዝል ደግሞ በየቦታው ተንጠልጥሎ ይታያል፡፡ ሁሉም ነገር የሚመች ይመስላል፡፡ በጠቅላላው ካምፕ ውስጥ የተረጋጋ መልካም ምኞት ስሜት እንዳለ ይሰማኛል፡፡

በካምፑ ውስጥ እየተዘዋወርኩ እያለ የምልክት ጥሩምባ ተነፋ፡፡ ወዲያውኑ ካምፑ ውስጥ ህይወትና እንቅስቃሴ መታየት ጀመረ፡፡ ወታደሮቹ፤ ሴቶች፤ አገልጋዮች ከተደበቁበት ቦታ ወጡ፡፡ የታሰሩት እንስሳትም ተለቀቁ፡፡

ቀደም ሲል ያናገርኩት ወታደር ከቀኑ አሥራ አንድ ሰአት በኋላ የጣልያኖች አውሮፕላን በአየር ላይ ጥቃት ሥጋት የለም ብሎ ነገረኝ፡፡ ስለዚህ አሁን ወጥተው እንጨት መልቀም ውሃ መቅዳት ለከብቶቹም ሳር ማጨድ



ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ካምፑ ውስጥ እንደፈለጉት መንቀሳቀስ ይችላሉ፡፡ ለሚቀጥለው ቀን የሚሆነው ምግብ በሙሉ ዛሬ ማምሻውን መዘጋጀት አለበት፡፡ በጠዋት ቡና ብቻ ነው የሚፈላው፤ እሱም ቢሆን ፀሀይ ሳትወጣ ነው፡፡ በምንም አይነት በቀን እሳት አይነድም ምክንያቱም ጭሱ ከሩቅ በአየር መታየት ስለሚችል ነው፡፡ "እንደምታውቀው እሳት ባለበት ሁሉ ጭስ አለ" በማለት ወታደሩ ተናገረ፡፡

እንደዚህ ያለ የተጠናከረ ጥበቃ ሁኔታ በአቢሲኒያኖች መዘጋጀቱ አስገረመኝ፡፡ ከዚህ በፊት የአውሮፕላን ጥቃት ደርሶባቸው አያውቅም ለመሆኑ ማነው ይህን ያስተማራቸው ብዬ ጠየቅሁ፡፡

"ጀግናው ጌታችን ደጃዝማች አያሌው" የሚል መልስ ተሠጠኝ፡፡ "እኛ የምናውቀው ነገር የለም፤ አውሮፕላን የሚባል ነገር እንኳን ገና አላየንም ነገር ግን አለቃችን እንደሚያውቁ ስለምናውቅ የታዘዝነውን መፈፀም ነው፡፡ ዋ! ትዕዛዙን ለማያከብር ሰው ክሙሉ ጦር ፊት አርባ ጅራፍ ነው የሚወርድበት"

ደጃዝማቹን እየወደድኳቸው መጣሁ፡፡ ጉልበትና ጥንካሬ ያለው አንድ ሀበሻም አለ አልኩ፡፡ እንግዲህ የቁርጥ ቀን ሲመጣ ወደኋላ ሳይሉ ገትረው የሚይዙ ሰው መሆናቸውን ደግሞ እናያለን አልኩ፡፡ የቁርጥ ቀን ሲመጣ መሸሽ እንግዳ ነገር አይደለም፡፡

አገልጋይ ልጅ መጥቶ ወደ ደጃዝማች ድንኳን እንደተጠራሁ ነገረኝ፡፡

ደጃዝማች አልጋቸው ላይ ግማሽ እንደመቀመጥ ብለው ከፊት ለፊታቸው ጠረጴዛ ተቀምጦ አየሁዋቸው፡፡ ወድያውኑ ምርመራ እንዳደርግላቸው ጠይቄ ተፈቀደለኝ፡፡ ምርመራው እንዳለቀና መድሃኒቱም ተሠጥቶ እንደጨረስን እጃችን ታጠብንና ወደ ምግብ ገበታ አመራን፡፡

የሚገርም የምግብ አይነት ነው የቀረበው፡፡ አውሮፓዊ እንደመሆኔ ምንም አውሮፓን ባያዩና ለሥልጣኔ የራቁ ቢሆንም ለኔ የሚሆን የፈረንጅ ምግብ ማዘጋጀት እንደሚቻል ለማሳየትም ነው፡፡ ለካስ ከጣልያኖች ቤት ይሠራ የነበረ አገልጋይ ያየውንና የተማረውን የአውሮፓ ምግብ እንዲሰራ ሙሉ ፈቃድ ተሠጥቶት የሚያውቀውን የምግብ አይነት በሙሉ አዘጋጅቶአል፡፡

የምግቡ አይነት ደግሞ በሚቀጥለው ተራ ቀረበ፡፡ የዶሮ ስጋ፤ ሳርዲን በዘይት የተጠበሰና ከጎመን ጋራ የተዘጋጀ፤ የሩዝ ቅቅል ከተምር ጋራ፤ የተቀቀለ የበሬ ስጋ ከሩዝና ከድንች ጋራ፤ የታሸገ ሳልመን (የአሳ ዝርያ) ከተቀቀለ ካሮት ጋራ ሌሎችንም ጨምሮ፤ በመጨረሻም የታሸጉ የተቀላቀሉ ፍራፈሬዎች ነበሩ፡፡

የምግብ አምሮትም ስለነበረኝ ከቀረበው ሁሉ እየቀማመስኩ ምግቡን ያዘጋጀውን ሰው እያመሰገንኩ የበላሁትን በጥሩ የኢጣልያ ወይን አወራረድኩት:: ከዚያም ቀስ ብዬ ጋባዤን የአቢሲንያ ምግብ እንድቀምስ እንዲፈቀድልኝ ጠየኩኝ::

"እንዴታ:: ምን አለበት፤ ነገር ግን ከወደድከውና ከቻልከው ነው ተባልኩ::"

"በሚገባ" አልኩ ቀጠል አድርጌም "ሌላ ነገር ሳይሆን እንጀራና ወጥ ነው የምበላው::" ብዙ ጊዜም ደጋግሜ ስለበላሁት እንደምወደው የውነቱን ተናገርኩ:: ከዚያ በኋላ አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር የፈረንጅ ምግብ እንዳይሰራ እኔም የሐበሻ ምግብ እንድበላ ተስማማን::

ተመግበን እንደጨረስን ደጃዝማች ሻምፓኝ ከፈቱልኝ:: እንኳን ደህና መጣህ አቀባበል ነው:: ቀጥሎም የአገሩን ቋንቋ መቻሌ የአገሩን ባህል በማክበሬ በጣም የረኩ በመሆኑ "ደስ ያሰኘኛል" አሉ "ምክንያቱም አሥራ አምስት ሺ ከሆኑት በኔ ሰዎች መሀል አንግድነት አይሰማህም" በማለት ገለፁ::

እኔም ከልባቸው እንደተናገሩ ነው የተሰማኝ ወደፊት በስንት መከራ የሚፈተሸው ወዳጅነታችን በዚህ ምሽት ተጠናከሮ ነው የተጀመረው::

እኩለ ሌሊት እስከሚሆን ቁጭ ብለን በጋራ ስለምናውቃቸው ሰዎች ማውራት ቀጠልን:: ደጃዝማች በአዲስ አበባና በውጭ አለም የሚሆነውን ማወቅ እንደሚፈልጉ ግልፅ ነው:: ስለሁኔታዎች ያላቸው እውቀትና ግንዛቤ የሚገርምና ከአንድ ኢትዮጵያዊ ከሚጠበቀው በላይ ነበር:: የተለያዩ ጥያቄዎችን እያነሳን ስንወያይ ደስተኛ ነበርኩ::

ለመሄድ ስነሳም ስለካምፑ ምን አስተያዬት እንዳለኝ ጠየቁኝ::

"አስገራሚ ነው እነደእውነቱ ከሆን እንደዚህ አይነት ዝግጅት አልጠበቅሁም" አልኩኝ

"መልካም! እየህ" አሉ "እነዚህ እውቀት የሌላቸው ወታደሮች ስለዘመናዊ ጦርነት የሚያውቁት ነገር የለም:: ቦምብ ከሰማይ ሲጣል አይተው አያውቁም:: ቦምብ የሚያደርሰው የጉዳት መጠን ምን ያህል እንደሚሆን ግምቱም የላቸውም:: ሀሳብ የላቸው ግደ የለሽም ሰለሆኑ እንግዲህ በኔ ነው የሚተማመኑት:: ሃላፊነቱ የኔ እንደመሆኑ መጠን የግድ ሀይለኛ መሆን አለብኝ:: በጠላት አስቀድሜ ሳልታይ የጦር ግንባር መድረስ እንዳለብኝ ትረዳለህ::"



አዎ ግን ይህን ያህል ቁጥር ያለው ሠራዊት ከሴቶች ከልጆች እና እንስሳቱን ጨምሮ ሳይታይ እንዴት ነው 250 ኪሎሜትር ርቀት የሚጓዘው አልኩኝ::

"መሄድ አለበት እናም ይሄዳል" አጭር መልስ ነበር::

ተሰናብቼ ወደ ድንኳኔ አመራሁ:: ይህ ብልህና ጠንካራ ሐበሻ ሰው አስደንቆኛል:: አመለካከታቸውና አቀራረባቸው አውሮፓዊ ሰው ነው የሚያስታውሱኝ:: ቁመናቸው ከመካከለኛ ቁመት በላይ የተሟላ የተደላደለ ሰውነት ሲኖራቸው ወፍራምም አልነበሩም:: ፀጉራቸው ጨብረር ያለ ሲሆን ፊታቸው እንደከብነት የቃጣውና አጠር ያለ በሥነ ሠርአት የተቆረጠ ፂም አለበት:: ግንባራቸው ሰፋ ያለ ሲሆን አይናቸው ገለጥ ያለ አመለካከት ከፈገግታ ጋር ያሳያል:: ሃምሳ አመት ዕድሜ ያለፉቸው በቅርቡ ነው::

ለሀያ አምስት ቀናት ቆይታ ባደረግንበት በዚህ ቦታ የደጃዝማች ጤንነት በየቀኑ እየተሻሻለ ሲሄድ ማየት አርከቶኛል:: ሐበሻ ሲታመም የፀሐይ ብርሃን ሆነ ሌላ ብርሃን እንዳይጥልበት ራሱን ዘግቶ ነው የሚቀመጠው:: ብርሀን ሲጥል አደገኛ ነው ተብሎ ነው የሚታመነው:: በጨለማው ምክንያትና በታሸገው አየር ምክንያት በሽታው እየከፋ በመሄድ የማገገሚያ ጊዜው ይራዘማል:: ከመጣሁ በሶስተኛው ቀን ግን ለአንድ ሰአት የሚሆን ውጭ ወጥተው በመቀመጥ ንፁህ አየር እንዲያገኙ አሳመንኳቸው:: ከዚያ በፊት ደግሞ የድንኳኑ በር እንዲከፈትም መከሬ ይከፈት ጀመር:: ውጭ ወጥተው በብርድ ልብስ ተሸፍነው የሚመች ወንበር ላይ መቀመጡን እየወደዱት ስለመጡም ቀኑን በብዛት በዚህ መልክ እንደተቀመጡ አሳለፉት:: ብዙ ጊዜ እንቅልፍ ያስቸግራቸዋል፤ ያን ቀን ማታ ግን እንደወደቀ ግንድ ጥሩ እንቅልፍ ተኝተው እንዳደሩ በነጋታው ነገሩኝ::

በነዚህ ቀናትም እኔም የካምፑን አኗኗር ለማጥናት አጋጣሚ አገኘሁ:: ከብዙዎች የደጃዝማች መኮንኖችና አዛዦችም ጋራ ተዋወቅሁ:: የመኮንኖችን የጀግንነት ታሪኮችና ለጌታቸው ያላቸውን ታማኝነት እሰማ ነበር:: ሁሉም በደጃዝማች ዕድሜ ክልል ያሉ ሲሆን በአሥራ ስድስት አመታቸው አፄ ሚኒሊክ የደጃዝማችነት ማዕረግ ሰጥተው የክፋ ገዥ ካደረጓቸው ጊዜ ጀምሮ አብረው ያገለገሉ ናቸው:: በብዙ ጦርነቶች ጎን ለጎን አብረው የተዋጉ ሲሆን ለነዚህ ሁሉ አመታት በድል ሆነ በውድቀት ሳይለያዩ አብረው የቆዩ ናቸው:: ቆራጥና የማያወላውሉ ወንዶች ናቸው እኔም በቀላሉ ወደድኳቸው::

በተጨማሪ ከደጃዝማች የንስሐ አባት አባ ጌታሁን ጋራ ተዋወቅን:: አባ ጌታሁን የዳባት ቤተክርስቲያን አለቃ ሲሆኑ ሀብታምና ተለሚነት የነበራቸው ናቸው:: መልካቸው እንደ ሥዕል የጠራ የሚያምር ነው:: የሚያሳዩት እንገት የደፋ አመለካከት ቢሆንም በውስጣቸው ኩራት እንዳለባቸው ያስታውቃል:: ሁለታችን ግን ልብ ለልብ አልተገናኘንም:: እኔ ያሰብኩዋቸው እንደ አስመሳይ አድርጌ ሲሆን እሳቸው ደግሞ እምነት የለሽ ወይም ፀረ ሀይማኖት አድርገው ነው የሚያስቡኝ:: ሁለት የማይገናኙና የማይተማመኑ አመለካከቶች ናቸው::

ጥቅምት ሀያ ሶስት ንጉሡ የነገሱበት ቀን ነበር:: ቀኑን በማክበር ለአምስት ሺ መኮንኖችና ወታደሮች ግብር ሊደረግ ነው:: ሁለት ትልልቅ የሾላ ዛፎችን እንደጣራ በማድረግ በእንጨትና በቅጠል የታጠረ በአንድ ጊዜ አንድ ሺ ሰዎች ማስተናገድ የሚችል ዳስ ተሠራ:: የአካባቢው ገበሬዎች ከበአሉ በፊት አምስት ሺ እንጀራና ሃምሳ ጋን ጠላ እንዲያቀርቡ ግብር ተጥሎባቸው ነበር:: የደጃዝማች አያሌው ወጥ ቤቶች በየጦር ግንባሩ አብረው የሚጓዙ ስላሳ የሚሆኑ አገልጋይ ሴቶች ያሉበት ሲሆን ለድግሱ የሚያስፈልገውን ጠጅና ወጥ እንዲያዘጋጁ ሃላፊነት ተጥሎባቸዋል::

አዳራሹ ውስጥ ለዝቅተኛ መኮንኖችና ለባለትዳር ወንዶች የተለየ ማዕድ ተዘጋጅቷል:: እንደጠረጴዛ ሆኖ የተሠራው ከሥር በተተከሉ ጉራጅ ግንዶች ላይ የተዘረጋ የቀርከሃ ሳጠራ ነው:: ርዝመት ያለው ሲሆን ስፋቱ ከግማሽ ሜትር አይበልጥም:: ላዩ ላይ እንደጠረጴዛ ልብስ ሸማ ተዘርግቶበታል::

በአዳራሹ በአንድ በኩል ደግሞ ከፍ ያለ መድረክ ተዘጋጅቷል:: ላዩ ምንጣፎች ተዘርግተውበታል:: የአለቃው የደጃዝማች መቀመጫ ተለይቶ ይታወቃል ምክንያቱም ምርጥ ምንጣፍ የተዘረጋበትና ሁልጊዜ የሚቀመጡ ሁለት ትራሶች ስላሉበት ነው::

ሞሰቦች ደግሞ በሚገባ ርቀት ተሰልፈው ተቀምጠዋል:: እነዚህ ደግሞ ለተከበሩ እንግዶች ማዕድ መሆናቸው ነው:: የደጃዝማች ቦታ ላይ ሞሰብ አልተቀመጠም:: ደንቡ ሞሰቡ የሚመጣው ደጃዝማች ከተቀመጡ በኋላና ሞሰቡ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሲሰጡ ብቻ ነው:: ይህም የሚደረገው በምግቡ ላይ መርዝ እንዳይደረግ ለመጠበቅ ነው:: በአቢሲኒያ በዚያን ጊዜ ሰዎችን መመረዝ ደጋግሞ የሚታይ ነገር ነው:: እንደሳቸው ከፍ ያለ ሥልጣን ወይም ማዕረግ ያለው ሰው ከምቀኛና ከጠላቶች ሁል ጊዜ መጠንቀቅ አለበት::



ሁሉም ከተዘጋጀ በኋላ ደጃዝማች በጥቂት አገልጋዮች ታጅበው ወደ አዳራሹ ገቡ:: ከሳቸው ቀጥሎ ደግሞ የከብር እንግዶች ወደ ውስጥ እንዲገቡ ተጠሩ:: የከብር እንግዶችን ተከትለው የንስሐ አባትየው ገቡ:: ሁሉም በደጃዝማች ግራና ቀኝ በኩል ተቀመጡ:: ለእያንዳንዳቸው ከፊት ለፊታቸው የተከደኑና የተሸፈኑ ሞሰቦች ተቀምጠዋል:: ሁሉም ተጋባዦች እንደማዕረጋቸው እየገቡ ተቀመጡ:: ከደጅ በኩል ውሀ በማስታጠቢያ ይዞ የቆመ አገልጋይ ስለነበር ሁሉም ከመግባታቸው በፊት እጃቸውን ታጥበዋል::

ደጃዝማች ምልከት እንደሰጡ ዋናው አሳላፊ በንፁህ ጨርቅ ላይ የተቀመጠ እንጀራ ይዞ ገባ እሱን ተከትለው ሌሎች አሳላፊዎች የቀረውን ምግብና መጠጥ ይዘው ገቡ:: ሁሉም እንግዶቹ ከተቀመጡበት ተነስተው ቆሙ የደጃዝማች ሞሰብ ከቀረበና ከተከፈተ በኋላ የንሰሐ አባትዬው የቡራኬ ፀሎት አደረጉ::

አሳላፊውም እንጀራውን ቆርሶ ከየወጡ አይነት ካራሰ በኋላ ሞሰብ ላይ አስቀመጠ:: ደጃዝማችም ከእያንዳንዱ ቁራሽ ትንሽ ጉርሻ እያነሱ አሳላፊውን አጎረሱት:: ለሳቸው የሚቀርበው ምግብ አይነት መርዝ እንዳይደረግበት ሐላፊነቱ የራሱ የዋናው አሳላፊ ነው::

ደጃዝማች መብላት ጀመሩና ለሌሎችም ምግብ እንዲጀምሩ ምልከት ሠጡ:: ሌሎች ተጋባዦች የቀረበላቸውን ሞሰብ እየከፈቱ መብላት ጀመሩ:: የነሱ ሞሰብ እንጀራና ወጡ አንድ ላይ ስለቀረበ ሳይቆዩ ወዲያውኑ መመገብ እንዲጀምሩ ይረዳቸዋል:: ቀጥሎ ደግሞ የጠጅ አሳላፊው ጠጅ በማንቆርቆርያ ይዞ ቀረበና ለደጃዝማች ከመቅዳቱ በፊት ራሱ መጀመሪያ መቅመስ ነበረበት:: ስለዚህ በእፍኙ ላይ ትንሽ ከቀዳ በኋላ ፉት አድርጎ ጠጣ:: ጠላውም እንደዚሁ ለእንግዶቹ ይቀርብ ጀመር::

ደጃዝማች ትንሽ ከበሉ በኋላ በር ላይ የቆመውን ሌላ ዋና አሳላፊ የትኞች እንግዶች ናቸው ወደ ውስጥ ያልገቡ ብለው ጠየቁ:: ዋናው አሳላፊ የእንግዶችን ስምና ማዕረግ በደንብ ማወቅ አለበት አዲስ የመጣ ቢሆንም:: ተከትሎም ደጃዝማች ውጭ የቀሩትን እንግዶቹ ማን ማንን ተከትሎ እንደሚገባና እንዴት እንደሚቀመጥ ትዕዛዝ ሰጡ:: አቀማመጥ ትልቅ ነገር ነው:: አንድ እንግዳ በስህተት ያልሆነ ቦታ ወይም እንደማዕረጉ ካልተቀመጠ እንደስድብ ነው የሚቆጠረው::

ሰዎቹ በቦታቸው እንዲቀመጡ በሚደረግበት ጊዜ ሌሎቹ ተራ አሳላፊዎች እንጀራና ወጥ በጠረጴዛው ላይ ማስቀመጥ ቀጠሉ::



ደጃዝማች ኢያሴው ብሩ (ላይብራሪ ኦፍ ኮንግረሰ)





ደጃዝማች እያሴው ብሩ ከጦር አለቆቻቸው ጋር(ላይብራሪ ኦፍ ኮንግረስ)

ከውጭ በኩል ደግሞ ከፍ ያለ ግርግርና የጩኸት ድምፅ ይሰማ ጀመር:: ወደ ውስጥ ለመግባት ከሚጋፉት ወታደሮች ነበር የመጣው:: እርቧቸዋል እንደገና ደግሞ ምግቡ እነሱ ሳይደርሳቸው ያልቃል የሚል ፍራቻም አለባቸው:: ሁለት በትር የያዙ ጠንካራ በር ጠባቂዎች በመግቢያው ግራና ቀኝ በኩል ቆመው የሚገባውን ሰው ይቆጣጠራሉ::

ከዚህ በፊት እንዲህ አይነት ግብር ሲጣል ያላየ ሰው ቀጥሎ የሆነውን ነገር መረዳት ይቸግረዋል::

ግርግርና ጫጫታው ተቀይሮ ወታደሮቹ እየተጋፉ ወደ አዳራሹ ዘለቁ:: እርስ በራሳቸው እየጮሁና እየዘለሉ አንዱ በአንዱ ላይ መጋፋት ቀጠሉ:: በትር የያዙት ጠባቂዎች በዱላቸውና በእጃቸው ዳሱን ጥሶ የሚገባውን ሰው በተቻለ አቅም ገፍተው ለመያዝ ይታገላሉ:: በእንደዚህ አይነት ግርግር ዱላው የት እንደሚያርፍም አይታወቅም:: ጭንቅላት ይፈረከሳል፡ አይን ይፈሳል፡ መሬት ላይ የወደቁ ሰዎች ደግሞ ተረግጠው ህይወት ማለፍም ይደርሳል::

ያለው ቦታ በሙሉ በእንግዶች ተይዞ ሲያልቅ ውጭ የቀሩት ውስጥ የገባው በልቶ እስኪወጣ ድረስ ተራቸውን የግድ መጠበቅ አለባቸው ::

በአጭር ጊዜ ውስጥ እንጀራና ወጡ ድራሹ ይጠፋል:: ቀጥሎ የሚቀርበው ወይም ሁሉም የሚጠብቀው ዋናው ምርጥ ምግብ ጥሬ ሥጋ ነው::

ጥሬ ሥጋው እስከሚቀርብ ጠላ በማንቆርቆሪያና በብርሌ ይሠጣል:: ጥሬ ሥጋውን ደጃዝማችና ታላላቅ እንግዶች ይጀምራሉ:: ምርጥ ብልት እየተቆረጠ ይቀርብላቸዋል:: ሥጋውም በደንብ ከደለበ ከብት ነው የሚሆነው:: ሌሎች ወታደሮች ሥጋው ከማንኛውም ከብት ይምጣ ብቻ የተሠጣቸውን ብቻ መብላት ነው::

ሥጋውን ተሸከመው የሚዞሩ አገልጋዮች ናቸው:: ሥጋው በብልት በብልት ነው የሚቆረጠው:: እኩል እኩል ድርሻ እንዲደርሳቸው ይደረጋል:: አንዱ ድርሻ ለአምስት ሰው እንደሚሆን እየሆነ ነው የሚሠጠው:: ስለዚህ አንድ ሰው በግምት አምስት ኪሎ የሚሆን ሥጋ ይደርሰዋል ማለት ነው:: ይህ ማለት ደግሞ አንድ በሬ ከሃምሳ እስከ ስልሳ ወታደሮች ይመግባል ማለት ነው:: እያንዳንዱ ሰው አገልጋዮች አንጠልጥለው ከያዙት ሥጋ በቢላዋ የእጅ ጭብጥ የሚያህል ከቆረጠ በኋላ ለጉርሻ የሚበቃውን ያህል በጥርሱ ነክሶ ይዞ በያዘው ቢላዋ ከስር ወደ ላይ ከጥርሱ እስጠግቶ ይቆርጣል:: ይህ አይነቱ አበላል ልምድ ይጠይቃል እለዚያ ከንፈርን ጨምሮ የአፍንጫን ጫፍ መቁረጥም ሲያስከትል ይችላል::



መጀመሪያ ላየው ሰው የጥሬ ሥጋው ሽታ በተጨማሪ የአውሬ ያህል አፍጥጠው ጥሬ ሥጋውን የሚበሉትን የአቢሲኒያ ሰዎች ማየት በጣም የሚያስፈራ ነበር:: የኋላ የኋላ ግን እኔም ራሴ መብላት ለመድኩና ጭራሹን እየወደድኩት መጣሁ:: ለጦርነት ከወጣን ወዲህ ቫይታሚን በሚጎላቸው የምግብ አይነቶች ተወስነን መከረም የግድ ነው:: ስለዚህ እንደዚህ አይነት የሥጋ ምግብ በማግኘት ጤንነታችን ተጠብቆ መቆየት ይቻላል::

በአቢሲኒያ ታሪክ ጥሬ ሥጋ መብላት የቆየ ጥንታዊ ባህል አይደለም:: የተጀመረው በ16ኛው ክፍለ ዘመን በግራኝ አህመድ[1] ወረራ ጊዜ ነው:: በጣም አክራሪና ጨካኝ ስለነበር ክርስቲያኖችን እያሳደደ ሀይማኖታቸውን ከደው የሱን እምነት ካልተቀበሉ ያለቃይና ይገላቸው ነበር:: ስለዚህ የአቢሲኒያ ሰዎች የግድ መሸሸና በየተራሮችና በየጫካዎች መደበቅ ነበረባቸው:: ለመኖር ደግሞ ይዘዋቸው የሄዱትን የቤት እንስሳት መመገብ ነበረባቸው:: ተደብቀው ስለሚኖሩ ግን እሳት ማንደድ አይችሉም:: ስለዚህ የግድ ጥሬ ሥጋ መመገብ መጀመራቸውና መልመዳቸው የሚያስገርም አይሆንም:: ቀላልም አማራጭ ነበር፤ እሳት እያስፈልግ ማብሰያ ቁሳቁስ እያስፈልግ:: እንስሳው ወዲያው እንደታረደ ጠጋ ብሎ ምግብ መጀመር ይቻላል:: በስንፍና አመለካከት ቢሆን ያለድካም በቀላሉ የሚገኝ ነገር ሁልጊዜ ጥሩ ነው:: ጣዕሙም ቢሆን ጥሩ ነው:: እንግዲህ በአቢሲኒያ ከዚህ በመነሳት ነው ጥሬ ሥጋ ተፈላጊ የምግብ አይነት የሆነው::

የሆኖ ሆኖ ይህ ምግብ ደግሞ የራሱ ጉዳትም አለው:: ያም በኮሶ በሽታ መያዝ ነው:: ሁሉም ዕድሜያቸው ከሁለት አመት በላይ የሆናቸው አቢሲኒያውያን ቅድመ አያቶቻቸውን ጨምሮ ኮሶ አለባቸው:: በኮሶ ያልተያዘ ሰው ይኖራል ብለው አያስቡም:: እንግዲህ በኮሶ ያልተያዘ ሰው ቢኖር ከጤነኛ ሰውም አይቆጠርም:: ውቃቢው ጥሎት ሄዷል ነው የሚሉት:: በነሱ አስተሳሰብ የኮሶው ትል እንኳን ሰውየውን ማወቅ ወይም መቀበል አልፈቀደም::

---

*1.ግራ እጅ ስለሚጠቀም "ግራኝ አህመድ" ኢትዮጵያኖች የሠጡት ስም ነው:: ሙሉ ስሙ አህመድ ቢን ኢብራሂም አልጋዚ ነው:: በ1506 -በ1543 እኤአ፤ በልጅነቱ የወታደራዊ ሥልጣናም ሊድርን ነበር:: የእስልምናን ሀይማኖት በሠይፍ በኢትዮጵያ እንዳስፋፋ ይነገርለታል:: በጎንደር ደምቢያ የሚባል ቦታ የግራኝ አህመድ ዋና ካምፕ ነበር:: (ከተለያዩ መረጃዎች የተዘገበ)*

የኮሶው ትል ከመጠን በላይ እንዳያድግ ለማድረግ በየሁለት ወሩ መድሃኒት ይወስዳል:: ተወላጆቹ ብዙ ከእፅዋት አይነቶች መድሃኒቶች የሚጠቀሙ ቢሆንም እንደኮሶ ዛፍ በብዛት የሚጠቀሙት የለም:: የዚህ ዛፍ (ሃገኒያ አቢሲኒካ Hagenia Abyssinica) ፍሬውም ሆነ አበባው ለጥቅም ይውላል:: ይህ ተክል ከባህር ወለል ከ2500 ሜትር ከፍታ በታች ጭራሽ አይበቅልም:: ስለዚህ መድሃኒቱ ከገበያም ይገዛል ወይም ተክሉ ከሚያድግበት አካባቢ ቀጥታ ይለቀማል:: ለአንድ ሰው ለመድሃኒት የሚሠጠው የእጅ ጭብጥ የሚያህል ሲሆን መድሃኒቱ ከውሃ ወይም ከማር ጋራ ተለውሶ ይደቆስና በጠዋት በባዶ ሆድ ይወሰዳል::

የኮሶ መድሃኒት ሀይለኛም ነው ሆድ ቁርጠትና ሠገራ የግድ ነው የሚመጣው ብዙ ጊዜም ማጥወልወል ያስከትላል:: ሐይለኛ የሠገራ መመላለስ ቢያመጣም ጠቅላላው ትል እንዳለ ከነጭንቅላቱ አልፎ አልፎ ነው የሚወጣው::

የኮሶ መድሃኒት መውሰድ እንደተቀደሰ ስርአት ስለሚቆጠር ሥርአቱን ማደናቀፍ ወይም መረበሽ አይቻልም:: መድሃኒት ከመወሰዱ ከአንድ ቀን በፊት ሰውየው ጓደኞቹን ይሰናበታል:: በሚቀጥለው ቀን በጥዋት መድሃኒቱን ሲወስድ መድሃኒቱን ያዘጋጀው አንድ ሰው ብቻ ነው አብሮት የሚሆነው:: ከዚያ በኋላ ብቻውን በር ዘግቶ ይቀመጣል:: ሙሉ ቀን ከቤተሰብ በስተቀር ሌላ ሰው ዝር አይልም አለበለዚያ ጥላ ይጥልበትና መድሃኒቱ ይረከሳል ወይም አይሰራም ይባላል:: ይህ የጥላ ነገር የመጣው ቤቱ አንድ መግቢያ ብቻ ስላለው ብርሃን የሚገባው በዚያ በኩል ስለሆነ ሰው ከጋረደው ብርሃኑ ስለሚሸፈንም ነው:: ጥላ አደገኛ ነው ተብሎ የሚታመነው:: ስለዚህ ነው ጠያቂ ሳይመጣ ብቻ መሆን የሚፈለገው::

በሌላ በኩልም ቢሆን የኮሶ መድሃኒት ሲወሰድ የሚደረገው ሥርአት ሌላ ጠቀሜታ አለው:: *(ዶክተር ሀኑር ለሀኪምና ባለሙያዎች ማሀበር በዚህ ጉዳይ ላይ ባደረገው ንግግር ትክክለኛ ነበር)*:: ጉዳዩ እንግዲህ የኮሶ መድሃኒት የወሰደን ሰው ምንም አይነት ትዕዛዝ ወይም ሥራ መስጠት አይቻልም:: በማንኛውም የሥልጣን ሀላፊነት ወይም ደረጃ ላይ ቢሆን የኮሶ መድሃኒት ከወሰደ ፈቃድ ይሠጠዋል:: የአቢሲኒያ መንግስታዊ ሥራ በዚህ በኮሶ መድሃኒት ምክንያት ምን ያህል እንደሚስተጓጎል ለማንም ግልፅ ነው:: አገረ ገዥ፤ ሚኒስትር፤ አሽከርና አገልጋዮችን ጨምሮ የኮሶ መድሃኒት በየጊዜው በመውሰድ ለብቻቸው ተከልለው ማንም ሳይረብሻቸው በሰላም ሲያጥወለውላቸው ይውላሉ::



# ምዕራፍ አምስት

## አያሌውን ተከተልኩ

ጥቅምት ሀያ ስድስት ከጋሞ ካምፕ ተነሳን:: በስሜን በኩል አስር ኪሎ ሜትር ርቀት ወደሚገኝ አዲ እትየ የሚባል ቦታ ለመጠጋት ነው:: በብዙ በተለያዩ ምክንያቶች በዚህ ቦታ ላይ ለብዙ ሳምንታት እንድንቆይ ሆነ:: የመጀመሪያው ምክንያት ሁሉም ሠራዊት ተጠቃሎ አንድ ላይ አልገባም:: እንቅስቃሴው ገና አየተጀመረ ነበር እና ግማሹ ዘማች ከቤቱም አልወጣም::

ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ከታች በቆላው የወባ በሽታ አየገነነ ነበር የዝናቡ ወራት አያለቀ ስለነበር ትግራይና የተከዜ ወንዝ ደግሞ የሚያቋርጡት ሆኖ አልተገኘም:: የሞላው ወንዝ መጠን እየወረደ እንደሆነም ወሬ ተነገረን::

ሶስተኛው ምክንያት ደግሞ ከአዲስ አበባ በመጣ ቴሌግራም ደጃዝማች አያሌው በየትኛው አቅጣጫ ወደ ግንባር እንደሚሄዱ አዲስ ትዕዛዝ እስከሚመጣ ድረስ እንዳይንቀሳቀሱ የሚል ነው:: የመጀመሪያው ትዕዛዝ በኤርትራ ምዕራባዊ ድንበር በዚያን ጊዜ የእንግሊዝ ሱዳንን ወደ የሚያዋስነው ሰቲት ወደ ተባለ ቦታ እንድንሄድ ነበር:: እንግዲህ ያ የዘመቻ እቅድ በአዲስ አበባ ታጥፏል ማለት ነው ምክንያቱ ለኛ አልተነገረንም:: ቆይተን ነው ያወቅነው::

አዲ እትየ ደስ የሚል ቦታ ነው ተራሮችና ጫካ አረንጓዴ ሜዳዎች ሞልተዉታል:: የድሮ ገዳም ፍርሥራሽ ያለበት ከፍታ ቦታ ለዋናው ካምፕ እንዲሆን ተመረጠ:: ያረጁ ትልልቅ ዛፎች ቅርንጫፎች ሽፋን ስለሚሰጡ ድንኳኖችን ከስር ተክለን እንደሚመቸን ለማድረግ ቻልን::

የደጃዝማች መኖርያዎች ሶስት ውድ የሆኑ በተርታ የተተከሉ ድንኳኖች ሲሆኑ አንደኛው ለእንግዳ መቀበያ አንደኛው ለምግብ ሶስተኛው ደግሞ ለመኝታ ነበር::

መኮንኖችና ወታደሮችም ድንኳናቸውን በቡድን በቡድን ዙርያውን ይተከሉ ጀመር አዲስ የሚቀላቀለው ጦርም እንደዚያው እየተከለ ካምፑ ዙርያውን በብዙ ማይል የሚቆጠር ርቀት ድረስ ሆነ።

የጦሩን ቁጥር መገመት እስቸጋሪ ነበር ምክንያቱም አጠገብ ከሰፈረው በስተቀር ሌሎች ተደብቀው ነው የሰፈሩት እኔም ማየት አልቻልኩም።

የአቢሲኒያ የጦር መሪ ሌላ ጊዜ ካምፑን ከፍት መሀል ሜዳ ላይ ያደርግና ወታደሮቹን በዙሪያው እንዲሰፍሩ በማድረግ ቁጥሩን በማወቅ ከጠላቱ ጦር ቁጥር ጋር ያወዳድራል። በዚህ ቦታ ግን የጦር መሪው የጦሩን ቁጥር ማወቅ ሆነ ማሳየት አይችልም።

በእዲ እትየ ቆይታችን በመጀመሪያዎቹ ቀናት ስአዲስ አበባ መንግስት ቴሌ ግራም ልኬ ነበር፤ እሱም በውላችን መሠረት ደጃች ኢያሴው ሙሉ በሙሉ ተሸኳቸው ስለሚገኙ እውሮፕላን ተልኮልኝ እንድመለስ ነበር። ደጃዝማች እብሬ እንድቆይ ይፈልጉ ስለነበረ ቴሌ ግራሙን እንድልከና እንድጠይቅ እያመናቱ ነበር የፈቀዱልኝ።

አውሮፕላን አስኪላከልኝ በምቆይበት ጊዜም ጊዜዬን የማሳልፈው ጥዋት ጥዋት ሕሙማንን በማየት ነበር። ሰዎች መሄዴን ሲሰሙ ያለ የሌለ ህመም ይዘው መቅረብ ጀመሩ። ከሁሉም በላይ ብዙ ጥርስ ነቀልኩ፤ ይህም ተደምሮ ሰሰባት እመታት ሰሰራ ካወለቁት በላይ ነበር። ወታደሮች ሌላው ቀርቶ የታመመ ከብቶቻቸውን ይዘው መምጣት ጀመሩ። የከብት ህክምና ትምህርት ስላልነበረኝ ይህንን መከራከሪያ ምክንያት አቀረብኩኝ። "እኔ የሰው ዶክተር ነኝ። እህያህን ዛሬ ባከምልህ የአህያ ዶክተር እሆናለሁ እና ወደፊት ደግሞ አንተን አሞህ ባከምህ የአህያ ዶኩተር ስለሆንኩ አንተም እንደአህያ ነው የምትቆጠረው።"

ይህ ብልሃት ሠራ ምክንያቱም ስህገሬው ሰዎች ከትልቁ ሰድብ አንዱ አህያ መባል ነው።

ምሳ ከደጃች እያሴውና ከሌሎችም ጋራ ከበላሁ በኋላ የማውቃቸውን ሰዎች ለመጠየቅ ወይም ህሙማኑን ለመጠየቅ ወጣ ብዬ እዘዋወራለሁ። እንደዚህ በእግሬ በምዘዋወርባቸው በአንዱ ቀን ለሕይወቴ የሚያሰጋ ነገር መኖሩን ተረዳሁኝ። ወደ ጦር ግንባሩም እየተጠጋን በሄድን ቁጥር ይህ ለኔ የሚያስጋኝ ነገር እየጨመረ እንደሚሄድ እርግጠኛም ሆንኩ።

ወታደሮች አካባቢ እሰፍ ብዬ ሰሄድ የምሰማው ንግግር "ይሄ ነጭ ሰው እዚህ ምን ያረጋል? ነጭ ሰው እዚህ ምን ሲረባ ነው? ነጮች እርስ በእርስ



ይ·ተ·ጋገዙ የለ እሁን ደግሞ ጦርነት ላይ ሰለሆን እየሰለለም ይሆናል። በጊዜ ማሰውገድ ነው የሚበጀው። ብቻ ጦር ሜዳ እንድረስ እንጂ ጥይት ከየት አቅጣጫ እንደተተኮሰ ማን ያውቃል።"

አልፎ አልፎ ደግሞ "ዝም በሉ! ጮሃችሁ እትናገሩ፤ እኛ አገር ስለተወለደ ቋንቋችንም ይናገራል" የሚል ንግግር እሰማለሁ።

ብዙ ጊዜ ደግሞ ሰዎች በፊት ለፊት ይተናኮሉኝም ነበር። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ምንም ምህረት ሳላሳይ ከንጉሡ የተላከሁ ሀኪም በመሆኔ ሥልጣኔን በመጠቀም የተተናኮለኝ ሰው በአደባባይ ቅጣት እንዲቀበል እጠይቃለሁ። ቅጣቱም ይፈፀማል። በዚህ አይነት በካምፑ ውስጥ ለቆሰሉና ለታመሙ ርዳታ እንድሠጥ በንጉሡ የተላከሁ መሆኔን እና ለሰኔም ደህንነት ደጃች እያሴው ሀላፊነት የወሰዱ መሆኑን እንዲታወቅ ሆነ። እንደዚያም ሆኖ በጎሪጥ ነበር የሚያዩኝ ምክንያቱም አቢሲኒያኖቹ በውስጣቸው ሁሉንም ፈረንጆች በጥርጣሬ ማየት ሰስጀመሩ ነው።

እኔ ተረድቻቸዋለሁ። በዚህ ምክንያትም ቂም ሆነ ጥላቻ እልያዝኩም ነገር ግን ያለችኝን በከር የተንጠለጠለች ህይወቴን ለማራዘም እራሴን ለመጠበቅ ምን ማድረግ እለብኝ ብዬ ደጃዝማችን ጠየቅሁ። ያለውን አደጋ ስለተረዱ ብቻዬን እንደማልወጣ ቃል ገብተው በሄድኩበት ቦታ እብረውኝ የሚሄዱ ሀምሳ ወታደሮች መደቡልኝ።

በዚያው ልክ ደግሞ ብዙ በጦርነቱ ጊዜ ትልቅ እርዳታ ያደረጉልኝ ወዳጆችና ጓደኞችም ነበሩኝ። ከነዚህ መሀከል አቶ ማሞ ባለቤቱ እና ቤት ውስጥ የተወለደች የእገልጋይ ልጅ ግን እንደልጅ የሚያሳድጓት የሰምንት አመት ልጅ አፀደን ይጨምራል። በከፉ ጊዜ እነዚህ ሰዎች ለኔ ያላደረጉልኝ ነገር የለም በአንድ አጋጣሚም አቶ ማሞ ህይወቴን አድኖልኛል። እነዚህ ጓደኞቼ ይህንን ቀጥሎ የምፅፈውን መስመር ቢያነቡ ምኞቴ ነው። እሱም እነሱ ለሀኪማቸው ላደረጉለት በጎ ነገር ምስጋና እንዳለውና እንደሚገባቸው ለሁልጊዜም የሚያስታውሰው ነገር መሆኑን ነው።

አቶ ማሞ ከአዲስ አበባ በመንግሥት ወደ ደጃዝማች እያሴው በመቶ የሚቆጠሩ የጥይት ጭነቶች እንዲያደርስ የተላከ ሰው ነው። ባለቤቱም አብራው ተከተለች ቢቆስል ልታስታምመው፡ ቢሞትም ልትቀብር ነው። ትንሿ አፀደም ሰባት መቶ ኪሎሜትር በእግርዋ ነው የተጓዘችው። የሚያዞር በሽታ ስላለባት በበቅሎ መሄድ አትችልም ነበር። ካምፕ ባደረግንበት ቦታ ሁሉ እፀደ እሳት አንድዳ፤ ቡና ቆልታ፤ ፈጭታ ታፈላለች። በእርሷ ምትክ ቡና

አፈላለሁ ያለ ቢጠነቀቅ ይሻለዋል ምክንያቱም እሷ እንደምታፈላው ቡና የሚሆን የለም ነበር:: አፏ ሰፋ ብሎ ከፍርግፉግ ጥርሶቿ ጋር ደፍጠጥ ያለ አፍንጫ ያላት የቤት ልጅ ነበረች:: ከዚያ በተጨማሪ በጣም ብልህና አሰቂኝም ነበረች:: ዘፈን መዝፈንና መወዛወዝ፣ ተረት ማውራት የሚያህላት ሰው አልነበረም:: ሰውንም ሆነ እንስሳውን አነጋገርና አያያዝ ትችልበታለች:: በሚገርሙ ቀልዶቿ በሣቅ እንፈነዳለን:: አባባሎቿ ሁሉ የሚገርሙ ነበር (ትንሿ የጦር ጓደኛዬ. ስለአንቺ ሳሰብ እናትሽ እንደምታስብልሽ ሁሉ መጨረሻሽ ምን ይሆን ብዬ አሰባለሁ:: አንቺ ትንሽ ጦጣ(በፍቅር አገላለፅ)

አንድ ቀን ህዳር ሁለት ይመስለኛል ከዳባት የተላከ በሰምንት የከብት ጭነት መድሃኒት መጣልን:: ከአዲስ አበባ በአውሮፕላን የተላከ ነበር:: ለደጃዝማች ደብዳቤዎች አብረው ተልከዋል፤ ለኔ ግን አልመጣልኝም:: በአስር ወራት ውስጥ ከቤተሰቦቼም ሆነ ከጓደኞቼ የሰማሁት ምንም ነገር የለም:: ደብዳቤዎቸ እንዲያልፉ ያልተፈቀደበት ምክንያት አስካሁን ድረስ ያልገባኝ እንቆቅልሽ ነው::

በአንደኛው ደብዳቤ ደጃች አያሌውን ተከትዬ አንድሄድ ተፅፎአል:: እኔ በነገሩ ልስማማ አልሰማማበት ለማወቅ ግን ለማንም ጉዳያቸው አልሆነም:: በሚቀጥለው ቀን በደብዳቤው የተፃፈውን የሚያረጋግጥ የቴሌግራም መልከት ተቀበልኩኝ:: ከአሁን በኋላ ምን ማድረግ እችላለሁ? በእጃቢ ወደ አዲስ አበባ እንዳልመለስ የማይታስብ ነገር ነው አገሩም መንገዱም አሰተማማኝ አይደለም:: ከደጃዝማችም የተሠጠኝ መሳሪያ የለኝም:: ደጃዝማች ከሳቸው ጋራ እንድቀርም ስለሚፈልጉ እርዳታ ብጠይቅ እንደሚሠጠኝ ተሰፋ አላደረግሁም::

እንግዲህ ያለሁበት ግንባር እንደሌላው ጦር ግንባር ጥሩም ወይም መጥፎ ሊሆን ይችላል:: ለማንኛውም ወደ ጦር ሜዳ እየሄድኩ ነው:: ረጋ ባለ መንፈስ ዕጣዬን ተቀበልኩና መዘጋጀት ጀመርኩ:: ተዘበራርቀው ተጭነው የመጡት መድሃኒቶች፣ ቁሰል መጠቅለያ ጨርቆች እና የህክምና ቁሳቁሶች እየተፈቱ በሰም በሰም እየሆኑ እንደገና ታሸጉ:: ለማንኛውም በቅደም ተከተል ወይም በከብደት አልተሰተካከሉም :: ይህ ሥራ ብዙ ቀን ወሰደ ነገር ግን እኔ በፈለግሁት መንገድ ሰለተዘጋጅ ደስ ብሎኛል::



ለግሌ የሚሆን ግን የሚረባ ነገር አላዘጋጀሁም:: ትንሽ ልብሶች ነው የያዝኩት:: ያደረግሁት ጫማም ቢሆን ከሶስት ወር በላይ አያዘልቅም:: ወደ አዲስ አበባ ቴሌግራም ልኬ ለአንድ አመት የሚሆን ልብስና ሌላም አሰፈላጊ ነገሮች ያስቀመጥኩበት አረንጓዴው ሣጥን እንዲላከልኝ ጠየቅሁ:: ይህንን ሣጥን በሚመለከት በቴሌግራም ሆነ በደብዳቤዎች በመላው ጦርነት ወቅት ልውውጥ ተደርጓል:: ሣጥኑ የት እንደደረሰ እስካሁን ድረስ የሚታወቅ ነገር የለም፤ እኔም አላየሁትም::

አብረውኝ እንዲሠሩ የተላኩ ሁለት ተጨማሪ ድሬሰሮች መጡ:: ለስምንት አመታት በትሪፖሊ ሆስፒታል የስሩ ናቸው:: ፈጠነ የተባለው ሻል ያለውና ጥሩ የእንግሊዝኛ ችሎታ ያለው በደረጃውም ከፍ ያሰ ስለነበር ዋና ድሬሰር ሆኖ ተመደበ:: ለሶስቱም ድሬሰሮቼ እያንዳንዳቸው ምን አይነት የሥራ ምድብ እንዳላቸው መመሪያ ሰጠሁኝ:: ከዚያ በተጨማሪ የትኛው ዕቃ ወይ መድሃኒት የትኛው ሣጥን ውስጥ እንዳለ እንዲያጠኑ ተደረገ:: ይህም የሚፈለገውን ዕቃ በፍጥነት ለማግኘት እንዲረዳ ነው::

እንደሁኔታውም ቢሆን ሁሉም ነገር በሥነ ሥርአት ተደራጅአቶል ብዬም አሰብኩ፤ ግን የሚበቃ መሣሪያ ስላለነበረኝ ቅር ብሎኛል:: በአዲስ አበባ የመሣሪያዎች ዕጥረትም ስለነበር ከጦሩ ሆሰፒታል የሚያሰፈልገኝን ቁሰል ማከሚያና መለስተኛ ቀዶ ህክምና ማድረጊያ ስላልወሰድኩ የያዝኩት የግሌን መሣሪያ ብቻ ነበር እንግዲህ ይህ የት ያደርሳል:: መንግስት ግን መሣሪያዎች ከአውሮፓ እንደመጡ ወዲያው እንደሚልከልኝ ቃል ተገብቶልኛል::

ሰዎች በእንቅስቃሴ ላይ ሰለሆኑ ተጨማሪ ሰዎች በየቀኑ ይመጡ ጀመረ:: በረጅም መስመር ተጓዦች፡ የተጫኑ አህዮች፡ በቅሎዎች፡ ፈረሶች በታጠቁ ወታደሮች እየተነዱ ከአገልጋዮች ሴቶችና ልጆች ጋር በመሆን ሲመጡ አየን::

በነጋሪት የከተት ጥሪ የከተማው ሰው ወደ ጦር ሜዳ እንዲዘምት ተጠርቷል:: ትልልቅ ግዛት የሚገዛው እያንዳንዱ ራስ ወይም ደጃዝማች የራሱ ነጋሪት አለው በሌላ ከተተካም ነጋሪቱን ለተተኪው እንዲያስረከብ ይደረጋል:: ነጋሪት እንደ ግዛቱ ስፋትና እንደ ገዥው ህይል ከአሥራ ሁለት እስከ አርባ ስምንት በቆዳ የተወጠሩ ከበሮዎች ይኖሩታል:: የከበሮዎቹ ሦስት የተለያዩ አይነት መጠኖች ሲኖሩ በቡድን በቡድን በመሆን በተወሰነ ተራ ይጎሸማሉ:: እንደ ነጋሪቱ አጎሻሸም ለጦርነት ከተት ጥሪ ወይም በሰላም ጊዜ ወይም ለቀብር ጥሪ ይደረግበታል::

ጉዞ በሚደረግበት ጊዜ ከበሮዎቹ በበቅሎ ጀርባ ይሆናሉ:: በቅሎዎችም

ወይ ሁለት ትንንሽ አለዚያም አንድ ትልቅ ከበሮ ነው የሚጫንባቸው፡፡ ነጋሪት መቺው ደግሞ ከበቅሎው ወደ ጀርባ ወደኋላ ይቀመጣል፡፡ ከበሮው በደንብ ፀሀይ ከሞቀ ፀጥ ባለ አኩለ ቀን እስከ ሀያ ኪሎሜትር ርቀት ድረስ ይሰማል፡፡ ግርማዊ የሆነ ታላቅ ድምፅ አለው፡፡

የነጋሪት ጦር ከተት ሲጠራ መሳሪያ መያዝ የሚችል ማንኛውም ወንድ ባላበት የከተማ ሰው ገበሬ ሳይል ሁሉም ሰው ይመዘገባል፡፡ ቄሶች ብቻ ነው የማይሰለፉት፤ ነገር ግን የቤተከርስቲያን አገልጋይ ካልሆነ በስተቀር የቄስ ልጅ እንኳን ቢሆን አይቀርም ፡፡ ብዙ የደረሱ ወንዶች ልጆች ያሉት አባት ከአንድ ልጁ ጋር ብቻ እንዲቀር ይፈቀድለታል፡፡ ባልዋ የሞተባት ሴት ከሆነች ደግሞ አንድ ልጅ ብቻ ካላት ልጁ ከዘመቻ ነፃ ይሆናል ብዙ ልጆች ካሏት ደግሞ አንዱ ብቻ ነፃ ይሆናል፡፡

መሳሪያና ጥይት ደግሞ ራሱ ዘማቹ ነው ማዘጋጀት ያለበት በርግጥ መንግስት ጥይት ያከፋፍላል ነገር ግን የወታደሩ ጥይት ካለቀ በኋላ ነው፡፡ የውጊያ መሣሪያው ደግሞ በየአይነቱ እንደአካባቢውና እንደሰውየው የገንዘብ አቅም ይለያያል፡፡ አንድ ሰው ጠመንጃ ከሌለው ጎራዴውን ይዞ ይወጣል፤ ያም ከሌለው ደግሞ ዱላውን ይዞ ይወጣል፡፡ ግማሹ ወታደር አብዛኛዎቹ የጦር መኮንኖች ከጠምንጃና ሽጉጥ በተጨማሪ ጎራዴ ይታጠቃሉ፡፡

ጎራዴ ረዥም ጠመም ያለ እንደምላጭ ስለት ያለው ብረት ነው፡፡ ከቆዳ በተሠራ አፎት ውስጥ ይደረግና በቀኝ በኩል ከወገብ ላይ በቀበቶ ጠበቅ አድርጎ ይታሰራል፡፡ ሁልጊዜም ቢሆን ይህን መሳሪያ ኢታልዮኖች በጣም ነው የሚፈሩት፡፡ የሚመዘዘው በቀኝ እጅ ወደፊትና ወደላይ በመሳብ ነው፡፡ በአንድ ሥንዝር ብቻ ጠላትን ጭንቅላት አልባ የማድረግ ችሎታ አለው፡፡ ለአቢሲኒያዊው ምርጥ መሳሪያው ነው አጠቃቀሙና አያያዙን ተከኖበታል፡፡ ጎራዴውን የታጠቀ ለታ ወኔው ልክ የለውም፡፡ ያስምንም ውድድር የጀግና ሰው መሣሪያ ነው፡፡

ወታደሮቹ የያዟቸው ጠመንጃዎች ደግሞ የተለያዩ አይነቶች ናቸው፡፡ ጥንታዊው በአፈ ሙዙ ባሩድ የሚጠቀጠቅበት የ1850 አመተ ምህረት ወይም ከዚያ በፊት የተሠራ ሞዴል ነው፡፡ ባሩዱ ከቤት የተሠራ ሲሆን ድንጋይ ወይም የብረት እርሳስ ጋራ ይደባለቃል፡፡ ለመጠቀጠቅም አርጌ ጨርቅ ይጠቀማሉ፡፡ ቤተ መዘከር መቀመጥ የሚገባው ነው፡፡ አንድ ሁለት መቶ

የሚሆኑ የዚህ መሳሪያ አይነቶችን የደጃች አያሌው ወታደሮች ይዘው አይቻለሁ፡፡



በአድሜ ከዚያ ቀጥሎ ሬሚንግተን የሚባል የ1863 ሞዴል ሲሆን ለዚህ መሳሪያም የራሱ ጥይቶች አልተሠሩለትም፡፡ አምስት ከመቶ የሚሆነው የዚህ መሳሪያ አይነት ነው፡፡

በግምት ሰላሳ ከመቶ የሚሆነው ደግሞ በ1870 የተሠራ ፉሲል ግራስ የተባለ የፈረንሳይ 11 ሚሊ ሜትር ካሊበር ጠመንጃ ነው፡፡ ይህም ቢሆን በፋብሪካ የተመረተ ጥይቶች አይጠቀምም ነበር፡፡

የ1880 ሞዴል የሆነ የኢጣልያ ጠመንጃ የራሱ የተመረቱ ጥይቶች የሚጎርስ አይነት ደግሞ ሀያአምስት ከመቶ የሚሆነውን ድርሻ ይዟል፡፡

ዘመናዊ ከሚባሉት ደግሞ የፈረንሳይ ለበል፤ የእንግሊዝ ሊ መትፎርድ፤ የጀርመን ሞውዜር፤ የአውስትሪያ ማንሊቸር እና የኢጣልያው ሞዴል 91 ይገኙበታል፡፡

የዚህ አይነቱ የተደበላለቀ መሳሪያ አይነት መኖር ደግሞ ትልቅ ችግር አለው እሱም ጥይት ማከፋፈል ላይ ነው፡፡ አንድ የወታደር ቡድን ከላይ የተጠቀሱት የመሳሪያ አይነቶች በሙሉ ሊኖረው ይችላል፡፡ ይህን ችግር ግን ደጃች አያሌው በብልሃት ዘዴ አግኝተውለታል፡፡

እያንዳንዱ ሰው እስከ ጦርነቱ መጨረሻ ድረስ ለራሱ ልብሰና ምግብ ሀላፊ ነው፡፡ የወታደር ዩኒፎርም የሚባል ነገር የለም፡፡ ሱሪና ሸሚዝ በላዩ ላይ ሸማ ወይ ኩታ ነው የሚያዘው፡፡ አንድ ተቀያሪ ልብስ፤ ቆርበት፤ ከብርድ ሊብስ ጋራ ይያዛል፡፡

በእንቅስቃሴው ወይም በዘመቻው ጊዜ ለተወሰነ ጊዜ የሚበቃ ምግብ ይሰበሰባል፡፡ የምግብ አይነቶች ደግሞ የሚከተሉት ነበሩ

1. ቆሎ
2. ዳቦ ቆሎ
3. በሶ
4. ጭኮ
5. ሽሮ
6. የጤፍ ዱቄት ለእንጀራ ወይም ለቂጣ መጋገሪያ የሚሆን
7. ሚጥሚጣ ወይም በርበሬ ከሁሉም የምግብ አይነት ጋራ የሚበላ
8. ቡና፣ አሞሌ ጨው
9. የበሬ የበግ ወይም የፍየል ሥጋ ቋንጣ
10. ቅቤና ማር

ይህ ሁሉ ምግብ ከተሰበሰበ በኋላ በስልቻ ይያዛል፡፡ ከቤት ዕቃ ደግሞ የብረት ምጣድ፤ የብረት ድስት፤ የቡና ጀበና፣ የቡና ሙቀጫ፣ መጥረቢያና ማጭድ ይዘናል፡፡ ሌሎች ጥቃቅን የሆኑ እያንዳንዱ ሰው የሚይዛቸው እቃዎችም ነበሩ፡፡

ሰባ አምስት ከመቶ የሚሆኑት ወታደሮች ደግሞ የሚጋለብ ጋማ ከብት፤ የጭነት ከብት እንደንብረታቸው መጠን ደግሞ መዝመት የማይገባቸው አጃቢ ሰዎች ይዘው ይመጣሉ፡፡ ከአጃቢዎች ውስጥ የተገዙ የወንድ አገልጋይ፤ የሴት አገልጋይ ወይም የተቀጠሩ አሽከሮች አሉበት፡፡ ከሰባት አመት በላይ የሆኑ ልጆችም አብረው ዘምተዋል፡፡ የነዚህ ሥራ እንግዲህ ምግብ ማዘጋጀት፤ ውሃ መቅዳት፤ እንስሳቱን መጠበቅ ከሁሉም በላይ ግን የቆሰለ ጌታቸውን መንከባከብ ወይም ሲሞት መቅበር ነው፡፡

ለኔ ግልፅ እንደሆነልኝ አብዛኛው የአቢሲኒያ ሠራዊቱ ቁጥር የተከታዩ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለሠራዊቱ እንቅስቃሴ ትልቅ እንቅፋት ነው የሆነው፡፡ አውሮፓውያን እንደሚጠብቁት የአቢሲኒያ ሠራዊት ፈጥኖ የሚንቀሳቀስ አይደለም፡፡ ተከታዮችን ወደኋላ ትቶ የሚወጣው ዋናው ጦር ከአውሮፓውያን ሠራዊት የበለጠ የመንቀሳቀስ ችሎታ አለው፡፡ እንደዚህ በሚሆንበት ጊዜ ተንቀሳቃሹ ጦር ለሶስት ቀን የሚሆን ስንቅ ይዞ ነው የሚጓዘው ያ ስንቅም ብዙ ጊዜ ቆሎ ነው፡፡ ከሶስት ቀን በኋላ ተመልሶ ከተከታዩ ጋራ መደባለቅ የግድ ነው፡፡ ይህ የእንቅስቃሴ ችሎታ የተወሰነ መሆን በጦርነቱ ጊዜ አስከፊ አደጋ ነው ያስከተለው፡፡





ደጃዝማች አያሌው ብሩ ከግል ዘበኞቻቸው ጋራ ከጦርነቱ በፊት የተነሣ ፎቶግራፍ (ምስጋና ፋንታሁን ጥሩነህ)

# ምዕራፍ ስድስት

## ውዝግብ

በአዲ አትየ ቆይታችን በመጨረሻዎቹ ሳምንታት ሁኔታዎች በፍጥነት ይካሄዱ ጀመር፡፡ በሰቲት ካሉ የደንበር ጠባቂዎች በመጣ መልከት ሶስት የኢጣልያ አውሮፕላኖች በአምቦ አወታ የሚገኘውን የጫካ ምሽግ በቦምብ መደብደባቸው ተሰማ፡፡ በዚህ ምሽግ ብዛት ያለው የምግብ ሥንቅ የተደበቀበት ቦታ ነበር፡፡ ወደ ስልሳ የሚሆኑ በንቦች ተጥለውበታል፡፡ ነገር ግን አንደኛቸውም ቢሆን ግንብ ወይም ቤት ላይ አላረፉም፡፡ ጥቂት ቦምቦች ምሽግ ውስጥ ባለው የውሃ ስፍራ ወደቁ ውሀውም ወደ ቀይ መልከነት ተቀየሮ በውሀው ውስጥ የነበሩ አሳዎችን ገደለ፡፡

የደንበር ጠባቂዎች ደግሞ ውሀውን መጠጣት ይቻል ወይም አይቻል እንደሆነ የኔን ህክምና ዕውቀት በመመርኮዝ ጠየቁኝ፡፡ እኔም በፍፁም ውሀውን እንዳይጠጡ የሚል መልስ ሠጠሁ፡፡ ያ ሁሉ አሳ በአንድ ጊዜ ማለቁ ራሱ ውሀውን ላለመጠቀም በቂ ምክንያት ነበር፡፡ ደጃች አያሌው ሥንቃችን ወደ ገደላማ ቦታዎች ተወስዶ እንዲደበቅ ትዕዛዝ አስተላለፉ፡፡

ከጎጃም ገዢ ከራስ እምሩ በኩል በመጣ ዜና አርባ ሺ ሰው ይዘው ወደ ጦርነቱ ግንባር እየተንቀሳቀሱ እንደሆነ ተሰማ፡፡ በጣና ሀይቅ ምዕራብ በኩል የሚገኝ ጣቢያ አለፋ ደርሰዋል፡፡ ነገር ግን ወደ የትኛው ግንባር ማለትም ወደ ቆላማው ስቲት (የሱዳንን ደንበር ይዞ መሄድ) ወይም ደግሞ በሰሜን በኩል ወደ ትግራይ ግንባር የሚሄዱ መሆኑ ግልፅ ስላልሆነ ወደ ጎንደር ተጉዘው ከዛው ሆነው ትዕዛዝ የሚጠብቁ እንደሆነ ተነገረ፡፡

የራስ እምሩ መልከተኞች በቅርብ የማውቃቸው ሁለት ወጣቶች ናቸው፡፡ ከአዲስ አበባ የመጡ ሲሆን፣ የጦር ሠራዊት አገልግሎት ውስጥ ገብተዋል፡፡ የፈረንሳይ ትምህርት ቤት ስለተማሩ ከሌሎች ሠልጠን ያሉ ናቸው፡፡ የለበሱት ልብሰም ጠቆር ያለ ሰማያዊ የሱፍ ልብስ ነበር የኋላ ኋላ ግን ይህ አለባበስ ለህይወት አስጊ የሆነ አደጋ ማስከተሉ አልቀረም፡፡ ሁለቱም ሰዎች በተጓዙበት



ባልሠለጠነው የሰሜን መንገዶች ከፍል ገበሬው በስህተት የጣልያን ሰላዮች አድርጎ ያያቸው ነበር፡፡ በዱላ እንዳይደበደቡ ራሳቸውን እየደበቁ መጓዝ ነበረባቸው፡፡ ከመድረሳቸው ከአንድ ቀን በፊት ራሳቸውን ለማዳን ቀጥ ባለ ገደል መውረድ ነበረባቸው፡፡ በዚህ አንገት በሚያሰደፋ ጉዟቸው አንደኛው ከበቅሎ ላይ ወድቆ ሁለት የጎን አጥንቶች ሰብራት ደርሶበታል፡፡ ከሰብራቱ ያልቅ በፍርሀት የተነሳ ሞራሉ ወድቋል፡፡ ከዚህ በኋላ እንደ ጓደኞቻቸው መልበስ ቢጀምሩ ምክንያቱን መረዳት ይቻላል፡፡

ሕዳር ዘጠኝ ቀን ለመጀመሪያ ጊዜ የኢጣልያ አውሮፕላን ድምፅ ሰማን፡፡ በርቀት መሆን አለበት፡፡ በአይን ማየት አልቻልንም በጠቅላላው ካምፕ ውስጥ ግን ስሜት በመፍጠር የመነጋገሪያ ርዕስ ሆነ፡፡ በሺ የሚቆጠሩት ወታደሮች በጣም ከራቀና ወጣ ካለ ቦታ ስለመጡ ሞተር የሚባል ነገር እንኳን አይተው አያውቁም፡፡

ጥቂቶቹ አውሮፕላኑ እንደ ንብ አይነት ድምፅ ነው ያለው አሉ፡፡ ምናልባትም ለዚህ ይሆናል የሴት ፆታ የሰጡት፡፡ በሰሜን ንብ የሴት ፆታ ነው ያላት፡፡ የኋላ ኋላ አውሮፕላን ቶሎ ቶሎ መታየት ሲጀመር "አሁን መጣች" መባል ተጀመረ፡፡ ቦምብ መጣል ሲጀመር ደግሞ "እንቁላል ጣለች" ይባላል፡፡ እንዲህ አይነቱ ቀልድ ያለበት አገላለፅ በራስ እምሩ ሠራዊትም ውስጥ ይነገር እነደነበር በኋላ ጎረቤት ስንሆን ለማወቅ ችያለሁ፡፡

የመጀመሪያ አውሮፕላን በታየችበት ቀን መሀመድ ኢማም የሚባል ሰው መጣ፡፡ በጣም ሀብታም አረብ ነው፤ በኤርትራ በሚኖሩ ጣልያኖች ዘንድ የተከበረ ሲሆን በእስልምና አማኞች ዘንድ ደግሞ ታላቅ ተሰሚነት ነበረው፡፡ ምክንያቱም የራሳቸው የነቢዩ መሀመድ የትውልድ ሀረግ ስለነበረው ነው፡፡ በደጃች አያሌው ግዛት ውስጥ በንግድ ሥራ ምክንያት ከደጃች አያሌው ጋራ ትውውቅና ወዳጅነትም ነበረው፡፡

ከአራት ቀናት በፊት ስለ ሰውየው መምጣት ሁለት የቴሌግራም መልእክቶች ስለደረሱን አመጣጡ እንግዳ አልሆነብንም፡፡ አንደኛው ቴሌግራም ከአዲስ አበባ ሰውየው ወደ ደጃዝማች ካምፕ እንደሚመጣ የሚገልፅ ነው፡፡ እንግዲህ ንጉሡ በሚሰጥራዊ መንገድ በሰሜን በኩል የሚሆነውን እንደሚያውቁ ለማሳወቅም ይመስላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ንጉሡና መንግሥታቸው በደጃች አያሌው ላይ ሙሉ እምነት እንደሌላቸው ሆኖ ደጃች አያሌው የሚያደርጉትን ነገር በቅርብ እንደሚከታተሉ ለማሳወቅም ነው፡፡

ስለዚህ እንግዳ ወደ ደጃች እያሌው መምጣት ጉዳይ በአዲስ አበባ በኩል መታወቁ በኤርትራ ደንበር ያለው የቴሌግራም ኦፐሬተር ነው የተጠረጠረው:: ከዚህ በፊት ለንጉሡ መልክቶችን እንዳሳለፈም ይታወቃል:: ምክንያቱም እሱን ጨምሮ በመላው አገሪቱ ያሉ የቴሌግራም ሠራተኞች ደሞዛቸውን መንግሥት ነበር የሚከፍለው::

ጥርጣሪያችን ግን ስህተት ሆኖ ተገኘ:: ከብዙ ወራት በኋላ እንዳወቅነው የደጃች እያሌው የራሳቸው የጦር መኮንን የደንበር ጠባቂዎች አዛዥ የሆነው ቀኛዝማች መንግስቱ ከንጉሡ ብዙ ብር ተከፍሎት እሊቃውን እየሰለለ ነበር:: የቴሌግራም ሠራተኛው ደግሞ እንደሰማሁት ከሆነ በደጃች እያሌው እየተከፈለው ለሁለቱም ወገን በመሰለል ሥራ ላይ ስለነበረ የንጉሡ ሠላይ ቀኛዝማች መንግስቱ የመሀመድ ኢማምን መምጣት በቴሌግራም ወደ አዲሰ አባባ እንዲያሰተላልፍ ፈቀደለት::

ሁለተኛው የደረሰን ቴሌግራም ደግሞ ከአዛዡ ከራሱ ከቀኛዝማች መንግስቱ ነው የነበረው:: በመልከቱም አሊቃውን ሲነግር ባለበት ሀላፊነት መሀመድ ኢማምን ያለ ማለፊያ ወረቀት ድንበር ሲያቋርጥ ስላገኘው እስረኛ አድርጎ ሰለያዘው ምን ማድረግ እንዳለበት ከእሊቃው ትዕዛዝ እንዲሰጠው ነው:: ደጃዝማች በአሰቸኳይ በቴሌግራም መልሰው እስረኛው ከጠንካራ ጥበቃ ጋር በአሰቸኳይ ወደሳቸው እንዲላክ የሚል መልከት ላኩ::

ሰውየው እንደደረሰ ስናየው የተጎሳቆለ ሆኖ ነው ያገኘነው:: ለደጃች አያሌው የሚገባውን ሠላምታ ካቀረበ በኋላ ወድያውኑ ስለደረሰበት በደል ተቃውሞ አሰማ:: የደንበር ጠባቂዎች የነበረውን ጓዝና ንብረት ወሰድውበታል:: የሚለብሰውን የሀር ሸሚዝ እንኳን እንዲለብስ እልፈቀዱለትም:: ለሶስት ቀናት እድርጎት የማያውቀውን በእግሩ እንዲጓዝ መደረጉን፤ ውድ ዋጋ ያለው በቅሎውን እንደተቀማ፤ ምግብ እንኳን ጭብጥ ሙሉ የተቆላ ገብስ ብቻ እንደተሠጠው ከሁሉም በላይ ደግሞ ቡናና ትምባሆ መከልከሉን ተናገረ:: እዘገፑ ደግሞ ጥፋቱ የራሱ የመሀመድ ኢማም እንደሆነ ነገሩት:: ምክንያቱም በጦርነት ጊዜ ያለ ይለፍ ድንበር ማቋረጥ እልነበረበትም:: ቀጥሎም በደረሰበት በደልና ችግር የሚያዝኑ መሆኑን ገልፀው ይቅርታ ጠየቁ:: ለእንግዳው ከዛፍ ስር ድንኳን ከተወጠረ በኋላ ለእንግዳው የሚሆን በግ ባርኮ እንዲያርድ መሀመዳዊ* የሆነ ሰው ተጠራ::

---

***በፀሀፊው አጠራር የነብዩ መሀመድ ተከታዮች በዚያን ጊዜ መሀመዳውያን ተብለው እንደሚጠሩ ነው የሚያሳየው፤ በሌሎች በዚያን ጊዜ የተፃፉ የአውሮፓያን ፅሁፎችም አጠራሩን ሲጠቀሙ ይታያል**



የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች በክርስቲያን የታረደ ከብት ሥጋ አይበሉም በአላህና በነቢዩ ደንብ መሠረት ከታረደ ብቻ ነው የሚባለው በዛው ልክ ደግሞ የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታዮችም በሥላሤዎች ሰም ካልተባረከ አይነኩትም:: ቡና በትልቅ መቋያ ላይ ሆኖ ቀረበ እኔም ካለኝ ትምባሆ የማካፈል ክብሩ ደረሰኝ:: ሆኖም እየጎደለ የነበረውን የነበረኝን የትምባሆ መጠን ቀነሰብኝ::

በሚቀጥለው ቀን መሀመድ ኢማምና ደጃች አያሌው ለብቻቸው በመሆን ለረዥም ጊዜ ተነጋገሩ:: ማምሻውኑ ደጃች አያሌው ለኔ በሚስጥር መሀመድ የተላከው ከጓደኛቸው ከኤርትራው ገዢ ጣልያን ነው መልክቱም ደጃዝማች በጦርነቱ እንዳይሳተፉ ለማሳመንና ለመወትወት ነበር:: ደጃች አያሌው ከተስማሙ ጣልያኖች ሲያሸንፉ የራስነት ማዕረግ ተሠጥቷቸው የጠቅላላው የሰሜን ምዕራብ ገዢ ሆነው ሊሾሙ ነው:: ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ብዙ ገንዘብ ስለሚሠጣቸው በሀገሪቱ ውስጥ ትልቅ ሀብታም እንደሚሆኑ ነው::

"እውነት ነው ንጉሡ በድለውኛል" ብለው ደጃዝማች ነገሩኝ:: "ነገር ግን እኔ ሀገሬን በምንም ያህል ገንዘብ የምከዳ እይደለሁም:: ጣልያኖች እኔን ይከዳል ብለው ማሰባቸው የሚያሳፍር ነገር ነው::"

ደጃች እያሌው መሀመድ ኢማምን ምን እንደሚያደርጉት እያሰቡ ነበር:: በርግጥ የጣልያን አምባሰደር ነበር:: ነገር ግን ያለንበትን ካምፕ ለማወቅና ወደፊት እንቅስቃሴያችን ምን እንደሆነ ለማወቅ ተልኮ ቢሆንስ? ሰለዚህ እንደ ጦር ምርኮኛ ሆኖ እንዲቆይ ተወሰነና እውሮፕላን ተልኮ ወደ አዲስ አበባ እንዲወሰድ መንግሥት ተጠየቀ:: ቴሌግራሙ ማምሻውኑ ወደ እዲሰ አበባ ተላከ::

ከሁለት ቀን በኋላ የመጣው መልስ ግን እስረኛው በአሰቸኳይ ታጅቦ ወደ ደንበሩ እንዲመለስ የሚል ነበር:: ደጃዝማች እያሌውም ሌላ ሰው ሊገነዘብ እንደሚችለው በውሳኔው አልተሰማሙም ነገር ግን የግድ ትዕዛዙን ተቀበሉ:: ሰውየውን እንዲሁ መልሶ በነፃ መልቀቅ ያለውን አደጋ እኔም ተረድቻለሁ:: ግን ለትምባሆዬ ስል ቶሎ እንዲሄድልኝ ፈልጌ ነበር::

ስለወደፊት እንቅስቃሴያችን ለሰላዮች የተሣሣተ መረጃ ለመስጠት የማስመሰያ እንቅስቃሴ በማድረግ ካምፑን በትነን መሀመድ ኢማምን ከኛ ጋራ በማድረግ ወደ ሰቲት በሚወሰድው መንገድ ሀያ ኪሎሜትር ገባ ብለን አዲስ ካምፕ መሰረትን:: ከዚህ ተነሰቶም በእጃቢ ወደ ኤርትራ እንዲመለስ ተፈቀደለት::

የሰፈርንበት ካምፕ በጠገዴና ወልቃይት መለያያ ካሳ የሚባል ወንዝ በግምት ወደ አንድ ሺ ሜትር ጥልቀት ባለው ሸለቆ ውስጥ በሚወርድበት ደንበር ላይ ነው፡፡ ወደ ምዕራብ በኩል ሸለቆው ሰፋ ይልና ቆላማና ረባዳ የሆነው የአንገረብ ወንዝ ወደሚፈስበት አቅጣጫ ያመራል፡፡ በምስራቅ በኩል ግን ሸለቆው ድንገት ያቆምና ለጠገዴና ወልቃይት ተራራ ሰንሰለቶች ተራ ይለቃል፡፡ በሌላ አቅጣጫ ደግሞ መሬቱ ዝቅ እያለ በመሄድ ከትግራይ ጋራ በተከዜ ወንዝ ከሚለያዩት ወደ ረባዳው ዋልድባና ቆላ ወገራ መሬቶች ይወሰዳል፡፡ የተከዜ ወንዝ በአቢሲኒያ ካሉ ትልቅ ወንዞች አንዱ ነው፡፡ እኛ ደግሞ ቀጥታ ተራራዎችን አቋርጠን ከተራራዎች ማዶ ነበር የምንሄደው፡፡ ቦታው ጠለሎ ይባላል የሰላሳ ኪሎሜትር ርቀትም ነበረው፡፡

በጠዋት የመጀመሪያው የዶሮ ጩኸት (በአቢሲኒያ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰአት ላይ ነው ዶሮ የሚጮኸው) መንገድ ጀመርን፡፡ ሁሉም ነገር ሰላም ከሆነ ከጥዋቱ ሁለት ሰአት ሲሆን እንደርሳለን፡፡ በጣም ጥዋት ስለሚሆን የጠላት አውሮፕላኖችንም ለማምለጥ ያመቻል፡፡

አዛዡ ወደ አንድ ሺ የሚሆኑትን የራሳቸው ጠባቂዎች በማስከተል ከኋላ ሆነው መንገዱን ሲቀጥሉ እኔም በቀጥታ ከእሳቸው ኋላ በመሆን መጓዝ ጀመርን፡፡ ከአንድ ቀን በፊት አንደኛውን ድሬሰር መድሀኒትና መሳሪያዎች ተጭነው ከኛ ፊት ለፊት እንዲጓዙ እንዲያደርግ ሀላፊነት ሰጥቸው ስለነበር ብዙም አልተጨነቅሁም፡፡

በግምት ሁለት ኪሎሜትር መንገድ እንደተጓዝን ሁሉም ነገር ድንገት ቀጥ አለ፡፡ ምን እንዳሰቆመን እንዲያጣራ አንድ ሰው ወደ ፊት ተላከ፡፡ አምስት ደቂቃ ሳይሞላ መልከቱን ሳይጨርስ ተመልሶ መጣ፡፡ ጠባቡ መንገድ በሰዎችና በእንሰሶች ስለተጨናነቀ ማለፍ አልቻለም፡፡

ጆሮ የሚያደነቁር ጩኸትና ግርግር ተጀመረ፡፡ እንደዚያም እያለ እስከማታው ድረስ ቀጠለ፡፡ ሁሉም ይጮሃል፤ ከኋላ ያለው ፊት ለፊት ባለው ላይ ሲጮህ የፊት ለፊቱ ደግሞ መልሶ ኋላ ባለው ላይ ሲጮህ ያለምንም ምክንያት ሳይስማማ ለግማሽ ሰአት የሚሆን ሳንንቀሳቀስ ቆመን ቆየን፡፡ በመጨረሻ የችግሩ መንስኤ መድፎቹ መሆናቸውን ጭምጭምታ ሰማን፡፡
ደጃች አያሌው ከራስ ጉግሣ የሠረቋቸው ሁለት የድሮ የተራራ መድፎች አሏቸው፡፡ በ1888 በአድዋ ጦርነት ጊዜም አብረዋቸው ነበሩ፡፡ የማያስተማምኑ አሮጌ አርበኞች እያሉ በቀልድ ይጠሯቸው ነበር ደጃዝማች፡፡ መድፎቹን ፈትቶ በበቅሎ መጫን ይቻላል፡፡ እንደዚያም ሆኖ ግን ለዚህ ጠባብ



የተራራ ማለፊያ መንገድ ትልቅ ሆነው ተገኙ፡፡ ምን ማድረግ ይቻላል መድፈኞቹ መላውን ሊያገኙለት እንደሚችሉ ተስፋ ማድረግ ነው፡፡



በአንችም በተደረገው ጦርነት የተሸነፉት የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ባለቤት የነበሩት ራስ ጉግሣ ወሌ
(Agenore Frangipani, L'equivoco Abissino)

ከጊዜ በኋላ ችግሩ ተፈታና ጉዞ እንደገና ተጀመረ፡፡ ነገር ግን ያዘገመ በሰአት አንድ ኪሎ ሜትር ብቻ የሚንቀሳቀስ ሆነ፡፡ ቀኑ ሲወጣብን ከኋላ ሆነን የምንጓዘው ሰዎች የሚያስፈራ ትዕይንት ማየት ጀመርን፡፡ መንገዱ ለቀቅ ባለበት ቦታ እንኳን የጎኑ ስፋት ሁለት ሜትር አይሞላም፡፡ በአንድ ጎኑ ቀጥ ያለ የሃምሳ ሜትር ርዝመት ገደል ነው ያለው፤ በሌላ ጎን ደግሞ 500 መቶ ሜትር የሚሆን ቁልቁለት ነው ያለው፡፡ ቁልቁል ስመለከት እኔ ራሴ ሆዴን ቁርጠት ነው የለቀቀብኝ፡፡ እልፎ እልፎ ወንዞ ቦርቡሮ ስንጥቅ ከፍተት ባለበት ቦታ ግንድ ድንጋይና የዛፍ ቅርንጫፎች እንደማለፊያ ተነጥፈውበታል፡፡

በዚህ መንገድ አንድ ላይ የተጨናነቁ ሰዎችና እንሰሳት መስመር ይዘው አይን ማየት እስከሚችለው ርቀት ድረስ ቀስ ብለው ይጓዛሉ፡፡ አህዮች ሲጓዙ ማየት ራሱ አእምሮን የሚረብሽ ሁኔታ ነው፡፡ አንደ ደንቡ አህዮች ወደ ገደሉ

ጠርዝ በኩል ሆነው ነው እንዲሄዱ የሚደረጉት፡፡ ብዙዎቹ በባለቤቶቹ ኪሳራ የህይወት ዋጋ ነው የከፈሉበት፡፡ አንዱ አህያ ሁለት መቶ ማር ትሬዛ እንደተጫነ ተንከባሎ ከፊት ለፊቴ ወደቀ፡፡

ሙሉ የቀን ብርሃን ስለወጣ ፊት ለፊት ያሉት መንገደኞች መፍጠን ጀምረዋል ሆኖም በቂ አልነበረም፡፡ ሰአቱ እየሮጠብን ነው፡፡ በድንገት የጩኸት ድምፅ እየተቀባበለ እንደሳት ተቀጣጠለ

"መጣች" " መጣች"

ሁሉም ሰው መዝለል፤ ባለበት መቆም ፤ ትንፋሹን መያዝ ጀመረ፡፡ እውነት ነው እየደመቀ የሚመጣ የአውሮፕላን ድምፅ ይሰማኛል፡፡

ደጃዝማች ሁሉም ሰው የየራሱን እንስሳ ይዞ በፀጥታ እንዲቀመጥ እና እንዳይንቀሳቀስ ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ ከድምፁ በስተቀር ምንም ሳናይ በመረበሽ መጠበቅ ጀመርን፡፡ እዚህ መሮጫ ሜዳ ወይም መጠለያ በሌለበት ቦታ ላይ ይይዙን ይሆን? መቆረጫ የሌለው የሚመስል ረዥም ጊዜ ከቆየን በኋላ ሁለት ባለነጠላ ሞተር ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች አየን፡፡ ዝቅ ብለው ነበር የሚበሩት፤ አርፈንበት በነበረው የካምፕ ቦታ በኩል አድርገው ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሄዱ፡፡

"ምንም ማየት አትችልም! እውር ነች!" በማለት ወታደሮች እርስ በርስ ይነጋገሩ ነበር መንገዱን እንደገና ስንቀጥል፡፡ በኔ ግምት እነዚህ አልባሌ ጀግኖች የአውሮፕላን ቦምብ አልወረደብንም እና ምን እንደሚመስል አናውቅም ብለው ሳያማርሩ አይቀሩም፡፡

ብዙም ሳንዘገይ ከሰአት በኋላ ጠለሎ(ፀለሎ) ደረስን፡፡ ለሰውም ለእንስሳውም ረዥምና አድካሚ ቁልቁል መንገድ ነበር፡፡ ለዚያን ቀን አድካሚ ጉዞ የመጨረሻው ወይም ማቆሚያችን ነበር፡፡



# ምዕራፍ ሰባት

## ጭስ የሌለው እሳት

ጠለሎ ከባህር ወለል 1800 ሜትር በላይ ይገኛል፡፡ ከዋልድባ ትይዩ በተከዜ ረባዳ ቦታ የመጨረሻው ደንበር ላይ ነው፡፡ የተለያዩ የመሬት ገፅታዎቹ አጠር ካሉ ጫካዎችና ሰፋፊ ሜዳዎች ጋር ያማረና ለካምፖችንም የሚስማማ ሥፍራ አድርጎታል፡፡ ከላይ ከተራራው ተነስቶ የሚወርድ ትንሽ ወራጅ ንፁህና በቂ የመጠጥ ውሃ እንደልብ እንድናገኝ አድርጎናል፡፡

ዕይታው አስደናቂ ነው፡፡ የተከዜን ሸለቆ ማየትም እችላለሁ፡፡ ሸለቆው በደቡብ ምሥራቅ በኩል ከሰሜን ተራሮች ጀርባ ተነስቶ እንደ ትልቅ ገደል እየተጠማዘዘ ወደፊት በመሄድ ፀሀይ በለበለበውና ሰው በማይኖርበት ረባዳ መሬት አድርጎ በሰሜን በኩል በአምባ ብርኩታ ጀርባ ይሰወራል፡፡ ካለንበት በቀጥታ በምሥራቅ በኩል ማዶው የትግራይ መሬት ነው፡፡ በጠራ ቀን በተለይ ከሰአት በኋላ የአድዋ ተራሮችን መለየት ይቻላል እነሱም በልጅነት ዘመኔ የድሮ ጓደኞቼ ሶሎዳ፣ ሰማይታ እና አባ ገሪማ ናቸው፡፡

የዚህ ሥትራቴጂያዊ አቀማመጥ ጠለሎን ልዩ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ ተነስቶ የወልቃይት ተራራ ሰንሰለቶችን በመከተል ባጭር ጊዜ ውስጥ ሰቲት መድረስ ይቻላል፡፡ ይህ አጭር ርቀትም በትግራይ ረባዳ መሬቶች አቋርጦ ሰቲት ከመሄድ ጋራ እኩል ነው፡፡ ነገር ግን በሁለቱም መንገዶች ወባው መታወቅ የሚገባው አስቸጋሪ ነገር ነው፡፡

የተከዜ ወንዝ ምንም አይነት እንቅፋት አይፈጥርም፡፡ ወንዙ ጎድሎ ስለነበረ አቋርጦ መሄድ ይቻላል፡፡ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ላደረገ ሰውም ከአውሮፕላን ጥቃት መደበቅ የሚቻልባቸው ጥሩ ቦታዎች አሉ፡፡ ሜዳዎችም ቢሆን የሚታጨድ የሚበቃ ሣር ሳላላቸው እንስሶችን ለግጦሽ መልቀቅ አያስፈልግም፡፡

ሌላው የጠለሎ ራቅ ብሎ መገኘት ጥቅም ደግሞ የኢጣልያ አውሮፕላኖች በየቦታው ቢበሩም ያተኮሩት ካርታ ላይ በሠፈሩት መንገዶች ላይ ነው፡፡

ጠርዝ በኩል ሆነው ነው እንዲሄዱ የሚደረጉት፡፡ ብዙዎቹ በባለቤቶቹ ኪሳራ የህይወት ዋጋ ነው የከፈሉበት፡፡ አንዱ አህያ ሁለት መቶ ማር ትሬዛ እንደተጫነ ተንከባሎ ከፊት ለፊቴ ወደቀ፡፡

ሙሉ የቀን ብርሃን ሳለወጣ ፊት ለፊት ያሉት መንገደኞች መፍጠን ጀምረዋል ሆኖም በቂ አልነበረም፡፡ ለአቱ አየሮጠብን ነው፡፡ በድንገት የጩኸት ድምፅ እየተቀባበለ እንደላት ተቀጣጠለ

"መጣች" " መጣች"

ሁሉም ሰው መዝለል፤ ባለበት መቆም ፤ ትንፋሹን መያዝ ጀመረ፡፡ እውነት ነው እየደመቀ የሚመጣ የአውሮፕላን ድምፅ ይሰማኛል፡፡

ደጃዝማች ሁሉም ሰው የየራሱን እንስሳ ይዞ በፀጥታ እንዲቀመጥ እና እንዳይንቀሳቀስ ትዕዛዝ ሰጡ፡፡ ከድምፁ በስተቀር ምንም ሳናይ በመረበሽ መጠበቅ ጀመርን፡፡ እዚህ መሮጫ ሜዳ ወይም መጠለያ በሌለበት ቦታ ላይ ይይዙን ይሆን? መቆረጫ የሌለው የሚመስል ረዥም ጊዜ ከቆየን በኋላ ሁለት ባለነጠላ ሞተር ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች እየን፡፡ ዝቅ ብለው ነበር የሚበሩት፤ እርፈንበት በነበረው የካምፕ ቦታ በኩል አድርገው ወደ ደቡብ አቅጣጫ ሄዱ፡፡

"ምንም ማየት አትችልም! እውር ነች!" በማለት ወታደሮች እርስ በርስ ይነጋገሩ ነበር መንገዱን እንደገና ስንቀጥል፡፡ በኔ ግምት እነዚህ አልባሌ ጀግኖች የአውሮፕላን ቦምብ አልወረደብንም እና ምን እንደሚመስል አናውቅም ብለው ሳያማርሩ አይቀሩም፡፡

ብዙም ሳንዘገይ ከለአት በኋላ ጠለሎ(ፀለሎ) ደረስን፡፡ ለሰውም ለእንስሳውም ረዥምና አድካሚ ቁልቁል መንገድ ነበር፡፡ ለዚያን ቀን አድካሚ ጉዞ የመጨረሻው ወይም ማቆሚያችን ነበር፡፡



# ምዕራፍ ሰባት

## ጭስ የሌለው እሳት

ጠለሎ ከባህር ወለል 1800 ሜትር በላይ ይገኛል፡፡ ከዋልድባ ትይዩ በተከዜ ረባዳ ቦታ የመጨረሻው ደንበር ላይ ነው፡፡ የተለያዩ የመሬት ገፅታዎቹ አጠር ካሉ ጫካዎችና ሰፋፊ ሜዳዎች ጋር ያማረና ለካምፓችንም የሚለማማ ሥፍራ አድርጎታል፡፡ ከላይ ከተራራው ተነስቶ የሚወርድ ትንሽ ወራጅ ንፁህና በቂ የመጠጥ ውሃ እንደልብ እንድናገኝ አድርጎናል፡፡

ዕይታው አስደናቂ ነው፡፡ የተከዜን ሸለቆ ማየትም እችላለሁ፡፡ ሸለቆው በደቡብ ምሥራቅ በኩል ከሰሜን ተራሮች ጀርባ ተነስቶ እንደ ትልቅ ገደል እየተጠማዘዘ ወደፊት በመሄድ ፀሀይ በለበለበውና ሰው በማይኖርበት ረባዳ መሬት አድርጎ በሰሜን በኩል በአምባ ብርኩታ ጀርባ ይለወራል፡፡ ካለንበት በቀጥታ በምሥራቅ በኩል ማዶው የትግራይ መሬት ነው፡፡ በጠራ ቀን በተለይ ከለአት በኋላ  የአድዋ ተራሮችን መለየት ይቻላል እነሱም በልጅነት ዘመኔ የድሮ ጓደኞቼ ሶሎዳ፣ ለማይታ እና አባ ገሪማ ናቸው፡፡

የዚህ ሥትራቴጂያዊ አቀማመጥ ጠለሎን ልዩ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ ተነስቶ የወልቃይት ተራራ ሰንሰለቶችን በመከተል ባጭር ጊዜ ውስጥ ሰቲት መድረስ ይቻላል፡፡ ይህ አጭር ርቀትም በትግራይ ረባዳ መሬቶች አቋርጦ ሰቲት ከመሄድ ጋራ እኩል ነው፡፡ ነገር ግን በሁለቱም መንገዶች ወባው መታውቅ የሚገባው አስቸጋሪ ነገር ነው፡፡

የተከዜ ወንዝ ምንም አይነት እንቅፋት አይፈጥርም፡፡ ወንዙ ጎድሎ ስለነበረ አቋርጦ መሄድ ይቻላል፡፡ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሳደረገ ሰውም ከአውሮፕላን ጥቃት መደበቅ የሚቻልባቸው ጥሩ ቦታዎች አሉ፡፡ ሜዳዎችም ቢሆን የሚታጨድ የሚበቃ ሣር ሳላላቸው እንስሶችን ለግጦሽ መልቀቅ አያስፈልግም፡፡

ሌላው የጠለሎ ራቅ ብሎ መገኘት ጥቅም ደግሞ የኢጣልያ አውሮፕላኖች በየቦታው ቢበሩም ያተኮሩት ካርታ ላይ በሠፈሩት መንገዶች ላይ ነው፡፡

አንደ ቦታው ርቀት ደግሞ ጉዳቱ የመንገዱ መጥፎ መሆን ነው:: እንደዚህ አይነት መጥፎ መንገድ አይቼ አላውቅም:: ከፍየል መሄጃ መስመር የከፋ ነው:: በመንገድ ምክንያት ብዙ እንሰሶች ነው ያለቁብን:: ጥቂቶቹ በገደሉ ተንከባለሉ ሌሎቹ ደግሞ የከፋ ቁስል ወጣባቸውና በዚህ ምክንያት ደካማና አገልግሎት የማይሠጡ ስለሆኑ መወገድ ነበረባቸው::

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ከሰአት በኋላ ሲሆን ጠለሎ ደረስን:: ማምሻው ድረሰ መድሃኒት ያለበት ጓዝ ሳላልደረሰ መጨነቅ ጀመርኩ::

ወይ ጠፍቷል ወይ ደግሞ በገደል ተንከባሎ ወድቋል ብዬ ማታውኑ ለደጃዝማች ተናገርኩ:: ወድያውኑ ሁለት ሰዎች በጥዋት ተነስተው እንዲሄዱና ሁኔታውን እንዲያጣሩ ትዕዛዝ ሰጡ:: የሚቀጥለው ቀን ማምሻ ድረሰ ምንም የተሰማ ወሬም የለም:: ከደጃዝማች ጋራ ቁጭ ብዬ እያለሁ ፈጠነ መጥቶ ጓዙ እንደደረሰና ተራግፎ ከኔ ድንኳን አጠገብ እንደተቀመጠ ነገረኝ:: አነጋገሩ ግን ያልሆነ ነገር እንዳለ እንድጠራጠር አደረገኝና ለማጣራት ወጥቼ ሄድኩኝ::

እንደፈራሁት ሆነ::

በድንጋጤ ፈዘዝኩኝ:: ሣጥኖቹ ተሰባብረው መሬቱ ላይ ተበትነዋል:: አንዳንዶቹም የተሰባበረውን አንድ ላይ ለመያዝ በገመድ ታስረዋል:: የተቀዳደዱ ከረጢቶች በየቀዳዳው ከዚህ በፊት ንፁህ የነበሩ የጥጥ ጥቅሎች ብቅ ብቅ ብለው ይታዩበታል:: የእስትራ ፋርማሲ የሠራቸው ጥሩ የቁስል ማሸጊያዎች ተቀዳደው በየቦታው ወድቀዋል:: ትልቅ ዚንክ ሳልፎ የሚባል መድሀኒት በውስጡ የነበረበት የቆርቆሮ መያዣ ተሰብሮ ከዳን አልባ ሆኖ ይታያል:: የቆርቆሮ ሣጥኖች ተቀደው ውስጣቸው የነበሩ የቆርቆሮ ጣሳዎች ተከፋፍተዋል:: ትንንሽ ሣጥኖች ተሰባብረዋል:: የህክምና መሳሪያዎችና መድሃኒቶች እንደ ኩዊኒን፣ አሰፒሪን ከኒኖች፣ በሙቶ የሚቆጠሩ በመርፌ የሚሰጡ መድሃኒቶች ጨምሮ በየቦታው ተበትነዋል:: የቁሰል መጠቅለያ ማሸጊያዎች ተከምረዋል። አየሩ በአዮዲን ሽታ ታውዷል:: በውስጣቸው አልኮል፣ ካሰተር አይል እና ሌሎችም ፈሳሾች የነበሩባቸው ብዙ የመድሃኒት ጠርሙሶች ባዷቸውን በሣጥን ውስጥ ተደርድረዋል::

ቁጭ ብዬ አነባሁ:: በመድሃኒትና የህክምና መሣሪያ ባለማግኘት ምክንያት ሌሎችን ሰዎች መርዳት ካልቻልኩ እራሴን ለአደጋና ለጦርነት ሽብር የማጋልጠው ለምንድን ነው? የቀይ መስቀል አምቡላንስ አባል አይደለሁም:: ብሆን ኖሮ በጠፋው መድሃኒትና መሳሪያ ትከ መጠየቅ እችል ነበር:: እነዚህ መድሃኒቶች ለኔ በጣም ትልቅ ነበሩ:: ምክንያቱም እነዚህን መጠነኛ መድሃኒቶችና የቁሰል መጠቅለያዎች ለማግኘት እንኳን መታገልና መለመን ነበረብኝ::

ይህ ጣጣስ እንዴት ሊፈጠር ቻለ?

መስፍንቶ በተባለ ቦታ መድሀኒቱን የተጫኑ አህዮች ልቅ ሆነው ተመልሰው ወደ አዲ አትየ ፈርጥጠው ተመልሰዋል:: ሰዎች አየሮጡ ተከተሏቸው፤ ከደረሱባቸው በኋላ ማታውኑ እዛው ማደር ነበረባቸው:: በመሳፍንት ጉጉት ያደረባቸው ልጆች ወደ ታደረበት የካምፕ ቦታ ሲመጡ ወድቀው የቀሩ ሣጥኖችን ያገኛሉ:: ልጆችም የማይረባ ነገር ቢሆን ነው የተጣለው በማለት የሣጥኖችን ቁልፎች በድንጋይ ይሰብራሉ::

የነዚህ ሣጥኖች መገኘት ዝና እንደነፋስ በመንደሩ ወድያው ይደርሳል:: እባትና እናት ቤተዘመድ እየሮጡ ቦታው ይደርሳሉ:: በዚህ ራቅ ባለ ቦታ የቆርቆሮ ሣጥኖች፣ የቆርቆሮ ጣሳዎች፣ ጠርሙሶች፣ ቢላዋዎች እና መቀሶች የሚፈለጉ ነገሮች ናቸው:: ጥጡን እንኳን ሳይቀር ሴቶቹ ለፈትል ጥሩ ሆኖ አገኙት::

ጓዙን ሲያጅቡ የነበሩ ሰዎች ወደ ቦታው ሲመለሱ የሆነውን ነገር ሲያዩ ለራሳቸው ቢፈሩ እንግዳ ነገር አልነበረም:: ከረዥም ውይይት በኋላ ሁሉንም ነገር እዛው ትተው ወደ የቤታቸው ለመሸሽ ወሰኑ::

ለዚያን ቀን ማታ ግን በቦታው ሲያድሩ ከደጃዝማች እያሌው የተላኩት ሁለት ወታደሮች ከንጋቱ ላይ ከተፍ ይሉባቸውል:: ወታደሮችም በየቤቱ እየተዘዋወሩ ማግኘት የቻሉትን የተዘረፈ ዕቃ ሰበሰቡ:: ሶስት ሽማግሌ ገበሬዎች፣ ሁለት ሴቶችና አራት ልጆቹን ድንገት ደጃዝማች መቅጣት ከፈለጉ በማለት ይዘዋቸው መጡ::

ቅጣትም አልተሠጠም:: እንደነዚህ ያሉ የማያውቁ ሰዎችን ምን ማድረግ ይቻላል? መተካት የማይቻሉ መድሃኒቶችን ግን አበላሹ::

እሰረኞቹም በነፃ ሲለቀቁ ነበር:: ዘመዶቻቸው ግን የተያዙትን ሰዎች እንዲለቀቁ እኔ ደጃዝማቾችን ካላማለድኩ በሕይወቴ ላይ አደጋ እንደሚያደርሱ ዛቱ:: ለዚህ ድፍረታቸው ሲባል ከኛ ጋራ ወደ ቆላው የአንድ ቀን የእግር መንገድ እንዲሄዱ ተደረገ::

በኔ በኩል የተበተነውን ጓዝ አንድ መልከ ለማስያዝ ሶስት ቀን ፈጀብኝ:: ያሳዘነኝ ነገር ግን ከነበረኝ መድሀኒትና ቁሳቁስ ግማሹ ነው የቀረኝ::

ጥዋትና ማታ እየተመላለሱ የሚጎበኙን የኢጣልያ አውሮፕላኖችን በየቀኑ ማየት እየተለመደ መጥቷል፡፡ ብዙ ጊዜ የሚታዩት ከአምባ ብርኩታ ወደ ሰሜን ወይም ከዚያ ሲመለሱ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ በኛ ላይ ዝቅ ብለው ይበራሉ፡፡ እንደሱ በሚያደርጉበት ጊዜ ቁጭ እንላለን፡፡ አይተውን ይሆን? ያለንበትን ቦታስ ወሬ አግኝተው ይሆን? ብለን እናሰባስን፡፡ ያም ቢሆን አይገርመንም ካምፓችን ውስጥ ብዙ ሰላዮች ነበሩ፡፡ በየቀኑ አንድ ወይም ሁለት ሰላዮች ይያዛሉ፡፡ ብዙ ጊዜ ነፃ የተሰቀቁ አገልጋዮች ወይም የገበሬ ልጆች ናቸው፡፡ ብዙም ጊዜ ያልበሰሉ ሰዎች ስለሆኑ ብዙም ትኩረት አንሠጣቸውም፡፡ በቀላል መንገድ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ማድረግና በዛኛው ወገን የሚሆነውን ማወቅ ይቻላል፡፡

አንዱ ግን ከሌሎቹ በስተ ያለ ነበር፡፡ ወደ ካምፑ ሲመጣ መነኩሴ መስሎ መጣ፡፡ የቆዳ ቆብ ጭኖ፤ ትልቅ የብረት መስቀል በእጁ ይዞ መፅሀፍ በቆርቆሮ ሣጥን አድርጎ ከጎኑ አንጠልጥሏል፡፡ ነገር ግን ሳያስበው በአንድ በጠረጠረ ወታደር የያዘውን መፅሀፍ እንዲያነብ ሲጠየቅ ዕጣ ፋንታውን አገኘ፡፡ መፅሀፉንም ማንበብ አልቻለም፡፡ ወታደሩም ከዳጃች አያሌው የመቶ ብር ሽልማት ተቀበለ፡፡ የሚገባውም ነበር፡፡

እነዚህ ሁሉ ሰላዮች መገደል ወይም መሰቀል ነበረባቸው፡፡ ደጃች አያሌው ግን ሁሉንም ወደ ዳባት እየላኩ በእስር ቤት እንዲማቅቁ አደረጓቸው "ስነዚህ አህዮች ገመድም ሆነ ጥይት አላባክንም ከዚያ ስተሻለ ነገር እጠቀምበታለሁ" ይሉ ነበር ደጃዝማቹ፡፡

እያንዳንዱ ሰው የካምፑን ቦታ ላለማጋለጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡ በራሳችን ሰላዮች እንደተረዳነው ጣልያኖቹ ያለንበትን ቦታ እስካሁን አላወቁም ግን ወደፊት የሚሆነው አይታወቅም፡፡ ሃምሳ ጠባቂዎች በካምፑ ውስጥ በየቦታው ተመድበው ከብቶች እንዳይለቀቁ እና በቀን እሳት እንዳይነድ ይቆጣጠራሉ፡፡

በአንድ አጋጣሚ አንደኛው ጠባቂ አንድ የወታደር መኮንን ይዞ በእኩለ ቀን ወደ ደጃች አያሌው መጣ፡፡ ትንሽ የጭስ መጠን በመኮንኑ ድንኳን ታይቷል፡፡ መኮንኑ ሲጠየቅ ደግሞ እውነት ነው አገልጋዩዋን ቡና እንድታፈላ ትዕዛዝ ሠጥቻለሁ ብሎ አብራራ፡፡ ነገር ግን ጭስ እንዳይኖርም ትዕዛዝ መስጠቱን ተናገረ፡፡



"ታዲያ አገልጋይዋ እሳት አላነድም ብትል ምን ታደርግ ነበር?"

"እገርፋት ነበር"

"እሳት ያለጭስ አይተህ ታውቃለህ ወይ?"

"የለም አይቼ አላውቅም"

"ታዲያ እንዴት ያን አይነት ነገር እንድታደርግ አገልጋይዋን ትጠይቃለህ?"

"እዝዣታለሁ የታዘዘችውን መፈፀም ሥራዋ ነው፡፡ ይህች ደደብ አህያ!"

"አህያ ከሆነችማ ሊገባት ስለማይችል ሀላፊነቱን አንተው ራስህ መውሰድ አለብህ፡፡ በግዴየለሽነትህ የመላው ካምፑን ህግ ተላልፈሃል፡፡ ስለዚህ ለዳኝነት ወደ ሠራዊቱ ፍርድ ቤት አሳልፌ ሠጥቼሀለሁ" የደጃዝማች ውሳኔ ነበር፡፡

ማምሻውኑ ሜዳ ላይ ሰዎች ዙርያውን ተሰበሰቡ፡፡ ደጃች አያሌው በግራና በቀኝ ጎናቸው ሌሎች ሽማግሌዎችን በማስቀመጥ መሀል ላይ ቁጭ አሉ፡፡ አጥፊው ተጠራና ለሁሉም እንዲሰማ ያጠፋው ጥፋት ጮክ ተብሎ ተነበበ፡፡ ደጃች አያሌው ምልክት ሲሠጡ ከሁሉም በእድሜ የገፉት የሰማንያ አንድ አመት እድሜ ያላቸው ፊታውራሪ እሉላ ከመቀመጫቸው ተነስተው የሚከተለውን መግቢያ ንግግር አደረጉ፡፡

"ሌሎች ላይ ዳኝነት የሚሠጥ ሰው ራሱ ይዳኝ፤ አጥፊው በሰይፍ ይቀጣ፤ የንጉሥ ጠላት ካለና ከቀረበ ለፍርድ ቀርቦ በሰይፍ በሞት ይቀጣ፤ ከለለ ደግሞ በፀሎት ይሁን፡፡ ዛሬ ትክክለኛውን ፍርድ እንድሠጥ ይርዳኝ"

ከዚያም ራሳቸው በገባቸው መንገድ አጥፊው ያደረሰውን በደል ከዘረዘሩ በኋላ ወደ ተቀመጡት ዞር ብለው

"በድሏልና ይቀጣ" አሉ

ሃምሳ የተለያዩ ሰዎች እየተነሱ ተመሳሳይ ሃሳብ ሠጡ፡፡ እኔም ብሆን ሃሳብ እንድሠጥ ተጠየቅሁኝ፡፡ እኔ ግን ጉንፋን ይዞኛልና ድምፄ ሻክሯል ብዬ ሃሳብ እንደማልሠጥ አሳወቅሁኝ፡፡ ይህ ጉንፋን ሲይዘኝ በመላው ጦርነት ጊዜ የመጀመሪያ ነበር፡፡ ሁሉም ሰው አስተያየቱን ከጨረሰ በኋላ ቅጣቱ ምን እንደሚሆን ውይይት ተጀመረ፡፡ መጨረሻም አጥፊው አርባ ጅራፍ እንዲገረፍ ተፈረደበት፡፡

በእንደዚህ አይነቱ ፍርድ ቦታ ሁልጊዜ ጠንካራ አገልጋይ ከቆዳ የተሠራ ጅራፍ ይዞ ይቆማል፤ ሶስት ገመድ የያዙ ረዳቶችም አብረውት ይገኛሉ፡፡ ፍርዱ እንደተወሰነ ወድያውኑ ሶስቱ ረዳቶች ወደ ተፈረደበት ሄደው የለበሰውን ልብስ ከሱሪው በስተቀር አስወለቁት፡፡ ከዚያም መሬት ላይ በሆዱ አጋድመው

እጆቹን ሰየብቻ፤ እግሮቹን አንድ ላይ አስረው በየቦታቸው ፈንጠር ብለው አያንዳንዳቸው አንዳንድ ገመድ ወጥረው ያዙ፡፡ ይህ ሁሉ በጥቂት ሰከንዶች ውስጥ ነው የተደረገው እጥፈውም መሬት ላይ በሆዱ ተኝቷል፤ እንዳይንቀሳቀስ በመስቀል ቅርፅ በገመድ ተወጥሯል፡፡

ገራፊው ጅራፉን እያወዛወዘ መጣ፡፡ ከታሰሩት እግሮች በኩል አንድ ሜትር ራቅ ብሎ ቆመ፡፡ የያዘው ጅራፍ ከበሬ ቆዳ የተሠራ ጉንጉን የሁለት ሜትር ርዝመት አለው፡፡ ወፈር ብሎ ይጀምርና ወደ ጫፉ እየቀጠነ ይሄዳል፡፡ አሥራ አምስት ሴንቲሜትር ርዘመት ያለው የአንጨት እጀታ ላይ ጠበቅ ብሎ ታስሯል፡፡

"ጠሽ!" የሚል ጩኸት ጅራፉ አየር ላይ ሲወነጨፍ በሚያሰማው ድምፅ ተከትሎ ጅራፉ ያሰምህረት የሰውየው ጀርባ ላይ ከትከሻው እስከመቀመጫው ባለው ሥፍራ ላይ ያርፋል፡፡ ወዲያውኑ ጅራፉ ያረፈበት መሰመር ማበጥ ይጀመርና ሰምበር መታየት ይጀምራል፡፡ ቆዳው መከፈት ሲጀምር ደም መታየት ይጀምራል፡፡




የተቀጣ ሰው በአደባባይ እርባ ጅራፍ ሲገረፍ (ምሥጋና ለፋሲል ጊዮርጊስ). from the book The City & Its Architectural Heritage Addis Ababa 1886 – 1941)

ጅራፉ ሲያርፍ ማየትና መስማት አስቃቂ ነው፡፡ እንዳችም ድምፅ ከሰውየው አልተሰማም፡፡ በጣም ኩሩ ሰስነበር ድምፅ ማሰማት አልፈለገም፡፡ ሌላ ጊዜ ግን ጅራፍ ባረፈበት ቁጥር የሚጮህና ምህረት የሚለምን ሰው ማየት የተሰመደ ነገር ነው፡፡



ሰላሳ ዘጠኝ ጊዜ ከተገረፈ በኋላ አርባኛው መሬት ላይ እንዲያርፍ ይደረጋል፡፡ ይህም ከፉ መንፈሶች ወይም መናፍስትን ለማስፈራራት ነው፡፡ የታሰረበት ገመድ ተፈታና የተገረፈው ሰውየ ተነስቶ ደጃዝማችን እጅ ነሳ፤ በጓደኞቹ ተደግፎም ወደ ቦታው ሄደ፡፡ ጥፋቱን ተናዞ በጦር ሜዳ ጓደኞቹ የተሠጠውን ፍርድ ምንም ሳያቅማማ ተቀብሏል፡፡ ቅጣቱን እንደ ወንድ ነው የተቀበለው፡፡ ይህ ሰው ባላምባራስ ተሰማ ይባላል፡፡ በኋላ እንዳወቅነው ከሆነ ሁነተኛ ጀግና ሰው ነበር፡፡

በህዳር ሶስት ከራስ እምሩ የተላከ ደብዳቤ ደረሰን፡፡ ደብዳቤው ራስ እምሩ ዳባት መድረሳቸውን ይገልፃል፡፡ ፊታውራሪ መርሶ በአባታቸው ስም ላበረከቱት 150 በሬዎች ደጃች አያሌውን እንደሚያመሰግኑ ጠቅሶ ራስ እምሩ በተሠጣቸው ትዕዛዝ መሠረት ወደ ምሥራቅ በኩል በሰሜን ተራሮች አድርገው ወደ ተምቤን በመሄድ የራስ ካሳን ጦር እንደሚቀላቀሉ ነው፡፡




ልዑል ራስ እምሩ

ይህ ደግሞ ፈፅሞ ያልተጠበቀ ነገር ነበር እኛም ወደ የትኛው አቅጣጫ እንደምንሄድ ማሰብ ጀመርን፡፡ ወደ ሰቲት እንድንሄድ ትዕዛዝ ከተሠጠን ወደ

ሽሬ ግንባር ማን ሊሄድ ነው? ያ ደግሞ ለጣልያኖች የሚመች ቀዳዳ ይከፍታል፡፡ በሰላዮቻችን መረጃ መሠረት ጠላት በተከዜ ሸለቆ ዳር ዳር እራት የተለያዩ በታዎች ላይ መሽጎ ተቀምጧል፡፡ በተጨማሪም ወደ እከሱም በሚወሰደው መንገድ ሶስት ምሽጎች እዘጋጅቶእል፡፡ ታዲያ የሽሬ ግንባር የኛ ድርሻ ይሆን?

እንደዛ ከሆነ ደግሞ ጠቅላላውን የደንበር መሬት ለቲትን ማን ሊጠብቅ ነው?

ራስ ካሳ ከዘጠና ሺ ወታደሮቻቸው ጋራ የራስ እምሩን ርዳታ ማግኘት የሚያስፈልጋቸው አይመስልም፡፡ በዚህ ምክንያት ይህ አሰላለፍ ግራ የሚያጋባና እንግዳ ነገር ነው ብለን ያሰብነው፡፡ ማድረግ የምንችለው ነገር ቢኖር እዲስ እበባ ያሉ እዛዦች የሚያደርጉትን የሚያውቁ የጅል ሥራ የማይሰሩ ይሆናሉ ብለን ተሰፋ ማድረግ ነው፡፡

ደጃች እያሌው መልከተኛውን
"ራስ እምሩ ብዙ ሰው እላቸው?" ብለው ጠየቁ
"ቁጥር ስፍር የሌለው እንደአንበጣ"
"ጥቢቃን በሚመለከት እኛ እንደምናደርገው ታደርጋላችሁ ወይ?"
"የለም፡፡ ሜዳ ላይ ነው ካምፕ የምናደርገው፤ የምንጓዘውም በቀን ነው"
"እንዴ ጣልያኖች ቢያዩዋችሁና በምብ መጣል ቢጀመሩባችሁስ?"
"እግዜር ያውቃል"

በሚቀጥለው ቀን በጥዋቱ ደመቅ ያለ የእውሮፕላን ድምፅ ሰማን፡፡ ወደ ዳባት አቅጣጫ ነበር የሚሄዱት፤ ቀጥሎም የፍንዳታ ድምፅ መሰማት ጀመርን፡፡ ሩቅም ቢሆን እስከ እኩለ ቀን ድረስ ድምፁ ይሰማ ነበር፡፡

ማምሻውኑ ቀረብ ካለው ወደ ምእራብ 20 ኪሎ ሜትር ርቀት ከሚገኝ ስልክ ቤት በመጣው መልከት የራስ አምሩ ጦር ዳባት እውሮፕላን ማረፊያ እጠገብ ሜዳው ላይ በአሥራ ሁለት የኢጣልያ አውሮፕላኖች በቦምብ መደብደቡን ሰማን፡፡ ከመቶ ሃምሳ በላይ የሚሆኑ ቦምቦች ተጥለዋል፡፡ ከሚታወቀው 18 ሰዎችና ብዙ እንስሳት ተገድለዋል፡፡ የጉዳቱ ሙሉ መጠን ግን ገና አይታወቅም፡፡ በጦሩ ላይ ያደረሰው የእእምሮ ሽብር ከፍተኛ ነበር፡፡ ሰዎችም ለነዚህ የሰማይ ላይ ጭራቆች በቂ መከላከያ የለንም ብለው ማማረር ጀመሩ፡፡

ከደጃዝማች እያሌው ጦር ጋር በመሆኔ አግዚእብሔርን እመሰገንኩ፡፡





የዳባት ከተማ በአውሮፕላን ሲደበደብ በኢጣልያኖች የተነሣ ፎቶግራፍ

የኢትዮጵያውያን ዘማቾች አይተው የማያውቁትን የአውሮፕላን ድብደባ በሚከተለው መንገድ ነበር የገለጡት (ከተርጓሚዎች)

በትግራይ ቢመጣ መች ይገባ ነበር
በጎንደር ቢመጣ መች ይገባ ነበር
በሸዋ ቢመጣ መች ይገባ ነበር
በጎጃም ቢመጣ መች ይገባ ነበር
በሰማይ ላይ መጣ በማናውቀው አገር

ያን ቀን ማምሻውን ከዳባት የተላከ የንጉሡ ደብዳቤ ደረሰ:: አንድ ቀን ቀደም ብሎ በአውሮፕላን ነበር ወደ ዳባት የተላከው:: ደብዳቤው የንጉሡ ነገሥቱ ማህተም አሰበት:: ደጃች አያሌው በአስቸኳይ ወደ ሽሬ ግንባር እንዲንቀሳቀሱ ትዕዛዝ ተፅፎበታል:: ራስ አምሩ ደግሞ አንደ ጦር አዛዥ ከአምስት ሺ ሰው ጋር ወደ ደጃዝማቹ መስፍን በመላክ የሰቲትን ድንበር እንዲጠበቅ እንዲያደርጉ ታዘዋል:: በዚያ በኩል ጣልያኖች የማጥቃት ምልክት አላሳዩም:: በቦታው ወታደሮች አላሰባሰቡም:: ሰሰዚህ ከላይ  የተጠቀሱት ሰዎች አሰላለፍ ሰጊዜው በቂ ነው ተብሎ ተገምቷል::

ደጃዝማች ወድያውኑ በመላው ካምፕ ሰሚቀጥለው ቀን ዝግጅት እንደሚደረግና ጠመንጃና ጥይት እንደሚታደል እንዲታወቅ አስደረጉ::

ከአምስት ሺ ወታደሮች ጋራ በወልቃይት ተራሮች ለተቀመጡትና የሰሜኑን ድንበር ለሚጠብቁት  ለደጃዝማች አያሌው ታላቅ ልጅ ለፊታውራሪ ዘውዱና ለፊታውራሪ ሙላው ደብዳቤ ተላከ:: በደብዳቤውም ወድያውኑ ወደ ምሥራቅ ተጉዘው የተከዜ ገባር ወንዝ ከሆነው ዛሬማ ወርደው እንዲጠብቁን ነው::

የደጃዝማች አያሌው ተወካይ ፊታውራሪ ተሻገር ከ2500 ወታደሮች ጋር በመሆን ቀዳሚ ወይም የግንባሩን ጦር እንዲመሩ ታዘዙ:: በሌሊት ከካምፕ ተነስተው ከዋናው ጦር የአንድ ቀን የአግር መንገድ ርቀት ቀድመው እንዲሄዱ ሆነ:: ሙሉ ጨረቃም ስለነበር ቁልቁል ገደሉን ወርዶ ለመሄድ ቀላል ሆነ:: በችኮላ የኩዊኒን መድሃኒትና የመጀመሪያውን የመድሃኒትና እርዳታ መሰጫ ሻንጣ ሰሁለት የጦር ክፍሎች እንደሚሆን አድርጌ አዘጋጀሁ::

ያን ቀን ማታ ብዙ እንቅስቃሴ በካምፑ ወስጥ ነበር:: ጫጫታና ሳቅ በየቦታው ይሰማ ነበር:: ሁለት ሺ የሚሆኑ ወታደሮች በዛው ልክ የሚሆኑ ሴቶች ልጆችና አገልጋዮች ከዘመዶቻቸውና ጓደኞቻቸው ጋራ ሲሰነባበቱ የተፈጠረ ነው:: በሺ የሚቆጠር እሳት በየቦታው እየነደደ ለካምፑ ተጨማሪ ብርሃን ሠጥቶታል:: የመጨረሻው ስንብት እንዳለቀ የቀሩት ወደ የቦታቸው ሲሄዱ እሳቱም ተራ በተራ እንዲጠፋ ተደረገ:: መጨረሻም ቀዝቃዛዋ ጨረቃ ብቻ ለካምፑ ብርሃን ሆነች::






ወደ ጦር ግንባር የሚሄዱ የኢትዮጵያ ዘማቾች ቤተሰቦቻቸውን ሲሰናበቱ በሐረር ግንባር



# ምዕራፍ ስምንት

## የሠራዊቱ ግምገማ

የሰሜን ቆዳ ስፋት ወደ ሰላሰ አምስት ሺ ካሬ ኪሎ ሜትር ነው ተብሎ የሚገመተው፡፡ የህዝብ ቆጠራ ተደርጎ ስለማይታወቅ የነዋሪውን ቁጥር ማወቅ አስቸጋሪ ነበር፡፡ በደጃዝማች አገዛ በኔ ስሌት ቁጥሩን ከሶስት መቶ ሺ እስከ አራት መቶ ሺ አድርጌዋለሁ፡፡

የሰሜን ግዛት በስድስት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ በሰላም ጊዜ እነዚህን ክፍሎች የሚያስተዳድሩ ገዥዎች በጦርነት ጊዜ ደግሞ የጦር አዛዥ ይሆናሉ፡፡ የሁሉም ማዕረጋቸው ፊታውራሪ ነው፡፡ ፊታውራሪ ከኮሎኔል ጋር የሚስተካከል ማዕረግ ነው፡፡ ከፍ ያለው ማዕረግ ደጃዝማችነት ነው ግን እያሌው ራሳቸው ደጃዝማች ስለሆኑ ለሌሎች መስጠት የሚችሉት ፊታውራሪነቱን ነው፡፡

የስድስት ክፍሎች ጠቅላላ ሠራዊት ብዛት ወደ 13500 ሰዎችን ያጠቃልላል፡፡ በዚህ ቁጥር ላይ 1500 የሚሆኑ የጥበቃ ወይም የቀኝ ዘቦችና 1000 የሚሆኑ በፊታውራሪ መርሶ የሚታዘዙ የዳባት ከተማን ስርአትና ደንብ የሚያስጠብቁ ይጨመርበታል፡፡

የቀኝ ዘቦች በቆዩና በሰለጠኑ ታማኝ በሆኑ በሰላም ጊዜ ቋሚ ጦር ሆነው የሚያገለግሉ ወታደሮች የተመሰረተ ነው፡ ይህ ጦር ለዳጃች እያሌው ጥበቃና ህይወት ሀላፊነት አለበት፡፡ ትጥቅን በሚመለከት ዘመናዊ መሳሪያም እንደ መውዜር፣ ሊ መትፎርድ እና ማንሊቸር፣ አራት ከባድ አውቶማቲክ መሳሪያዎች፣ አስር ቀለል ያሉ አውቶማቲክ መሳሪያዎች ከበቂ ጥይት ጋራ የታጠቁ ነበሩ፡፡ የሚከበሩ ጠባቂዎች ናቸው፡፡ ከሌሎች ወታደሮች የሚለዩት እነዚህ ዘቦች ተብለው ስለሚጠሩና ከመላው ጦር የወታደር ዩኒፎርም የሚለብሱ እነሱ ብቻ ስለሆኑ ነው፡፡

የእዝ ሰንሰለቱ የተወሳሰበ ነው፡፡ ምክንያቱም በአብዛኛው የሚከተለው ህግ ወይም ደንብ ስላልነበረው ነው፡፡ ለምሳሌ እንደ ኮሎኔል የሚቆጠረው



ፊታውራሪ መቶ ሰዎች ብቻ ሊያዝ ይችላል ይህ ደግሞ ከንጉሡጋራ እንዳለው ቅርበት ወይም ሽረት ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም የትንሽ ከተማ ገዢ ይሆንና በቂ የሰው ቁጥር ላያሰልፍ ይችላል፡፡ ባጠቃላይ የማእረግና የሚያዟቸው ሰዎች ቁጠር እንደሚከተለው ነው፡፡

| | |
|---|---|
| አስር አለቃ | የ25 ሰው አዛዥ |
| አምሳ አለቃ | የሀምሳ ሰው አዛዥ |
| መቶ አለቃ | የመቶ ሰው አዛዥ |
| ሻምበል | የኮምፓኒ አለቃ ሁለት መቶ ህምሳ ሰው አዛዥ |
| ሻለቃ | የአንደ ሺ ሰው አዛዥ |

ፊታውራሪ ደግሞ በስሩ የሶስት ሻለቃ ጦር ይኖረዋል

የማዕረግ እርከኑ ደግሞ ከታች ወደ ላይ ከባሻ፣ ባላምባራስ፣ ግራዝማች፣ ቀኛዝማች፣ ፊታውራሪ፣ ደጃዝማች እና ራስ (ማርሻል) ነው፡፡ ማዕረጉ በትክክል የሚያዙትን ሰው ቁጥር ላይገልፅ ይችላል፡፡ ምናልባትም ቀደም ሲል የተወሰነ ደንብ ሊኖረው ይችላል አሁን ግን የለውም፡፡

በታህሳስ አምስት በጥዋቱ ደጃዝማች የሠራዊቱ ቁጥር እንዲታወቅ ትዕዛዝ አስተላለፉ፡፡ ምልክት በሚሰጥበት ጊዜ ብረት ወይም መሳሪያ መያዝ የሚችል ወንድ ወደ ከፍት ሜዳው ወጥቶ መሰለፍ አለበት፡፡ ሁሉም ሰው ድምፁን አጥፍቶ እንዲንቀሳቀስ ታዟል ምክንያቱም ድንገት አውሮፕላን ቢመጣ ከፍታ ቦታ ላይ ሆነው የሚጠብቁ ሰዎች የሚተኩሱቱን የማስጠንቀቂያ ተኩስ መስማት እንዲቻልና ሁሉም ወደ መጠለያ ወይም ጫካ በመግባት መደበቅ እንዲችል ነው፡፡ አጋጣሚ ሆኖ ያን ቀን ምንም አውሮፕላን አልመጣም፡፡

ከጥዋቱ ሶስት ሰአት ሲሆን ሰው እንዲሰበሰብ ጥሩምባ ተነፋና ከአንድ ሰአት በኋላ ቆጠራው ተጀመረ፡፡ ስድስት ሺ ሰዎች ብቻ በሶስት ረድፍ ተሰልፈው ከሜዳው በአንድ በኩል ቆመዋል፡፡ ከዚህ ውጭ በሌላ ቦታ አራት ፊታውራሪዎች ከጦራቸው ጋራ እንዳሉ ታወቀ፡፡

መጀመሪያ የቀኝ ዘቦች በየኮምፓኒያቸው በመሆን በሁለት ረድፍ ተሰልፈው በደጃዝማች ፊት አለፉ፡፡ ተጨማዶ የተሰፋው ዩኒፎርማቸው አላሳመራቸውም፤ የሰልፍ መስመራቸውንም አልጠበቁም፤ ነገር ግን ጠንካራ ይመስላሉ፡፡ መሳሪያዎቻቸው ደግሞ በደንብ የተያዙ ሲሆን ሁለት ጥምጥም ዝናር ሙሉ ጥይት በትከሻቸው ላይ አድርገዋል፡፡ አራቱ ከባድ አውቶማቲክ መሳሪያዎችም በደንብ ተይዘዋል፤ ካርታና የጥይት ሣጥኖች ሳይቀር

በደንብ ተይዘዋል፡፡ የጋማ ከብቶቹ ፈረሶችና አህዮቹም ሳይቀር ያረፉና የወፈሩ ናቸው፡፡ ለሶስት ቀን ስንቅ የሚይዝቡት ከረጢት በስተቀር ወታደሮቹ ሌላ ጓዝ አልያዙም፡፡ አያሌው በነዚህ ወታደሮች እንደሚኮሩ ግልፅ ነበር፡፡ አልፎ አልፎ እኔን ሠረቅ እያደረጉ በማየት ወታደሮቹ ያሳደሩብኝን ስሜት ለማየት ሲሞክሩ አስተውያለሁ፡፡

ከዘቦቹ በኋላ ሌሎች ወታደሮች በየደረጃቸው ተሠልፈው መጡ፡፡ በአንዱ መስመር ሁለት ሰዎች ብቻ አንድ አይነት ጠመንጃ ይዘዋል፡፡ በግምት ከየመቶው ሰው ሰባቱ ጎራዴ ብቻ ወይም በትር የያዙ ናቸው፡፡ በተለይ የማስታውሰው የአሥራ ስምንት አመት ወጣት ልጅ በኩራት መንፈስ ዱላውን በቀኝ ትከሻው ላይ አድርጎ ይንጎራደድ ነበር፡፡ ዱላው የአንጨት ሲሆን ቀይ ቀለም ያለው ሆኖ አላዩ ላይ ጌጥ ተቀርፆበታል፡፡ የዚህ ወጣት ልጅ የተለየ ኩራትና አካሄድ የሰዎችን አይን የመሳብ ችሎታ ፈጥሯል፡፡

ደጃዝማችም አስጠሩትና

"ዕድሜህ ስንት ነው?"

"አባቴ የሚነግረኝ በንጉሥ ሚካኤልና በሸዋ ገዥዎች መሀከል በተደረገው የሰገሌ ጦርነት ወር ነው የተወለድኩት"

"መልካም በዚህ በሚያምር ዱላህ ምን ልታደርግበት ነው?"

"በዚህ ዱላ ነጭ ልገልበት ነው"

"እንደሱ እንኳን ማድረግ አትችልም በምትኩ ጠመንጃ ልሰጥህ"

"የለም አመሰግናለሁ፤ ለአባቴ የማልኩት ቃለ መሀላ ጣልያን ገድዬ ጠመንጃውን ወስጄ አሳያለሁ፤ አለዚያ በዚህ በጦር ሜዳ እቀራለሁ"

ቀጥሎ ደግሞ ጠመንጃና ጥይት ሁሉም ተመልሶ ተሰብስቦ እንደገና በየአይነቱ ተመድቦ ለእያንዳንዱ ወታደር ስም እየተፃፈ የወሰደው ጠመንጃና አይነትና የጥይት ቁጥር እንዲመዘገብ የሚል ትዕዛዝ ተላለፈ፡፡ የማጉረመረም ድምፅ ተለማና በሚከራከሩ ድምፆች ተከተለ፡፡ ሁኔታው አደገኛ መሰለ ነገር ግን ደጃዝማች ለዚህም ተዘጋጅተው ስለነበር ሰዎቹን ማረጋጋቱን አወቅውበታል፡፡ ወድያውኑ ይህንን ትዕዛዝ መስጠት የተገደዱት በቂ ምክንያት ስላላቸው ነው፤ በምትኩ ግን እያንዳንዱ ወታደር ከጠላት የወሰደውን ጠመንጃና ጥይት የራሱ ማድረግ እንዲችል ተፈቅዶለታል አሉ፡፡ የደስታ ጩኸት ከመላው ሠራዊቱ ተሰማ፤ ተከትሎም መዝጋቢዎቹ ከሚችሉት በላይ እስኪሆን ድረስ በፈቃደኛነት መሳሪያዎች በፍጥነት መመለስ ጀመሩ፡፡



በአቢሲኒያ ከጥንት ጀምሮ በጦርነት ምርኮ የተገኙ ዕቃዎች በሙሉ ለተዋጊ ወይም ለማራኪው ነው የሚሆኑት፤ ሆኖም መሣሪያና ጥይት ግን ጦርነቱ እንዳበቃ ያለምንም ሽልማት ለመንግሥት መመለስ አለባቸው፡፡

የመጨረሻው ወታደር ተመዝግቦ እንደጨረሰ ጦሩ እንደገና ተጠራ፡፡ እያንዳንዱ የሻምበል ጦር አንድ አይነት ጠመንጃ ለእያንድዳንዱ ሰው ከመቶ ጥይቶች ጋር እንዲሰጥ ተደረገ፡፡ ጠመንጃ ያልደረሳቸው ሰዎች ለደህንነታቸው ሲባል ጠመንጃ ከያዙት ጋር እንዲመደቡ ሆነ፡፡ ይህም ከጠላት የተማረከ ጠመንጃ እስከሚያገኙ ድረስ ወይም ጠመንጃ የያዘ ሰው ሲሞት የሟቹን ጠመንጃ እስኪወስዱ ድረስ ነው፡፡

ይህንን አሰላለፍ ማየት የሚገርም ነበር ቀኑም በፍጥነት ወደ ምሽት ተቃረበ ልክ ከምሽቱ 12 ሰአት ሲሆን ሁሉም ነገር ተከናወነና ወደ ካምፓችን ተመለስን፡፡

ዘማየት ብሎ ማምሻውን ለሌሎች ጦር አዛዦች በተመሳሳይ አይነት ሥርአት ጠመንጃና ጥይት እንደገና እንዲከፋፈል እንዲያደርጉ ትዕዛዝ ተላለፈ፡፡

ማታውኑ ደግሞ ወደ ራስ እምሩ የተላከው መልከተኛ ተመልሶ መጣ፡፡ የራስ እምሩ የጎጃም ጦር ዳባትን ለቆ በሊማልሞ በኩል አድርጎ ወደ ሽሬ እየተጓዘ መሆኑን ተናገረ፡፡ እንግዳ የሆነ ነገር፡፡

በዚህ ዜና ምክንያት ደጃዝማች ካምፑን ለመልቀቅ ወሰኑ፡፡ በሌሊት ተነስተን ከፍታው 500 ሜትር ከሚሆን ከራስ ኮረብታዎች ግርጌ ለመሰፈር ነው የተወሰነው፡፡ ርቀቱ ወደ አስር ኪሎሜትር ይሆናል፡፡ ዝቅ ያለው ቆላማ ቦታና ወይም ደረቁ መሬት ጫካ ለላልነበረው ድንኳን እንዳይተከል ትዕዛዝ ተላለፈ፡፡ ደጃዝማችም ቢሆን ከአንድ ድንኳን በስተቀር ሌሎች ድንኳኖቻቸውን ትተው ነው የመጡት፡፡ ጦሩ ዝቅ ያሉ ቁጥቋጦዎችን ለመኝታ ለመደበቂያ ወይም ለመከላከያ እንዲጠቀም ስለታዘዘ ከበድ ያለ ወይም የተንዛዛ ጓዝ እንዲቀር ተደረገ፡፡

ወደ ሁለት ሺ የሚሆኑ እያንዳንዳቸው ሁለት ሊትር የሚሆን ውሀ መያዝ የሚችሉ ከረጢቶች ብዙ ዕቃ ላልተሸከሙ ሰዎች እንዲሠጡ ሆነ፡፡ ውሀ የትኛው ቦታ ሊኖር እንደሚችል ማንም ለው መገመት አይችልም፤ ስለዚህ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ከረጢቶች በውሀ መሞላት አለባቸው፡፡

እንግዲህ አንድ ነገር እንደሚሆን እያወቅን መጣን፡፡

ወታደሮች የሚይዙትን ነገር ማዘጋጀት፤ መሳሪያቸውን መወልወል፤ ጎራዴያቸውን መሳል ጀመሩ:: የጦርነት ቀረርቶና ፉከራ ተጀመረ:: ከዚህ በፊት ጦር ሜዳ የዋሉ ለአዲሶቹ ታሪካቸውን መንገርና መፎከር ተጀመረ:: ጀግናው መሳሪያውን ጨብጦ ወደ ፊትና ወደኋላ እየተንጎራደደ ሰላደረገው ጀግንነት ፉከራ ያሰማል:: በመሀል ወደ ፊት ይገሰግስና አዳማጮቹ ፊት ጉራዴውን መዞ እንዴት ጠላቱን እንደሚያጠቃ ያሳያል:: ላልተዘጋጀ ሰው አደገኛ ነው:: በእንደዚህ አይነት ትዕይንት ብዙ የአውሮፓ ሰዎች በድንጋጤ አመድ ሲመስሉ አይቻለሁ:: ነገሩ ግን ከፉት የሌለው ነገር ነው:: እንዲህ አይነቱ እንቅስቃሴ በአገሬው ሰዎች በጣም ነው የሚከበረው::

በጣም የዷጉት ሰዎች መንቀሳቀስ ከሚገባን ሰአት ቀደም ብለው ጉዞ ጀምረዋል:: ረጅም የማያቋርጥ የሰዎች መሰመር ከካምፑ እየለቀቀ ሲሄድ ይታያል:: ሰዎቹን ማሰቆምም አልተቻለም::

ከካምፑ መልቀቅ ስንጀምር ከደቡብ አቅጣጫ አንድ አውሮፕላን መጣ፤ በሚገርም ሁኔታም እኛን ሳያየን ወደ ሰሜን አቅጣጫ መንገዱን ቀጠለ:: እየመሸ ከቀኑ አሥራ አንድ ሰኣት ስለነበር በዚያን ቀን የመጣው አውሮፕላን አንድ ብቻ ነበር::

የቁልቁለቱ መንገድ ካሰብነው በላይ አስቸጋሪ ነበር:: የከብት መተላለፊያ መንገድ ሆኖ ቁልቁል ሰለት ወዳላቸው የአለት ድንጋዮች ነው የሚወሰደው:: በአንድ ቦታ መንገዱ የሚያዳልጥ ዳገትነት ባለው የአለት ንጣፍ ላይ ነው የሚያልፈው:: ከሰር የሞቱ ፈረሶችና አህዮች ይታያሉ:: አለቱ ላይ ቆንጥጠው መርገጥ ሰላልቻሉ ተንከባለው ወድቀዋል:: እዚህ ቦታ ላይ ሁሉም የጭነት ከብቶች ጭነታቸው መውረድ ነበረበት::

አልፎ አልፎ የድንጋይ ናዳዎች ከላይ ወደታች ይወርዳሉ:: ከዳጃዝማቹ ጎን ለጎን እየሄድኩ ግማሽ መንገድ የሚሆን እንደሄድን ድንገት ከላይ በኩል ጩኸት መሰማት ጀመረ:: ለማሰብም ጊዜ አልነበረንም፤ የሰዎች እጆች ሁለታችንም ጎትተው ወደ አለቱ ግድግዳ ወረወሩን:: እዛው ላይ ተደግፈን ቆጭ እንዳልን በላያችን ላይ እንደጉም ጥላ አለፈ:: ድንጋይ ናዳ ከነአቧራው ነበር:: ከስር ናዳው መሬት ላይ ሲወርድና ሲንከባለል መሰማት ይቻል ነበር:: ከናዳው ጋር አብሮ የወረደው ከላይ ከከፍታው የተንከባለለ የጭነት ፈረስ ነበር:: ንቁ ዘቦች ተፈናጥረው ባይወረውሩን ኖሮ እኛ ላይ አርፎ ይጨፈልቀን ነበር::

ከብዙ ችግር በኋላ ከምሽቱ ሶስት ሰአት ሲሆን ካምፕ የምናደርግበት



ቦታ ደረስን:: አዲስ ነገርም ነው የጠበቀን:: ሰው ያልነካው ቦታ ነበር:: ሳሩ ራሱ ከሰው ቁመት በላይ አድጓል ግን እንደ ማገዶ እንጨት ድርቅ ያለ ነው:: አንድ ግድ የለሽ የሆነ ሰው በጀመረው እሳት ሳሩ መንደድ ጀመረ:: በቅፅበት ቁመት ያላቸው የእሳት ነበልባሎች በከፍተኛ ድምፅ ወደ ፊት እየተቀጣጠሉ ሲወረወሩ ማየት ጀመርን:: እራሳችን በዚህ ሣር ሜዳ መሃል ላይ ነው የነበርነው:: ተመስገን ነፋስም አልነበረምና በመቶ የሚቆጠሩ ወታደሮች ተረባርበው እሳቱን ባያጠፉት ኖሮ ብዙዎቻችን በዚሁ እሳት ተቃጥለን እንሞት ነበር:: ይህ ሁሉ የሆነው በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ነበር::

አባቦች ደግሞ ሌላ ችግር ፈጥረውብን ነበር:: ያን ቀን ማታ የተገደሉት አባቦችን ቁጥር ሳይ መሬቱ በሙሉ እንዳለ በአባብ የተሞላ ነው ያሰብላል:: በየቦታው አባብ በዱላ ሲቀጠቀጥ ከዚያ ቀጥሎ በአፎይታ "እንካ ቅመስ የታባከንሰና" የሚል ድምፅ እንሰማለን::

ከአንዲት ሴት በስተቀር በአባብ የተነደፈ ሰው አልነበረም::

እንደ አባብ ፈርሃቱ ምንም እንቅልፍ ሳይዘኝ ነው ያደርኩት፤ ሆኖም ሙሉ ጨረቃ ራሱም ተጨምሮ ነው:: ሙሉ ጨረቃ ሲሆን መንገድ ላይ ከሆንኩ እንቅልፍ ነሰቶ ቅዠት የሚለቅብኝ ነገር አለ:: በቀን ደግሞ በሙቀቱ ምክንያት ምንም ዕረፍት ማግኘትም አልቻልኩም::

በምሳ ሰአት ደጃች እያሌው ከአንድ ጣልያኖችን ከሰለለ ከኛ ሰው አዲስ መረጃ እንዳገኙ ነገሩኝ:: በእንዳባጉና ሰፍሮ የነበረው በሜጀር ከሪኒቲ የሚመራ ጦር ከጥቂት ቀናት በኋላ ካምፑን ለቆ እንደሚሄድ ነው:: ሰውየው የጣልያኖቹ ወታደሮች ወደኋላ ይሸሹ ወይም ወደ ፊት ወደ ተከዜ ወንዝ ይንቀሳቀሱ ያወቀው ነገር የለም::

ደጃዝማች ወድያውኑ ወደ ጦር ግንባር መሄድ እንዳለብን ወሰኑ:: የሰሰት ቀን ስንቅ ብቻ እንዲያዝና ወታደሮች ብቻ እንዲንቀሳቀሱ፤ የምንነሳበት ሰአትም ከቀኑ አሰር ሰአት ላይ እንዲሆን ሆነ:: ሌሎቹ ተከታዮችና ጓዝ የሚያጓጉዙት ከኛ በኋላ በጥንቃቄ በአንድ መኮንን ትዕዛዝ እንዲከተሉ ተወሰነ::

ቀጥሎ የተደረገው ጉዞ ግን ከዚህ በፊት አይቼው የማላውቀው ወደፊትም የማልመኘው አይነት ነበር:: ደጃዝማችም የመነሳሳት ሰሜት ይታይባቸዋል:: በቅሏቸውም ቢሆን የመቁነጥነጥ ሁኔታ ታሳይ ነበር:: ሰለዚህ እንደፈለገች እንድትጋልብ ለቀቅ አደረጓት:: እኛ ሁላችን መከተል ነበረብን:: አህዮችም እየጋለቡ ተከተሏት፤ ወታደሮቹ በሶምሶማ ወይ በሩጫ ይከተሉ ነበር፤ ይህ ሁሉ አንደ ቁንጥንጧ የአዛዡ በቅሎ ፍጥነት ነበር::

እስከ ምሽቱ አንድ ሰአት ጉዞው በዚህ ፍጥነት ተካሄደ፡፡ መሀል ላይ የጥቂት ደቂቃዎች እረፍት ነበር ያደረግነው፡፡ መጨለም ሲጀምር ሰላሳ ኪሎሜትር የሚሆን መንገድ ከኋላችን ጥለን መተናል፤ ጨረቃዋ ሙሉ በሙሉ እስከትወጣ መጠበቅ ነበረብን፡፡

የደረስንበት ቦታ ነፃ የወጡ የቀድሞ አገልጋዮች ሠፈር ነበር፡፡ ድንኳን ወጥረው ጠበቁን፡፡ ጠላና ቡናም ተጋበዝን፤ በጣም ጥሩም ነበር፡፡ እነዚህ ነፃ የወጡ አገልጋዮች በደንብ ተደራጅተው ማየት አስገራሚ ነበር፡፡ የራሳቸው አለቃ መርጠዋል፤ የራሳቸው ቤተክርስቲያንና ቄስም ነበራቸው፡፡ በአብዛኛው ወደ ደጋው እየወሰዱ በሚሸጡት በጥጥ እርሻ ነው የሚተዳደሩት፡፡ ቦታውም ለም ነበር፡፡ በሰው ተይዞም ስለማያውቅ የመሬት ባለቤትነት ከርከርም አልነበረም፡፡ ዋናው ጠላት ወባ ነበር፡፡ በያመቱ ብዙ ልጆች ይሞታሉ እንደዛም ሆኖ ቁጥራቸው በመቶዎች የሚቆጠር ደርሷል፡፡

ከሁለት ሰአታት እረፍት በኋላ ጉዞ እንደገና ተጀመረ፡፡ አሁን ግን ረጋ ያለ አካሄድ ነው የምንሄደው፡፡ ሰውም እንስሳውም በጉዞው ምክንያት ተወጥሮና ደክሞም ነበር፤ የጭነት ከብቱና አውቶማቲክ መሳሪያ የተሸከሙ ወታደሮችን ጨምሮ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ብዙ ወታደሮች እግራቸው ውሀ መቋጠር ጀምሮ ነበር፡፡ በሾህ የተወጋውም በዚያው ልክ ነበር፡፡ መንገዱ ድንጋይ የበዛበትና ዳገት ነበር፤ የነበረው ብርሃን ደግሞ የጨረቃዋ ብቻ ነበር፡፡

የደከሙ ወታደሮች እንስሳቱም ጉልበታቸው እስኪመለስ ረዘም ያሉ የእረፍት ጊዜዎች መውሰድ ነበረብን፡፡ እንደዚሁ ተጉዘንም መጨረሻ ዛሬማ የሚባል ወንዝ አጠገብ ስንደርስ አቆምን፡፡ ከሌሊቱ አስር ሰአት ነበር፤ የጥዋት ኮከቦች መውጣትም ጀምረው ነበር፡፡ ባጠቃላይ ወደ ሃምሳ ኪሎሜትር የሚሆን ተጉዘናል፡፡

ማረፍና እቧራና ላባችን መታጠብ ጥሩ ስሜት ነው የፈጠረልን፡፡ ከዚህ ጋር ደግሞ ቡና መጠጣት ብርታት ጨመረልን፡፡ ከዚህ በኋላ እያንዳንዱ ሰው ለመኝታ የሚሆን ቁጥቋጦ ወይ ዋሻ ፈልጎ ማግኘት ነበረበት፡፡

ፊታውራሪ ዘውዱና ፊታውራሪ ሙላው እንዲጠብቁን የተባለው ቦታ ስላልደረሱ ዕቅዱ ተቀየረ ይህም የሆነው ባልታሰበው ብዙ ሰው ባደከመው የፍጥነት ጉዞ ምክንያት ነው፡፡ የደጃማቹን ትግሰት ማጣር ስሜት ለማሟላት ካልሆነ በስተቀር መንገዱ የጠቀመው ነገር ያለ አልመሰለም፡፡ ምናልባትም ይህን የጉልበት ፍተሻ እንቅስቃሴ ያደረጉበት በቂ ምክንያት ይኖራቸው ይሆናል፡፡ ማን ያውቃልለ በድንገተኛ ጊዜ የጦሩን ችሎታ ለማወቅ በዚህ መንገድ ወስነውስ ከሆነ፡፡



# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ጦር ግንባር ደረስን

በነጋታው በአቶ ማሞ ከእንቅልፌ ሰቀሰቀሰ ፀሀይዋ ወጥታ ሰማዩ ላይ ከፍ ብላ ነበር፡፡ ጀርባው ላይ ትልቅ የአሳ ማጥመጃ መረብ ተሸክሟል፡፡ እኔንም አሳ ለማጥመድ ወደ ወንዝ ተከትየው እንድሄድ ጠየቀኝ፡፡ አሳ ማጥመድ አስደለቶኝም አያውቅም ነበር ለማንኛውም አብሬው ሄድኩ፤ የሚያዝናናም ሆኖ አገኘሁት፡፡

የወንዙ ውሀ ከሚወርድበት ግርጌ ቦታ መረጥን፡፡ ውሀው የጠራ ነበር ብዙ አሳዎች ነበረው፡፡ ከትንሽ ሙከራዎች በኋላ እያንዳንዳቸው ሁለት ኪሎ የሚሆኑ ሰምንት ትልልቅ አሳዎችና ብዙ ትንንሾች ጨምረን ያዝን፡፡ ካጠመድናቸው አሳዎች ግማሹን ለደጃዝማች ላከን፤ የተረፉት ደግሞ ወደ አቶ ማሞ መጥበሻ ተወሰዱ፡፡

በዛው ጊዜ ውስጥ በቀዘቃዛው የወንዝ ውሀ ሰውነታችን በደንብ ታጥበን በትኩሱ በሰሎ የደረሰውን አሳ በላን፡፡ የሚጣፍጥ ነበር፡፡

በዛሬማ ወንዝ ብዙ ጉማሬ እንዳለ ሰምተን ነበር፡፡ በወንዙ ዳርቻ ብዙ የጉማሬ ኮቴ በማየታችን መኖራቸውን አረጋገጥን፡፡ ነገር ግን ሙሉ ቀን ሰንፈልግ ብንውል ደግሞ ጉማሬዎችን ማግኘት ሰላልቻልን ፍለጋውን አቆምን፡፡ እንስሶቹ ብዛት ያለው የሰው ቁጥር ሲያዩ ሸሽተው ሳይሄዱ አልቀሩም፡፡ የጉማሬው መንጋ ገና በጠዋቱ ያየን ይመስላል፡፡

አመሻሹ ላይ ፊታውራሪ ዘውዱና ሙላው ከወታደሮቻቸው ጋራ ደረሱ፡፡ ካምፓቸውን የአንድ ሰአት መንገድ ርቀው የዛሬማ ወንዝ ገባር የሆነች ትንሽ ወንዝ አጠገብ አደረጉ፡፡ በሚቀጥለው ቀን ደጃዝማች የጦራቸውን አሰላለፍ ግምገማ በሚያደርጉበት ጊዜ አብሮ የመሄድ አጋጣሚ አገኘሁ፡፡

የሁለቱን ሠራዊት አሰላለፍ ማየት የሚገርም ነገር ነበር፡፡ የሁለቱም ሰዎች ወታደሮች ጎን ለጎን ቆመዋል፡፡ የፊታውራሪ ሙላው ወታደሮች የቆላ ሰዎች ሰለሆኑ በለውነት መጠናቸው አነስ ያሉ ናቸው፡፡ ቀጠን ደረቅ ያሉ ሆነው ግን

ንቁና ቅብጥብጥ ናቸው፡፡ የፊታውራሪ ዘውዱ ወታደሮች ደገኞች ናቸው፡፡ ሁሉም በቁመት ከአማካኝ በላይ ረዘም ያሉ ናቸው፡፡ ሰውነታቸው
ፈርጠም ያለ ሆኖ ረጋ ያለ መንፈስ ነው የሚያንፀባርቁት፡፡ ከነዚህ ሁለት አይነት ሰዎች የትኛው በጀግንነትና በድፍረት ጦረነት ላይ ውጤት እንደሚያመጣ በቀላሉ ማወቅ አይቻልም፡፡

እኔን ሲያዩ የሚያሳዩት ባህሪና አመለካከታቸው አላስደሰተኝም፡፡ ደጃዝማች አየቀለዱ የመጀመሪያው የነጭ ምርኮኛ ይኸውና ሲሉ ያሳዩት ሁኔታ በተጨማሪ ጥሩ አልነበረም፡፡ በእኔ ጥያቄ ደጃዝማች በኋላ  እኔ ማን እንደሆንኩ ከነሱ ጋራም ምን እያደረግሁ እንደሆን ማብራሪያ ሰጡ፡፡

ማምሻውኑ ካምፑን ለቀን ሰሙን የረሳሁት ትንሽ ወንዝ አጠገብ ሌሊቱን አሳለፍን፡፡ የማልታውሰው ነገር ቢኖር አንድ ወታደር ዘንዶ መግደሉን ነው፡፡ ሰውየው ከአንድ ዛፍ ስር ተጋድሞ ነበር፡፡ በጥዋት ሲነጋ ከላይ የዛፉ ቅርንጫፍ ትልቅ የተጠመጠመ ነገር ያያል፡፡ ተነስቶ ምን እንደሆነ ለማወቅ ጠጋ ብሎ ሲያይ የተጠመጠመው ነገር መንቀሳቀስ ይጀምራል፡፡ ሰውየው ወዲያው ገባውና ከመቅፀበት ጠመንጃውን አንስቶ ዘንዶው ላይ ካርታውን እንዳለ ጨረሰበት፡፡

የሞተው ዘንዶ ቁመት ሲለካ ሰባት ሜትር ነበር፡፡ በግንድ ላይ አንጠልጥሎ ዘንዶውን ወደ ደጃዝማች ለመውሰድ ስድስት ሰዎቹ መሸከም ነበረባቸው፡፡ የቀኑ ጀግና የተኮሰው ጥይት መጠን ተተከቶለት የሃምሳ ብር ሽልማት ተሠጠው፡፡ በተጨማሪም ጥሩ ንግድ ቀናው፡፡ የዘንዶውን የጎን አጥንት በአሰር ብር ሸጠ፡፡ ይህ አጥንት መድሃኒትነት አለው ስለሚባል በጣም ተፈላጊ ነበር፡፡ ከመድሃኒትነት በተጨማሪ ደግሞ ለአስማት ይሆናል፤ ፍቅር ያስይዛል ተብሎም ይታመናል፡፡

ማታውኑ ጨረቃዋ ብርሃን መስጠት ስትጀምር መንቀሳቀስ ጀመርን፡፡

በዛሬማና በዱኮኮ ወንዝ መሀል ያለው መሬት የሚቀጥለው ካምፕ ቦታችን ነው፡፡ ይህ ቦታ በአቢሲኒያ ስመጥር የሆነው የዋልድባ ገዳም ቦታ ነው፡፡ መሬቱ ቅዱስ ነው ስለሚባል ለአርሻ አይጠቀሙበትም፡፡ ለው የማይነካው መሬት ስለሆነ የተለየ አንግዳ የሆነ የዛፍ አይነት በብዛት ያድግበታል፡፡ ይህ ዛፍ ቅጠል የማይኖረው ጊዜ አለ፤ ግንዱም አንደ አገዳነት ይቃጣዋል፡፡ በጣም በፍጥነት ስለሚያድግ አንጨቱ ለስላሳ ይሆንና ከእንጨት ይልቅ ወረቀት ይመስላል፡፡



ገዳሙ በአንድ ትንሽ ወራጅ ውሀ ከሁለት ቦታ ተከፍሏል፡፡ በአንድ በኩል ቤተክርስቲያኑና መኖሪያ ቤቶች ያሉበት ነው፡፡ ተራ መነኩሴዎችና ዲያቆናቱ በዚህ ቦታ ይኖራሉ፡፡

በሌላው በኩል ግን ማንም አንግዳ አንዲገባ የማይፈቀድለት ቦታ ነው፡፡ በዚህኛው ቦታ የሚኖሩት ደግሞ የበቁ መነኩሴዎች ወይም መናኞች ናቸው፡፡ እነዚህ መነኩሴዎች ወይም መናኞች ለአንድ አመት ከሰው ተለይተው የጫካ ሥራስርና ቅጠል አየበሉ ለመኖር መሀላ የገቡ ናቸው፡፡ አንድ አመት ሲያልፋቸው ወደ መኖሪያው ቦታ ይመለሱና በቦታቸው ደግሞ ሌሎች መናኞች ይተካሉ፡፡

ለዋልድባ አካባቢ የተቀደሰ መሆን ሁለት ምክንያቶች አሉት ይባላል፡፡ አንደኛው ምክንያት አዳኛችን (ኢየሱስ ክርስቶስ) በምድር በነበረበት ጊዜ ይህን ቦታ በእግሩ ተራምዶበታል፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በክርስትና ሀይማኖት መጀመሪያ አካባቢ 999 ቅዱሳን ከሮማ ተነስተው ወደዚህ መጥተዋል ነው፡፡ የመጡበት ምክንያት ደግሞ በዚህ ስፍራ በሰላም ለመሞት ነው፡፡ ስለዚህ እነሱ በተቀበሩበት በዚህ ቦታ የቀረው የቅዱሳኑ አፅም መረበሽ የለበትም፡፡

የዋልድባ ገዳም አከብሮት ሀይል በግልፅ መታየት የሚችል ነገር ነበር፡፡ ሁሉም ወታደሮች ቦታውን በአምነትና በአከብሮት ስለሚያዩት ሲነጋገሩ እንኳን አየተንሾካሾኩ ነበር፡፡

አኩለ ሌሊት ሲሆን ብጫ ቀሚስ የለበሱ መነኮሳትና ዲያቆናት በሰልፍ ተቀበሉን፡፡ መምጣታችን ስለሰሙ አቀባበል አደረጉልን፤ ምግብና ጠላ ቀረበልን፡፡ የፍራፍሬ ከምሮች አንደ ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ፐላም አየተዘረ ለሰው ተሠጠ ተጋባዦችም በደስታ ተቀበሉት፡፡ ለረዠም ጊዜ እንደዚህ የመሰለ ነገር ያየ ሰው አልነበረም፡፡ የገዳሙ ትልቅና በደንብ የተያዘ የፍራፍሬ ተከል አርሻ አለ ተብሎ የሚወራውን ወሬም አረጋገጠልን፡፡

የገዳሙ ሀላፊ አባ ገብረ ሥላሤ መጥተው ተገናኘን፡፡ አባ ገብረ ሥላሴ ሶስት መቶ የሆኑ የታጠቁ ወታደሮቻቸውን ይዘው ጦር ሜዳ ሲከተሉን ነው፡፡ የቤተከርስቲያን ሰው ስለሆኑ ጠመንጃ መያዝ አይችሉም ነገር ግን በሁለት ጎኑ ስለት ያለው ጎራዴ ከኮርቻቸው ላይ ተንጠልጥሎ ይታይ ነበር፡፡

ከሌሊቱ ሰምንት ሰአት ሲሆን ደቀቆ የሚባል ወንዝ ስንደርስ ፊታውራሪ ሸፈራው ከቦታው ሲጠብቁን አገኘናቸው፡፡ ምንም ሌሊት ቢሆንም

የፌታውራሪው ወታደሮች ነቅተው ሲጠብቁን ስለነበረ በፉከራና በሽለላ ነው የተቀበሉን፡፡ እንዳበደ ሰው ወዲያ ወዲህ እያሉ የሚያቅራሩትና የሚፎከሩ ሰዎች ከዚህ በፊት አይቸው የማላውቀው አይነት ነበር፡፡ ዋነኛው የጦርነት ስሜት መታየት ጀምሮአል ለእኔ ግን የበዛና የተጋነነ መሰለኝ፡፡

በሚቀጥለው ቀን እዲስ የተቀሳቀሰን ጦር እስላለፍ ግምገማ ተደረገ፡፡ ግምገማው በኢጣልያ ቃኝ ወይም ሰላይ አውሮፓላኖች ምክንያት ሁለት ጊዜ መቋረጥ ነበረበት፡፡ በዚህ ሁኔታ እያለን እንዳባጉና ያለው የኢጣልያ ሜጀር ወደኋላ እንዲያፈገፍግ ትዕዛዝ የተሠጠው መሆኑን ሰማን፡፡ ምክንያቱም የነበረበት ቦታ ቀደም ያለ ወይም ገባ ያለና አደጋ ያለበት ነው ተብሎ ነው፡፡

ውይይት ተደረገና ውሳኔው የሚሸሸውን የኢጣልያ ወታደር ለመዝጋት ምሽጉን ከበን እንድንይዝ ሆነ፡፡

ምሽቱ ላይ የሶስት ፊታውራሪ ጦር ተሻገር፣ ሙላው ና ዘውዱ ወደኋላ ተመልሰው ተከዜ ወንዝን በማቋረጥ በምሽጉ ምዕራብ በኩል እንዲከቡ ታዘዙ፡፡ ያም የሌሊት መንገድ ነው፡፡ ፊታውራሪ ሽፈራው ደግሞ የራሳቸውን 2500 ወታደሮች ይዘው አንድ ሺ ወታደር ተጨምሮላቸው በምሥራቅ በኩል ተንቀሳቅሰው ሐይዳን እቋርጠው ማይ ጥምቀት በመሆን ትዕዛዝ እንዲጠብቁ ተወሰነ፡፡

የጦርነት እንቅስቃሴው ተጀምሯል፡፡ ደጃዝማች በሚሠጡት ትዕዛዝ የረኩ ይመስላል፡፡ በኋላ እንደነገሩኝ ከሆነ በዚህ በጣም ደስተኛ እንደነበሩ ነው፡፡ “ጠላት ላይ ጥቃት ሰማድረስ የመጀመሪያው ስለሆንኩ ሸዋ ላሉት ገዥዎች የማልፈራ መሆኔን እስመሰከራሁ" ቀጥለውም “ እገራችን አደጋ ላይ ባለችበት በእሁኑ ጊዜ የአንድ ሰው ምኞትና ፍላጎት ምን ሚና አለው? ንጉሡ እንደኛ ሰው ናቸው፤ አቢሲኒያ ግን የሁላችንም እናት ነች፡፡”

በሚቀጥለው ቀን ታህሳስ አምስት ከራስ እምሩ የተላከ ደብዳቤ ይደርሳል፡፡ በደብዳቤው መሰረት ራስ እምሩ አዳርቃይ እንደሚገኙ ይህም የተሠጣቸው ትዕዛዝ ወደ ሽሬ ግንባር እንዲሄዱ ስለሆነ ነው፡፡ ደብዳቤውም ደጃች አያሌው ወደ እርሳቸው እንዲመጡና ስለ ጦርነቱ አሰላለፍ እንዲነጋገሩ ይጠይቃል፡፡ ደጃዝማች ሰረኸርም ሰእት በማሰብ ከተቀመጡ በኋላ ለመልከተኛው

“ተመሰስና ለጌታህ ዛሬ ማታውን ወደ እሰዎ እመጣለሁ ብለህ ንገር” ብለው ነገሩት፡፡



ወደ አዳርቃይ መንገዱ ወደ ሰላሳ ኪሎሜትር ይሆናል እና ራስ እምሩ እንዲህ ያለ የማይመች ነገር ለምን እንደጠየቁ ማሰብ ጀመርን፡፡ ነገሩ በጣም አስቸኳይ ከሆነ ለምን ግማሽ መንገድ መጥተው አንገናኝም?

ሙሉውን ቀን ደጃዝማች እጠር ያሉ ትዕዛዞች ከመስጠት በስተቀር በሀሳብ ተውጠው ነው የዋሉት ፡፡ በታህሳስ ሰባት በጥዋቱ ተነስተው ሰመሄድ እቅድ አድርገዋል፡፡ ሶስት መቶ የሚሆኑ የራሳቸውን ዘቦች ይዘው ሰመሄድ የቀረው ጦር ግን በፊታውራሪ ተሻገር መሪነት ወደ ሀይዳ እንዲሻገር ተወሰነ፡፡ ፊታውራሪ ሽፈራው ደግሞ ሌሊቱን ወደ እንዳባጉና እንዲገሰግሱ ተመከረ፡፡

ደጃዝማች መንገዳቸውን ፀሀይ ገና ሳትጠልቅ ጀመሩ ሆኖም ጨረቃዋ እስክትወጣ ድረስ መጠበቅ ነበረብን፡፡ መንገዱ በወንዞችና በገደሎች መሀል ሰለሆነ አስቸጋሪ ነበረ፡፡ ጉዟችንም አዘገየብን፡፡ ቋጥኞችና የዋርካ ዛፎች በጨረቃው ብርሃን መሬቱን የተለየ መልከና እቀማመጥ ሰጥተውታል፡፡

የዋርካ ዛፍ ትንንሽ ቅጠሎች ያሉት ሲሆን ሙሉ በሙሉ ሲያድግ ከሰምንት እስከ አሰር ሜትር ከፍታ በላይ ይሆናል፤ የጎን ስፋቱም ከሁለት እስከ ሶስት ሜትር ነው፤ የግንዱ ወይም የልጡ መልከ የድንጋይ መልከ ያለው ነው፡፡ ዛፉ ሲያረጅ ከብዙ መቶ አመታት በኋላ ግንዱ ከውስጥ መበስበስ ይጀምርና ወደላይ ወደ ቅርንጫፎቹ ይሄዳል፡፡ በነዚህ በበሰበሱ ግንዶች መሃል የዝናብ ውሀ ስለሚቋት በደረቅ ቦታ የሚኖሩት የሀገሬው ሰዎች ውሃ ይቀዱበታል፡፡

ከአቶ ማሞና ባለቤቱ ጋራ ጎን ለጎን እየጋለብን ከኋላችን ደግሞ የጭነት ከብትና አገልጋዮችን አስከትለን እየሄድን ነበር፡፡ በሁለት የወታደር ምድቦች መሀከል ባለው ከፍተት ሰለምንጓዝ ብቻችን ነበርን፡፡ አገልጋዮቻችን እርስ በራሳቸው ታሪክና ቀልድ እያወሩ ይጓዙ ነበር፡፡ በአቢሲኒያ ያለፈ ታሪክ እያወሩ ጊዜ ማሳለፍ ከሚወደድና ከሚከበሩ ነገሮች አንዱ ነው፡፡ በወሬያቸው መሀከል ይስቁ ሰለነበር የመረጋጋት ምልከት ነበር እኛም ቢሆን ጨዋታውን ማዳመጥና አብረን መሳቅ ጀመርን፡፡

ምናልባት የአንድ ሰአት መንገድ የሚሆን እንደተጓዝን መንገዱ ድንገት የያዝነው ጓዝ ማለፍ በማይቻልበት ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ተዘግቷል፡፡ አንድ ሰው እንደምንም ብሎ ወደ ጫካው ውስጥ ገብቶ ወዲያውኑ ተመለሰ፡፡ የነገረን ጥሩ ዜናም አልነበረም፡፡ ከጫካው ቀጥሎ ደረቅ ወንዝ ነው እንጂ መንገድ እንደሌለ ነው፡፡ እሽከሮቹን እንዲጣሩ ጠይቀን ቢጣሩ ቢጣሩ መልስ የለም፡፡ እንግዲህ ጠፍተናል ማለት ነው፡፡

አሁዱን ታህሳስ ስድስት ከኢጣልያ አውሮፕላኖች ጋራ ድብብቆሽ መጫወት ጀመርን፡፡ አንድ ነገር እንደሚሆን ገብቶናል፡፡ ከኢጣልያ ጦር ተጠግቶ ያለው የኛው ወገን የፊታውራሪ ሽፈራው ጦር ውጤት ምን ይሆን ብለን ማሰብ ጀመርን፡፡

ያን ቀን ብቻቸውን ከሚጓዙ መንገደኞች በፊታውራሪ ሽፈራውና በጣልያኖች መሀከል ጦርነት እንደተደረገ ሰማን፡፡ እንደወሬው ከሆነ ጣልያኖቹ ተሸንፍው ሸሽተዋል፤ እኛ ግን አስተማማኝ መረጃ ስላልሆነ በጥርጣሬ ነበር የተቀበልነው፡፡

ከፀሃይ ግባት በፊት አንደ መነኩሴ ከሚታመን መረጃ ጋራ ጥሩ ወሬ ይዞ መጣ፡፡ ከፊታውራሪ ሽፈራው አማች ከፊታውራሪ ነጋሽ የተላከ ደብዳቤ ይዟል፡፡ ደብዳቤው ጣልያኖች በሚገባ ድል የተመቱ መሆኑን ይገልፃል፡፡ አስር ታንኮች የተጎዱ ሲሆን የጣልያን አስረኞች መማረካቸውን ብዙ መሳሪያ በአቢሲኒያውያኖች እጅ መውደቁን ይገልፃል፡፡ ደብዳቤው ጨምሮም አንድ አጃቸው ላይ ሰለቆሰሉ ፊታውራሪው መፊረም አስመቻላቸውን ያስረዳል፡፡

ጦሩ ሰሰልፍ ሲሰበሰብ ደብዳቤው ተነበበ፡፡ ጆሮ የሚቀድ እልልታ ቀለጠ፤ በአውቶማቲክ መሳሪያ ሀምሳ የሚሆኑ ጥይቶች ወደ ሰማይ ተተኮሱ፤ ይህ የመጀመሪያው ድል ሰለሆነ የደስታ መግለጫ ምልክት ነው፡፡

በዚያ ቀን ምሽት ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ወደ ተከዜ ጉዞ ቀጠልን፡፡ መንገዱ እንደተለመደው አስቸጋሪ ነበር፡፡ ማታውኑ ከወንዙ ሁለት ኪሎ ሜትር ርቀት ከአንድ ትንሽ ወራጅ ውሀ አጠገብ አደርን፡፡

በሚቀጥለው ጠዋት ነጎድጓድ በመሰለ አሰቃቂ ድምፅ ከእንቅልፌ ነቃሁ፡፡ መሬቱም ይርድ ነበር፤ ያለምንም ማወላወል ወደ መሬት ተወረወርኩና እራሴን ሰብስብ አድርጌ በቅሎዎችን ማየት ጀመርኩ፡፡ በቅሎዎቹ ተረብሸው የታሰሩበትን ገመድ መበጠስ ጀመረዋል፡፡

አሥራ ዘጠኝ በምብ ጣይ አውሮፕላኖች በላያችን ላይ ያንዣብባሉ፡፡ ከኛ በፊት ወደ ሀይዳ ሄደው የከተማውን ግማሽ እንዳልሆነ አድርገው ፍርሥራሽ ብቻ አድርገውታል፡፡ አሁን ተከዜ ላይ እያንዣበቡ ነው፡፡ የወንዙን መሻገሪያ እየደበደቡ ነው ደግነቱ በቦታው ማንም አልነበረም፡፡ ከአንድ ሰአት ድብደባ በኋላ ተመልሰው ጠፉ፡፡ እንደገናም ሳንታይ አመለጥን፡፡

ቀን ደግሞ ተመሳሳይ ድምፅ መስማት ጀመርን፡፡ ይኸኛው ግን ራቅ ካለ ቦታ ነበር የሚመጣው፡፡ የራስ እምሩ ጦር ለሁለተኛ ጊዜ ትምህርቱን እያገኘ ነበር፡፡ ያሁነኛው ግን በመርዝ ጋዝ ነበር፡፡ ጣልያኖቹ የራስ እምሩ ጦር ተከዜን



እንዳይሻገር ፈልገዋል፡፡ ውጤቱም ከስስት መቶ በላይ ሰዎች የሞቱና የቆሰሉበት ነው፡፡

ያን ቀን ማታ ተከዜን ስናቋርጥ የታየው ነገር ሰላማዊ ነው፡፡ ጨረቃዋ ገና አልወጣችም የተከዜ ማቋረጫው ሀምሳ ሜትር ስፋትና የአንድ ሜትር ጥልቀት አለው፡፡ በመቶ የሚቆጠሩ ችቦዎች መሻገሪያው ላይ ለብርሃን እንዲሆን በርተዋል፡፡ ወንዙ ውስጥ ያሉ አዞዎችን ለማስፈራራት በወንዙ ዳርቻ ጥይት ይተኮሳል፡፡ ሰውን ከውሀ መስመጥ የሚያድኑ ዋናተኞች ስርአት አስየዘው ጦሩ በሙሉ ያለምንም ችግር በአራት ሰአታት ውስጥ መሻገር ቻለ፡፡

ወደፊት ጉዞ ቀጠልንና ከጠዋቱ አሥራ አንድ ሰአት ሲሆን በታህሳስ ሰምንት ደብረ አባይ ገዳም ደርሰን መጠለያ አገኘን፡፡ ግማሹ ገዳሙ ውስጥ ግማሹ ደግሞ በሶሰት ዋሻዎች ውስጥ ነበር፡፡ ጦሩ ከገዳሙ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ግማሽ ማይል ርቀት የሚገኘውን ጫካ አልፎ እንዳይሄድ ጥብቅ ትዕዛዝ ተሠጠ፡፡




*በሀሬው የዘገቧቸው ቦታዎች በካርታው ላይ ይታያሉ*
*(1) ከተከዜ መሻገሪያ ማይ ጥምቀት ጀምሮ (2) እንዳባጉና (3) አፍጋጋ (4) ሰለከላካ የራስ እምሩ ጦርና የደጃዝማች አያሌው ጦር የተጓዙበትን አቅጣጫና የተገናኙበትን ቦታ ያሳያል፡፡ (5) ሳይታሰብ ጎንደር ገስግሶ የገባው የጄኔራል ስታራቼ መካናይዝድ ጦር በኦም ሀጀር በኩል መነሻውን ያሳያል*

# ምዕራፍ አስር

## በቦምብ መጠመቅ

ስኛ የተመደበልን ዋሻ ማለትም ለደጃዝማች እና ለአሽከሮቻቸው መውጫው በትልልቅ ዛፎች የተደበቀ ትንሽ ወራጅ ውሀ ያለበት ጎድጎድ ወዳለ ቦታ ነው፡፡ ለጥበቃ ሰንል በችኮላ አንድ ሜትር ቁመት ያለው ግንብ በገደሉ በከፍቱ በኩል ገነባን፡፡ ለአየር መከላከያ ደግሞ በሶስት አግር ብረት ላይ የተጠመዱ ሶስት አውቶማቲክ መሳሪያዎች የተለያዩ ቦታዎች ላይ እንዲቀመጡ ተደረገ፡፡ ለእነዚህ መሳሪያዎች ደግሞ የታወቁ ኢላማ ተኳሾች ሀላፊነቱን እንዲወስዱ ሆነ፡፡

ይህ እንዳለቀ ወደ ቤተከርስቲያኑ አመራን የጠዋት ፀሎትም እየተደረገ ነበር፡፡ ስነፃ አውጭው ለደጃች እያሴው የምስጋና መዝሙርና ፀሎት ተደረገላቸው፡፡

ጉዳሙ በንጉሠ ነገሥቱ ሞግዚትነት ስር ስለነበር ቤተከርስቲያኑ በብዙ ገንዘብ ተሠርቶ አልቋል፡፡ ከብ ሆኖ ከሚገባው በላይ ትልቅ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን የአይሁድ ህግ መሠረት እንደ ሌሎቸ የአቢሲኒያ ቤተከርስቲያኖች ውስጡ ከሶስት ይከፈላል፡፡ ከውጭ ወደ ውስጥ ቅኔ ማህሌት፣ ቅድስትና፣ መቅደስ ናቸው፡፡ አራቱ በሮችና አሥራ ሁለት መስኮቶቹ ደግሞ ከጥድ የተሰሩና ጌጥ የተደረገባቸው ናቸው፡፡ የውስጥ ግድግዳ ሥዕሎች በአቢሲኒያ ደንብ መስረት የተሣሉና በደንብ የተያዙ ናቸው፡፡ ከሀይለኛ ብርሃንና ከአቧራ ለመከላከል በከባድ የከፌይ መጋረጃዎች ተሸፍነዋል፡፡ ጣራው ደግሞ በቀርከሃ አገዳና በጥድ እንጨት ተጠላልፎ የተሰራ ነው ደማቅ ቀለምም ተቀብቷል፡፡ ከላዬ ላይ የሳር ከፍከፍ ከዛ በላይ ደግሞ የቆርቆሮ ጣራ ተደርጎበታል፡፡

ቤተከርስቲያኑን እየዞርን ልናይ የነበረው ዕቅዳችን ድንገት "መጣች" በሚል ድምፅ ተቋረጠ፡፡ ውጭ የነበሩ በሙሉ ወደ ውስጥ ገቡ ከአውቶማቲክ መሳሪያዎቻችን አንዱ መንጣጣት ጀመረ፡፡

"እሃ! እንዴት ያለ ነገር ነው?"



ሰዎቹ፣ አውሮፕላኑ ቀድሞ ካልተኮሰ በስተቀር አስቀድመው እንዳይተኩሱ ጥብቅ ትዕዛዝ ተሠጧቸው ነበር፡፡ በችኮላ ለመፎከር ሲሉ ተኩስ ጀምረው አሳልፈው ሠጥተውን ይሆን? እንዳው ሳታየን ቀርታ ይሆን? ጉዳሙ በኛ ምክንያት ቢደበደብ ደግሞ በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው፡፡

ሰላዩ አውሮፕላን ለጥቂት ጊዜ ደጋግሞ ዝቅ ብሎ ከበረረ በኋላ ተመልሶ ሄደ፡፡ ፓይለቱ ያየውን ነገር ተመልሶ እንደሚናገር ተጠራጥረንም ስለነበር እኛም በችኮላ ወደ መደበቂያ ቦታችን ሮጥን፡፡

እንደተጠራጠርነውም ሆነ፡፡




*የኢታልያ ሰላይ ወይም ቃኚ አውሮፕላን (ላይብራሪ ኦፍ ኮንግረስ)*

ሶስት ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች በከፍተኛ ፍጥነት በአናታችን ላይ አለፉ፡፡ ያን ቀን ማከሰኞ ጠዋት ታህሳስ ስምንት ቀን የቦምብ ጥምቀታችን ተቀበልን፡፡

ቀደም ሲል ከርቀት የቦምብ ፍንዳታ መስማት ራሱ በጣም አስቃቂ ነበር፡፡ አሁን ግን በጣም ቅርብ ሲሆን ጠቅላላ ገሃነም ነው፡፡ ፍንዳታው የብርሃን ጨረር እያሳየ ምድሩን አንቀጠቀጠው፡፡ ዛፎች፣ የቦምብ ፍንጣሪዎች፣ ድንጋይ ሰባሪዎች በየአቅጣጫው ሲወረወሩ የፉጨት የመሰለ ድምፅ ከተከታተይ ማጉረምረም ጋራ ይሰማል፡፡ ከዚህ ጋር አብሮ መትረየሶች ከላይም ከታችም ሆነው ይንጣጣሉ፡፡

ግድግዳ ይዘን ተጠጋግተን ቁጭ ማለት፤ እለዚያ ወለሉ ላይ ተዘርግቶ መተኛት ነው፡፡ ደቂቃዎች የረዘሙና የማያልፉ መሰለ፡፡ ፍንጣሪዎች ዋሻው ዙሪያ እየተወናጨፉ ይላተማሉ፤ አልፎ አልፎ አንዱ ወደ ውስጥ ይገባል ሆኖም ጉዳት አያደርስም፡፡ ከመቁሰል ወይም ከፍርሃት የተነሳ ከወጣቶቹ በኩል ልብ የሚሰብር ጩኸት ከውጭ በኩል አልፎ አልፎ ይሰማል፡፡

በኋላ በተለያዩ ጊዜዎች እንዳረጋገጥኩት ከሆነ እንዲህ አይነቱ የቦምብ ድብደባ አንግዳ የሆነ የማደንዘዝ ስሜት ይፈጥራል፡፡ አንድ ሰው ምንም ማድረግ የማይችል መሆኑን ካወቀ የሚያደርገው ነገር አይኖርምም አይሞከርምም፡፡ ለሞት ፍራቻ አልነበረኝም፡፡ ነገር ግን መልሶ ወደ ሀሳብ የሚገባው ነገር ቢኖር በእነዚህ ፍንጣሪዎች መቁሰል ነው፡፡ ከመቁሰልና ከመሰቃየት ደግሞ ቀኑ ደርሶ ከሆነ ፈጣን ሞት ስጠኝ ብሎ ሰው ይመኛል ወይም ይፀልያል፡፡

ይህ የእሳት ትዕይንት እንዳጀማመሩ ወዲያው ቆመ፡፡ ሶስቱ አውሮፕላኖች ያላቸውን በሙሉ አራግፈውብን ሄዱ፡፡ ብዙ ስንቅና ጓዝ ከጥቅም ውጭ አደረጉ፡፡ አሁን እንግዲህ ተመልሰው የአያሌውን ጦር ሙሉ በሙሉ ደመሰስን ብለው ሪፖርት ያቀርቡ ይሆናል፡፡

ሰኛ የነበረን ስሜት አውሎ ነፋስ ሲያባራ እንደነበረ ነው፡፡ ለብዙ ደቂቃዎቾ እየራቀ ከሚሄደው የአውሮፕላኖች የሞተር ድምፅ በስተቀር ሁሉም ነገር ፀጥ ያሰ ነበር፡፡

በኋላ ግን ሁሉም ነፍስ ዘራ መጀመሪያ ሁሉም ማወቅ የፈለገው ነገር ሁኔታው እንዴት እንደሆነ ዘመድና ጓደኞች እንዴት እንደሆኑ ነው፡፡

የቆሰሉት መምጣት ጀመሩ፤ እኔም ለሁለት ሰአታት ስማስን ሀያ ስድስት ቁስለኞችን መርዳት ችያለሁ፡፡ አንዳንዶቹ በአሰቃቂ ሁኔታ ተበጣጥሰዋል፡፡ አንዱ ሰምሳሌ እጁ ከትከሻው ላይ ተገንጥሎ በጥቂት ጅማቶች ብቻ ተይዞ ተንጠልጥሎ ይታያል፡፡ በሌላኛው ከአሥራ ስምንት ያላነሱ የቆሰሉ ቦታዎችና ሶስት ስብራቶች ቆጥሬአለሁ፡፡ ሁለቱም ለመርዳት ምንም ጊዜ ሳይኖረኝ ወዲያው ሞቱ፡፡

የሞቱት ቁጥር አሥራ ሰባት ነበር፡፡ ከነዚህ አንዱ በጣም የሚታወቅና በሁሉም ዘንድ የሚከበር የዘቦች መኮንን ነበር፡፡ ትልቅ የቦምብ ፍንጣሪ በግራ ደረቱ በኩል አስከትከሻው ድረስ በመዝሰቅ ሰውነቱን ቦጭቆታል፡፡ ቆስሎ የወደቀ ጓደኛውን ሊረዳ ሲል ነው የተመታው፡፡

አሥራ አንድ እንሰሶች ሞተዋል፡፡ ወደኋላ ሁሰት በጣም የቆሰሉ አህዮችን ተኩሼ ከስቃያቸው ገላገልኳቸው፡፡ ይህ ግን ማጉረምረም ነው የፈጠረው ምክንያቱም ያገሩ ሰዎች ምንም አንስሳት ላይ ጨካኝ ቢሆኑም አንስሳቱ የሆነውን ያህል ቢሰቃዩም በራሳቸው እንዲሞቱ ይተዋቸዋል፡፡

አመሻሹ ላይ አንድ አውሮፕላን መጣና አስር የአሳትና የፈንጂ ቦምቦች ጣለ፡፡ አላማው ቤተከርስቲያኑን ለመደምሰስ ነበር፡፡ ያም ሆኖ



አልተሳካለትም፡፡ ምናልባትም ፓይለቱ በመሳቱ አፍሮ ይሆናል የቀረውን ቦምብ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ኪሎሜትሮች ርቀት ባለ ሜዳ ላይ አራግፎ በፍጥነት ተመለሰ፡፡ የሚሰጠውን ሪፖረት ማወቅ የሚያጓጓ ነበር፡፡

ከዚህ በኋላ የዚህ አይነቱን ሁኔታ በጦርነቱ ጊዜ ደጋግመን ማየት ችለናል፡፡ አውሮፕላን ዛፍ የሌለበት ጠፍ ሜዳ ላይ ቦምቦችን በተከታታይ ሲጥል እናያለን፡፡ ይህ ሲሆን ሰዎች የሚሰጡት አስተያየት

"ተመልከት! ልዩ አይን ነው ያላት! አሁን አይጥ ወይም እባብ አይታ ይሆናል" ወይም " አሁን ምጥ ይዟት ነው፤ ይህን ሁሉ እንቁላል መሸከም አልቻለችም"

አውሮፕላኖቹ እንደሄዱ የሞቱትን በቤተክርስቲያኑ መቃብር ቦታ ከቀበርን በኋላ ወደ ጦር ግንባሩ ወደ እንዳባጉና መጓዝ ጀመርን፡፡ ልክ አኩለ ሌሊት እንዳለፈ ጠላት የነበረበት ባዶ ካምፕ ውስጥ መሀል ላይ ያለ ከፍታ ላይ ደረሰን፡፡

በደንብ የተሠሩትን ምሽግ መስመሮችና በየቦታው የወደቁትን ቁጥር ስፍር የሌላቸው ባዶ የምግብ ቆርቆሮ ጣሳዎቸ ላየ ሰው እዚህ ቦታ ነጮች እንደነበሩ ግልፅ ነው፡፡ ሶስት በቀርከሀ ቅጠል የተሰሩ ጎጆዎች ቆመው ይታያሉ፡፡ ውስጣቸው ደግሞ ግድግዳቸው በሲኒማ ተዋናይ ኮከቦች ፎቶ ወይም ኢለስትሬትድ ከተባለ መፅሄት የተወሰዱ ፎቶዎች ተለጥፎባቸዋል፡፡

ከፍታው የሚገኘው ወደ አክሱም በሚወስደው መንገድ ባሰበት ሜዳማ ቦታ ነው፡፡ የውሃ ነገር አስቸጋሪ ነበር ምክንያቱም በቅርብ ያለው የውሀ ቦታ አንድ ኪሎሜትር ርቆ ነው የሚገኘው፡፡ በዚህ ምክንያት ምሽጉ ከጥቂት ቀናት በላይ ከበባ መቋቋም አይችልም ነበር፡፡

ከከፍታው ወደ ምሥራቅ በኩል የሚገኝ ሸሰቆ ካምፕ የምናደርግበት ቦታ ሆኖ ተመረጠ፡፡ እዛ ሰመድረስ ግን አግድሞሽ በጦር ሜዳው ደቡብ በኩል አቋርጠን መሄድ ነበረብን፡፡ በየቦታው ሁሉም አይነት ነገር ተበትኖ ይታያል፡፡ ስኳር፣ በርበሬ፣ ዱቄት፣ ጥጥ፣ ሲጋራ የመሳሰሉት፡፡ የነበረኝ የትምባሆ ስንቅ አልቆ ነበር ብዙ ወታደሮች ጠቀም ያለ የትምባሆ መጠን ከሜዳው መሰብሰብ ችለዋል፡፡

በተጨማሪ ተጎድቶ የቆመ ታንከ ለማየት እድሉ አጋጠመን፡፡ ሞገደኛ ልጅ ተጫውቶ ሲጨርስ የወረወረው የአሻንጉሊት መኪና ከምር ይመስላል፡፡ ከሾፌሩ መቀመጫ ስር የነዳጅ መያዣው ፈንድቶ የታንኩ ውስጡ እንዳለ ተቃጥሏል፡፡ በውስጡ የነበሩ ሁለት ሰዎችም አብረው ጋይተዋል፡፡

የቀረው ታንኩ ላይ የሚታየው መሰባበር ግን በወታደሮቹ ነው የተደረገው። የተሽከርካሪው ከፍሎች፣ ብሎኖች፣ ከሲሊንደሩ የወጡ ስስት ፒስተኖች ዙሪያውን ወድቀው ይታያል። መሄጃ ሰንሰለቱ ሳይቀር ባንድ በኩል ተሰብሮ ተለያይቷል። ሌላው ሳይቀር የአንድ ሴንትሜትር ውፍረት ያለው መከላከያ ብረት እንኳን የነዚህን ወታደሮችን ንዴት መቋቋም አልቻለም። ምንም አይነት መፍቻ መሳሪያ እንዳልበራቸው አውቃለሁ። ነገር ግን በላዩ ላይ ቁጥር 1935 የተቀረፀበት ታንክ ተበታትኖ ከምር ብቻ ሆኖ ቀርቷል።

እንዴት አድርገው እንደበተኑት እኔ ማስረዳት አልቻልኩም። ሌላ የሚያውቅ ሰው ካለ ማስረዳት ይችላል። ከዚህ በፊት ያገሬው ሰዎች ከባድ መሮዎች እስኪጣመሙ ድረስ ድንጋይ ሲሰብሩ አይቻለሁ።

በሚቀጥለው ቀን ካምፑ ውስጥ ጫጫታና ግርግር ነበር። ሁሉም ሰው ሴቶችና አገልጋዮችን ጨምሮ ታንክ፣ አውቶሞቢልና የሞቱ ጣልያኖችን ምን እንደሚመስሉ ማየት ይፈልግ ነበር።

አውሮፕላኖች ተመላልሰው እየመጡ በምብ ያወርዱብን ነበር። ነገር ግን ሁሉም ሰው በፍጥነት እንደ አይጥ በዛፍ ስር፣ ጫካ ውስጥ ወይም በድንጋዮች ጀርባ ስለሚደበቅ ያን ቀን ሰው ሳይጎዳ ዋለ። በሌላ በኩል ግን ለግጦሽ ተሰቀው ስለነበረ በርከት ያለ ቁጥር ያላቸው አህዮች ተገደሉ። በሬና ላሞች ከነበረው ቁጥራቸው ሰማንያ ስድስት አሥራ አራት ብቻ ቀሩ።

የንፁህ እንስሳት ግዙፍ ጭፍጨፋ ነበር።

የፊታውራሪ ሽፈራው ሰዎች ከአንዳባጉና አሰራአምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ከሚገኝ ጠላት ትቶት ከሄደው እንዳስላሴ ካምፕ አጠገብ ሰፍረዋል። ያን ቀን ማታ ጀብዱ የሰሩ ሰዎች የማረኩትን እና እስረኞቻቸውን ይዘው ደጃች አያሌው ፊት እየቀረቡ ፎከሩ።

እዛዡ በትልቅ ድንኳን መሀል ቦታ ወንበር ላይ ተቀመጡ። እኛም አሽከሮቹን ጨምሮ ከኋላቸው ግማሽ ክብ ሠርተን ቆምን። መጀመሪያ እንደአውሬ እርስ በርሳቸው በጩኸት የሚፎካከሩ ዘጠኝ ሰዎች መጡ። ቀጥሎም እንዴት አድርገው የጣልያን ምርኮኞችን እንደያዙ በሥነስርአት ማሳየት ጀመሩ፤ አብረዋቸውም በፍርሃት የተዋጡ አራት ጣልያኖች ነበሩ። ሁለቱ ሰውነታቸው ላይ አራፊ ልብስ እንኳን አልነበራቸውም። አንደኛው ራቁቱን ውስጥ ሱሪ ብቻ ነው ያደረገው። አንደኛው ደግሞ ጫማ ካልሲ ኮት ወይም ኮፍያም አልነበረውም። ጣልያኖቹ እዛው አመድ መስለው ቆመዋል



እነዚህ ያልሰለጡኑ ሰዎች ወይ ይሰልቡናል ወይ ከነህይወታችን ይበሉን ይሆን ብለው ማሰባቸው አልቀረም። ነገር ግን እንደዛ ራቁታቸውን ቆመው ሲታዩ በዙሪያቸው በቆሙት በሙሉ የርህራሄ ስሜት ነበር የፈጠሩት።

ማራኪ ጀግኖቹ ድምፃቸው እስኪጎረንን ድረስ ጮኸው ሲያቆሙ ደጃዝማች ምርኮኞቹን ወደፊት አሰጠሯቸው ምርኮኞቹ ደግሞ የፋሺስት ሰላምታ ሰጥተው ቆሙ።

ደጃች አያሌው ደግሞ "የለም" " አሁን ያላችሁት አቢሲኒያ ስለሆነ በኛ ደንብ ነው ሰላምታ መሰጠት ያለባችሁ። እንኳን ደህና መጣችሁ" አሉና ወደ መሬቱ ሲጠቁሙ ለማስተርጎም ካለሁበት ብቅ አልኩ። በፍርሃት ተውጠው ስለነበር እስካሁን ድረስ አላዩኝም ነበር። ከዚያም ፊታቸው ፈካ ብሎ ወዲያውኑ ወደ መሬት ሰጥ ብለው እጅ ነሱ። ቀና ሲሉ አይናቸው በደስታ እኔ ላይ ተተክሎ ሳያቸው እኔ ራሴ እንባዬ መጣ።

"ጣልያናዊ ነህ ወይ?" ሁሉም ባንድ ድምፅ

"አይደለሁም ግን ቋንቋችሁን እናገራለሁ"

"አሁን ሊገሉን ነው ወይ?"

"አትፍሩ ቃሌን እሰጣችሁዋለሁ በደንብ ነው የምትያዙት"

"ሀኪም ነህ ወይ?"

"አሀ"

"ግራዜ ሲኞር ዶክቶር" እናመሰግናለን ዶክተር ማለት ነው

ደጃዝማች ምርኮኞቹ ምግብ አግኝተው እንደሆን ጠየቁ። የተቀቀለ የባቄላ አፍኝ ብቻ ነበር ለዛን ቀን የበሉት። ልብስ እንዲመጣላቸው ትዕዛዝ ሰጡ። እንዲቀመጡ ተፈቀደላቸውና ዳቦና የማር ብርዝ ቀረበላቸው። ሰዎችን የማረኩት ሰዎች ምርኮኞቹን በሚያሳፍር ሁኔታ ስለበደሏቸው ተግሳፅ ተሠጣቸው፤ የወሰዱትን የሰዎችን ልብስና ጫማዎች በአስቸኳይ እንዲመልሱ ታዘዙ። የወሰዱት ነገር ለነሱ የሚሆንም አልነበረም።

ከዚያ በኋላ ወታደሮች ጠላት ለመግደላቸው መረጃ የሚሆን የራስ ቆብ፣ ሳንጃ፣ አውቶማቲክ መሳሪያ፣ ጥይት፣ መፅሀፎች፣ ሱሬዎች፣ ጫማዎች እና ሌላም ነገር ካለ ይዘው አቀረቡ።

ታንኩንና አውቶሞቢሎችን የሰበሩ ሰዎች ወደፊት እንዲቀርቡ ሲጠየቅ ከፍተኛ ጫጫታ ተፈጠረ። እያንዳንዱ ሰው እነዚህን ጭራቆች ብቻውን

እንደማረከና እንደሰበረ የይገባኛል ከርከር ጀመሩ:: ለዚህ ፋከከር መልሰ ማግኘት እልተቻለም ያለው እማራጭ እነዚህን ጉረኞች ማስወጣት ነበር::

ከመሀከላቸው ግን ከሰው ሁሉ በፊት ዘሎ የመጀመሪያው ታንክ ላይ ለመውጣቱ መረጃ ያለው ሰው ነበር:: ያ ሰው ደግሞ ባላንባራሰ ተሰማ* ነበር:: ያ ሰው እገልጋዬን ቡና ያለ ጭሰ እፍይ ብሎ ትእዛዝ በመሰጠቱ እርባ ጅራፉን በኩራት ዋጥ እድርጎ የተቀበለው ነው::

ደጃዝማች ምርኮኞቹን ጥያቄ መጠየቅ ሰሰፈለጉ ወደፊት እንዲቀርቡ ትዛዝ ሰጡ:: ምርኮኞቹ እሁን ደፈር ያሉ እንዲያውም ደሰተኞች ይመሰሉ ነበር::

*ሥራቸው ምን ነበር?* ከሶሰት እንዱ መልከመልካም የእሥራ ዘጠኝ እመት ልጅ ያለበት መካኒኮች ነበሩ የቀረው ግን የጦር ሀኪም ነበረ:: ሁሉም ማዕረጋቸው ማሰተር ሰርጀንት ነበር::

ጥያቄው እየተካሄደ እያለ ሰድሰት ሰዎች በማቋረጥ ከአንድ በኩል ሾል ያለ የበርሜል ቅርፅ ያለው ብረት ከደጃማች እግር ሰር በጥንቃቄ እሰቀመጡ::

"ጌቶች ይህንን ነገር እገኘነው የእሩብላ እንቁላል ይመሰለናል ሰለዚህ ልናሳይዎ ብለን እመጣነው::"

በቅፅበት እሰከምችለው ድረሰ ራቅ ብዬ ወደኋላ እፈገፍግኩ

እያሴው ቁጭ እንዳሉ በምቡን ለተወሰነ ጊዜ ካሰተዋሉ በኋላ ወደ እሥራ ዘጠኝ እመቱ ጣልያናዊ ዞር ብለው "እናንተ መካኒከ የሆናችሁት ይህንን ነገር ፍቱና ውሰጡ ምን እንደሚመሰል እሳዩኝ" እሉ

ወጣቱ ልጅ ደጃዝማቹን እየ፤ መልሶ በምቡን እየ፤ በጆሮው የሰማውን ነገር ያመነ አይመሰልም፤ ከዚያም ወደኔ ዞር ብሎ "ዶክቶሬ እንዲያሰተረጉሙ ላሰቸግርዎት?" እለ

ቀጥሎ የሚናገረውን ነገር ከአይኑ መረዳት እችላለሁ

"ደሰ ይለኛል፤ ግን ራሴን ከዚህ ቦታ ራቅ ማድረግ ብችል" እልኩኝ

ሳቅ በማለት "ኖን ሴ ፐሪኮሎ" እደጋ የለም እለ

---

**የባላምባራሰ ተሰማ ታንከ መማረከ በሌላ ተጨማሪ መፅሐፍ ተዘግቧል። ባላምባራሰ ተሰማ በአርበኝነት በአምባ ጊዮርጊሰ አካባቢ በመንቀሳቀሰ ጠላት ላይ ብዙ ጉዳት ያደረሰና ከዚያም የፊታውራሪ ማዕረግ እንደተሰጠው በዚህ መፅሐፍ በሰፊው ተፅፏል::*

*Amedeo: A True story of love and War in Abyssinia; Sebastian O'Kelly*



ቀጥሎም "እኔ ለማለት የምፈልገው ይህን ብቻ ነው:: እኛ ኢጣልያውያን ነን እርሰዎ ደግሞ ጠላታችን ነዎት:: በሀገራችን ለሀገር መሞት ከብር ነው፤ እኛም እሰፈላጊ ከሆነ ለመሞት እዚህ ድረሰ መተናል"

"እሁን ይህን ቦምብ ፍታ ብለው ትዕዛዝ ሲሰጡኝ ያለምንም ችግር በቀላሉ ላፈነዳው እችላለሁ:: እራታችን እዚሁ እብረን እንፈነዳለን፤ ነገር ግን ኢጣልያ የጠላቶቿ ቁጥር ይቀነሳል በተለይ የእርሰዎ እይነቱ"

"እንገደላለን ብለን እርግጠኛ ነበርን:: ነገር ግን እርሰዎ ከምንጠብቀው በላይ ነው የተንከባከቡን:: ላደረጉልን ነገር ምሰጋና ለማቅረብ ሰል ትዕዛዘዎን እልቀበለም::"

እኔም ቀጥታ ጣልያናዊው እንደተናገረው እድርጌ በትክከል እሰተረጎምኩ:: ደጃማቹ ላይ ጥልቅ ሰሜት እንደፈጠረም ማየት እችላለሁ:: ከመቀመጫቸው ተነሰተው ወታደሮቹን እመሰገኑ "ይህ ጀግንነት ነው:: ይህ እርበኝነት ነው:: እንደዚህ ወጣት ያለ እንደ ሺ ሰው ቢኖረኝ ማን ይቋቋመኝ ነበር?"

ወደፊት ተራመዱና የወጣቱን ጣልያናዊ እጅ ይዘው በሚያቃጭል ጣልያንኛ "ግራዚ" እሉ:: በዚህ ሁኔታ እያለን ቦምቡን ይዘው ለመጡ ለስድሰቱ ሰዎች መልሰው እንዲወሰዱትና መሬት ውሰጥ እንዲቀብሩት ትዕዛዝ ተሠጠ::

ጣልያኖቹም ወደ ዋሻ እንዲሄዱ ተደረገ:: እኔም የሚያሰፈልገውን ነገር ለማመቻቸት ሰል ተከትልኳቸው:: እዲሰ የታጨደ ሳር ወለሉ ላይ ተበትኗል:: ሁለት መኝታ ከብርድልብሰና እንሶላ ጋር ተዘጋጅቷል:: የበራ ኩራዝ በአለቶች መሃከል ባለ ቦታ ተቀምጧል:: ተጨማሪ ምግብና መጠጥ መጣላቸው:: እሰረኞችም ምግባቸውን እየበሉ ያጋጠማቸውን እጫወቱኝ::

"**ቡም** !" ምንድነው? መድፍ ነው? ረጭ ሰላለ እዳመጥን ለእፍታ ያህል ነበር፤ ወዲያው ከውጭ በኩል ግርግርና ድምፅ ይሰማ ጀመር፤ እኔም በጨለማው ወደ ደጃዝማች እየሮጥኩ ሄድኩ " ምንድነው ነገሩ?"

"እንደሰማኸው መድፍ ነው:: ጣልያኖች የኛን መሰመር እያጠቁ ነው::" እሉ ጫማቸውን እጠለቁና ጎራዴና ሽጉጣቸውን እየታጠቁ:: ሰዎች ከደጃማች ትዕዛዝ ለመቀበል ወደ ውሰጥና ውጭ ይመላለሱ ነበር:: ከውጭ ትልቅ ጭንቀት ተፈጥሯል:: ሰዎች ወዲያና ወዲህ ይሮጣሉ ይጣሩና ይጮሁም ነበር::

"መጀመሪያ የሆነውን ነገር ብናጣራ እይሻልም" ወይ ብዬ ህሳብ ሰነዘርኩ

"አዎ እሱ ጥሩ ሀሳብ መሰለኝ" አሉና አያሌው አምስት ወታደሮች ይዤ ወደ ጣልያናዊያን እስረኞች እንድወስድና በዚህ ግርግር ጥበቃ እንዲደረግላቸው እንዳደርግ ጠየቁኝ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ደጃዝማቹ ራሳቸው ወደአለንበት መጡና እየሳቁ ያ መከረኛ በምብ ነው ግርግሩን የፈጠረው እንጂ ሌላ ነገር አልነበረም ብለው ነገሩን።።

ወደኋላ ሙሉ ታሪኩን ሰማን። እነዚያ ሰድስት ሰነፍ ሰዎች ጉድጓድ መቆፈሩን አልፈለጉም። ስለዚህ ሁሉም ተሰማምተው በምቡን በእሳት ሰማቃጠል ወሰኑ። ወደ ማደሪያቸው በታም ሄዱና እሳት እንድደው ጓደኞቻቸው ቢያስጠነቅቋቸውም ችላ ብለው በምቡን እሳቱ ላይ አስቀመጡት። "የታባቱና!" የሚሆነውን ለማየት በአሳቱ ዙርያ ቁጭ አሉ።

ቢያዩ ምንም ነገር አልሆነም። አንደኛው ተነስቶ እሳቱን ሲቆሰቁስ በምቡ ፈነዳ። በሚቀጥለው ቀን ሲታይ ብጫቂ ልብስና የተበጣጠሰ አካላቸው በየቦታው ዛፍና ቁጥቋጦ ላይ ተበትኖ ተገኘ። በሃምሳ ሜትር እቅራቢያ የነበሩ ስምንት ሰዎች ተጎድተዋል።



# ምዕራፍ አሥራ አንድ

## ድል በእንዳባጉና

ተከዜን ሳንሻገር ስለ እንዳባጉና ጦርነት ወሬ እንደሰማን ሁለት ድሬሰሮችን ከሚያስፈልገው መሳሪያ ጋራ አስቀድሜ ልኬ ነበር። ደጃችዝማች የኔን መሄድ በጣም ይቃወሙ ነበር። በድል ስሜት ላይ ያሉ ወታደሮች እንደገና ደግሞ በጓደኞቻቸው ሞት በሀዘን ላይ ስለሆኑ ነጭ ሰው ካዩ ምንም ሳያወላውሉ ሊተኩሱበት ይችላሉ። ሁለት የኢጣልያ እስረኞች አንደኛው የቆሰለ ዶክተር በጦርነቱ ማግሰት ጠዋት ጭንቅላታቸው ተቆርጦ ተገኝቷል። ባልተጠበቀ ሁኔታ አንዱ በማታ ሾልኮ ገብቶ የጓደኞቹን ሞት ተበቅሎባቸዋል።

እንግዲህ ስንት የቆሰሉ ሰዎች መርዳት የምችልባቸው አራት ቀናት በከንቱ አለፉ። ምናልባትም ሕይወታቸውን ማትረፍ የምችልበት ሁኔታም ይኖር ነበር። ማምሻውኑ ከድሬሰሮቹ የመጣ መልከት ሥራውን ብቻቸውን ማከናውን ያልቻሉ መሆናቸውን ይገልፃል።

በዚህ ምክንያት ነገሩ ተወሰነ። መሄድ አለብኝ

ደጃች አያሌው የመሄዴን ነገር ተጠራጥረዋል። ደግነቱ ከወዳጇ ከቀኛዝማች ንጋቱ ጥያቄ መጣ፤ ቀኛዝማቹ እራሳቸው ሰኔ ደኅንነት ሀላፊነት እንደሚወስዱ ገለፁ። ጦርነት ላይ ነበሩ። ከነበራቸው መቶ ሰዎች ሀያ ሁለቱ ሞተዋል ወይም ቆስለዋል ለዚህ ነው እርዳታ የጠየቁት።

በነጋታው በጠዋት ለመሄድ ወሰነናል። በመጨረሻም የተጎዱ ወታደሮችን በተቻለኝ አቅም መርዳት የምችልበት ሥራዬን መጀመር አችላለሁ። እስካሁን ምንም ነገር ማድረግ አለመቻሌ የኔ ጥፋት አልነበረም። ምንም እንኳን ሊደርስብኝ የሚችለው አደጋ ቢገባኝም ምናልባት ሙሉ በሙሉ ባይሆንም የነበረኝ የሙያ ግዴታ መንፈሴ ራሴን ለማዳን ከነበረኝ ፍላጎት በላይ ነበር።

ለማንኛውም አሁን ለመሥራት ነፃ ነኝ፡፡ የቆሰሉትን ሰዎች ለመርዳት ባለመቻሌ ከሚሰማኝ አሳዛኝ ስሜትም ነፃ አሆናለሁ፡፡

አራት ከበላን በኋላ ደጃች አያሌው በጦርነቱ ድል ለላደረጉ የተላከላቸውን ቴሌግራም በሚመለከት ወሬ አካፈሉኝ፡፡ በቴሌግራሙ ንጉሠ ነገሥቱ የምሥራች መልክት ልከዋል፡፡ ነገር ግን በሌላ በተከታይ ቴሌግራም ደግሞ ሌላ አዲስ ጥቃት እንዳይሰነዘር የሚል ትዕዛዝ አለበት፡፡ አያሌው በመከላከል ብቻ እንዲቆዩ እና በጥንቃቄ የሚሆነውን ነገር እንዲከታተሉ፡፡ አያሌው የሰው ህይወት ያለአግባብ እንዲጠፋ እንዳያደርጉ፡፡ የተያዙት የኢጣልያ እስረኞች ባስቸኳይ ወደ ዳባት እንዲላኩና ከዚያም በአውሮፕላን አዲስ አበባ እንዲወሰዱ የሚል ነው፡፡

"በግልፅ እንደሚታየው እኔው ራሴ ሪፖርት ላደረግሁት ድል መረጃ ይፈልጋሉ" በማለት አያሌው በሽርደዳ መልክ ተናገሩ፡፡

ንጉሠ ነገሥቱ ጠቅላላው ምዕራብ ትግራይ በአንዳባጉና ጦርነት ምክንያት ነፃ እንደወጣ አስተማማኝ የሆነ መረጃ ደርሷቸዋል፡፡ ሁሉም የጠላት ምሽጎች ተወስደዋል፤ ጣልያኖችም ወደ አክሱም ሸሽተዋል፡፡ ያ ሁሉ ሆኖ ባለህበት ቆይ የሚል ትዕዛዝ ተላልፏል፡፡

ደጃች አያሌው የተረበሹ ይመስላሉ፡፡ "የአዲስ አበባ ገዥዎች ምን ማለታቸው ነው?" ይህንን ትዕዛዝ ለወታደሮቹ ቢናገሩ አመፅ ይፈጠራል፡፡ ባገኙት ድል የተደሰቱት ወታደሮች ወደ አክሱምና አድዋ መገስገስ ነው የሚፈልጉት፡፡ በዚያን ጊዜ የኢጣልያ ቅኝ ግዛት ዋና ከተማ ወደ ነበረችው አስመራ ድረስ ካልሄዱ የሚያረካቸው ነገር አልነበረም፡፡ በዚህ አይነት መንገድ ነው የሚዋጉት እና አትቀጥሉ የሚባል ነገር ቢነገራቸው ወኔያቸውን እንደሚጎዳ ነው፡፡ ሰምንስ አሁን ካውያው እንደጋለ በትኩሱ ጥቃቱ አይቀጥልም?

ምን ማለት እችላለሁ? በዚያን ጊዜ ደጃማቹ ትክክል እንደነበሩ አውቃለሁ ዛሬም ቢሆን ሰውየው ትክክል እንደነበሩ በተሻለ ሁኔታ አውቃለሁ፡፡ ነገር ግን የጦር አማካሪ የመሆን ሥልጣን አልነበረኝም፡፡ እነዚያ ሰዎች ከጦርነቱ ርቀው መናገሻ ከተማው ነው የተቀመጡት፡፡ በደንብ መረጃ ያላቸው ነገር ግን በጦር ግንባሩ ተሰልፈው የራሳቸውንም ሆነ የጠላትን አሰላለፍ በደንብ የሚያውቁ ሰዎችን አስተያየት ሳይቀበሉ ትዕዛዝ ማስተላለፍ እንችላለን ብለው ያስባሉ፡፡ የተመቻቸው እነዚህ ገዥዎች በነበራቸው የድንቁርና በራስ መተማመን ያሰምንም ርህራሄ በአፍሪካ የመጨረሻዋን ነፃ ሀገር ዕጣ ፈንታ ወሰኑ፡፡



ሌላው ዜና ደግሞ ምንም መልክት ሳይልኩ ራስ እምሩ በሌሊት በመጓዝ ከኛ ኪሎሜትሮች ራቅ ብለው ካምፕ አደረጉ፡፡ ጠዋት ፀሀይ ሳትወጣ እንዲገናኙ ጥያቄ ላኩ፡፡ አሁን ግን ራሳቸው አያሌው ዋሻ ድረስ ሲመጡ ነው፡፡ ሰማሁ፤ ገረመኝም፤ ምንም አይነት እንኳን ደስ ያለህ ነገር የለም፡፡ ስለ ድሉ እንኳን አንድ ቃል አልተናገሩም፡፡

በነጋታው ጠዋት ከአሥራ ሁለት እጃቢዎች ጋራ ካምፑን ለቅቄ ሄድኩ፡፡ ቀኛዝማች ንጋቱ እንደተራ ሰው አያነክሱ በእግራቸው መጡ፡፡ እግራቸውን ሾህ ወግቷቸው ነበር፡፡ የነበሩበት በቅሎ ጦርነቱ ላይ ራሱን በጥይት ተመቶ ተገሎባቸዋል፡፡ የቆሰሉት ሰዎች ያሉበት ቦታ ለመድረስ በሙሉ ጦር ሜዳው መሀከል መሄድ ነበረብን፡፡ በቅርብ ጊዜ በሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ለሞት ወይም ለድል በተዋጉበት መሬት ላይ መራመዴ እንግዳ ስሜት እንዲሰማኝ አደረገኝ፡፡

ቀኛዝማች እየመሩን ስለ ጦርነቱ ስለተካሄደው ሁኔታ ከቀኛዝማቹ በሚደረግልኝ መግለጫ በቦታው የነበርኩ ያህል የመስማት እድል አጋጠመኝ፡፡

ሰላዮቻችን እንደነገሩን ከሆነ በአንዳባጉና የነበረው ሜጀር ከጠቅላይ አዙ ምሽጉን ለቆ እንዲሄድ ትዕዛዝ ተሠጥቶት ነበር፡፡ የመጀመሪያው ቀን በሰስት ማለት ነው ሁሉም ካምፑን ጥለው ለመንቀሳቀስ ዝግጁ ነበሩ፡፡ ነገር ግን ሰላሳ ግመሎች ያሉበት ጓዝ ከአክሱም ሰለተላከ ትዛዙ ተቀየረ፤ ሜጀሩም የሬዲዮ መገናኛዎችን እንደገና ሰቅሎ እስከ እሁድ ድረስ ለመቆየት ወሰነ፡፡

ያ ውሳኔ ግን መጥፊያው ሆነ

ፊታውራሪ ሽፈራው ከደጃዝማች አያሌው ወደ ፊት እንዲሄዱ ትዛዝ በደረሳቸው ሰአት ከአክሱም ጓዝ መምጣቱንና ሜጀሩ እስከ እሁድ ድረስ ለመቆየት መወሰኑን ዜና አገኙ፡፡ በተጨማሪም ምሽጉ የሚጠበቀው በአንድ ሺ አምስት መቶ ከኤርትራ ከተመለመሉ ባንዳዎች ከመቶ ሃምሳ ነጮች ጋራና ሀያ አምስት መትረየሶች እያንዳንዳቸው ሁለት መትረየስ የተጠመደባቸው አስር ታንኮች መኖራቸውን መረጃ ይደርሳቸዋል፡፡ በተጨማሪ አራት የጭነት መኪኖች፣ አንድ አውቶሞቢል፣ መቶ የጭነት በቅሎዎችና ሰላሳዎቹ ግመሎች ነበሩ፡፡

ወታደሮቹ ደግሞ የተናፈሰ የሰሙት ወሬ ነበር ይህም ከአከሱም የመጣው ጓዝ ማር ትሪዛ ጭኖ እንደመጣ ነው:: በዚህ ዜና ምክንያት ወታደሮችን ይዞ መቆየት የማይቻልበት ሁኔታ ሲደርስ ምንም አልቀረውም:: ፊታውራሪ ሽፈራው በሌሊት ተጉዘው የጠላትን መንገድ መዝጋት ምሽጉን ከቦ ከመቀመጥ የተሻለ ጠቀሜታ አለው ብለው አሰቡ::

ፀሀይ ሳትወጣ በጠዋቱ ወታደሮቻቸውን በሀይዳ በኩል አድርገው በተከዜ ተንቀሳቀሱ፤ ሁሉም ሴቶችም አገልጋዮችም ጨምሮ ተከተሉ:: እያንዳንዱ ሰው በሚቀጥለው ቀን ጦርነት እንደሚኖር አውቋል እና የቆሰለውን ለመርዳት የሞተውን ለመቅበር አብሮ መሄድ ፈልጓል::

እነዚህ ሰዎች በተከዜ ወንዝና በገባሩ በማይቆላ በችግርና በመከራ ነው የተጓዙት:: ባበዶ አግራቸው በጠጠሮች ላይ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ግማሹን ሌሊት ያለምንም የጨረቃ ብርሃን ነበር:: የጠዋት ኮከብ ብቅ ሳትል ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርሰቲያን ደረሱ፤ እሱም ከጣልያን ምሽግ አራት ኪሎሜትር ርቀት ነበር:: ሀገሩን አቋርጠው ሲጓዙ ከጠዋቱ አሰራ አንድ ሰአት ላይ ቀጥታ ከጠላት ካምፕ በሰሜን አቅጣጫ በሚገኝ ከአንድ መጠነኛ ወራጅ ውሀ አጠገብ ለትንሽ ጊዜ አርፈዋል:: በዚያ መንገድ ወደ ስልሳ ኪሎሜትር ርቀት የሚሆን ሲገሰግሱ አድረዋል :: ጓዝ የያዘው ክፍል ወደኋላ ቀርቷል::

ጣልያኖች መኖራቸውን ካረጋገጡ በኋላ መንገዱን በማቋረጥ ትንሽ ግንብ ቢጤ ሰሩና ጉድብ ቆፈሩ፤ አላማው ለጠመንጃ ተኳሾች መከለያ ሲሆን ጭነት መኪኖችና ታንኮችም እንዳይሻገሩ ለመከላከልም ነበር:: ያሰቡት እንደዛ ነበር::

ነገር ግን ግንቡም የግማሽ ሜትር ከፍታ ያለው የድንጋዮች ድርድር ጉድቡም ቢሆን ጥቅም አልነበረውም:: ግማሽ ሜትር ስፋትና ግማሽ ሜትር ጥልቀት ነው የነበረው::

ሁሉም ዝግጅት ካለቀ በኋላ ሰዎች ቦታ ቦታቸውን ያዙና ፍፁም ፀጥታ እንዲኖር ታዘዘ:: እንደሚባለው ከሆነ ግማሹ ጦር ወዲያውኑ እንቅልፍ ወስዶታል::

ልክ ሁለት ሰአት ሲሆን የመጀመሪያው አላሽ ጦር የጫነ መኪና ከጣልያኖች ካምፕ አቅጣጫ መጣ:: ትግስት ያጠራቸው የሽፈራው ወታደሮች በችኮላ ተኮሱ:: ጠላት ጊዜ አግኝቶ ዞሮ መሸሸ ጀመረ:: በዚህ ጊዜ ሁሉም የሽፈራው ጦር ቦታቸውን ለቀው ማጥቃት ጀመሩ:: ፊታውራሪ ሽፈራው አራሳቸው ተነስተው በፈረሳቸው መንገዱን መዝጋት ነበረባቸው፤ አለዚያ



እነዚህ ስርአት የሌላቸው ወታደሮች እቅዳቸውን በሙሉ ሊያፈርሱባቸው ነው::

ከምሽጉ የሚመጣውን ጥቃት ለመከላከል አንድ ሺ የሚሆኑ ወታደሮች ከካምፑ ግማሽ መንገድ የሚሆን ቦታ ጫካና ዛፎች ውስጥ ተደብቀዋል:: ከምሽጉ አጠገብ ያለ ሜዳ ላይ አንድ አውሮፕላን አረፈ:: አንድ ሰው ሲሮጥ ሄዶ ከፓይለቱ ጋር ለትንሽ ጊዜ ካወራ በኋላ አውሮፕላኑ ተነስቶ ሄደ::

በኋላ እንደተረዳነው ቃኚው አወሮፕላን ከምሽጉ በተደረገለት ምልክት ነበር ያረፈው:: ምክንያቱም ፓይለቱ የሚያስጠረጥር እንቅስቃሴ አይቶ እንደሆን ለመጠየቅ ነበረ:: ፓይለቱ ግን ምንም አላየሁም ስላለ ሜጀሩም ትንሽ ቀማኛ ሽፍቶች ይሆናሉ ሰዎቹ ላይ የተኮሱት በማለት ተረጋጋ:: ከዚያም ለቅኝት ታንከ ወጥቶ እንዲሄድ አዘዘ::

ታንኩ በደረሰበት ጊዜ በመሪ ጦሩ አካባቢ እንቅስቃሴ ተጀመረ

"ተመልከት! ስትሄድ እንደ አሳማ ነው የምትወዛወዘው! ስማ እንደመቶበላ ደግሞ ትጮሃለች"

"ታንከ ነው?"

"እንዴታ! ደደብ"

ከዛ ቀጥሎ ታንኩ እንዳይሰማቸው ማንሾካሾክ ጀመሩ፤ ምኑ ላይ ነው ጥሩ ቦታ ተኩሰን የምንገለው እያሉ ይወያዩ ነበር:: ወዲያውኑ ከአዛዡ በተላለፈ ትዛዝ ታንኩ መስመራቸውን አልፎ እስኪሄድ ድረስ እንዳይተኩሱ ተነገራቸው::

እንዲህ እንዳለ ታንኩ እየተወዛወዘ ጠጋ ማለት ቀጠለ:: በመቶ ሜትሮች ርቀት የተሠጣቸውን ትዛዝ ጥሰው ትግስት ያጠራቸው ተዋጊዎች የተኩስ ውድድር ጀመሩ::

ታንኩ ወዲያውኑ መልስ ተኩሰ በመስጠት በመንገዱ ዳርና ዳር ጉዳት አደረሰ:: የፈሩና የደነገጡት ወታደሮች በየአቅጣጫው ሲበተኑ አንድ ሰው ብቻ ቀረ:: ባላምባራስ ተሰማ ነበር:: ከታንኩ በኋላ ተስቦ ዘሎ አናቱ ላይ ወጣና ከዳኑን በሰደፍ እየደበደበ "ከፈት" እያለ ጮኸ::

የታንኩ መሳሪያ ተኳሽ በድንጋጤ አደጋ መኖሩን ይርሳ አናውቅም ግን አውቶማቲክ መሳሪያውን መተኮሱን አቆመ፤ የታንኩ መግቢያም ተከፈተ:: ወዲያውኑ ባላምባራስ በተከፈተው መግቢያ ተኮሰ::

የታንኩ ሾፌር ቆመ፤ ወደኋላ ነድቶ ዞሮ መሄድም ሞከረ፤ ነገር ግን በሁለት ዛፎች መሀከል ተቀርቅሮ ቆመ:: በዚህ ጊዜ ተሰማ የዚህን ጭራቅ

መግቢያ ቦታውን ስለተገነዘበ በሩን እንዴት እንደሚከፈትም አውቋል:: መግቢያውን ከፈት ያደርግና ጠመንጃውን ወደ ውስጥ አሾልኮ በፍጥነት ወደ ውስጥ ይተኩሳል::

ይህን ያዩ ሌሎች ወደ ታንኩ እየሮጡ መጡ፤ ሁሉም መተኮስ ይፈልጋል:: ሁሉም "አሳማው" ላይ ዘሎ መውጣት ይፈልጋል:: ታንኩ በድንገት መቃጠል ጀመረ:: የጋዝ መያዣው እሳት ተነስቶበታል::

ከዚህ በኋላ ይህ ታንክ ያጋጠመው ዕጣ ለአንባቢ ግልፅ ነው::

በጣልያኖች ምሽግ ውስጥ ያሉ ሰዎች የሚሆነውን ሁሉ ቆመው ያያሉ፤ ማድረግ የሚችሉት ነገር አልነበረም:: ርቀቱ ለጠመንጃ የሚሆን አይደለም፤ መድፍ ደግሞ አልነበራቸውም:: ሁሉም ነገር በቅፅበት ስለሆነ ተጨማሪ ወታደር በጊዜው ከቦታው መድረስ አይችልም ነበር:: መንጋ ሰው ወደ ታንኩ ሲሮጥ ማየት ይችላሉ፤ ቁጥሩን ለመገመት ግን ዛፎችና ቁጥቋጦዎች ሙሉ እይታ ስለሚከለከሉ አስቸጋሪ ነበረ:: ማየት እስከቻሉበት ድረስ ግን የጥቁሮች ቁጥር የበላይነት ነበረው::

ሜጀሩ አጭር ውይይት ካደረገ በኋላ ምሽጉን ከከበባ እየተከላከሉ መቆየት የማይታሰብ ሆነ:: ተጨማሪ ሀይል እስከሚመጣ ጊዜ ይወስዳል:: ያለው አማራጭ እየተዋጉ ጥሶ መሄድ ነው:: "የጠላት ቁጥር ከኛ በላይ ነው ነገር ግን ምን ፋይዳ አለው? ከታንክ ከአውቶማቲክ መሳሪያና በደንብ ከሰለጠነ ወታደር ጋር ሲወዳደር:: ዛሬ እነዚህ አውሬ ሰዎች የኢጣልያ ወታደር ምን ማድረግ እንደሚችል ትምህርት ያገኛሉ:: ቪቫ ለ ዱቼ! ቪቫ ላ ኢጣልያ!"

አሁን ደግሞ አቢሲኒያኖች ከምሽጉ ወጥቶ ቁልቁለቱን እየተጠማዘዘ የሚወርድ የጠላት ሰልፍ ማየት ጀመሩ:: በአንድ ጊዜ ዘጠኝ ታንኮች በሰልፍ ወጡ፤ እነሱን ተከትሎ አራት ኮምፓኒ ወታደር ይወርዳል:: ከትንሽ ከፍተት በኋላ ሜጀሩ ፈረስ እየጋለበ ወጣ፤ እሱን የተከተለው ደግሞ ጠቅላላው ስንቅና ትጥቅ ከተጨማሪ ሁለት ኮምፓኒዎች መሀከል ነበር:: ለፊታውራሪ ሽፈራው ወታደሮች ይህ በስነስርአት በሰልፍ የሚጓዝ ረጅም መስመር የሚያስደንቅ ዕይታ ነበር:: ስንቅና ትጥቅ ከፍሉ አራት የጭነት መኪናዎች፣ መቶ የጭነት ከብቶችና ሰላሳ ግመሎች አሉበት::

ስጊዜው ፊታውራሪ መላውን ጦራቸውን ወደኋላ ወራጅ ውሀ ወዳለበት ቦታ እንዲመለስ አደረጉ:: መሬቱ ዳጋታማና በቁጥቋጦ የተሞላ ነው:: በመንገዱ ቀኝ በኩል የዘንባባ ዛፍ ጥቅጥቅ ብሎ ያደገበት ሰፊ ጫካ ጥሩ



መጠለያ ሆነ ተገኘ:: እዚህ ሆነው ጠላትን ይጠባበቁ ጀመር፤ ሳይዘገይ ጠላት መድረስ ጀመረ:: ሁሉም ዘጠኝ ታንኮች ሜዳው ላይ በመስመር ተሰለፉና ወደ ዘንባባ ዛፍ ወዳለበት ጫካ ተኩስ ጀመሩ:: እግረኛው ደግሞ ወደ ቁጥቋጦዎች አቅጣጫ ማጥቃት ጀመረ::

መትረየስና ቀላል አውቶማቲክ መሳሪያዎች ተኩሱን ሲያቀልጡት ሁለት ቀላል አውቶማቲክ መሳሪያ ብቻ ለያዙት አቢሲኒያውያን ከአቅም በላይ ነበር:: በጫካ ውስጥ ተደብቀው የነበሩ ሁለት ሺ ሰዎች በድንጋጤ ወደ ራሳቸው ስንቅና ትጥቅ ጓዝ ወዳለበት መሮጥ ጀመሩ:: ሌሎች ደግሞ በየአቅጣጫው ይበተኑ ጀመር::

ሽፈራው ግን የሚሸሹ አይደሉም:: ያ ሁሉ ጥይት እየተተኮሰባቸው ፊትና ኋላ እየተመላለሱ ጥሩምባ እየነፉ ይጮሁ ጀመር "እናንተ ሴቶች ናችሁ? እኔ ራሴ እዚህ እንዳለሁ አታዩም? ወዴት ለመሄድ ነው የምታስቡት?"

በዚህ ሁኔታ አምስት መቶ የሚሆኑ ወታደሮች ማሰባሰብ ቻሉ:: ከነሱ ጋራ በመሆን ወደኋላ ተመልሰው በመንገዱ ቀኝ በኩል በአራት ጎጆዎች ተጠለሉ::

በዚህ ጊዜ ደግሞ ፊታውራሪ በላይ የተባሉ ሰው ከአሥራ ስምንት አመት ልጃቸው ጋራ በመሆን ሌላ ጦር አሰባስበው በጋራው ዙርያ በመሄድ ከጠላት ጀርባ ጥቃት ጀመሩ ጣልያኖችም በሁለት እጥፍ ተኩስ መሀከል ሆኑ::

እልክ አስጨራሽ ውጊያ ተካሄደ:: ሜጀሩ ቆስሎ በቃሬዛ ተጭኗል:: በጣልያኖች በኩል አንድ *ሻምበል፣ መቶ አለቃ፣ ሶስት የበታች መኮንኖችና ሁለት ሾፌሮች ሞቱ::

ጣልያኖቹ እነሱ ላይ የተነጣጠረውን ትኩረት ለማስቀየር ብለው የጭነት ከብቶችን በየአቅጣጫው ለቀቋቸው:: ይህ ተንኮልም ሥራውን ሠራ:: አቢሲኒያኖቹ ከብቶችን በጥይት ተኩሰው ከጣሉ በኋላ ሁሉንም ነገር ረስተው የተጫነውን ንብረት ለመውሰድ ጎራዴያቸውን እየመዘዙ ወደ ወደቁት ከብቶች መሄድ ጀመሩ:: በዚህ ጊዜ ጣልያኖች በብዙ ግፊት መንገዳቸውን አስከፍተው ወደ ፊት ጉዞ መቀጠል ጀመሩ:: ያም ሆኖ ከአደጋ ማምለጥ አልቻሉም::

---

**የሞተው ሻምበል ስም ኤቶሬ ክሪፓ ይባላል (Ettore Crippa) ሁለት ሰው ብቻ የሚይዙት የአስሩ ፊያት አንሳልዶ የሚባሉ ታንኮች አዛዥ ነበረ:: አሰከሬኑን ያገኘው አሜዲዮ የሚባለው የሊቢያ ፈረሰኞች አዛዥ ነው::*

*Amedeo: A True Story of Love and War in Abyssinia. Sebastian O'Kelly*

ፈርጥጠው የሄዱት ወደ ሁለት ሺ የሚሆኑት አቢሲኒያውያን ማስተዋል ጀመሩና እንዲያውም ጦርነቱ ላይ ያሉትን ጓዶቻቸውን ለመርዳት ወሰኑ:: አንድ ወገን በጋራው ዙሪያ በመሄድ ከጣልያኖቹ ጋር ሲፋጠጥ ጣልያኖቹን የግድ ወደኋላ ከመንገዱ ወደ ምእራብ አቅጣጫ ወደ ሚገኝ ከፍታ እንዲሸሹ አደረጋቸው::




ሜጀር ከሪኒቲ ቆስሎ በቃሬዛ ሲሄድ ከኢታልያኖች በኩል የተነሳ ፎቶግራፍ

ሌላው ወገን ደግሞ የጣልያኖችን ስንቅና ትጥቅ የሚያጓጉዘውን ከፍል ወረረው:: በጣም አሰቃቂ ግን አጭር ጦርነት በኋላ ጣልያኖቹ እጃቸውን መስጠት ጀመሩ:: የቆሰለ ሰው እያከመ የነበረው የኢጣልያ ዶክተር ከትከሻው ላይ በተሰነዘረበት ጎራዴ ምክንያት ወድቆ ህሊናውን ሳተ:: በኋላ እንደሰማነው ታስሮ እያለ ማታውኑ ተገደለ::

ሌላው የጦሩ ህክምና ባለሙያ የሆነውን ስላየ ጉድጓድ ውስጥ ተደበቀ በኋላም ተገኝቶ እስረኛ ሆኖ ተወሰደ::

ሌላው ጣልያናዊ በዱላ ጭንቅላቱ ላይ ተመቶ ህሊናውን ስቶ በሚቀጥለው ቀን ነው የነቃው:: የሱን ዕጣ ወደፊት እንነጋገርበታለን::

ሴቶችና ልጆች ስንቁንና ትጥቁን ሲረባረቡበት ወታደሮቹ ጠላትን ከጀርባ ለማጥቃት ገሰገሱ:: ሾፌሮቻቸው የተገደሉባቸው ሁለት የጭነት መኪኖች



በእሳት ጋዩ:: የቆሰሉ ጣልያኖችና ሌሎች መንገዱ ላይ የነበሩ በሙሉ ያለምንም ምርጫ ተገደሉ::

ጣልያኖች እንደገና በሁለት ተኩስ መሀል ተከበቡ:: አቢሲኒያኖቹ ከፍታውን ጥሰው ገብተው የተደበቁ ጣልያኖችን በሙሉ ገደሉ:: ብዙ መኮንኖች አብረው ተገደሉ:: የውሃ ጥሙ እስቸጋሪ ሆነባቸው ወኔያቸው ወደቀ:: ሁሉም ጦር ጋራው ላይ ተሰበሰበ መሳሪያቸውን ጥለው እጃቸውን ወደላይ አነሱ::

ይህንን ማድረግ አልነበረባቸውም::

ያልሠለጠኑት የኛ ጀግኖች የእጅ ወደላይ ማንሳቱ ምልክት አልገባቸውም:: እንዲያውም ጠላትን ለመምታት አጋጣሚ ፈጠረላቸው::

የጠፋው ህይወት ትልቅ ነው በተሰይም ፊታውራሪ ሽፈራው ሶስት መቶ ሜትር ርቀት በሚገኝ ከፍታ ላይ ከወጡ በኋላ ተኩሱን ያቀልጡት ጀመር:: የያዙትን ቀላል አውቶማቲክ መሳሪያ ሲተኩሱ ጥይቱ በተንጣጣ ቁጥር ጎፈሬያቸው ይወዛወዝ ነበር::

ጣልያኖቹ የፈፀሙት ስህተት ወዲያው ገባቸው:: ወድያውኑ ሰንደቅ አላማቸውን አንስተው ከመኮንኖቻቸው ጋራ በመሆን መጮህ ጀመሩ:: "ቪቫ ላ ኢጣልያ" የመጀመሪያ ዙር ከተኮሱ በኋላ ሁሉም ወታደሮች ከጋራው ቁልቁል ወደ ሜዳው መሮጥ ጀመሩ:: ሜዳው ላይ የነበሩ ታንኮችና መኪኖችም መንቀሳቀስ ጀመሩ::

አቢሲኒያኖች ባሉበት ጋራ ላይ ግን አንድ ትንሽ ጥይት አንበሳውን ከነሸበቶ ጋማው መታቸው:: *ሽፈራው ወደቁ:: አማችየው የሚስታቸው አባት አጠገባቸው ነበሩ ወደ መሬት አጎንብሰው "ልጄን!" አሉ ግን ወዲያውኑ ሁሉም ነገር እንዳቆመ ተገነዘቡ:: ፈጣን ሞት ነበር::

ይህ ሁሉ ሲሆን አብረው የነበሩት የንስሃ አባት መጡና "እኔ እሸከፈዋለሁ:: ሥራዬ ነው:: ግን የሱን ሞት ብድር የማይመልስ ሰው የተረገመ ይሁን" አሉ::

የሰማንያ አመቱ የሽፈራው አማች ይህን አይነት ንግግር መስማትም አላስፈለጋቸውም:: በፍጥነት እንባቸውን ጠረጉ ሰውነታቸው ተንቀጠቀጠ አይናቸው ግን እንደ እሳት ይፋጃል:: ጉራዴያቸውን በቅፅበት መዘዙ::

---

*የፊታውራሪ ሽፈራውንና የባላምባራስ ተሰማን ገድል በሌላ መፅሀፍ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፅፎ አግኝተናል (Haileselassie's War, Anthony Mockler)*

**ፊታውራሪ ሽፈራው አባከንትር ሽፈ ተብለው ይጠሩ ነበር*

የመሪው መሞት ወሬው ወድያው ተዛመተ:: ዜናው በየመስመሩ ሲሰራጭ ተኩሱ ቆመ:: ሁለም ሰው ምንድን ነው የምናደርገው ብሎ የሚያስብ ይመስላል:: በጣም አሰፈላጊ ደቂቃዎች በከንቱ አለፉ:: ጣልያኖቹ አንድ ላይ ሆነው እያመለጡ ናቸው::

በዚህ ጊዜ ፊታውራሪ ነጋሽ እየሮጡ ወረዱ:: ከአድሜያቸው ጋራና በንዴት የሚንቀጠቀጠው ጎራዴ የያዘውን እጃቸውን ከፍ አድርገው ወደ ላይ አነሱ::

"ልጆች!" አሉ በሚንቀጠቀጥ ድምፅ" ሽፈራው አልሞተም! ጠላት እንዳያመልጥ አዟችኋል። ተከተሉኝ!" ሰዎች መሰብሰብ ሲጀምሩ አይኑን ጨፍኖ እንደሚሄድ ሰው ወደ ፊት ገሰገሱ::

አምልጠናል ብለው ማሰብ የጀመሩት ጣልያኖች ከጀርባቸው የጭነት መኪናና ሁለት ታንኮች በያዘ በአግረኛ ኮምፓኒ የኋላ ጦር ሽፋን አግኝተዋል:: ነገር ግን በንዴት እየከነፉ የመጡት አቢሲኒያውያን ደረሱባቸው:: መኪናው ወዲያውኑ ተወረረ:: በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ከጥቅም ውጭ ሆነ:: መኪናው ውስጥ የነበሩትን ሰዎች ለማዳን ተስፋ በማድረግ ታንኩ ዞሮ መጣ:: ወዲያውኑ ፊት ለፊት የነበሩ ሰዎች ታንኩ እናት ላይ ዘለው በመውጣት የታንኩን ሰዎችና ታንኩን ከጥቅም ውጭ አደረጓቸው:: ሌላኛው ታንከ ራቅ ብሎ ሄዶ ወንዙን ለማቋረጥ በመሞከር ላይ እያለ መሻገሪያው ላይ ሲደርስ ተገለበጠ:: ከታንኩ ስር እየተንፏቀቁ ከወጡ በኋላ ለመሸሽ የሞከሩት ሁለት ጣልያኖች በጥይት ወደቁ::

ኮምፓኒው ከወንዙ ማዶ ባለው ገደል ውስጥ አድፍጦ ተቀምጧል ነገር ግን ትንሽም ሳይቆይ መቋቋም አልቻለም:: ይህንን የኢጣልያ የኋላ ጦር ለመርዳት ቆመው የነበሩ ሁለት ታንኮችም በአቢሲኒያኖቹ ከጥቅም ውጭ ሆኑ:: ነጋሽ ጦሩን በጩኸት ያበረታታሉ "እነዚህ ውሾች እንዳያመልጧችሁ!" ለመበቀል ያላቸው ፍላጎት አልበረደም የድካም ስሜትም አልተሰማቸው:: ጣልያኖቹ ራሳቸውን መከላከል እንዳለባቸው ተገንዘበዋል በፍጥነት በታንክ ጀርባ በድንጋዮችና በዛፎች ጀርባ መጠለል ጀመሩ::

እንደገና ከፍተኛ ውጊያ ተጀመረ:: ሁለት ተጨማሪ ታንኮች ተደመሰሱ አንድ መኪና ከነሙሉ ጭነቱ በተዋጊዎች እጅ ወደቀ:: ሌላ ታንከ በፍርሃት በፍጥነት ሲሸሽ የገደል ሥንጥቅ ውስጥ ተገለበጠ፤ መውጭያ ከዳኑም ሊከፈት አልቻለም:: ከሁለት ቀን በኋላ ታንኩ ሲገኝ በውስጡ የነበሩ ሁለት



ጣልያኖች ጉድጓድ ተቆፍሮ ነው የወጡት:: በነበራቸው እስከፊ ሁኔታ ኢትዮጵያኖቹ አዘኑላቸው በዚህ ምክንያት ህይወታቸው ተረፈ::

ጊዜው አሁን ከቀኑ አስር ሰአት ሆኗል:: ለሰው ልጅ ጥንካሬ ገደብ አለው ለአቢሲኒያኖችም ቢሆን:: ለሀያ አራት ሰኣታት ምግብ የሚባል ነገር አልቀመሱም ከዚህ በኋላ ምንም ማድረግ የማይችሉበት ደረጃ ደርሰዋል::

ስለዚህ ለተወሰነ ጊዜ ቆም አሉ ጠላት በመስመር ከሁለት ታንክና ከአንድ መኪና ጋራ ሲሸሽ ተመለከቱ:: ጠቅላላ አትኩሮታቸውን ወደ ራሳቸው አድርገው የቆሰለውን መርዳት ፀሀይ ሳትገባና ጅቦች ሳይመጡ የሞቱትን መቅበር ጀመሩ::

"ስማ! ምንድነው?"

ከደቡብ አቅጣጫ አቧራው እንደደመና ትጉልል ብሎ ይታያል:: ቀጥሎም በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ሲጨፍሩ ይሰማል::

አንበለው! እንበለው ደሞ!
አሃ!
አንበለው!
አሃ!
አንበለው ደሞ!

በመጨረሻም ደረሱ:: የፊታውራሪ ተሻገር ሰዎች ነበሩ፤ ከምዕራብ በኩል ነው የመጡት:: የጦርነት ድምፅ ሰምተዋል:: ጠላት የት እንዳለ ማወቅ ይፈልጋሉ::

ጣልያኖቹ እየሸሹ እንደሆነ ተነገራቸው::

አንዳንድ የሽፈራው ሰዎችም ወኔያቸው እንደገና ተነስቶ እነዚህን አዲስ የመጡትን ተከተሉ

ሽፈራው ቆመ:: አሁን በሙሉ ጉልበታቸው ከጠላት ኋላ መሮጥ አለባቸው፤ እያንዳንዷ ደቂቃ ወሳኝ ነበረች:: ጠላት ላይ መድረስ ነበረባቸው፤ እንዳሰቡትም ተሳካላቸው::

በተራራው ዙሪያ ሮጠው ቀስ እያለ ከሚጓዘው የጣልያን ጦር ጋራ ተገናኙ:: ጣልያኖቹ ደከመዋል፤ ከጠላት እጅ አምልጠናል ብለው አስበው ነበር:: ጎራዴውን እያወዛወዘ በጩኸት የሚመጣውን አዲስ የጠላት ሀይል ሲያዩ ወኔያቸው ቢሰበር ሰው ሊረዳው የሚችለው ነገር ነው::

ይህ ቀን ማቆሚያ የለውም?

ነገር ግን ጀግኖቹ የሚያቆሙ አይነት አልነበሩም፡፡ መጠለያ የለም፤ መሬቱ ሜዳማ ነው ሳሩም በእሳት ተቃጥሏል፡፡ አማራጭ ስላልነበር ጣልያኖቹ መሬት ላይ ተጋድመው መተኮስ ጀመሩ፡፡ ወድያውኑ ደግሞ ዘለው ይነሱና የሚችሉትን ያህል ነብሳቸውን ለማዳን ይሮጣሉ፡፡ እንደዚህ እያደረጉ እየደጋገሙ የሚችሉትን ያህል ራቁ፡፡

አቢሲኒያኖች ደግሞ ቀደም ብሎ እንደሆነው ሁሉ ትኩረታቸውን መኪናው ላይና ታንኮቹ ላይ አደረጉ፡፡ ብዙ ጊዜም ሳይወስድ ቁጥጥር ስር አደረጓቸው *ሁለት የኢጣልያ ታንከኞች ብቻ አመለጡ፡፡

ማሳደዱም ቀጠለ በዚያው ልክ ደግሞ ከጣልያኖች ጋራ የተሰለፉት የኤርትራውያኑ ጉብዝና የተሞላበት መከላከል እስከ ማይ ሚኒ ወንዝ ድረስ ቀጠለ፡፡ እዚያ ሲደርስ ቆመ፡፡ ምክንያቱም ጨለማው እየመጣ ነበር፡፡ አቢሲኒያኖች ደግሞ ከዚያ በላይ መግፋት አልቻሉም፡፡ ምክንያቱም የአንዳ ሰላሴ የጠላት ካምፕ ማዶ እንዳለ ያውቁ ነበር፡፡

ያን ቀን ከረፋዱ በኋላ የጠላት ቦምብ ጣይ አውሮፕላን በጦር ሜዳው ላይ እያንዣበበ ትንንሽ ቦምቦች እየጣለ አውቶማቲክ መሳሪያም ይተኩስ ነበር፡፡ አቢሲኒያኖች ደግሞ ከጠላት ጋራ ግብግብ ይዘው ጉዳይም አልሰጡትም ነበር፡፡ ተቀላቅሎ ስለነበር ለቦምብ ጣይ አውሮፕላኑ ጠላትና ወዳጅ መለየት ሰላልቻለ ብዙ ጉዳት አላደረሰም፡፡ በኋላ ግን የአቢሲኒያኖች ስንቅና ትጥቅ ክፍሉን አግኝቶ ብዙ ጥይትና ሌላም ዓዝ በእሳት በምብና በሚነደው ሳር ምክንያት ከጥቅም ውጭ ሆነ፡፡

---

** ያን ቀን ካመለጡ የኢጣልያ ወታደሮች አስራ አለቃ ብሩኖ የሚባል እንደነበረና ታንኮቹን የማይረቡ ናቸው ብሎ እንዳማረረ ተጠቅሷል፡፡ አሰር አለቃው በአካባቢው ከነበሩ የሊቢያ ስፓሂ ወታደሮች ጋር እንደተደባለቀ ተዘግቧል፡፡*
*Amedeo: A True Story of Love and War in Abyssinia. Sebastian O'Kelly*

*ከዚህ ፅሁፍ ታሪክ በመነሳት ከጣልያኖች ጋራ የመጀመሪያውን ጦርነት ያካሄዱት የደጃዝማች አያሌው ተከታዮች ከሆኑ፤ በዚህ ጦርነትም ታንክ የተደመሰሰበት ከሆነ፤ የመጀመሪያውን ታንክ የማረከው የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ባላምባራስ ተሰማ መሆኑ ነው፡፡ ይህንን ግን አንባብያንና የታሪክ ባለሙያተኞች በአዎንታ ሆነ በአሉታ እንዲነጋገሩበት እንጋብዛለን፡፡*



# ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## ቁስለኞችን ማከም

በታህሳስ ስድስት በእንዳባጉና የተደረገው ጦርነት ምዕራቡን የትግራይ ክፍል ከጣልያኖች ቅኝ ግዛት አስለቅቋል፡፡ ገና በሰቲት አካባቢ ነው የተባለው ግን ድንገተኛና ሀይለኛ ጥቃት ያካሄደው የአቢሲኒያ ጦር ሌሎች በአዲያቦ፣ ሽሬ እና ዛና የሚገኙ ስድስት የጣልያን የጦር ካምፖችን አስጊ ሁኔታ ፈጥሮባቸዋል፡፡ ስለዚህ ጣልያኖቹ በስባት ማታውኑ ጓዛቸውን ጠቅልለው በጥንቃቄ ወደ ዋናው ካምፕ አክሱም ገቡ፡፡

በአቢሲኒያኖች በኩል የደረሰው ጉዳት ግን ከፍተኛ ነበር፡፡ ሶስት መቶ ሰማንያ ሁለት ሰዎች ተወዳጁንና ጀግናውን ፊታውራሪ ሽፈራውን ጨምሮ ሞተዋል፡፡ ሁለት መቶ ሃምሳ ስድስት ሰዎች ደግሞ ቆስለዋል፡፡

አቢሲኒያኖቹ ለህይወት ስለማይሳሱ ከተገኘው ውጤት ጋራ ሲወዳደር ጉዳቱን የከፋ አላደረጉትም፡፡ በችኮላና በድንቁርና ታንኮችን ባያጠቁ ኖሮ የደረሰው ጉዳት ከዚህ ያንስ ነበር ፡፡ ያም ሆኖ በዚህ ሁኔታ ትልቅ ድል ነው ያገኙት ለድፍረት የሚሆን የጦርነት ልምድም አገኙ፡፡ እነዚህ ጭራቆች (ታንኮችን ማለት ነው) ሊደፈሩ የሚችሉ መሆናቸውን ተገነዘቡ፡፡

በጣልያኖች በኩል ደግሞ ስባት መኮንኖች፣ ሃያ ሶስት ነጭ ወታደሮች፣ አርባ ስምንት የኤርትራ ተወላጆች መኮንኖችና መቶ ሃያ ስባት ባንዳ ወታደሮች ሞተውባቸዋል፡፡ የቆሰሉት ቁጥር ሰላሳ ብቻ ነው ተብሎ የተዘገበው፡፡

የዚህ የተሰጠው ቁጥር አጠራጣሪ ነበር ምክንያቱም ሃምሳ አንድ የነጭ ወታደሮች ሜዳው ላይ ሞተው ተገኝተዋል፡፡ ስንቶቹ መኮንኖች እንደሆኑ ማወቅ አይቻልም ነበር፡፡ ምክንያቱም ልብሳቸው ስለተውሰደ ራቁት ነበሩ፡፡ ልብስ በጣም ተፈላጊ ነበር፡፡

ሁሉም ሞተው የተገኙት አቢሲኒያውያን የጦርነቱ ለት ማምሻውን አጠገብ ባለ ቤተክርስቲያን በዘመድና ወዳጆቻቸው ተቀበሩ፡፡

ይህ ቀን ማቆሚያ የለውም?

ነገር ግን ጀግኖቹ የሚያቆሙ አይነት አልነበሩም:: መጠለያ የለም፣ መሬቱ ሜዳማ ነው ሳሩም በእሳት ተቃጥሏል:: አማራጭ ስላልነበር ጣልያኖቹ መሬት ላይ ተጋድመው መተኮስ ጀመሩ:: ወድያውኑ ደግሞ ዘለው ይነሱና የሚችሉትን ያህል ነብሳቸውን ለማዳን ይሮጣሉ:: እንደዚህ እያደረጉ እየደጋገሙ የሚችሉትን ያህል ራቁ::

አቢሲኒያኖች ደግሞ ቀደም ብሎ እንደሆነው ሁሉ ትኩረታቸውን መኪናው ላይና ታንኮቹ ላይ አደረጉ:: ብዙ ጊዜም ሳይወስድ ቁጥጥር ስር አደረጓቸው *ሁለት የኢጣልያ ታንከኞች ብቻ አመለጡ::

ማሳደዱም ቀጠለ በዚያው ልክ ደግሞ ከጣልያኖች ጋራ የተሰለፉት የኤርትራውያኑ ጉብዝና የተሞላበት መከላከል እስከ ማይ ሚኒ ወንዝ ድረስ ቀጠለ:: እዚያ ሲደርስ ቆመ:: ምክንያቱም ጨለማው እየመጣ ነበር:: አቢሲኒያኖች ደግሞ ከዚያ በላይ መግፋት አልቻሉም:: ምክንያቱም የእንዳ ስላሴ የጠላት ካምፕ ማዶ እንዳለ ያውቁ ነበር::

ያን ቀን ከረፋዱ በኋላ የጠላት ቦምብ ጣይ አውሮፕላን በጦር ሜዳው ላይ እያንዣበበ ትንንሽ ቦምቦች እየጣለ አውቶማቲክ መሳሪያም ይተኩስ ነበር:: አቢሲኒያኖች ደግሞ ከጠላት ጋራ ግብግብ ይዘው ጉዳይም አልሰጡትም ነበር:: ተቀላቅሎ ስለነበር ለቦምብ ጣይ አውሮፕላኑ ጠላትና ወዳጅ መለየት ስላልቻለ ብዙ ጉዳት አላደረሰም:: በኋላ ግን የአቢሲኒያኖች ስንቅና ትጥቅ ክፍሉን አግኝቶ ብዙ ጥይትና ሌላም ጓዝ በእሳት በምብና በሚነደው ሳር ምክንያት ከጥቅም ውጭ ሆነ::

---

** ያን ቀን ካመለጡ የኢጣልያ ወታደሮች አስራ አለቃ ብሩኖ የሚባል እነደነበረና ታንኮቹን የሚይረቡ ናቸው ብሎ እንዳማረረ ተጠቅሷል:: አስር አለቃው በአካባቢው ከነበሩ የሊቢያ ስፖሂ ወታደሮች ጋር እንደተደባለቀ ተዘግቧል::*

*Amedeo: A True Story of Love and War in Abyssinia. Sebastian O'Kelly*

*ከዚህ ፅሁፍ ታሪክ በመነሳት ከጣልያኖች ጋራ የመጀመሪያውን ጦርነት ያካሄዱት የደጃዝማች አያሌው ተከታዮች ከሆኑ፣ በዚህ ጦርነትም ታንክ የተደመሰሰበት ከሆነ፣ የመጀመሪያውን ታንክ የማረከው የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ባላምባራስ ተሰማ መሆኑ ነው:: ይህንን ግን አንባብያንና የታሪክ ባለሙያተኞች በአዎንታ ሆነ በአሉታ እንዲነጋገሩበት እንጋብዛለን::*



# ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## ቁስለኞችን ማከም

በታህሳስ ስድስት በእንዳባጉና የተደረገው ጦርነት ምዕራቡን የትግራይ ክፍል ከጣልያኖች ቅኝ ግዛት አስለቅቋል:: ገና በስቲት አካባቢ ነው የተባለው ግን ድንገተኛና ሀይለኛ ጥቃት ያካሄደው የአቢሲኒያ ጦር ሌሎች በአዲያቦ፣ ሽሬ እና ዛና የሚገኙ ስድስት የጣልያን የጦር ካምፖችን እስኪ ሁኔታ ፈጥሮባቸዋል:: ስለዚህ ጣልያኖቹ በሰባት ማታውኑ ጓዛቸውን ጠቅልለው በጥንቃቄ ወደ ዋናው ካምፕ አክሱም ገቡ::

በአቢሲኒያኖች በኩል የደረሰው ጉዳት ግን ከፍተኛ ነበር:: ሶስት መቶ ስማንያ ሁለት ሰዎች ተወዳጁንና ጀግናውን ፊታውራሪ ሽፈራውን ጨምሮ ሞተዋል:: ሁለት መቶ ሃምሳ ስድስት ሰዎች ደግሞ ቆስለዋል::

አቢሲኒያኖቹ ስህይወት ስለማይሳሱ ከተገኘው ውጤት ጋራ ሲወዳደር ጉዳቱን የከፋ አላደረጉትም:: በችኮላና በድንቁርና ታንኮችን ባያጠቁ ኖሮ የደረሰው ጉዳት ከዚህ ያንስ ነበር :: ያም ሆኖ በዚህ ሁኔታ ትልቅ ድል ነው ያገኙት ለድፍረት የሚሆን የጦርነት ልምድም አገኙ:: እነዚህ ጭራቆች (ታንኮችን ማለት ነው) ሊደፈሩ የሚችሉ መሆናቸውን ተገነዘቡ::

በጣልያኖች በኩል ደግሞ ሰባት መኮንኖች፣ ሃያ ሶስት ነጭ ወታደሮች፣ አርባ ስምንት የኤርትራ ተወላጆች መኮንኖችና መቶ ሃያ ሰባት ባንዳ ወታደሮች ሞተውባቸዋል:: የቆሰሉት ቁጥር ስላሳ ብቻ ነው ተብሎ የተዘገበው::

የዚህ የተሰጠው ቁጥር አጠራጣሪ ነበር ምክንያቱም ሃምሳ አንድ የነጭ ወታደሮች ሜዳው ላይ ሞተው ተገኝተዋል:: ስንቶቹ መኮንኖች እንደሆኑ ማወቅ አይቻልም ነበር:: ምክንያቱም ልብሳቸው ስለተወሰደ ራቁት ነበሩ:: ልብስ በጣም ተፈላጊ ነበር::

ሁሉም ሞተው የተገኙት አቢሲኒያውያን የጦርነቱ ለት ማምሻውን እጠገብ ባለ ቤተክርስቲያን በዘመድና ወዳጆቻቸው ተቀበሩ::

የፊታውራሪ ሽፈራው የንስሃ አባት ከዚያ ወዲህ አልታዩም:: የተወሰኑ ወታደሮችን የፊታውራሪ ሽፈራውን አስከሬን እንዲጠብቁ ከጠየቁ በኋላ ጦርነቱን ተቀላቅለው በዚያው ወድቀዋል::

ብዙ ንብረት ደግሞ በድል አድራጊዎች እጅ ወድቋል:: ሰባት ታንኮችና አራት መኪኖች ብትንትናቸው ቀርቷል:: ሁለቱ ስለተገለበጡ ማንቀሳቀስ አልተቻለም:: ሶስተኛው ግን አጠገብ ወዳለ ሰፈር ተወስዶ የአሥራ ዘጠኝ አመቱ ጣልያናዊ እንዲነዳው ተገዷል:: ማራኪዎቹ የተማረከውን ወታደር ይዘው በሰፈሩ ላሉ ሴቶች በማሳየት እየተዝናኑ ነው:: ይህ እስፈሪ ብረት እየተንኳኳ በሰፈር ሲያልፍ ያዩ ሴቶች ጀግኖቻቸውን በእልልታ ተቀበሏቸው::

አንድ የግል አውቶሞቢልም በከፊል ተጎድቷል:: መኪናው የራሱ ታሪክ አለው:: የቆየ የፎርድ መኪና ሞዴል ቲ በስዊድን ዋና ከተማ ስቶክሆልም የተገዛ ነበር:: ሚሲዮናዊ አባ እንደርሰን መኪናውን በመላ አውሮፓ ኢጣልያ ድረስ ከቤተሰቦቹ ጋራ ነድቶ ከወሰደው በኋላ በመርከብ ወደ ግብፅ አስልኮ ከግብፅ ደግሞ እየነዳ ወደ ኤርትራ ይዞ ዘልቋል:: በኋላም ወደ አድዋ እንዲዛወር ሲታዘዝ መኪናውን እስከ ደንበሩ ድረስ እየነዳ መጣ፤ ከዚያ በኋላ መንገድ ስላልነበረ ማቆም ነበረበት:: በዚያን ጊዜ አዛዡ ራስ ስዩም መንገድ እንዲሰራ ትዕዛዝ ሲሰጡ "ያማ በማዕከላዊው መንግስት በአዲስ አበባ ከልክል ነው" ተባለ::

የቫይኪንግ ደም ያለበት አባ አንድርያስ ግን በዚህ ማቆም አልወሰነም:: ስለዚህ ሰዎች መኪናውን እንዲሸከሙ ጠየቀና ከአካባቢው ወደ ሺ የሚቆጠሩ ገበሬዎች ተሰበሰቡ:: ሃምሳ ኪሎሜትር የሚሆነው መንገድ በሚጮሁና በሚዘፍኑ ገበሬዎች ትከሻ ከተጓዘ በኋላ የመጀመሪያው መኪና አድዋ ውስጥ በዚህ መልክ ገባ::

ይህ ታሪክ እየተነገረን በሰፊው ጦርነት በተካሄደበት መሬት አቋርጠን አሰፍን:: ብዙ ጊዜ ነው የወሰደብን:: ብዙ ጊዜ ደግሞ ከኢጣልያ አውሮፕላኖች መደበቅ ነበረብን:: በየቦታው ሬሳ ነበር:: በቅሎና ፈረስ ግመልን ጨምሮ ከጥቁርም ከነጭ ሰው ሬሳ ጋር ተደባልቆ ወድቋል:: አቢሲኒያኖች ጠላቶቻቸውን አይቀብሩም በተለይ ከነሱ ውጭ ሌላ ዝርያ ወይም ሌላ ሀይማኖት ከሆነ::

የሚቀፍ ሽታ አየሩን ሞልቶታል



የመጨረሻውን ታንክ እንዳየን ወደ ደቡብ አቅጣጫ መንገዳችን ቀይረን የቆሰሉ ወታደሮች ወዳሉበት ካምፕ ሄድን:: ቦታው ልንደርስ ትንሽ ሲቀረን ከጫካው መሀል ጎራዴ የያዘ ሰው ድንገት እየሮጠ ወደኛ መጣ

"አሃ! እኛ በእግራችን እየሄድን ይሄ እሳማ በፈረስ ይሄዳል? አሳየዋለሁ! አሳየዋለሁ!!" ጣልያናዊ ነው የመሰለኩት፤ ከዛም በላይ አስረኛ

ወድያውኑ ሽጉጤን መዘዝኩ

"የታጠቀ አስረኛ ነው እንዴ ይዛችሁ የምትዞሩት?" አለ በመገረም

ቀኛዝማች ንጋቱ በመሀከላችን ገቡና ማን እንደሆንኩ ነገሩት:: ሰውየውም ጉልበቴን ሳመና ይቅርታ እንዳደርግለት ጠየቀ:: ሰው እንዴት አድርጎ ነው ከነዚህ አይነት ያዋቂ ልጆች ላይ ቂምስ ወይም ጠላትነት የሚይዘው?

ካምፑ ውስጥ ስንገባ የቁስለኛው ካምፕ ማለት ነው ሽማግሌው ፊታውራሪ ነጋሽ ከነበሩበት ዋሻ ውጥተው ተቀበሉኝ:: የጣልያን የወታደር የብረት ቆብ እናታቸው ላይ አድርገዋል፤ ቆቡ ላይ የተፃፈውን ምልክት ሳስተውል አዩኝና

"ይህ ብረት ቆብ የጣልያን ጄኔራል ነው በምልክቱ እንደምታየው፤ ከጄ ሳያመልጥ ደርሼ ጉሮሮውን ቆረጥኩት"

የጄኔራል ነው የተባለውን ምልክቱን ሳየው የሬድዮ ሠራተኛ ነው የነበረው ነገር ግን ነገሩን ላለማበላሸት ስል ሰውየውን እንኳን ደስ አለዎት አልኳቸው::

ዋሻው ውስጥ ምግብ ተዘጋጅቶ ነበር:: ብዛት ያለው የአተር አሸት አምጥተው ፊታችን አስቀመጡ:: አተሩን እየፈለፈልን ስንበላ ሽማግሌው ነጋሽ ሀሳብ የገባቸውና የተጨነቁ ይመስላሉ:: ምን እንደሚያስጨንቃቸውም ጠየቅኋቸው::

አንድ ያላቸው ልጅ በፅኑ ቆስሏል

"ለምን ቀደም ብለው አልነገሩኝም?"

"ትንሽ እረፍ ሳትል ላስቸግርህ አልፈለግሁም"

ወዲያውኑ ወደ ቆሰለው ሰውየ ሄድን:: አሳዛኝ ሆኖ ልጃቸው የመጨረሻ ሰአቱ ላይ እንደነበረ ግልፅ ነው:: እንደቆሰለ ብዙ ደም ስለፈሰሰው ደክሟል:: ደሙም መመረዝ ጀምሮአል:: ማድረግ የምንችለውን ሁሉ አደረግን ሌላው ቢቀር ጥሩ እልጋ ላይ እርፎ ነበር::

ጥቂት ቆይቶ ደግሞ ቁጥራቸው በርከት ያሉ ሰዎች በዋሻው መግቢያ በር ላይ ተሰበሰቡ:: ሐኪሙን ማየት ይፈልጋሉ:: መልኩ ምን እንደሚመስል የፀጉሩ ቀለም፤ ትልቅ ነው ወይስ ትንሽ፤ ደግሞስ ምንድነው የለበሰው?

የመሳሰሉት፡፡ በመልኩ ማወቅ ይፈልጋሉ ምክንያቱም በኋላ ቁስለኞች አከባቢ ሲሄድ ሰው እንዳይገለው ነው፡፡ ቁመቴ(የዶክተር ናየስተሮም ቁመት ስድስት ጫማ ከሁለት ኢንች ነበር) ለመለየት ይረዳቸዋል፤ ምክንያቱም በነሱ አስተሳሰብ ጣልያኖቹ ቁመታቸው አጭር ነው፡፡ በራሳቸው ቋንቋ መናገር ስጀምር በመሃከላችን የነበረው መከለያ ተወገደ እና እንደወንድማቸው አድርገው አዩኝ፡፡

ሁሉም ዋሻዎችና ቁጥቋጦዎች በወታደሮች ስለተያዙ ለኔ ማረፊያ የሚሆን ቦታ ማግኘት አስቸጋሪ ነበር፡፡ ውነት ነው ብዙዎቹ አብሬያቸው እንድሆን ጋብዘውኝ ነበር ግን በብዙ ምክንያቶች ይቅርብኝ ብያለሁ፡፡ በመጨረሻ ሜዳ መሀከል ላይ ወዳለ ባዶ የገበሬ ቤት ለመሄድ ወሰንኩኝ፡፡ ሶስት በጥሩ ሁኔታ የነበሩ ጎጆዎች ነበሩ፡፡ ሶስቱን ለመኖርያ፤ ለእቃ ማስቀመጫና ለማከሚያ ቦታ ማድረግ ይቻላል፡፡ በተጨማሪ ያስተዋልኩት ነገር ቢኖር የኢጣልያ አውሮፕላኖች የሚጠረጠር ነገር ካላዩ በስተቀር ጎጆዎች ላይ ቦምብ አይጥሉም ነበር፡፡

በቅጠል የተሰራ ጎጆ ቆመ ለታካሚዎች እንደመቆያ ከፍል መሆኑ ነው፡፡ ሰዎች ከፊት ለፊት ሜዳ ላይ እንዳይሰባሰቡ ዘቦች እንዲቆሙ ተደረገ፡፡ መሀል ጦርነት ላይ ስላለሁ የቀይ መስቀል ባንዴራ መሰቀል ትክክል ነው ብዬ አላሰብኩም እንዲያውም ለኢጣልያ አውሮፕላኖች የኢላማ ምልክት መስጠት ይሆናል፡፡

እንግዲህ በዚህ ሁኔታ አውሮፕላኖችን ሳልፈራ መድፈሬ በአንዳንድ ወታደሮች ዘንድ ደፋር ሰው የሚል ሙገሳ አስገኝቶልኛል በሌሎች ዘንድ ግን ከሞኝ ነው የተቆጠርኩት፡፡ በቀን ብርሃን ሰላሳ ሰዎች ብቻ ደፍረው ለህክምና መጡ በዚህ ምክንያት ሥራዬን በሚከተለው ሁኔታ አደላደልኩኝ፡፡

1. የመጀመሪያ የታመሙ ሰዎች ማያ ጊዜ ከጠዋቱ ፲፩ ሰአት እስከ ጠዋቱ ፩ ሰአት ድረስ
2. ከአንድ ሰአት እስከ ጠዋቱ አራት ሰአት ማረፊያ ጊዜዬ፤ በዚህ ሰአት ቁርስ የምበላበት፤ የህክምና መሳሪያዎችን የምቀቅልበት እና ለሚቀጥለው ሥራ ክሊኒኩን የማዘጋጅበት ጊዜ ነው



3. ከአራት ሰአት እስከ እኩለ ቀን ስድስት ሰአት መንቀሳቀስ የማይችሉ በየዋሻው ያሉ ቁስለኞችን እየዞርኩ የምጎበኝበትና ቁስላቸውን የማከምበት
4. ከስድስት ሰአት እስከ ዘጠኝ ሰአት የምሳና የእረፍት ጊዜ
5. ከዘጠኝ እስከ ምሽቱ አንድ ሰአት ህሙማን የሚታዩበት ጊዜ፤ ከዚያም ቀጥሎ እስከ ምሽቱ ሶስት ሰአት ተጨማሪ ሕሙማን የሚታዩበት ጊዜ ሆነ

ሁለት ትልልቅ ፋኖሶች ቀዶ ህክምና ለማድረግ በቂ ብርሃን ይሰጡ ነበር፡፡

ለብቸኛ ዶክተር ከሶስት ያገሩ ተወላጅ ረዳቶች ጋራ ብቻ መሥራት የሥራ ጫናው በጣም ከባድ ነበር፡፡ ሁሉን የሚያስፈልግ ነገር ለማድረግ አስቸጋሪ ነበር፡፡ በተጨማሪ በቂ እንቅልፍ ማግኘት አልቻልኩም፤ በማረፊያ ሰአቶች ሙትኛት ብፈልግ በጣም ታሟል በሚባል በሽተኛ ምክንያት እቀሰቀሳለሁ፡፡ በቀን እንዳልተኛ ደግሞ በአውሮፕላኖቹና በቦምቦች ፍንዳታ ድምፅ ድንገት እነቃለሁ፡፡

ያም ሁሉ ሆኖ ብዙ የሚያስገርሙ ብዙም የሚያስቁ ሁኔታዎች ስለነበሩ ብቸኝነቱ እንደሚቻል እንዲሆን ረድተዋል፡፡

ለምን እንደሆን በማይገባኝ ምክንያት በመትረየስ ጥይት መቁሰል እንደክብር ይቆጠር ነበር፡፡ እኔ ቁስሉ ከጠመንጃ ነው ወይም ከቦምብ ፍንጣሪ ነው ብዬ ብናገር ከስድብ ነበር የሚቆጠረው፡፡ ሐኪሙ ምንም አያውቅምም አባላለሁ፡፡ ቁስሉ ከመትረየስ አይደለም ብዬ ከተናገርኩ እንዳንዶች መታከሙን እምቢ ይላሉ ወይም ተከታታይ ህክምና አያደርጉም ፡፡

አንድ ሰው በፍንጣሪ ተመቶ የተለያየ ሰውነቱ ከፍል ላይ አስር ቦታ ቆስሏል፡፡ ሳላስበው ሰውየውን "እድለኛ ነህ እንኳን ቦምቡ ወደ አየር አልወረወረህም" ስለ በጣም ተናደደ፡፡ "አታይም እንዴ? ይሄ ሁሉ ቁስል በመትረየስ ጥይት እንደሆን እንዱ በዚህ በኩል ነው የገባው" አለ በቀኝ ትከሻው በኩል ወዳለው ቁስል እያሳየ "ይኸውና የወጣው ደግሞ በዚህ በኩል ነው" ብሎ በግራ ጭኑ ላይ ያለውን ቁስለ አሳየኝ፡፡

መከራከሩ ፋይዳ የለውም እቆሳስሉ እንዳሰበውና እንደሚያምንበት እንደሆን ቢሆንለት ቶሎ እንደሚድንም አውቃለሁ፡፡

ከሆነ እኔን እንደ ትልቅ ጅል ነው ያዩኝ:: ከነበራቸው ህመም በተጨማሪ ነካከቼ ሁኔታውን አባብሼዋለሁ ማለት ነው:: ለማስረዳትና ለማረጋጋት ያደረግሁት ሙከራ አልተሳካም:: በብዙ ምክንያት ሞርፊን የተባለ የህመም መቆጣጠሪያ መድሃኒት ልሰጣቸውም አልደፈርኩም::

በሁለተኛው ቀን ጠቅላላ ሁኔታቸው የተሻለ ሆኖ ታየ:: ከሳምንታት በኋላ ቁስሉ ሁሉም ዳነ:: ይህ ደግሞ ሁላችንም ያስደሰተ ነገር ነበር:: ጉንጮቻቸው ላይ ቀለል ያሉ ሁለት ጠባሳዎች ነበሩ፤ ነገር ግን ያን የነበረውን ሁኔታ የሚገልጥ ሌላ ምልክትም አልነበረም:: ንግግራቸውም ሙሉ በሙሉ ተመለሰ:: በደም መርፌ በመስጠት ጥሩ ውጤት ካገኘሁባቸው አንዱ ይኸው የቀኛዝማቹ ቁስል ነው::

ንጉሡ የቆሰሉት በሙሉ በሶስት ደረጃ ተከፍለው እንዲመዘገቡ ትዛዝ ሰጥተዋል:: ቀለል ያለ ቁስለት፤ መካከለኛ እና ከባድ ቁስል:: የመጨረሻዎቹ ማለትም ከባድ የመቁሰል አደጋ የደረሰባቸው ሽልማት አንድ ጊዜ በሚሠጥ ገንዘብ መጠን ወይም ጡረታ ይሠጣቸዋል:: ይህንን ደግሞ ሁሉም ወታደሮች ጠንቅቀው ያውቁ ነበር:: እንግዲህ ቁስሉ ትንሽ ሲሆን ጩኸቱ ግን ከመጠን በላይና የሚረብሽ ይሆናል::

"ሀኪም መሞቴ ነው! ሀኪም በጠና ነው የቆሰልኩት ሊገለኝ ነው! ሀኪም አንዳሻህ አድርገኝ! እጄን ቆረጠው ጉሮሮዬንም ጨምረህ ቁረጠው:: ተበላሽቻለሁ!" ይህን የመሰሉ ጩኸቶች ከጥዋት እስከ ማታ ድረስ እሰማ ነበር::

ቀደም ባሉ በአቢሲኒያ በተደረጉ ጦርነቶች የቆሰለ ሰው ወደ ቤቱ እንዲመለስ ይፈቀድለት ነበር:: ከቆሰለ ለሱ ጦርነቱ አበቃ:: እሁን ግን ጥብቅ ትዛዝ ተሰጥቶ የቆሰሉት በሙሉ አዛው ግንባር ላይ እየታከሙ ሲሻላቸውና ሀኪም መዋጋት ይችላሉ ሲል ወደ ጦር ሜዳ እንዲመለሱ ይደረጋል::

አንድ ቀን ከአዛዥ ከደጃች አያሌው ጥያቄ መጣ:: አንድ ፊታውራሪ ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሆን? ነገር ግን ደጃዝማች ደግሞ ይፈልጉታል:: ይህ የተባለው ፊታውራሪ ብዙ ጣጣ እድርሶብኛል:: ቁስሉ ቀለል ያለ ቢሆንም አልዳነም:: አንዲህ እይነት ቀለል ያለ ቁስል ባለቸው ሰዎች ላይ ግራ የሚያጋባ ሁኔታ በግማሾቹ ላይ አስተውያለሁ:: ቀላሉ ቁስል እንዴት ቶሎ አይድንም ነው ጥያቄው:: ድሬስሩ የሚያደርገውንም ነገር ጠጋ ብዬ በደንብ ተመለከትኩ ነገር ግን እእምሮየን በመላምት ሆነ በምርመር መልከ ብወጥረውም መልስ ማግኘት አልቻልኩም::



ድሬስሩ ፈጠነ ፊታውራሪው ቁስሉን ለረዥም ጊዜ ያላሰጠረገ ወይም ያላሳከመ መሆኑን አሲታወለኝ:: ወደ ዋሻው ሄጄ ቁስሉን ማየት አለብኝ አልኩኝ:: የተለያዩ ምክንያቶች እያቀረበ እምቢ ለማለት ሞከረ እኔ ግን ድርቅ አልኩኝ::

ቁስሉ የተሸፈነበት ጨርቅ ሲፈታ ቡናማና ግራጫ መልክ ያለው ነገር ከቁስሉ መሀል ላይ ተከምሮ እየሁኝ፤ ከለሩ ደግሞ አረንጓዴ ቀለም ያለው መግል መውረድ ጀመረ:: ቁስሉ ደግሞ ከነበረው መጠን በአራት እጥፍ ጨምሯል፤ ቁሰልን እየበላ የሚያሰፋ ኬሚካል ያለበት ይመስላል::

ምንም መጠየቅም አላስፈለገኝም:: የችግሩ መንስኤ ገብቶኛል:: ቁስል የሚበላው መድሃኒት ከሆነ ሥር ነው የሚዘጋጀው ሰሙን ግን አላውቀውም:: ከቅቤና ከማር ጋር አንደ አጅ ከሁለት እጅ በሆነ መንገድ ተለውሶ ሲደረግ ቁሰል እንዳይድን የማድረግ ችሎታ አለው::

እነዚህ ወሮበሎች በአፍንጫዬ እየንተቱ ሲያዞሩኝ ለንብተዋል:: ጥያቄው ደግሞ ማነው የሚረዳቸው? ነው::

ለካስ ወጌሻው ነበር:: ለኔ እንኳን እንደ ሥራ ጓደኛ ማለት ነበር የማላውቀው ሰውም አልነበረም:: በፊታውራሪ ነጋሽ እርዳታ ተደዞ እንዲቀመጥ አስደረግሁኝ:: ችሎት ቀርቦ ስንስማ እያንዳንዱን ሰው በዚያ ሁኔታ ለማከም እምስት አምስት ማርትሪዛ ያስከፍል ነበር:: የወሰደው ገንዘብ እንዲመለስ ተደረገና ሶስት ሰዎች ዋስ ጠርቶ ሁለተኛ ካምፑ ወስጥ ፊቱን እንዳያሳይ ተደረገ::

ሌሎች በጠና የቆሰሉ የሞቱም ብዙ ነበሩ:: አገሜቸው ብትንትኑ የወጣ፤ ፊታቸውን መለየት እስከሚያቅት ድረስ የቆሰለባቸው፤ ምንም መሳሪያ ሳላለነበረኝ ያለአማራጭ እኔ ራሴ እጅና እግራቸውን የቆረጥኩባቸውን ይጨምራል::

አንደነዚህ አይነቱ ቁስለኞች ላይ ይህን ሁሉ ጉዳት ባደረሱ ሰዎች ላይ ምርር ያለ የጥላቻ ስሜት ይፈጥርብኛል:: ሥልጣኔ ነው ተብሎ ንብረት ለመዝረፍ ጥማት ያለበት ጉልበተኛ ደካማውን የሚያጠቃ ከሆነ በዱር እንስሳትስ ይህንን አይነት ሁኔታ አይደለም ወይ የምናዬው? ብዙ የቆሰሉ ሰዎችን እየሁ አብዛኞቹ እጅና እግራቸውን አጥተዋል:: እነዚህ ሰዎች የተገኘባቸው ወንጀል ቢኖር እባት አገራቸውን ለመከላከል መሞከራቸው ብቻ ነው:: ታዲያ ይህ በራሱ ድል አደረግን ተብሎ ሲጨፈር አንድ ጠብታ ቅሬታ ወይም ቁስል መፍጠር አልነበረበትም ወይ?

በመጣሁ በሁለተኛው ቀን የፊታውራሪ ነጋሽ ልጅ ሞተ፡፡ ሽማግሌው ስሜታቸውን በምንም መንገድ አላሳዩም፡፡ እንደገናም ጀግና ሰው መሆናቸውን አስመሰከሩ፡፡

"ደህና ሁን ልጄ፡፡ አሁኑኑ እኔው እከተልሃለሁ" ነበረ ቃላቸው ያረፈውን የልጃቸውን ቅንድብ እየሳሙ፡፡ እኔም በዚህ አምልኮና ህሲናን በሚፈትሽ ሰአት ተካፋይ ነበርኩ፡፡



*የደጃዝማች አያሌው ተወካይና የሥንቅና ትጥቅ ሀላፊ የነበሩት ፊታውራሪ ተሻገር*

*በቤተሰቦቻቸው መልካም ፈቃድ*



# ምዕራፍ አሥራ ሶስት

## የአፍ ጋጋ ጦርነት

በእንዳባጉና በተደረገው ድርጊት ጠላት በንዴት የተቃጠለ ይመስላል፡፡ ከጠዋት እስከ ማታ ትልልቅ ባለ ሶስት ሞተር በምብ ጣይ አውሮፕላኖች ራስ እምሩና ደጃች አያሌው ያሉበት ካምፕ ላይ ሲያንዣብቡ ይውላሉ፡፡ ትልቅና ትንንሽ በምቦች የተገኘው ቦታ ላይ ሁሉ ይጣሉ ነበር፤ እኛም ከፍንዳታው ድምፅ ጋር ተላምደናል፡፡ ጉዳቱ መጠነኛ ነው የነበረው ምክንያቱም ጦሩ በሀያ ኪሎሜትር ካሬ ስፋት በየቦታው ተሠራጭቶ በየዋሻውና በየጉድጓዱ ተደብቆ ስለነበር ነው፡፡




*የሰማይ ላይ "ጭራቆቹ" የጣሊያን በምብ ጣይ አውሮፕላኖች በቡድን ሲበሩ*

በገበሬው ቤት ያሳለፍኳቸው ቀናቶች በሙሉ ነርቭ የሚሰቀጥጡ ነበሩ፡፡ ከረዥም ጊዜ በኋላ እሁን ረጋ ባለ መንፈስ ሆኜ ሳስበው እንዴት አድርገን እንደዚያ ያለ አእምሮ የሚበጠብጥን ነገር እንደተቋቋምነው ሊገባኝ አይችልም፡፡ በምቦች ቀረብ ባለ ቦታ ሲፈነዱ ወዳዘጋጀሁት መጠለያ

እየተንፏቀቅሁ እገባለሁ። መጠለያዬም በዕቃዎች በፍራሽና በኮርቻ መሀከል ነበር። በዚህ መንገድ ትንሽ ደህንነት ይለማኝ ነበር።

የድሬስሩ የፈጠነ ነገር ግን የባሰ ነበር። ደብረ አባይ እያለ ቦምብ ሲወርድ ሰላየ አውሮፕላን በጮኸ ቁጥር እርፎ መቀመጥ አይችልም ነበር። ላያስበው አየሮጠ አውሮፕላኑ ወዴት እንደሚሄድ ለማየት ይወጣና "ዶክተር እየመጣች ነው" "she is coming" ይላል። ፈጠነ ሲፈራ በእንግሊዝኛ መናገር ነው የሚቀናው። ደግሞ እየሮጠ ተመልሶ ይገባል። እኔም ድምፁን እጥፍቶ መጠለያው ውስጥ አጠገቤ እንዲጋደም ትዛዝ እለጠዋለሁ። እንደ ውሻ ነው የሚታዘዘው። ነገር ግን ወዲያው ተነስቶ ደግሞ መልሶ ይወጣል። እሱን እርፎ እንዲቀመጥና ዝም እንዲል ማድረግ አይቻልም።

በእንግሊዝኛ "ዶክተር እናታችን ላይ ናት። ርግጠኛ ነኝ የመጨረሻችን ቀን ነው! ምን ማድረግ ይሻለናል?" ማበረታታት ሆነ መገሠፅ ወይም መቅጣት ሊያቆመው የሚችል ነገር አይደለም። ተሰፋ ቢስ! የሚያደርገውን እንዲቀጥል መተው ይበጃል!

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እንደተጋደምኩ በሳቅ እንፈራፈራለሁ። የሚያደርገውን ነገር ማየት የሚያስቅ ነበር፤ ግማሽ ሰውነቱን ከበሩ ውጭ እድርጎ የአውሮፕላኖቹን እንቅስቃሴ ለመመልከት እንገቱን ግን ወደ በሩ ወደኋላ አጣሞ መሬት ላይ ይተኛል።

እኔም ብሆን በጣም ሲበዛብኝ አንዳንድ ጊዜ እየዳህኩ ወደ ሜዳው ወጥቼ በረዥም ሳሮች ውስጥ እደበቃለሁ። ፈጠነና ሌሎች ድሬሰሮችም እኔን ተከትለው ይወጣሉ። ንፁህ የሚነፍሰው አየርና የፀሀይዋ ሙቀት አእምሮየን ያረጋጋዋል። ድንገት ጎጆው ቢመታ ደግሞ ጎጆው ውስጥ እንዳለን አለመቀበሩም ሌላ ማረጋጊያ ጭምር ነው።

አውሮፕላኖቹ ሲሄዱ ተመልሰን ጤነኛ ሰዎች እንመስላለን ግን እስከሚቀጥለው ጊዜ ድረስ ነው።

ሌሎች ጉዳዮችና ሥራ ጊዜያችን ስለሚወስዱልን ሳቅና ጨዋታችን እንደተጠበቀ እንዲቆይ አድርገውልናል። ከመጠን በላይ የሆኑ ንብረቶችና ሌሎችም እቃዎች በእንዳባጉና ጦርነት ተገኝተዋል። የተለያዩ አይነት ዕቃዎች በየዋሻው ውስጥ ተደርድረዋል። የፍራፍሬ ጭማቂ ጠርሙሶች፣ ዶቄት፣ ስኳር፣ የሬድዮ ከፍሎች፣ መድሃኒቶች፣ ወይን በጠርሙስ፣ ዘይት፣ ቅቤ፣ መላሪያዎች፣ ጥጥ፣ የተጠበሰ ዳቦ በሣጥን፣ የአልጋ ልብስ፣ የስፓኒሽ ኮፍያዎች፣ አልጋ፣ ጋዜጣ፣ ብሎኖች፣ ልብሶች፣ መፅሀፍቶች በየዋሻው ተከምረዋል።



በተጨማሪም ሁለት አዲስ ግራማፎኖች፣ ሶስት ታይፕ መፃፊያዎች እና ሰላሳ የፎቶ ካሜራዎችም ነበሩ።

ወታደሮች በመጀመሪያ ማወቅ የፈለጉት ነገር ምግቦቹ መርዝነት እላቸው ወይም መበላት የሚችሉ መሆኑን ነው። እኔ እንድቀምሰላቸውና እንዳረጋግጥላቸው ይፈልጋሉ፤ ከቀመስኩ ደግሞ ከምግቡ ባለንብረት ፊት መሆን አለበት።

ወዲያውኑ ላረጋግጥላቸው አችል ነበር ምክንያቱም ጣልያኖቹ እስከመጨረሻው ሰአት ድረስ ምግቦቹን ይጠቀሙ እንደነበርና ሲለቁም በችኮላ ለቀው ስለወጡ ነው። ለማንኛውም ግን ለማረጋገጥ ብለን እንዱን አህያ ከዱቄቱ፣ ከሰኳሩና ከተጠበለው ዳቦ እንዲበላ አደርግን።

አህያውም ምንም እልሆነም ወታደሮችም ተረጋጉ

ከታሸጉት ምግቦች መሀል ወታደሮች የፈለጉት ላርዲኑን ብቻ ይመስላል። ሌሎቹን ለምሳሌ ሳልመን (የአሳ ዝርያ)፣ ስጋ፣ የተለያዩ ፍራፍሬዎች፣ ሎብስተር፣ ማርማላት የመለሰሉትን ለድካሜ ዋጋ የምቸለውን ያህል መውሰድ ቻልኩኝ። የቀረው ወደ እንድ ሺ የሚሆን ጣላ ለሽያጭ እንዲቀመጥ ሆነ።

እነዚህ ነገሮች ዋጋቸው ምን ያህል እንደሆነ ስለማያውቁ ወደ ሀኪሙ እየመጡ ዋጋቸውን እንድነግራቸው ይጠይቁ ነበር። አሁን መሸጥ መግዛትና እርስ በራሳቸው መነገድ ጀምረዋል። እዚህ ቦታም ቢሆን ሌላ ቦታ እንደሚደረገው ሁሉ የዕቃ ዋጋ እንደተፈላጊነቱና እንደዕጥረቱ ነው።

አንዳንድ በጣም የሚፈለጉ እቃዎች በመጠኑ ነው የተገኙት። በተቃሪኒው ደግሞ የማይፈለጉ ዕቃዎች በብዛት ይገኛሉ። በፍፁም አዲስ የሆነ ግራማፎን ("ማስተርስ ቮይስ የሚባል ስም ያለው) ከሶስት ሸከላዎች ጋራ ዋጋውን በአራት ማርትሬዛ ተመንኩት። ታይፕ መፃፊያዎች ያን የህል ጥቅምም አልነበራቸውም። ትልቅ ታይፕ መፃፊያ በሶለት ማርትሬዛ ገዛሁ። የኋላ ኋላ የዋጋዎችን ዝርዝር በፅሁፍ አዘጋጀሁ፤ አለዚያ እረፍት አላገኝም።

አንድ ቀን አንድ ወታደር ወረቀቶች በጁ ይዞ መጣና የምገዛው ከሆነ ጠየቀኝ።

አዎ በርግጥ ዋጋውን ከፍ ካላደረገ በስተቀር አገዛለሁ።

ሰውየው ለለምንት አንድ ሺ የጣልያን ሊሬ ኖቶች ሃምላ ማርትሬዛ ጠየቀ። ከሌሎች ከተዘረፉ ንብረቶች ጋራ የጠላት ካዝና ተገኝቷል፤ በውስጡም ብዛት ያለው የጣልያን ሊሬ ተገኝቶበታል።

እነዚህን በደንብ የተሣሉና የተዘጋጁ ወረቀቶች እውነተኛ ዋጋቸውን እስኪያውቁ ድረስ ብዙ ቀን ወሰደባቸው:: በመጀመሪያ ዝም ብለው በየሜዳው እየጣሉ ለነፋስ ይበቱናቸውም ነበር:: በኋላ ግን ትግራይ ውስጥ ባለንበት ጊዜ በሙሉ በነዚህ ወረቀቶች ሞቅ ያለ መገበያየት ነበረ:: በኔ ግምት ወደ ግማሽ ሚሊዮን የሚሆን ሊሬ በዚሁ ገበያ ሲዘዋወር ነበር::

ወታደሮችም በጦርነቱ ለዘረፉት ወይም ለያዙት ነገር በሙሉ እንዲከፈላቸው ፈለጉ ለመድሃኒቶች፤ ለቁስል መጠቅለያ ጨርቆች፤ መሳሪያዎች ጭምር:: ስለዚህ ደጃች አያሌው ገንዘብ እንዲሰጡኝ ጠየቅሁኝ:: እሳቸውም ሁለት መቶ ማርትሬዛ ላኩልኝና ለአገናኟቸው ዕቃዎች መግዣ ተከፋፈለ:: የነበረኝ የመድሃኒትና መሳሪያዎች መጠን ሲጨምር ሳይ ደስታዬ ከልክ ያለፈ ነበር:: አሁን ያለኝ የመድሃኒትና መሳሪያ መጠን ለወራት ያህል እንደሚያዳርሰኝ ነው፤ ነገር ግን ሁሉም አልነበርም ምክንያቱም ኤተር(ለማደንዘዣ የሚሰጥ) የሚባል መድሃኒት አንዲ ኪሎ ብቻ ነው የነበረኝ:: እራሴን ደግሞ የዚህ መድሃኒት ዕጥረት ቢኖርም በቁለል አካባቢ በሚሰጥ ማደንዘዣ እጠቀማለሁ ብዬ እረጋጋሁኝ:: አቢሲኒያኖች ደግሞ ህመም የመቋቋም ችሎታ ስላላቸው ለቀላል ቀዶ ህክምና ሥራ ማደንዘዣ አይፈልጉም ነበር::



ማርተሬዛ (ማርያ ቴሬዛ) በዚያን ጊዜ መገበያያ ገንዘብ በፊት ለፊትና ጀርባ

ደጃች አያሌው ገንዘቡን ሲልኩልኝ ጣልያኖቹ መሀል አገሩን በቦምብ መደብደብ እንደጀመሩ እስታውቀውኛል:: የደብረ እባይ ገዳም ከነሚያምረው ቤተክርስቲያኑ አመድ ሆኗል:: በየሁለቱ ቀን ዳባት በአየር ይደበደብ ነበር:: አሁን እርሻውን ሰፈሩንና መንገዶችን በቦምብ ይደበድቡ ጀመር:: በፀለምት አንድ ትንሽ ልጅ ያልፈነዳ በምብ አግኝቶ ጓደኞቹን ጠርቶ

"ይሀ አስቀያሚ ነገር ነው አባቶቻችን የሚገድል ኑ እንደብደበው"



በማለት ባለማወቃቸው በንዴት በድንጋይ እስኪፈነዳ ድረስ ደበደቡት:: እንግዲህ እነዚህ ንፁህ ትንንሽ ፍጥረቶችም የወራሪው መጥፎ መሳሪያ ሰለባ ሆነዋል::

በተጨማሪ ደግሞ ሶስት ፊታውራሪዎች ማለትም ተሻገር፤ ገሰሰ እና ሽማግሌው ሳይሆኑ ነጋሽ ከበለሳ ወደ ግንባር ጦር ወደ እፍ ጋጋ እንዲሄዱ መታዘዛቸውን ሰማሁ::

አፍ ጋጋ ወደ አክሱም ወደሚሰደው መንገድ ማለፊያ በር ነው:: የሚገኘውም በተከዜና በእንዳለላሴ የጠላት ምሽግ መሀከል ባለ ቦታ ነው:: እንግዲህ ጣሊያኖቹ ጥቃት ቢጀምሩ የመጀመሪያውን ጥቃት ሊቀበሉ ነው:: የፈለገው እመቺ ሁኔታና አጋጣሚ ቢፈጠርም ምንም አይነት ጥቃት እንዳይሰነዝሩ ተከልክለዋል::

ራስ እምሩና ደጃዝማች ለለወታደሮቻቸው አቀማመጥ የተለማሙ መሆናቸውንም ሰማሁ:: የራስ እምሩ ሰዎች ወደ አክሱም በሚወስደው መንገድ በምእራብ በኩል እንዲቆዩ፤ የደጃች አያሌው ሰዎች ደግሞ በምሥራቅ በኩል እንዲሆኑ ሆኗል:: በዚህ መንገድ ጥላቻ ስሜት እንዳይፈጠርና በሁለቱ ሠራዊት በኩል የማይሆን ከርከር እንዳይጀመር ነው::

አንድ ቀን ፀሀይ ሳትወጣ በሽተኞች እይቼ ወደቤቴ ስመለስ ሶስት የጣልያን ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች ድንገት እየሁ:: የገረመኝ ነገር ደግሞ ከአንደኛው አውሮፕላን ትልቅ ነገር ወደመሬት ሲጣል ቀስተደመና በመሰለ ህብረ ቀለም ተከትሎ በሚያፏጭ ድምፅ መሬት ላይ ወደቀ:: ወዲያውኑ ሰምተነው የማናውቀው አይነት የፍንዳታ ድምፅ ሶስት ጊዜ ሰማን:: ሌሎቹ ሁለቱም እውሮፕላኖች ተመሳሳይ ቦምብ ጣሉ::

እኔ እንዳየሁት ሁሉ ድሬሰሮቹም አይተዋል:: እኔም ይህ አዲስ ነገር ምን ይሆን ብየ አሰብኩ፤ የራሴ ጥርጣሬ ነበረኝ ግን እርግጠኛ አልነበርኩም::

ልክ እውሮፕላኖቹ እንደሄዱ ቦምቡ ወደ ተጣለበት አቅጣጫ ሮጥን:: የወደቀው ከኛ ቦታ ሶስት መቶ ሜትር ርቆ ከሚገኝ ትልቅ የእርሻ ቦታ ነው:: ልክ ከቦታው ለመድረስ ሲሶ መንገድ ሲቀረኝ ድንገት እንግዳ የሆነ የነጭ

ሸንኩርት ወይም መስታርድ ሽታ ሸተተኝ:: የትኛው እንደሆነ መለየት አልቻልም:: ለማንኛውም ግምቴ ልክ ነበር:: የጋዝ ቦምቦች ነበሩ::

"መርዝ! መርዝ!" እያሉ ሰዎች እየጮሁ ከሜዳው እየሮጡ ይወጡ ጀመር::

እኔም ዞሬ መሮጥ ጀመርኩ:: የነበረኝ የመርዝ ጋዝ መከለያ ጭምብል ቤቴ ውስጥ ግድግዳው ላይ እንደተንጠለጠለ ነበር::

አንድ የጋዝ ቦምብ ብቻ ነው መሀል እርሻው ላይ የወደቀው:: ሌሎች ሁለቱ ራቅ ብሎ ሜዳው ላይ ከእርሻው ማዶ ነው የወደቁት:: በውጤቱ ሰባት ሰዎች ሲሞቱ ዘጠኙ ቆሰለዋል:: ሁሉም የሞቱት የቤት አገልጋዮች ነበሩ:: አንድ ቤት ውስጥ ሆነው እህል እየፈጩ ዳቦ ይጋግሩ ነበር:: የመርዝ ጭሱ በከፍቱ በር በኩል በበቂ መጠን ገብቶ ሳንባቸውን በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ አቃጥሎታል::

ከቆሰሉት መሀል ደግሞ ሁለቱ አይነ ስውር ሆነዋል:: አንዱ ገና የአሥራ አራት አመት ልጅ ነበር:: በፍንጣሪውና በመርዝ ጋዙ ብትከትክ ብሎ ቆስሎ ስለነበር ከሳምንት በኋላ ሞተ:: የቀሩት የቆሰሉት ስድስቱ ቆይተው አገግመዋል::

ማስታወሻ መያዣ ካላንደሬ ጠፍቶብኝ ሊቀር ነበር ነገር ግን ከዚህ ድርጊት ከሁለት ቀን በኋላ አገኘሁት:: ቀኑን ሳየው የመርዙ ቦምብ የጣልያኖች የገና ስጦታ ነበር:: ቦምቦችን የጣሉት የገና ዋዜማው እለት ነው:: እኔም ትልቁ በአላችን መምጣቱ ትዝም አላለኝም ነበር:: የሃበሾች ገና ከአውሮፓውያን ገና አሥራ አራት ቀን ዘግይቶ ስለሚከበር እኔም እብሬ በዛው ቀን ባከብር ይሻለኛል ብዬ ወሰንኩ::

በአውሮፓውያን ገና የቀኑ ለት ጠዋቱኑ ከፊታውራሪ ተሻገር የተላከ ደብዳቤ ደረሰኝ:: የጣልያን ሬጅመንት አከሱምን ለቆ ወደ አፍ ጋጋ እየሄደ ነው:: ውጊያ የማይቀር ነገር ነው ስለዚህ ሁለት ድሬሰሮች ከመሳሪያና ቁስል ማከሚያ ቁሳቁስ ጋራ በአስቸኳይ እንድልክ ጠየቀኝ:: እኔም ወዲያውኑ ሁለት በቅሎ ጭነት ሙሉ ዓዝ አዘጋጀሁኝ:: ነገር ግን መንገድ ወዲያውኑ መጀመር አልቻልንም:: ምክንያቱም ሁለት አውሮፕላኖች በኛና በእንዳ ስላሴ መሀል ባለው ሜዳ ላይ እያንዣበቡ ነበር:: ተደራቢ ወይም ተጨማሪ ሀይል እንዳይሻገር እየከለከሉ እንደነበር ግልፅ ነበር:: ሆኖም ከአፍ ጋጋ በኩል ምንም አይነት የተኩስ ድምፅ ገና አልሰማንም:: እያቅማሙ ሁለቱ ድሬሰሮች አውሮፕላኖቹ ከሄዱ ከአንድ ሰአት በኋላ ሄዱ



ይህ ሁሉ ሲሆን ሽማግሌው ፊታውራሪ ነጋሽ የተረፉቸውን ጦር አሰባስበው ድንገት የሚፈስጉ ከሆነ በማለት የዘንባባ ዛፎች ጫካ ውስጥ ሆነው ይጠባበቃሉ:: የወታደሮች የውጊያ ፍላጎት ምንም አልቀነሰም ከምንም ጊዜ በላይ ያቅራሩና ይፎክሩ ነበር::

ከቀኑ ሰባት ሰአት የተኩስ ድምፅ ይሰማ ጀመር:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተከታታይ የተኩስ ድምፅ መሰማት ቀጠለ:: ውጊያው በሙሉ ሀይል እየተካሄደ ነው::

በሩቅ መነፀር ስመለከት የኛ ሰዎች በድንጋዮችና በዛፎች ጀርባ አድፍጠዋል:: ነገር ግን ሲተኩሱ ጉፍ እያለ ወደ ሰማይ የሚወጣውን ጭስ ሳይ በሚያሳዝን ሁኔታ አብዛኛው ጦር የያዘው መሳረያ ያለፈበት አሮጌ ሞዴል መሆኑ ትዝ አለኝ:: እንዲያውም በጭሱ ምክንያት የጠላት ኢላማ እንዲሆኑ ነው ያደረጋቸው::

አልፎ አልፎ ወታደሮች በቡድን እየዘለሉ ወደፊት ሲሮጡ ይታያል፤ ወይም የተለማመዱትን የከበባ ዘዴ ይሞክራሉ ሆኖም በየጊዜው ወደኋላ እንዲያፈገፍጉ ይገደዳሉ:: ጠላትን ማየት አልቻልኩም ምክንያቱም ቆየሳ ጋራ ጀርባ ተከልለው ነበር::

ብዙ ሰአታት አለፉ:: ከፊታውራሪ ተሻገር የተላከ ትንፋሽ የሚያጥረው ሰው እየሮጠ መጣ፤ የተላኩት ድሬሰሮች አልደረሱም ብሎ ነገረኝ:: መልከተኛውም ድሬሰሮቹን ከወንዙ ባሻገር ከሜዳው ሳይደርሱ ዛፍ ስር ተቀምጠው ያያቸው መሆኑን ጠቆመኝ:: የተረገሙ ፈሪዎች ህይወታቸውን ለማዳን ሀላፊነታቸውን ዘንግተዋል::

አስር ሰዎች ያሉበት አጃቢ ከፊታውራሪ ነጋሽ መጣልንና መንገድ ጀመርን:: ብዙ ኪሎሜትሮች ተጉዘን ከወንዙ ማዶ እንደደረስን አስፈሪ የሆነ የአውሮፕላን ድምፅና ፈንጂ መስማት ጀመርን:: በደንብ ለማየት ጋራ ላይ ወጣን::

አንድ በአንድ እየተከታተለ የአቧራ ጭስ ሽቅብ እንደምሰሶ ወደላይ ትጉልል ይልና ወዲያውኑ በየአቅጣጫው ሲፈነጣጠር እናያለን:: ሀያ ሰባት አውሮፕላኖች በዙሪያው እያንዣበቡ በየቦታው ድምሰሳና ጥፋት ያስፋፋሉ:: በተጨማሪ የኛ የቀዳሚው ጦር ስንቅና ትጥቅ ከፍል ሰዎች በሜዳው ሲሮጡ አየሁኝ፤ በአውሮፕላኖቹ ጥቃት እየደረሰባቸው ነበር:: ውጊያው ጨበጣ ስለነበር የራሳቸውን ሰዎች ላለመጉዳት አብራሪዎቹ ውጊያው ቦታው ላይ ቦምብ መጣል አልደፈሩም::

በዚህ ሁኔታ ውጊያው ወዳለበት ቦታ መቀጠል አልተቻለም፡፡ ከዛፉ ስር ያገኘኋቸው ድሬሰሮች ለራሳቸው መጠለያ እንዲፈልጉና ጓዙንም እንዲጠብቁ ትዛዝ ተሠጣቸው፡፡ እኔና አጃቢዎቼ ባየነው ነገር ፈዘን ጋራው ላይ ባሉ ቁጥቋጦች ስር ቆምን፡፡

አሁን ወደ ማለፊያው በር በመሄድ ቦታ እየያዘ ያለውን የጠላት ጦር ማየት ቻልን፡፡ አቢሲኒያኖች ደግሞ በእልከ መቋቋም ጀመሩ፡፡ አንድ ቡድን ጣልያኖችን ከጀርባ ለማጥቃት ወደ ቆየትሳ ተራራ ሲገሰግስ በብዙ የጣልያን አውሮፕላኖች ታየ ያም ሆኖ ተበታተኖ ግፊቱን ቀጠለ፡፡

አቢሲኒያኖቹ መሪ እንደጎደላቸው ማየት አችላለሁ በጭራሽ መሪ ያለም አይመስልም፡፡ በመቶ በመቶ ሰዎች ያሉባቸው ቡድኖች በየአቅጣጫው ይተራመሳሉ፤ ብዙ ጊዜም እርስ በራሳቸው ይተላለፉ ነበር፡፡

በሌላ በኩል ጣልያኖቹ ያለማቋረጥ ወደፊት ይገፉሉ፡፡ ተፋላሚዎቻቸው ኢትዮጵያውያኑ ጣልያኖቹን ከጀርባ ለመከበብና ለማጥቃት መንገዱን ከፍተውላቸው የሄዱ ይመስላል፡፡ ይህ ታኩቲከ ጠላትን ያሳሰበው ይመስላል፡፡ ነገር ግን የኛ ሰዎች ለረዥም ጊዜ ውጊያውን መቀጠል ይችላሉ ወይ?

"እህ! ተመልከት! ያ ምንድን ነው?"

እውሮፕላን በላያችን ላይ አለፈና ቁልቁል ወርዶ ከኛ የኪሎ ሜትር ርቀት ላይ አረፈ፡፡ ገና ሞተሩ ሳያቆም ሶስት ሰዎች ዘለው ወጡና ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ መሮጥ ጀመሩ፡፡

ወዲያውኑ ሌላ እውሮፕላን በላያቸው ላይ ከነፈ፡፡ ነገር ግን በራሱ እንደ እንዝርት መሽከርከር ጀመረና በአፍንጫው ተከሰከሰና ተገልብጦ በጀርባው አንደወደቀ በእሳት መያያዝ ጀመረ፡፡ ይህ ሁሉ በጥቂት ሰከንዶች ውስጥ ነው የሆነው፡፡ ገና ምንም ቃል ሳልተነፍስ የኔ አጃቢዎች የሚሮጡትን ጣልያኖች ለመያዝ ወደ ሜዳው መሮጥ ጀምረዋል፡፡ አነሱን ያዩ ሌሎች ደግሞ ተከተሏቸው፡፡ የጣልያን እውሮፕላኖች አሳዳጆችን ለመግታት በመሞከር አውቶማቲከ መሳሪያ በቅርብ ተጠግተው ይተኩሱና ቦምብ ይጥሉም ነበር፡፡ በማለፊያው በር ያለው የጣልያን አዛዥ ሶስቱ ጓዶቹ ያሉበትን አደጋ ይመለከት ነበር፡፡

ከዚህ ቀጥሎ አይቸው የማላውቀው አስደናቂ ትዕይንት ተፈጠረ፡፡ ወደ መቶ የሚሆኑ ፈረሰ ጋላቢዎች ከማለፊያው በር በኩል የአቧራ ጉም እያስነሱ መጋሰብ ጀመሩ(ቁጥራቸውን ወደኋላ ነው ያገኘሁት)፡፡ እንገታቸውን ወደ ፊት



ለግደድ አድርገው ሲከንፉ ፈረሶቹ መሬት ላይ የተኙ ነው የሚመስሉት፡፡ ጋላቢዎቹ ደግሞ ወይ የፈረሶች አንገት ላይ ተጋድመዋል፤ ወይም ፈረሱ ላይ ቆመው ወይ ወደኋላ ዞረው ተቀምጠው በግራና በቀኝ እየተኮሱ የጦርነት ጩኸት ያሰማሉ፡፡ ሌሎች ሳይሆኑ ካዛኮች ወይም የሰሜን አፍሪካ አረቦች ናቸው እንዲህ አይነት ግልቢያ የሚችሉት ብዬ አሰብኩ፡፡ ከትሪፖሊ (ሊቢያ) የመጡ ስፓሂዎች(ፈረሰኞች) ነበሩ፡፡




*(ስፓሂ ዴ ሊቢያ በሮማ ትርኢት በማሳየት ላይ ለያሉ የተነሳ ፎቶግራፍ እኤአ 1936. Sebastian O'kelly, Amedeo: A True Story of Love and War in Abyssinia) ለስባስቲያን አኬሊ መልካም ፈቃድ*

ሶስቱ የሚሸሹት ጣልያኖች ጋላቢዎቹን ሲያዩ ወደነሱ ሮጡ ወዲያውኑ ፈረሰኞቹን ተቀላቅለው ተሰወሩ፡፡ ጋላቢዎቹ ፍጥነታቸውን የቀነሱ በሚስልም ያቆመ ሰውም አልነበረም፡፡ ከዛም ትልቅ ከብ ሰሩና በመጡበት ፍጥነት ወደ አቢሲኒያኖች ተመለሱ፡፡ ትከ በማይገኝለት ድፍረት ሞትን ሳይፈሩ በመደናገጥ ከፈዘዙት አቢሲኒያኖቹ መሀከል ገብተው ማጥቃት ቀጠሉ፡፡ ማቆሚያ የሌለው ከሚመስል አንድ ሰአት በኋላ ጋላቢዎቹ ወደ ማለፊያው በር ተመለሱ፡፡

---

*እነዚህ ፈረሰኞች በደንብ ከሚታወቁት የፈረንሣይ ስፓሂዎች የተለዩ ናቸው፡፡ ለዚህ ነው ስፓሂ ደ ሊቢያ ተብለው የሚጠሩት፡፡ ኢጣልያኖች ኢትዮጵያን በወረሩበት ጊዜ ይህን የሊቢያ የፈረሠኛ ቡደን መጠቀማቸው ተዘግቧል፡፡ ጣልያኖች በአፍሪቃ ከነበሯቸው ቅኝ ግዛቶች አንዱ ሊቢያ ነበር፡፡*

ጣልያኖቹን አድነዋቸዋል ግን አምስት አረቦችና ፈረሶች ሜዳው ላይ እንደተጋደሙ ቀርተዋል፡፡ የአረቦቹ ጋላቢዎች ላይ የነበረውን ትኩረት ለመቀነስ ቃኝ የአስካሪስ ወታደር ቡድን በሜዳው በግራ በኩል ሄዷል፡፡ ነገር ግን በሁሉም አቅጣጫ ተከበ ነበር፡፡ ሌላ ተጨማሪ ቡድን ደርሶ ባያስጥላቸው ሙሉ በሙሉ ይደመሰሱ ነበር፡፡




*በሰባሰቲያን ኦኬሊ (Sebastian O'Kelly) መልካም ፈቃድ*

*አሜዲዮ የተባለ የጣልያን መኮንን ከአጃቢ ስፓሂው ጋር በፈረንጆች በገና ማግስት የተነሳው ፎቶግራፍ፡፡ ይህ ሠው ከሊቢያ ሁለት ሺ የሚሆኑ እነዚህን ፈረሰኞች ይዞ ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱ በመፅሐፉ ተዘግቧል፡፡ መኮንኑ በሰለህለህ አጁ ላይ እንደቆሰለም ተዘግቧል፡፡ በዚህ ውጊያ ኢትዮጵያዊ ተዋጊ ሰውየውን ከፈረሱ ላይ አውርዶ ለመጣል ያደረገውሙከራ አልተሳካለትም፡፡ መኮንኑ ለኢትዮጵያውን ተዋጊዎች አክብሮት እንዳለው አሜዲዮን በቅርብ ከሚያውቀው ከመፅሀፉ (Amedeo: A True story of Love and War In Abysisinia) ደራሲ (Sebastian O'Kelly) ጋራ ባደረግነው ልውውጥ መረዳት ችለናል፡፡*



ከባድ ውጊያ ቀጠለ፡፡ ብዙ የጣልያን መኮንኖች ሞቱ፤ የጠላት ጦርም ተበታትኖ ወደኋላ ማፈግፈግ ጀመረ፡፡በዚህ ሰአት ከተራረው ጀርባ የሄደው የአቢሲኒያኖች ጦር ከጀርባ ያጠቃ ይመስላል ምክንያቱም ጨለማው ሳይመጣ ጣልያኖቹ ማለፊያ በሩን ትተው ሸሽተዋል፡፡ ከዚያ ከግማሽ ሰአት በፊት የመጨረሻው አውሮፕላን ተመልሶ ሄዷል፡፡




የስፓሂ ዲ ሊቢያ ፈረሰኞች የጣልያን እግረኛ ጦርን እየመሩ
(በሲባስቲያን ኦኬሊ (Sebastian O'Kelly) መልካም ፈቃድ)

አቢሲኒያኖች ማታውኑ በዚያው ቦታ አደሩ

የውጊያውን የተለያየ ደረጃ ሰከታትል ተመስጬ ሰለነበር ሰለራሴ ምንም ሳላስብ ብቻዬን መቅረቴን አላስተዋልኩም ነበር፡፡ አጃቢዎቼ አልተመለሱም ድሬሰሮቹም የት እንደሄዱ አላወቅሁም፡፡ ወደ ቦታዬ ብቻዬን መንገድ መጀመሩ ራሰን ከመግደል ነው የሚቆጠረው በዚህ ግርግር ሰአት ብቻውን የሚጓዝ ነጭ ሰው ከታየ ሰመተኮሰም የሚያቅማማ አይኖርም፡፡

ያለሁበት ቦታ ሌሊቱን ማሳለፍ ነበረብኝ፡፡ ሲነጋ ሰው እኔን ፍለጋ መምጣቱ አይቀርም፡፡ በቅጠሎቹና በቅርንጫፎች መኝታ አዘጋጅቼ ወዲያውኑ ተጋደምኩ፡፡ እሳት ሰማንደድ አልደፈርኩም፡፡ እንቅልፌ አልመጣም ነገር ግን አልተሰላቸሁም ነበር፡፡

ሀሳቤ ቀን በሆነው ነገር ላይ ነበር በተለይ ከጣልያኖቹ በኩል ፈረሰኞቹ ተአምረኛ በሆነ መንገድ ጣልያኖቹን ያዳኑበት ሁኔታ:: እኔ እንኳን ፈረስ የምወድ ሰው አይደለሁም::

ከጥዋቱ ሶስት ሰአት ሲሆን የሆነ ሰው "ሀኪም" ብሎ ሲጣራ ሰማሁ:: የተከበሩት ሽማግሌ ፊታውራሪ ነጋሽ ራሳቸው ነበሩ:: እንደሳቸው አባባል ከሞት ሊያድኑኝ ነው የመጡት:: በውጊያው ሳቢያ ሁሉም ሰው ረሰቶኛል::

አውሮፕላኖች በጊዜ መጥተው በጦርነቱ ሰምን እንዳልተካፈሉ ማሰብ ጀመርን:: ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት አስከሚሆን አልመጡም:: ከብዙ ቀናት በኋላ ሰላዮቻችን ሲመለሱ ምክንያቱ ግልፅ ሆነልን:: እኔም ከጦርነቱ በኋላ ሁለት የኢጣልያ መኮንኖችን አነጋግሬ ሁኔታውን አረጋግጫለሁ:: የገና ሰት ጠዋት ሰባት ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች ሙሉ ቦምብ እንደጫኑ ከአከሱም ወደ አፍጋጋ እንዲበሩ ታዘዋል:: ሲድሰቱ ተጭነው ነበር ሰባተኛውን ለመጫን ዝግጅት በሚደረግበት ጊዜ አንድ ነገር ተፈጠረ:: ሁኔታው በትክከል እንዴት እንደሆነ አየታወቅም ነገር ግን የሚባለው አንድ ሰው ቦምብ መሬት ላይ ጥሎ ፍንዳታ ተጀመረ:: ጥቂት ደቂቃዎች ዘግየት ብሎ ሁሉም በቦታው የነበሩት ሰባቱ አውሮፕላኖች ወደ ሰማይ ተነሱ በዚህ ጊዜ ግን ወደፊት ሌላ ጉዳት እንዳያደርሱ በፈንጂው ብትንትን ብሰው ነው::



# ምዕራፍ አሥራ አራት

## ዘንዶ

ጣልያኖቹ በገና ቀን በአፍ ጋጋ በተደረገው ውጊያ መሸነፋቸውን ለማመን አልፈለጉም:: ይሄ ደግሞ የሚያስገርም አይደለም በተለይም የጣልያኖቹ አዛዥ ጀኔራል ዲ ቦኖ ታህሳስ ስለ እንዳባጉና ውጊያ በሚገርመው መረጃ አይን ሲታይ ጀኔራሉ ባስተላለፈው መልከት ከሁለት ቀናት ከባድ ውጊያ በኋላ ጠላት እንዲሸሽ ተደርጓል ብሎ ፅፎ ነበር::

በርግጥ ከሆነ ጣልያኖቹ በመጥፎ ሁኔታ ነው የተጎዱት:: ለዚህ ደግሞ ምንም ጥርጣሬ የለም:: አለዚያ ለምን የዚያኑ ቀን ወደኋላ ወደ አከሱም ተመለሱ? ከዛ በኋላም ለድፍን ሁለት ወራቶች ከአከሱም ውጭ አልወጡም:: ታከቲካዊ ሽሽት ነው ብሎ መናገርም የውነት አይመስልም፤ ምክንያቱም ሀያ መኮንኖቻቸውና ከመቶ በላይ የሚሆኑ ሰዎቻቸው ሞተዋል:: በተጨማሪ ደግሞ ስድሰት መትረየሶች፣ ሀያ ሁለት ቀላል አውቶማቲከ መሳሪያዎች፣ ወደ ሁለት መቶ የሚሆኑ ጠመንጃዎች፣ አሥራ ሁለት ሳጥን ሙሉ ጥይትና ሌሎችም ነገሮች ጥለው ባልሄዱና አቢሲኒያኖቹም ባልዘረፉት ነበር::

በኛ በኩል ደግሞ መቶ አሥራ ስምንት ሰዎች ሲሞቱ ሁለት መቶ ሰዎች ቆሰለዋል::

ጣልያኖቹ ሲሸሹ አቢሲኒያኖቹ አላሳደዷቸውም ነበር ምክንያቱም ወዲያው ጨልሞ ነበር:: በተጨማሪ ግን የነሱ ትጥቅና ስንቅ ጓዝ የሚይዘው ወገን ወደኋላ ይጎትታቸው ስለ ነበር ነው:: አውሮፕላኖቹ በተደጋጋሚ ስንቅና ትጥቁን የሚያጓጉዘውን ከፍል ይደበድቡ ነበር:: ወታደሮችም ይህን አስተውሰው ስለነበር በጉዳዩ በጣም ተጨንቀው ነበር:: ምናልባትም ወይ ሚስት ወይ ልጅ አለዚያ ታማኝ አሽከር ቆስሎ ሊሆን ይችላል:: ታዲያ ሰዎቻቸውን ወይም ንብረታቸውን አንይ ቢሉ አሁን ማን ያማቸዋል? ውጊያው እንደሆነ አልቋል::

ፊታውራሪ ተሻገርና ፊታውራሪ ገሰሰ ያስ ፊታውራሪ ነጋሽ (የበለሳው) ርዳታ የጠላትን ጥቃት ብቻቸውን ባይጋፈጡ ኖሮ የጣልያኖች ሽንፈት በጣም ግልፅ ይሆን ነበር ፡፡ ዕቅዱ ፊታውራሪ ነጋሽ ለእርዳታ እንዲደርሱላቸው ነበረ፤ ግን የራሳቸው የሆነ ችግር አጋጥሟቸው ለሰዎቹ ሳይደርሱላቸው ቀሩ፡፡ የሰጡት ምክንያት ቆየሳ ተራራ ያለ ማስፈያን መጠበቅ ነበረባቸው ምክንያቱም ጠላት በዚያ እንዳይመሽግ ለመከላከል ነበር፡፡ ነገር ግን ጓደኞቻቸው ምክንያቱን አልተቀበሉትም፡፡

ነጋሽ የበለሳው የጦር አዛዥነታቸውን እንደያዙ እንዲቆዩ ቢደረግም መላው ጦሩ ስለሰውየው ያለው አስተያየት ግን ሌላ ነበር፡፡ ከሀዲ ነው ባይባሉም የተረገመ ፈሪ ነው ብሎ ፈርጆባቸዋል፡፡ ከዚህ ቀደም ጀግና ነው ተብሎ የሚታወቀው ይህ ሰው በስሙ ላይ የተፈጠረውን ይህን ጥቁር ነጥብ ማስለቀቅ አለበት፡፡ ይህ ደግሞ የሚሆነው በጀግንነት ተዋግቶ በማሳየት ነው፡፡ በአብዛኛው በራሳቸው ጥያቄ የግንባር ጦር መስርተው አዳጋ ሰኞ በተባለ ከዚህ ቀደም በጠላት ተይዞ በነበረ ቦታ እንዲጠባበቁ ተወሰነ፡፡ ቦታው ከአፍ ጋጋ ሰሜን ከአክሱም አስር ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው የሚገኘው፡፡

በሚቀጥለው ቀን የአየር ድብደባው የከፋ እንደሚሆን ለኛ ግልፅ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ያለኝ የመድሃኒቶች ጓዝ በሙሉ በሌሲት ሽማግሌው ነጋሽ ወደ እዘጋጁልኝ ትንሽ ዋሻ እንዲወሰድ ተደረገ፡፡ ያለውን እቃ በሙሉ ፀሀይ ከመውጣቷ በፊት እጓጉዘን ጨርሰናል፡፡

ለራሴ ጥሩ መጠለያ በማግኘቴ ውጭ ምንም አይነት ነገር ቢደረገም በደንብ ማረፍና መተኛት እችላለሁ፡፡ ቀኑ ከመጀመሩ በፊት ሁለት ድሬሰሮች አዲስ የቆሰሉ ሰዎችን እንዲረዱ ልኬ ለከትትል ደግሞ ማምሻውን እኔ ራሴ ለመሄድ አቀድኩኝ፡፡ በዚያን ጊዜ ቁስለኞቹ የት እንደሆኑም አላውቅም ነበር፡፡

አውሮፕላኖች አልዘገዩም፡፡ አምስቱ ከጠዋቱ አንድ ሰአት ሲሆን እየበረሩ መጡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ጠቅላላ የውጊያ ስፍራውን ቦምብ በቦምብ አደረጉት፡፡ ቆስለው የወደቁ የራሳቸውን ሰዎች ለመጨረስ የፈለጉ ይመስላሉ፡፡

ከዚሁ በኋላ ጠቅላላ ሽሬን ያለማቋረጥ እስከሚመሽ ድረስ በቦምብ ደበደቡ፡፡ ያን ቀን በላያችን ላይ የወረደውን የብረት ቁራጭ መጠን ማወቅ የሚያጓጓ ነበር፡፡

የአየር ድብደባው ውጤት

የሞቱ፡ ስምንት አህዮች፤ አንድ በቅሎና ሶስት ላሞች



የቆሰሉ ሁለት ወታደሮችና ሶስት ሴቶች (ሴቶቹ የተመቱት እየሮጡ ወደ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሊገቡ ሲሉ ነው)

ደጃች አያሌው የሞቱና የቆሰሉ ቁጠር ዝርዝር እንዲላክላቸው ጠይቀው ሰለነበር እነዚህን ቁጥሮች ትክክለኛ ነበሩ፤ እኔ ራሴ ነበር ያረጋገጥኳቸው፡፡

በፊት እኖርበት የነበረው እርሻ ቦታ ያሉት ጎጆዎች በዚህ ቀን አልተነኩም ነበር ነገር ግን ከሳምንት በኋላ አጠገባቸው የወደቀ ቦምብ ሲፈነዳ ጎጆዎቹ ብትንትን ብለዋል፡፡ አጋጣሚ ሆኖ በቦታው ማንም ሰው አልነበረም፡፡ በአሥራ ሰባት ምሽት ወደ ሁለተኛው የቁስለኞች ካምፕ ተንቀሳቀስኩ፡፡ ቦታው ከቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ቀረብ ብሎ በምሥራቅ አቅጣጫ ኪሎ ሜትሮች ይርቃል፡፡ በዚህ ቦታም ያሉት ዋሻዎች በሙሉ ስለተወሰዱ ለራሴ መጠለያ የሚሆን ወደ ገደሉ በኩል ወጣ ካለ አለት ስር ማድረግ ነበረብኝ፡፡ ቦታው ከመጠን በላይ ባደጉ የጫካ ፅጌረዳዎች ተሸፍኗል፡፡ ማታውኑ በእንጨት በድንጋይና በአፈር አድርገን በጎኑ በኩል ግድግዳ ሠራን፡፡

ለቦምብ መጠለያ የሚሆን አድርገን ሠርተነዋል፡፡ ለሥራ ግን በፍፁም የማይመች ሁኔታ ነው ያለበት፡፡ የክፍሉ ስፋት ሀያ አራት ካሬ ሜትር ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለክሊኒክ ሥራ፤ እቃ ማስቀመጫ እና መኝታ ቦታ ሊሆን ነው፡፡ ሙሉ በሙሉ ቀጥ ብሎ ለመቆም አይቻልም ምክንያቱም ከወለሉ እስከጣራው ድረስ ያለው ከፍታ አንድ ሜትር ተኩል ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ጦርነት ጦርነት ነው እኔም ለራሴ መጠለያ እስካገኘሁ ድረስ ደስተኛ መሆን እንዳለብኝ ተምሬያለሁ፡፡ ከውጭ ሰማዩን እያየሁ እተኛ ነበር፤ አሁን ግን ያም አይቻልም ምክንያቱም ቅዝቃዜው በዚያን ጊዜ በረዶ መፍጠር ደረጃ ድረስ ይወርድ ነበር፡፡

በአፍ ጋጋ ከቆሰሉት ሰዎች መሀል አብዛኞቹ አግራቸውን ነበር የተመቱት፡፡ የሚገርም ነገር ነው ምክንያቱም ሁለቱም ተፋላሚ ወታደሮች ከመቶ ሜትር ርቀት ባልበለጠ ተጠጋግተው ነበር፡፡ ስለዚህ በመሀከላቸው በነበረው ርቀት ጥይት ዝቅ ብሎ አግራቸውን ለመምታቱ በቂ ምክንያት አልነበረም፡፡ ፊታውራሪ ገሠሠ ሁለት አግራቸውን ተመተው ነበር ቁስሉ ግን ወዲያው ዳነ፡፡

የጣልያኖች ጥይቶች ብዙ ጉዳት የማያደርሱ እንደነበር መቀበል ወይም ማመን አለብኝ፡፡ ጣልያኖች የሚይዙት ሞዴል 91 ሌሎች አገሮች ከሚይዙት

መሳሪያ ጋር ሲወዳደር አነስተኛው ካሊበር ነው ያለው ሆኖም ግን ከመጠን በላይ ባሩድ ነበር ያለበት፡፡ እነዚህ ጥይቶች በስጋ ውስጥ እንደመርፌ ሾልከው ሲሄዱ፤ ምንም ስብራት ሳያስከትሉ በአጥንቱ ውስጥ ሰርስረው እንደገናም በደረት ውስጥ ከአንዱ ጎን በሌላው ጎን ከፍተኛ ጉዳት ሳያደርሱ አልፈው ሲሄዱ አይቻለሁ፡፡ ተዋጊ አገሮች የግድ መዋጋት ካለባቸው ሌሎች የሚቃወሙ ሰዎች ማለት የሚፈልጉትን ቢሉም ሌላው ቢቀር አነስተኛ ካሊበር ያላቸው መሳሪያዎች መጠቀም ይችላሉ፡፡ በዚህ ምክንያት የሚቆስሉ ሰዎችና የቁስሉ መጠን ወደ ሚቻለው ዝቅተኛ ቁጥር ሊወርድ ይችላል፡፡

የአቢሲኒያኖችን ህመም መቋቋም ችሎታ ማሳየት በሚችል አንድ ጥሩ ምሳሌ በቀኝ ጆሮው በኩል የቆሰለ አንድ ወታደር አከምኩኝ፡፡ ጥይቱ ከላይኛው አገጭ ስር አልፎ ከጆሮ መግቢያ በኩል ባለ ማስቶይድ በሚባል አጥንት ውስጥ ተቀርቅሯል፡፡ እኔ ማየት የምችለው ነገር ቢኖር የጥይቱን ግማሽ ብቻ ነው፡፡ ጥይቱ በጆሮው ቀዳዳ በኩል ከውስጥ ዘልቋል፡፡

ጥይቱን ለማውጣት ማደንዘዣ መስጠት ነበረብኝ፡፡ ነገር ግን በፍፁም ፈቃደኛ አልነበረም አልፈለገውም፡፡ ከዚያም ማደንዘዣውን በመርፌ ጆሮው አካበቢ ለመጠቀም ፈለግሁ፡፡ እሱም እንዴት እንደሚሰራ ማወቅ መፈለጉን ተናገረ፡፡ እንግዲህ ወደ ጥይቱ ለመድረስ በቢላዋ በጆሮው ቀዳዳ በኩል መቁረጥና ቦታውን ማስፋት ነበረብኝ ነገር ግን ልክ ቢላዋውን ሳነሳ በተቃውሞ

"ቢላዋ አደገኛ ነው" በቀላሉ እንጎሉን ሊወጋው ይችላል አለ፡፡

በጥንቃቄ ነው የሚሰራው ብዬ ቃል ብገባም ምንም አልረዳም፡፡

ስለዚህ በመቀስ በጆሮው ቀዳዳ በኩል ቆርጬ በጥርስ መንቀያ ጉጠት ጥይቱን ማውጣት ቻልኩኝ፡፡ ይህ ሁሉ የሚያሰቃይ ሥራ ሲሰራ፤ በኋላም የተቆረጠው ሰውነት ሲሰፋ ወታደሩ ምንም አይነት የህመም ስሜት አላሳየም፡፡ ልክ ኦፐሬሽኑ ወይም ቀዶ ህክምናው ሲያበቃ "በጣም ጥሩ ነገር ነው" የሚል ቃል ብቻ ነው የተናገረው፡፡

በዚህ በነበርንበት አዲስ ቦታ በሶስተኛው ቀን ፀሀይ እየሞቅሁ በመርዝ ጋዝ ምክንያት ሲታወር ከደረሰ ወታደር ጋር እያወራሁ ነበር፡፡

"ዶክተር! እባክህ ናልኝ! ሊገለኝ ነው"



ድንገት ፈጠና ከዋሻው ውስጥ ሆኖ ሲጮህ ለማሁት

ሽጉጤን ውስጥ ትቼው ነው የወጣሁት፡፡ እንደ በሽተኛ የያዘውን ዱላ እየሁና ከእጁ ነጥቄ ወደ ውስጥ ገባሁ፡፡ ወደ ውጭ መውጣት ከሚፈልግ ዘንዶ ጋር ፊት ለፊት ግጥም አልኩ፡፡ እኔን ሲያየኝ ተመልሶ ገባና በግድግዳውና በጣራው ባለ ከፍተት ውስጥ ለመደበቅ ሞከረ፡፡ በሀይለኛ ምት ጀርባውን ግማሽ ወገቡ ላይ መታሁት፡፡

በቅፅበት ዞረና ሰውነቱን ወደላይ ከፍ አድርጎ ወደ ዱላው መጣ፡፡ ጭንቅላቱም ጣራው ድረስ ደርሷል፡፡ አይኖቹ ያበራሉ፤ ምላሱ ከአፉ ውስጥ ብቅ ጥልቅ ይላል፤ በንዴት የሚያሰማውን ድምፅ መስማት እችል ነበር፡፡ በዋሻው ከፍታ ምክንያት ራሴን ዝቅ ማድረግ ስለነበረብኝ ግማሽ ሜትር በማይሞላ ርቀት አይን ለአይን መተያየት ጀመርን፡፡ ዘንዶው ለሕይወቱ እንዳልሳሳ ምንም ጥርጣሬ አልነበረም፡፡ በጅራቱ እግሬ ላይ መጠምጠም ሲጀምር ይታወቀኛል በጣም የፈራሁት ነገር ግን በጭንቅላቱ ራሴን ቢመታኝና ነብሴን ለቼ ብወድቅ ነው፡፡

ይህን ሀሳብ እንደጀመርኩ ወዲያውኑ ኩጉልበቴ ዝቅ በማለት በሀይለኛ ምት ራሱን መታሁት፡፡ ዱላው ከፈለግሁት በታች ዝቅ ብሎ አረፈ ግን አንገቱን ለመስበር በቂ ነበረ፡፡ እንዳለ ሰውነቱ ወለሉ ላይ ዘፍ አለ፡፡ ዋናው ጂምናስቲክ የመጣው ግን ከዚህ በኋላ ነበር፡፡ ተለጣጭ ሰውነቱ እንደ ጅራፍ በዚያች ጠባብ ክፍል ወዲያና ወዲህ ይወናጨፍ ጀመር፡፡ መድሃኒቶቹ በየቦታው ተበተኑ፤ እግሮቼም እንደተጠለፉ ናቸው እና እኔም የሚያሙለጨለጭ ቀዝቃዛ ሰውነት ላይ ወደቅሁኝ፡፡ ቢሆንም በዱላ ድብደባዬን ቀጠልኩ በመጨረሻም ልገድለው ቻልኩኝ፡፡

ይህ ሁሉ ውጊያ ሲካሄድ ፈጠነ ዋሻው ውስጥ የሚችለውን ያህል ርቆ ጥግ ይዞ ቆሞ በፍርሃት የተነሳም ደንዝዞ ነበር፡፡

ሌሎቹ ዱላውንና ትርምሱ ሰምተዋል ያሰቡት ግን በዱላ ፍዳውን የሚያይ ሰው አለ ብለው ነበር፡፡ ቅጣቱን የሚቀምሰው ሰው ማን እንደሆነ ለማየት ወደ ውስጥ መመልከት ጀመሩ፡፡ እኔን ለመርዳት ወደ ውስጥ መግባቱ ግን ትዝም አላላቸውም፡፡ እውነት ነው የኔ የግል ጠባቂ እግሬን ለማስለቀቅ ሞክሮ ነበር ግን በጣምም አልጣረም እንደገናም እልተላካለትም ዋናው ሃሳብ ዘንዶው ካየለ ለመታገል መዘጋጀት ነበር፡፡

የሀኪሙ ገድል በካምፑ ውስጥ ወዲያው ተሠራጨ፡፡ ሰዎችም ለማየትና እንኳን ደስ ያለህ ለማለት ይጎርፉ ጀመር፡፡ አዛዡ ሳይቀር አንድ ጠርሙስ

ሻምፓኝ ላኩልኝ፡፡ ሻምፓኙን ግን ለሌላ ለበለጠ በአል ብዬ አስቀመጥኩት፡፡ ለመጪው አዲስ አመት ማክበሪያ፡፡

ዘንዶው ሙሉ በሙሉ ያላደገ ገና ወጣት መሆኑ ታወቀ፡፡ ውፍረቱ የክንድ ያህል ሲሆን ርዝመቱ ደግሞ 4.1 ሜትር ነበር፡፡ ከአልጋዬ ስር ተጠቅሎ ተኝቶ ሰንብቶ ነበር፡፡ ሲርበው ነው ከዋሻው ሊወጣ የነበረው፡፡

ታህሣሥ 21 ለኛ በጣም አስቸጋሪ ቀን ነበር፡፡ ለሁለት ሰአታት ሶስት አውሮፕላኖች በካምፓችን ላይ እያንዣበቡ ቦምብ ይጥላሉ፡፡ ዋሻው ውስጥ ተኮራምተን በራሳችን ላይ ፍራሽና ጆንዴ አድርገን ተኝተን ጆሮ የሚበጥሰውን ድምፅ እንሰማለን፡፡ የቦምብ ፍንጣሪዎችና ድንጋዮች ወደ ውስጥ እንደዝናብ እየገቡ ግድግዳውና የመጠለያውን ጎን ይመቱ ነበር፡፡ እንደጉም የሆነው የአቧራው ክምር ለመተንፈስ አስቸጋሪ ሁኔታ ፈጠረ፤ በኋላም ሸፈነን፡፡ ሁሉም ነገር ውፍረት ባለው የአቧራ ሽፋን ተሸፈነ፡፡

በደንገት አንድ ሴት ሰትሮጥ ገባች፡፡ የለበስነውን ገፋ በመሀከላቸን ዘላ ገባች፡፡ ሰውነትዋ ይንቀጠቀጥ ነበር፤ ታለቅሳለች፤ በመሀል ደግሞ ትስቃለች፡፡ ደግማ ደጋግም እጄን ጥብቅ አድርጋ ይዛ

"ሐኪም! አድነኝ!" ትላለች፡፡

የቦምብ ድንጋጤ (Bomb shock) ይዟታል፡፡ ለፈጠነ ይህ የመጨረሻው ነገር ነበር፡፡ አልቻለም፡፡ እየጮኸ ድንገት ተነስቶ ዘሎ ወጣ፡፡

ቦምብ ድብደባው እቁሞ ሰለነበር እኔም ተነሳሁና አቧራውን አራግፌ ምን እንደሆነ ለማየት ወጣሁ፡፡ የታፈነ ጩኸት ከመስማቴ በፊት በየቦታው ፈለግሁ፡፡ ከገደሉ ስር የአንድ ሰው መቀመጫውንና የሚንፈራፈሩ ጥንድ እግሮቹን እያለሁ፡፡ ጠጋ ብዬ ስመለከት የፈጠነ እግሮች ናቸው፡፡ ከመጠን በላይ በነበረው ፍርሃት የተነሳ በአለቶች መሀከል ባለ ሰንጥቅ ውስጥ እየተሳበ መግባት ፈልጓል፡፡ ጭንቅላቱን ከንድና እጆቹን ከትከሻው ጋራ ማስገባት ችሏል ነገር ግን ከዚህ በኋላ ተጣብቆ ቀረ፡፡ ወደ ውስጥ መግባትም ሆነ ወደኋላ መውጣት አልቻለም፡፡

ከሌሎች ጋራ በመተባበር ወደ ጎን ካዞርነው በኋላ በሰንት መከራ አወጣነው፡፡ ሸሚዞቹ ተቀዳደዋል፤ ክርኖቹ ትከሻዎቹና ጎኑ ተላልጠው ደም በደም ሆነዋል፡፡ እንዳለው ከሆነ መጀመሪያ ራሱን ሲያስገባ ተረጋግቶ ነበር፡፡ ጭንቅላቱ ከገባ በኋላ ግን በሃሳቡ ዘንዶ ውስጡ ቢኖርስ ብሎ ማሰብ ጀመረ እና ለመውጣት ሲሞክር ተቀርቅሮ በመቅረቱ አሰቃቂ ስቃይ ደረሰበት፡፡



የዛን ቀን ቦምብ ድብደባ የስድስት ሰዎች ህይወት ከብዙ ከብቶች ጋር ወሰደ በተጨማሪም ብዙ ሰዎች ቆሰለው ነበር፡፡

ማታውኑ በጨረቃው ብርሃን ደጃዝማች እያሴው ራሳቸው መጡ፤ የደረሰውን ጉዳት ለማየትና የቆሰሉትን ለመጎብኘትና ሰላምታ ለመሰጠት ነበር፡፡ ለሁሉም ለቆሰሉት ሰዎች ስጦታ የሚሆን ገንዘብ፣ ልብስ፣ ትኩስ ዳቦ፣ ወተት፣ ጠላ፣ ጠጅ የመሳሰሉት ይዘው መተዋል፡፡ ከሳቸው ጋራ አብረው እየዞሩ እያንዳንዱን ቁስለኛ በመልካም ቃላት በጓደኝነት ሲያናግሩ ማየት ልብ የሚሰብ ነገር ነበር፡፡ እያንዳንዱ ሰው እንዴትና የት ቦታ ላይ እንደቆሰለ ለመዳን ምን ያህል ጊዜ እንደሚወሰድበት ከዚያ በኋላስ ቋሚ የአካል ጉዳት ይደርስበት እንደሆን ማወቅ ይፈልጉ ነበር፡፡

የነበርኩበትን መጠለያ ከተመለከቱ በኋላ ሁለት ዋሻዎች ያሉበት መጠለያ ለራሴና ለመስሪያ እንዲሆን እንደሚያገኙልኝ ቃል ገቡልኝ፡፡

በታህሳሰ ህያ ሰምንት በጥዋቱ ሰሜን በሚጣራ ሰው ድምፅ ነቃሁኝ፡፡ የኪብር ዘብ ወይም የዘቦቹ አለቃ ፊታውራሪ ነበር፡፡ ማወቅ የፈለገው ነገር ትናትናውኑ ከሰአት በኋላ አውሮፕላን ላይ መተኮሱን አይቼ እንደሆን ነው፡፡

አዎ በርግጥ አይቻለሁ

ከዚያም የመጨረሻውን ጥይት እንደተኮሰባት ወዲያው ጅራትዋ ተገንጥሎ ሲወድቅ እንደተመለከተ ነገረኝ፡፡ ኮማንደሩ የሚነግረኝ አውሮፕላን ተኩሶ እንደጣለ ነው፡፡ ሁለት ሰዎችም ወደቀ የተባለውን ጅራት ሊያመጡ ወተዋል፡፡ በኋላም በእውነትም ሁለት ግዙፍ አገልጋዮች ያልፈነዳ ቦምብ ይዘው መጡ፡፡

በጥንቃቄ ወለል ላይ እንዲያስቀምጡት ነገርኳቸውና ፊታውራሪውን ጅራት የተባለው ነገር ምን እንደሆነ ነገርኩት፡፡ ለማሳመንም ጋዝ ያለበትን ቦታ ብሎን ፈታሁና ተጠንቅቆ እንዲያሸተው ፈቀድኩለት፡፡ ከዚያም ቦምቡን ይዘው የመጡትን ሁለት ሰዎች ለሁለት ሰአታት እንዲከታተላቸው ነገርኩት፡፡ በዚያ ጊዜ ውስጥ ምንም ካልሆኑ ከአደጋ ነፃ ናቸው ማለት ነው፡፡

ሁለት ሰአት ሳይሞላ አንደኛው አገልጋይ በህመም እየተንቀጠቀጠ መጣ፡፡ በቀኝ በኩል ሰውነቱ ከጭንቅላቱ ጀምሮ እንገቱ፤ ትከሻው፤ በከፊል ክንዱና ጀርባው በአባጭ ተሞልተዋል፡፡ አባጩ ሲከፈትም ብጫ ቀለም ያለው ፈሳሽ ይወጣ ነበር፡፡

አሁን ለመጀመሪያ ጊዜ ሎሳንቲን የተባለ መድሃኒት ለመጠቀም ልሞክር ነው፡፡ ከሎሚና ከሎራይድ ከተባለ ኬሚካል የተቀመመው የጀርመን

መድሀኒት በብዙ መጠን ከአዲስ አበባ ነበር የተላከልኝ፡፡ በርግጥም መድሀኒቱ መሥራት እንደሚችል ተረጋገጠ፤ ሰውየውም ከጥቂት ቀናት በኋላ አገገመ፡፡

በንጉሡ ትዛዝ ቦምቡ በአዲስ የበሬ ቆርበት ተጠቅሎ ለምስከርነት ወይም ለመረጃ ወደ አዲስ አበባ ተላከ፡፡

በታህሳስ በመጨረሻዎች ቀናት በአንደኛው አንድ የኢጣልያ አስረኛ ለህክምና ወደኔ ተላከ፡፡ መቀመጫው በአዲስ ውሀ በቋጠሩ እባጮች ተሸፍኗል፡፡ ይህም የሆነው ከስአታት በፊት በመሰታርድ ጋዝ ምክንያት ነው፡፡ ይህ አስረኛ ከዚህ ቀደም የገለፅኩት በአንዳባጉና ውጊያ በዱላ ተመትቶ ለአንድ ሙሉ ቀን ህሲናውን ስቶ የነበረው ነው፡፡

ከዚያ በኋላ የሆነው ነገር በራሱ አገላለፅ እንደሚከተለው ነው

በታህሳስ ሰባት ወታደሩ ሲነቃ ብርቅ ያለ የከሰአት በኋላ ፀሀይ ነበር፡፡ የነበረበት ሜዳ ባዶ ነበር፡፡ ትንሽ ግራ ተጋብቶ ዙሪያውን በሙሉ ተመለከተ፡፡ በኋላ ግን ምን እንደሆን በአእምሮው ብልጭ አለበት፡፡ ነገር ግን ለጊዜው ትኩረቱ ጥሙን የሚያረካበት ውሀ መፈለግ ነበር፡፡ እያዞረውና ደከሞት ሰባት ኪሎሜትር ከተጓዘ በኋላ ጥልቅ ሸለቆ ውስጥ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ አንደ ትንሽ ወራጅ ውሀ ያለበት ቦታ ይደርሳል፡፡ ውሀ ከጠጣ በኋላ ዛፍ ሥር ቁጭ ብሎ ሲያንሰላስል የሆነውን ሁሉ እና ምን ያህል ጊዜ አእምሮውን ስቶ እንደነበር በርግጠኛነት የማያውቅ ለመሆኑ ውሳኔ ላይ ይደርሳል፡፡ ጓደኞቹ ሰላላነሱት ደግሞ ተሸንፈው የሸሹ ለመሆናቸው ምክንያት ሆኖለታል፡፡ ስለዚህ በእነዚህ ያልሠለጠኑ ሰዎች እጅ እንዳይወድቅ መጠንቀቅ አለበት፡፡ ሕይወቱ ከማለፉ በፊት ስውነቱን ምን ለማድረግ እንደሚያልሙ ማንስ ያውቃል? ሰለ ጨካኝ ሥራቸው ብዙ ወሬ ሰምቷል፡፡

ለአስር ቀናት እንደሚሳደድ እንሰሳ በየቦታው በቁጥቋጦችና ጫካ መሀል እየተዘዋወረ ሰነበተ ህይወቱን ለመጠበቅም ሥራስር እና እንቁራሪት እየበላ ውሀ እየጠጣ ነበር፡፡ ቀስ ብሎ ግልፅ የሆነለት ነገር ቢኖር ውሎ አድሮ የዱር አራዊት ሰለባ እንደሚሆን ነው፡፡ ለከፋም ለደጉም በአካባቢው ወዳሉ ገበሬዎች ወደ አንዱ ለመሄድ ወሰነ፡፡



መጨለም ሲጀምር ቀረብ ወዳለው ወደ አንድ ቤት ሲሄድ በንዴት ከሚጮሁ ጥንድ ውሾች ጋራ ይገጣጠማል፡፡ በዚህ ጊዜ ገበሬው ሁኔታውን ለማጣራት ይወጣል፡፡ ገበሬው በመገረም ሲመለከት ጊዜ ወሰደበት፡፡ በኋላ ግን ጣልያናዊው የፈለገውና የሚጠይቀው ትንሽ ምግብ መሆኑን ከጣልያኑ የሰውነት ምልከት ይረዳል፡፡

በቤቱ ውስጥ የነበረ የአቢሲኒያ ወታደር ደግሞ ሁኔታው ምን እንደሆን ለማየት ይወጣል፡፡ ልክ ጣልያናዊውን እንዳየው ለመማረክ ተንደርድሮ ሲሄድ ገበሬው ያሰበው እሱኑ ስለነበር ሁለቱ ጭቅጭቅ ይጀምራሉ፡፡ ጭቅጭቁ ጠንከር ማለት ሲጀመር እያንዳንዳቸው ጣልያናዊውን ወደ ተለያየ አቅጣጫ መጎተት ጀመሩ፡፡ በመጨረሻ ገበሬው የያዘውን ለቆ ወደ ቤቱ ገባና የተቀባበለ ጠመንጃ ይዞ ወጣ፡፡ ሌላኛውም ነገሩ ገባውና ወደ ቤት ገብቶ የራሱን ጠመንጃ ለመያዝ ሲሞከር ትንሽ እርምጃ ሳይራመድ ተኩሰ ተተኮስ ወታደሩ በሙሉ ሰውነቱ መሬቱ ላይ እንዳለ ወደቀ፡፡

በሚቀጥለው ቀን የኢጣልያው ወታደር ወደ ሠፈር አለቃው ተወሰደ፡፡ አለቃውም ወደ ደጃዝማች አያሌው እንዲወስደው ነበር የታሰበው፡፡ ነገር ግን ሁልጊዜ እንደሚሆነው ሁሉ ዘገየ፡፡ ጣልያናዊው ጭብጥ የአተር ንፍሮ እየበላ ለብዙ ቀናት መቆየት ነበረበት፡፡

በመጨረሻም የሠፈር አለቃውና ጣልያናዊው መንገድ ሲጀምሩ ጣልያናዊው ለአጭር ጊዜ ከመንገድ ወጣ ብሎ መሄድ እንደሚፈልግ ተናገረ፡፡ ነገር ግን አቢሲኒያዊው ሰላልገባው ዝም ብለው መንገድ ሲቀጥሉ በገና ዋዜማ የጋዝ ቦምብ የተጣለበት ቦታ ይደርሳሉ፡፡ (ይህንን ቦታ ግን አሳጥሬ በአማርኛ መርዝ አለ የሚል ምልከት በትልቁ አስፅፌ ተከየበት ነበር) አደጋ መኖሩን ሳይጠራጠር ጣልያናዊው አጥሩ ውስጥ ገብቶ ለመፀዳዳት ተንቆራጠጠ፡፡

ከሁለት ሰአታት በኋላ ደጃዝማች አያሌው ፊት ሲቀርብ አቢሲኒያኖቹ አሰኪገርማቸው ድረስ ይዘልና ይጮህ ነበር፡፡

# ምዕራፍ አሥራ አምስት

## የካምፕ ኑሮ

በጥር ሰባት ድሬሰሮችና የቆሰሉት ሰዎችን ጨምሮ ደጃዝማቻ አያሌው ወደ ሰጡን ዋሻዎች ቦታ ቀየርን፡፡ ዋሻዎችም ከሳቸው ዋሻ አጠገብ ነበሩ፡፡ ጥሩ ቦታ ነው የተመረጠው፡፡ ብዙ ዛፎች ባሉበት ትልቅ ሜዳ መሀል በጎንና በጉኑ ቀጥ ያለ ገደል ያለበት ሸለቆ የሚጀምርበት ቦታ ነው፡፡ መውጫቸው ወደ ሸለቆው አቅጣጫ የሆኑ አሥራ ስምንት ዋሻዎች በተርታ ይገኙበታል፡፡ የዋሻዎቹ ጣራ ከአሳት ገሞራ የወጣ ፍም በሶስት እስከ አራት ሜትር ውፍረት ደርቆ የተጋገረበት ነው፡፡ የአብዛኛዎች ዋሻዎች መግቢያዎች በትልልቅ ዛፎች የተሸፈኑ ናቸው በለዚህ ከላይ ከአየር ላይ መታየት አይችሉም፡፡ በለዚህ ከማንኛው የአየር ጥቃት መከለል እንችላለን፡፡ ቦምቦቹ ወይ ሜዳው ላይ አለዚያም ሸለቆ ውስጥ ነው የሚወድቁት በሁለቱም ቦታ ቢወድቁ እኛ ላይ ጉዳት አያደርሱም፡፡

ከዋሻዎቹ ትልቅ ስፋት ያለው ለዳጃች አያሌው ምግብ አዳራሽ እና እንግዳ መቀበያ ሆኗል፡፡ ስፋቱም ሰላሳ ሁለት ሜትር ርዝመት የጎን ስፋት ስምንት ሜትርና ከፍታው ደግሞ ስድስት ሜትር ነበር፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ስፋት ያለው ደግሞ ሆስፒታሉ ነው ያም ሰላሳ በሽተኞች የሚያስተኛ ሆኖ ለክሊኒክ ሥራ ቦታ ነበረው፡፡ እነዚህ ዋሻዎች በአንድ በኩል ግድግዳ ስላልነበራቸው የግማሽ ሜትር ከፍታ ያለው ግንብ በድንጋይ ተሠርቶ ላዩ ላይ አሸዋ የተሞላበት ከረጢት እንዲደረደርበት ተደረገ፡፡

የኔ መኖርያ የነበረው ለአልጋ መኝታ የሚሆን የተፈጥሮ ኪስ ቢጤ ነበረው፡፡ ከፍሉንም በእቃ መያዣ ሳጥኖች ከተሰራ ሶፋ ፤ እቃ መደርደሪያ እና ጠረጴዛ በማስገባት አደራጀሁት፡፡ ሀያ ስድስት ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ደጃች አያሌው የሰጡኝ የፋርስ ስጋጃ ወለሉን በአብዛኛው ሸፍኖታል፡፡ በየቀኑ ጠዋት ጠዋት የኔ ሰራተኛ አዲስ አበቦች እየቀጠፈ በጠርሙስ አድርጎ ጠረጴዛው ላይ ያስቀምጣል፡፡ ይህንን ደግሞ ራሱ አስቦ ነበር የሚያደርገው እና አበተጓጉሎም አያውቅም፡፡



በዚህ ቦታ ለሁለት ወራት ያሳለፍኩት ጊዜ በጣም ደስተኛ የነበርኩበትና በጦርነቱ ጊዜ የሚበቃ እረፍት ያገኘሁበት ነው፡፡ የነበረው ሥራም አጣዳፊ ወይም አደገኛ አልነበረም፡፡ በየቀኑ ከጠዋቱ አራት ሰአት ላይ አዲስ በቦምብ የቆሰሉ ሰዎች ይመጣሉ ይህ ግን የሥራዬ አንዱ ክፍል ነበር፡፡ ከደጃች አያሌው ጋራ ጠንከር ያለ ወዳጅነት ነው የነበረኝ፡፡ ደጃዝማቹ ለኔ የጎደለብኝ እንደ የተሟላላኝ እንዳልሆነ አድርገው ነው የሚያስቡት፡፡ ከዋሻዬም ጋራ በጣም ተላመድኩ፡፡ ጥሩ ምግብ ይመጣልን ነበር፡፡ ጤንነቴም እንደዚያን ጊዜ ተስማምቶት አያውቅም፡፡ ለብዙ አመታት ያሰቃየኝ የነበረው ወባ ለቆኛል፡፡

አንድ የሚያሳሰበኝ ነገር ቢኖር ከቤተሰቦቼ ምንም አይነት ወሬ አለመሰማቴ ነው፡፡ በሃሳቤ የሚመጣው የባለቤቴና ልጆቼ የወላጆቼና ቤተሰቦቼ ናፍቆት ነው፡፡ ነገር ምንም የሚደረግ ነገር አልነበረም አውቄ የገባሁበት ነገር ስለሆነ መቻል ነበረብኝ፡፡

በዚህ ጊዜ የነበረው በጠቅላላው ጦር ውስጥ የሚታየው ወደር የሌለው ግድየለሽነት ደግሞ እኔንም ይነካኛል፡፡ ከውጭ የምንሰማው ትንሽም ወሬ ቢሆን ጥሩ ነበር፡፡ ተስፋ የተጣለው ጣልያኖቹ ላይ የተጣለው ማዕቀብ ሥራውን እንደሚሰራና ጣልያኖችም መሳሳታቸውን አይተው ሰላም እንደሚፈጥሩ ነበር፡፡ ከአዲስ አበባ በሚላከው የውሸት ዘገባ መቀሌ በጦር ሚኒስትሩ እጅ ተመልሶ መያዙ ያለምንም ጥርጥር የተቃረበ ነገር ይመስላል፡፡

ጊዜው ረዥም ሆኖ እልታየኝም ምክንያቱም የነበረኝን ትርፍ ጊዜ የምጠቀምበት ሌላ ሥራ አግኝቻለሁ፡፡ ባንክ ሠራተኛ ሆኛለሁ፡፡ ብዛት ያለው የወረቀት ገንዘብ ነበር፡፡ አብዛኛው የኢጣልያ ሊሬ ነበር፤ ዋጋውም በቀን ሁለት ሶስት ጊዜ ወደላይ ወደ ታች ይወርድ ነበር፡፡ ያም በየቀኑ በሚወራው ጣልያኖች ላይ በተጣለው የኢኮኖሚ ማዕቀብ የተነሳ ነው፡፡ አዲስ ሰላይ መጥቶ በቅርቡ ሰላም ሊፈጠር ነው የሚል ከሆነ የሊሬው ዋጋ ወደ ላይ ይወጣል፡፡

የሚገርመው ነገር የጣልያኖች ሊሬ የአንድ ሺ ብር ኖት በአንድ ጊዜ ይሸጥም ይገዛም ነበር፡፡ በመጀመሪያ አንድ ሺ ሊሬው ሶስት ማርትሬዛ ነበር የሚያወጣው በኋላ ግን ወደ ሀያአምስት ከዛም ወደ ሰላሳ ከፍ እያለ መጣ፡፡ ብዙ ጊዜም ወደ አከሱም ለራሳቸው የሚበቃ ትርፍ በሚወስዱ በሰላዮችና በነጋዴዎች በኩል ተልኮ ወደ ማርትሬዛ ይቀየር ነበር፡፡ ሰዎቹ ከወረቀቱ ይልቅ የሚያቃጭለውን ማር ተሬዛ ነው የሚፈልጉት፡፡

እያደገ የመጣው የሊሬ ዋጋ በኔ አስተሳሰብ ከአቢሊኒያ እየተባባለ ከሚሄደው ውድቀት ጋራ የተያያዘ ነበር፡፡

ለአቢሊኒያኖች በገንዘብ የመጣ ነገር የራሳቸውን ዘመዶች አለማማን የተለመደ ነገር ነው፡፡ ከነሱ ይልቅ ነጭ ሰው ላይ ሙሉ አምነት ነበራቸው፡፡ ሌላ ሰው ገንዘባቸውን እንዳይሰርቅባቸው ሊፈሩ እኔን አደራ ጠባቂ አደረጉኝ፡፡ ቁልፍ ያለው ሳጥን እንደካዝና ሆነ፡፡ በአብዛኛው ጊዜ እስከ መቶ ወይም መቶ ሃምሳ ሺ ሊሬ ድረስ ይይዝ ነበር፡፡ ሳጥኑ በየጊዜው ይቆለፋል ይከፈታል ምክንያቱም ሁሉም ሰው ገንዘቡን ከመቅበር ይልቅ መነገድና ማትረፍ ይፈልግ ነበር፡፡

ከሁሉም አደገኛው ነጋዴ የኔው ሠራተኛ ነበር፡፡ የብዙ ወራት ደሞዙን አስቀድሞ ወስዶ ግን ወዲያው ጨርሶታል፡፡ አንድ ቀን የአስር ብር ብድር ይጠይቅና ይወስዳል፡፡ በዚህ በተሠጠው ብር ይነግድበትና ከአንድ ወር ተኩል በኋላ የኩራ የአራት መቶ ብር ባለቤት ይሆናል፡፡ ይህ ንግድ ሥራ ረድቶታል የንግድ አውቀቱ ወይም ችሎታው አሌ የማይባል ነገር ነው፡፡

ለጠሩ ታማኝ የባንክ ሠራተኛ ሆኜ መሥራቱን በደስታ የማደርገው ነገር ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግን ከማያቆመው የብርና ሊሬ ውይይት ውጭ በሌላ ነገር እአምሮዬን ብወጥረው እመኝ ነበር፡፡ መፅሐፍ ቅዱሴን ይዣለሁ ግን የነበረኝ አንድ መፅሀፍ እሱ ብቻ ነበር፡፡

አንድ ቀን ማታ ምን እንደሆነ ያላውቅኩት ነገር ይሰማኝ ጀመር፡፡ ከውጭ የሚያምር የጨረቃ ብርሃን ስለነበር እንደ ሁልጊዜዬም አንቅልፍ ነሳኝ፡፡ ከነልብሴ አልጋዬ ላይ ተጋደምኩ፡፡ ስለ ሁሉም ነገር አሰብኩኝ፤ የቀረኝም ነገር አልነበረም፡፡

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ጭንቅላቴ ውስጥ የሚመላለስ ዜማ መኖሩን አውቅሁኝ፡፡ ከሎንገሪን የግራል ታሪክ ነበር፡፡(የሰዊድን አገር ዜማ ነው)፡፡ አሁን ምን እንደሆነ ስላወቅሁ እንደገናም የምወደው ሙዚቃ ስለሆነ ተነሳሁና ግራማፎኑን ማጫወት ጀመርኩ ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ የዚህ አይነት ሙዚቃ በቃኝ፡፡ በንዴትም ሶስቱን የሙዚቃ ሬከርዶች ግድግዳው ላይ ወረወርኳቸው፡፡

የኔ ሠራተኛ በድምፁ ነቅቶ እንደጥያቄ ምልክት ተጣሞ ቆሟል፡፡ ጌታው በድንገተኛ አብደት ተለከፎ ይሆን ብሎ ያሰበ ይመስላል፡፡

"ህብቱ! በገና ደርዳሪውን ጥራውና እንዲጫወትልኝ" በአምስት ደቂቃ ውስጥ በገና ደርዳሪው ከባለአስር ክር በገናው ጋራ ከተፍ አለ፡፡



ብዙ ነጮች አፍንጫቸውን ነፍተው ከአፍሪካ ተወላጆች ደስ የሚል ሙዚቃ ደግሞ አለ ወይ ብለው ያስባሉ፡፡ እንግዲህ ሙዚቃ የመንፈስና የሕይወት መግለጫ ከሆነና እያንዳንዱ ሰው ደግሞ ከየትም አገር ይኑር ጥሩና ደስ የሚል ነገር በመንፈሱ ሊኖረው እንደሚችል አንድ ሰው ከተቀበለ ከሙዚቃ ላይ የአቢሲኒያን ሙዚቃ ጨምሮ የውበት ብልጭታ ሊኖር እንደሚችል መጠበቅ አለበት፡፡

የአቢሊኒያውያን በገና ደስ የሚል ነው፡፡ በተለይ አንድ ሰው ለሰለሰ ካለና ደስ ከሚለው ሙዚቃው ጋር አብሮ የሚሄድ ትክክለኛ የውስጥ ስሜት የሚኖረው ከሆነ፡፡ ከዚያ ሁሉ በፊት ግን አንድ ሰው ከሙዚቃው ጋራ አብረው የሚወርዱትን ቃላቶች መረዳት መቻል አለበት፡፡ ይህም የሚሰማው ሙዚቃና የሚደረደረው ግጥም ያልተሰማሙ ወይም የሚጋጩ እንዳይመስል ነው፡፡

አቢሲኒያውያን ሌሎች የራሳቸውን የሙዚቃ መሳሪያ ሲሰሙ አረፈት ቢስ ወይም ቁንጥንጥ ናቸው፡፡ ነገር ግን በገና ሲሰሙ ትልቁም ሆነ ትንሹ በፊሪሀ ነው የሚያዳምጡት፡፡ እልፎ እልፎም በጉንጮቻቸው ላይ እንባ ይኮላል፡፡ በገና የሚደረደረው አልፎ አልፎ ነው ያውም በማታ ነው፡፡ የሚጫወቱት ሰዎች ደግሞ ባለሙያተኞች ብቻ ናቸው፡፡ ያን ቀን ማታ ወዳጄ አሰፋው እንደዚህ አድርጎ ተጫውቶም አያውቅም። ወይስ እኔ ብቻ ነኝ እንደዛ ያሰብኩት?

መጀመሪያ ከዳዊት መዝሙሮች አንዱን ተጫወተ፡፡ ቀጥሎም ስለፈጣሪ መሀሪነትና ጠባቂነት፤ ስላለፉ ጀግንነት ሥራዎች፤ አንዳንድ ጊዜ በዘመናቸው የተሳካላቸውን የጀግኖች ታሪክ ከመፅሐፍ ቅዱስ በመጥቀስ ሌሎች ተስፋ አስቆራጭና መድረሻ በሌለው ሁኔታ ትግላቸውን የቀጠሉትን በማውሳት ተጫወተ፡፡ አስፋው ሁሉም ነገር ሀላፊ መሆኑን በማስታውስ ዜማውን ጨረሰ፡፡

በአባ ዳኘው ጊዜ (የሚኒሊክ መጠሪያ)
አባቶቻችን ያላዩት ነገር ሆነ
ውሃ ወደዳገት ወጣ
ሸቦዎች ተናገሩ
ባቡርም ተነዳ
ምኒሊክ ፈጣሪን መሰለ ወይ? ብሎ ልቤ ዋለለ
ያም ሆኖ ምኒሊክ ካለፉት ጋር አለፈ
ሁሉም ነገር ጊዜያዊና ሀላፊ ነውና

አንድ ቀን አንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን ከአዲስ አበባ መጣ:: የተሳከውም በንጉሡ ትዛዝ በጦር ሚኒስትሩ በኩል ነው:: ሰውየው እንደሚለው በእንዳባጉና በተገኘው ድል እያሌውን እንኳን ደስ ያለህ ለማለት ነው የመጣው:: በኋላ ሲጣራ ግን የመጣበት ጉዳይ የተወራው የድል ወሬ እውነት መሆኑን ለማጣራት ሀላፊነት ወስዶ ነው:: ጠላት በታህሳስ ስድስት የተገኘውን የአቢሲኒያውያን ድል ከደል:: ስለዚህ በአዲስ አበባና በሌሎች ግንባሮች ደጃች እያሌው የሳኩት የድል መልከት ጥርጣሬ ውስጥ ወድቋል::

ሳምንቱን በሙሉ ባለሥልጣኑ የጦር ሜዳ ውጊያውን ሲያሰስ ሰነበተ:: ሜዳ ላይ ያልተነሱት አስከሬኖችን እየቆጠረ መዘገበ፤ ታንኮችንና ሞተራቸውንም መዘገበ:: ከዚህ በተጨማሪ ሁለት ጀንያ ሙሉ ከፍያዎች፣ ኮከቦች፣ ትከሻ ላይ የሚደረጉና ሌሎችም የወታደር ምልክቶች ከሞቱ የኢጣልያ መኮንኖች ሰበሰበ::

ይህ ባለስልጣን በሌሎች ግንባሮች ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ ነው በማለት እኛን ለማረጋጋት ሞከረ:: እንደሱ አባባል ራስ ካሳ ጣልያኖች ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሰው አብይ አዲንና ተምቤንን ለመያዝ እያመሩ ነው:: ራስ ሙሉጌታም ቢሆን መቀሌን ለማጥቃትና መልሶ ለመያዝ አመቺ ሁኔታ እየጠበቁ ነው:: ወታደሮች ብዙ የአየር ጥቃቶች ደርሰባቸዋል ቢሆንም ወኔያቸው በጥሩ ሁኔታ ነው ያለው:: የወታደሩ ስንቅም እያለቀ ነው በአንዳንድ ቦታ ገበሬዎች በራባቸውና ስነ ሥርአት በጎደላቸው ወታደሮች እየተመዘበሩ ነው:: የጦር ሚኒስትሩ ራስ ሙሉጌታና ራስ ካሳ ግን በጥሩ ሁኔታ ነው የነበሩት:: የሚበቃ ምግብ ነበራቸው:: የሚኖሩበት ጥሩ መጠለያ ዋሻ ግድግዳው በከፈይ መጋረጃ ተሸፍኗል በየቀኑም ሻምፓኝ ይጠጡ ነበር::

በኛ ግንባር ምስጋና ለደጃች እያሌው አርቆ ማሰብና ድርጅት ይሁንና ጦሩ የአስፈሳጊ ነገሮች አጥረት አላጋጠመውም:: ለአምስት አመታት እህል እየሰበሰቡ ተከዜ ወንዝ ጥግ ድርስ ከዝነዋል:: ጦርነቱ እንደሚመጣም እርግጠኛ ነበሩ:: የሳቸው ጦር ከነዚህ የእህል ካዝናዎች በየሶስት ቀናት ሌላ ዙር ስንቅ ይታደሰዋል::

የኛ ካምፕ ባለበት አካባቢ ያሉ ገበሬዎች ምንም አይነት ረብሻ እንደማይደርስባቸው ደጃዝማቹ ቃል ገብተውላቸዋል:: አንድ ጊዜ ብቻ ሁለት ወታደሮች በጉልበት የገበሬ ቤት ውስጥ ገብተው የገበሬውን የቤት እቃ ወስደዋል:: እነሱም ለፍርድ ቀርበው የሞት ፍርድ ተፈረደባቸው::



ቄሱ ጣልቃ ገብተው የሞት ፍርዱ ወደ ግርፋት እንዲቀየር ተማፅነው አስቀይረውላቸዋል:: አመሻሽ ላይ አጥፊዎቹ እንዲቀርቡ ተደረገ:: እጃቸውም ታስሮ ነበር:: የሠረቁት ዕቃም አንገታቸው ላይ እንዲንጠለጠል ተደረገ ከዛም ከካምፕ ወደ ካምፕ እየዞሩ እንዲወሰዱ ተደረገ:: አብሯቸው የሚሄደው ቀጪው ደግሞ በየአጋጣሚው ባስ በሌስ ሀይሉ በአለንጋ ይሰመጥጣቸው ነበር:: በእያንዳንዱ ግርፋት ደግሞ

"ሥርቄያለሁ! እኔን ያየህ ተቀጣ" እያሉ መጮህ ነበረባቸው::

ደጃዝማች አስቀድመው የቄሱን ሽምግልና ገለል ለማድረግ ወስነዋል:: ስለዚህ በቅጣቱ ላይ እያሉ በጎን መላከተኛ ልከው ቀጪውን የሌቦቹን ሕይወታቸወን እንዳያስተርፍ መከረውታል:: ከአራት መቶ ግርፋት በኋላ አእምሮአቸውን ሳቱ:: አንደኛው ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ሞተና ተወሰደ:: ሌላኛው ሰው ግን የት እንደደረሰ እላወቅንም::

ገበሬዎቹም በጣም ተደሰቱ ደጃዝማች እያሌውን አሞገሱ:: በሳቸው ወታደሮች እንደማይመዘበሩ እርግጠኛ ነበሩ:: ነገር ግን ደስታቸው ለአጭር ጊዜ ነበር:: የራስ እምሩ ሠራዊት ይዞት የመጣውን ስንቅ ጨርሷል:: ደጃች እያሌው ደግሞ ከተከዜ ማዶ ከከማቹት እህል እንዲወስዱ ቢጋበዟቸውም ተከዜ ማዶ ሄደው እህል ለመውሰድ ሰንፈው ነበር::

በዛ ፋንታ ከጎጃም የመጣው የራስ እምሩ ጦር የአካባቢውን ገበሬ ቤት መውረርና መመዝበር ጀመረ:: ብዙ ጊዜ በገበሬውና በሠራዊቱ መሀል ውጊያ ተደርጎ ብዙ ሰዎች አለቁ:: ገበሬዎቹ ግንባር ፈጥረው ንብረታቸውን ከእንዳባጉና በወሰዷቸው ጠመንጃዎችና ቀላል የአውቶማከ መሳሪያዎች ለመከላከል ወስነዋል:: ሰላሳ የሚሆኑ የራስ እምሩ ወታደሮች ከሞቱ በኋላ ገበሬዎቹ ሰላም አገኙ::

ነገር ግን አንድ ሰው በዚህ በታየው ጉድለት ምክንያት የጎጃም ሰዎች ላይ መፍረድም የለበትም:: ከረጅም ጊዜ መቦዘን በኋላ ለጦርነት በነበራቸው ጉጉት ምክንያት ጦርነት ለመጫር ሰበብ ነበር የሚፈልጉት:: አንድ የራስ እምሩ ፊታውራሪ ከሶስት ሺ ሰዎች ጋራ ሆኖ እስከ አኩሱም ድረስ ቢጓዝም ተቃዋሚ ወይም ጠላት አላጋጠመውም:: ጣልያኖቹ ለሶስት ቀናት ሙሉ ባደረጉት ጀሮ በሚያደነቁር የመድፍ ድብደባ ስለረኩ ከአኩሱም ወጣ አላሉም::

ስለ ራስ እምሩ የጦር ሚኒስትርና ተወካያቸው ስለነበረው የሀያ ሁለት አመት ወጣት ዮሐንስ ሳልናገር ማለፍ አልችልም:: ወጣቱ በአንድ እንግሊዛዊ

በባሪያ ንግድ አሰበት ተብሎ ተከሶ ለሶስት አመት አዲስ አበባ ከታሰረ በኋላ ሲፈታ የራስ አምሩን ጦር የተቀላቀለ ነው፡፡ ሁለት ጊዜ ከደጃች አያሌው ጋራ ስለ ጦርነቱ ዕቅድ ለመወያየት ተልኮ ቢመጣም በመጣ ቁጥር ደጃች አያሌው ስለ አቢሲኒያ በጣም ወሳኝ ጉዳዮች ልምድ ከሌለው ወርበሳ ወጣት ጋር መወያየት ደስተኛ ስላልነበሩ ፊት ነስተውት ካከምፑ ይባረር ነበር፡፡

በየካቲት መጀመሪያ ላይ ዮሐንስ ቢድሮው በኤርትራ ድንበር ከመረብ ወንዝ አጠገብ ራማ በተባለ ቦታ ስለ ሰፈሩ የጣልያን መንገድ ሰሪዎች ቡድን ወሬ ይሰማል፡፡ ጣልያኖቹ ራማ ከጦርነቱ ቦታ ሃምሳ ኪሎ ሜትር ርቀት ወደኋላ ስለሆነ የሚያሰጋ ነገር የለም ብለው ይጠብቋቸው የነበሩት አንድ ሺ ወታደሮችን ወደ ሌላ ቦታ ወስደዋቸዋል፡፡

አንድ ቀን ከሰአት በኋላ  ዮሐንስ ሶስት መቶ ሥርአት አልባ የሆኑ ወታደሮች ይዞ ራማ ላይ ጥቃት ለማድረስ መንገድ ይጀምራል፡፡ ዙርያ ጥምዝ መንገድ ስለወሰደ ርቀቱ ወደ ሰባ ኪሎሜትር ተራዝሞ ከሌሊቱ አስር ሰአት ሲሆን ከቦታው ይደርሳል፡፡

አምሰቶ መቶ የሚሆኑት ሠራተኞች ጠባቂ ሳያቆሙ ካምፑ ውስጥ ተኝተው ነበር፡፡ የሚጮሁት አቢሲኒያኖች በየድንኳኑ እየገቡ በጥይት የደረሱበትንም በጎራዴ ይቆርጣሉ፡፡ አብዛኛዎቹ ለመነሳት ጊዜ ሳይኖራቸው የተኙበት ሳይ ነው የተገደሉት፡፡ ኢንጂነሩ ብቻ ነበር የታጠቀው፡፡ እሱም ሚስቱንና ልጆችን ለመከላከል አጥብቆ የአንበሳ ያህል ተዋጋ፡፡ ሶስት ጥይት ሲቀረውና ምንም ተስፋ ያለው ነገር አለመሆኑን ሲያውቅ መጀመሪያ ልጁን ከዚያ ሚስቱን ተኩሶ ከገደለ በኋላ  በሶስተኛው ጥይት ራሱን ገደለ፡፡ ያገሩ ተወላጅ የሆነችው ሠራተኛው ደግሞ አልቀረላትም በጎራዴ ተገደለች፡፡

ሰማንያ የኢጣልያ ሠራተኞች ተገድለዋል፡፡ የቀሩት ከአራት ከተማረኩት ውጭ በሙሉ በየጫካው ሸሽተው አምልጠዋል፡፡

አጥቂዎቹም ጉዳት ሳይደርስባቸው ከውጊያው አልተመለሱም፡፡ ዳይናሚት ያሰበት ሳጥን ፈንድቶ ብዙ ሰዎች ሞተዋል፡፡ በኋላ  ደግሞ ካምፑ ሲዘረፍ እርስ በርስ እየተጣሉ ተተኳኩሰዋል፡፡ የቀሩት ዘጠና አምስት የሚሆኑት የተረፉት ወታደሮች የሞቱትን ወንዶች  እየሰሰቡ ሁለቱን የተገደሉ ሴቶችን ጡቶች ቆርጠዋል፡፡

የራሰ አምሩ የጦር ሚኒስትር ዮሐንስ በዚህ አሰቃቂ የሚያሳፍር ድርጊት ያገኘው ነገር አልነበርም፡፡ ሁሉም በተፈፀመው ድርጊት ደስተኛ አልነበረም፡፡ በተጨማሪም በኛ ወገን በኩል በዚያን ጊዜ የተፈፀመው መሰሰብ ለመጀመሪያም ለመጨረሻ ጊዜ እንዲሆን ሆነ፡፡



# ምዕራፍ አሥራ ስድስት

## የነጋሽ ስማቸውን መመለስ

የደጃች አያሌው ወታደሮች በምግብ በኩል አጥረት እንዳልነበራቸው ገልጫለሁ፡፡ በልብስ ሲመጣ ግን ከጥር ጀምሮ ሁኔታቸው በጣም የሚያሳዝን ነበር፡፡ ብዙዎቹ እራፊ ብቻ ነበር የለበሱት፡፡ ደጃዝማች እያንዳንዳቸው ሀያ ሰባት ሜትር ርዝመት ያለቸው ከጥጥ የተሰሩ ሁለት ሺ ጣቃ ጨርቅ ከሱዳን እንዲመጣ አዘው ነበር ነገር ግን ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ ጨርቁ አልመጣም፡፡ ከአከሱም በሹልከታ የሚመጣው ልብስ ደግሞ ዋጋው በጣም ውድ ስለነበር ተራው ሰው አንድ መለወጫ ልብስ እንኳን ለመግዛት አቅም አልነበረውም፡፡

ውሀ እንደልብ እያለ ወታደሮቹ ያላቸውን ልብስ ማጠብ አልፈለጉም፡፡ ምክንያቱ በከፊል ጨርቁ ሲታጠብ ጭራሹን ስለሚበጣጠስ ሲሆን ሌላው ምክንያት ደግሞ የአውሮፕላን ጥቃቱ ነው፡፡

የዚህ ውጤት ደግሞ ጊዜ ሳይፈጅ መታየት ጀመረ፡፡ የሰውነት ቅማል መራባት ጀመረ፡፡ ወታደሮቹ ሰውነታቸውን እስኪደማ ድረስ ማከክ ጀመሩ እጃቸው የማይደርስበትን የሰውነታቸውን ክፍል ከግንድ ወይም ድንጋይ ላይ እየተጠጉ ያሹት ጀመር፡፡ ይህም በየቦታው የሚታይ ድርጊት ነበር፡፡ ተባዩ እየረገፈ በየቦታው ይርመሰመስ ነበር፡፡

የኔ የግል ሠራተኛ በሚደነቅ ጉብዝና ያለኝ የሌለኝ ልብሶቹን በውሃ አፍልቶ አጠባቸው፡፡ ግን ምን ጠቀመ? አዲስ የታጠቡትን ልብሶች ለአንድ ቀን ከለበስኩ በኋላ  ሀብቱ ከልብሴ ላይ ቢያንስ ቢያንስ ደርዘን የሚሆኑ ተባዮችን ለቀምኩ ብሎ ይፎክራል፡፡ በኛ በኩል የነበረን አማራጭ ከመጠን በላይ እንዳይራቡ ለማድረግ በየቀኑ መልቀም ነው፡፡ ለአንድ ቀን እንኳን ማሳለፍ አንችልም፡፡ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የመሻገር ችሎታቸው ወደር የለውም፡፡ ለጥቂት ጊዜ ተባዩ ካለበት ሰው ልብስ ጋራ ከተነካካሁ ከሰውየው ልብስ ወደ እኔ ለመሻገር በቂ ጊዜ ያገኛሉ፡፡

በነዚህ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተባዮች ምክንያት የተሰቦ ወረርሽኝ ሊነሳ ይችላል ብዬ ሁልጊዜ እንደሰጋሁ ነበር፡፡ ያ ከሆነ ደግሞ የኛ ሠራዊት አለቀለት ማለት ነው፡፡ በሁለት ሳምንታት ውስጥ መዋጋት የማንችልበት ደረጃ እንደርስ ነበር፡፡ ምናልባትም እንዳለ እንደመሰለ ነበር፡፡ በተአምር ግን ከዚህም ሆነ ከሌላ ወረርሽኝ አመለጥን፡፡ አንድ ሰው ብቻ የአሜባ ተቅማጥ ይዞት ተገኝ እሱም ወደ ሌሎች እንዳያሻግር ተከልሎ እንዲቀመጥ ተደረገና ከህክምና በኋላ ወደ ቤቱ እንዲመለስ ተደረገ፡፡

ከአይን በሽታዎችና አልፎ አልፎ ከሚከሰት የወባ በሽታ ውጭ ወታደሮቹ ጤንነታቸው የተጠበቀ ነበር፡፡ ለዚህም ብዙ ምክንያቶች ነበሩ፡፡ የአየር ፀባዩ፤ በብዛት ጊዜን ከቤት ወይም ከዋሻው ውጭ ማሳለፍ፤ በቂ ምግብ መኖር፤ የሚበቃ ቀዝቃዛ ወራጅ ውሀ በበቂ መጠን መኖርን ይጨምራል፡፡

በዛው ልክ ደግሞ የቁንጫ ችግር፤ ዝምቦቸ እና ደግሞ ቡጀሌ አሰቸግረውን ነበር፡፡ *ቡጀሌ የሚያመጡት ተባዮች በአይን የማይታዩ ጥቃቅን ናቸው፡፡ ከደቡብ አሜሪካ ከህምሳ አመት በፊት ነው የመጡት አሁን ግን በአፍሪካ ተሰፋፍተዋል፡፡ ይህ ተባይ እንደቁንጫ የመሰለ ሲሆን ሴት ፆታ ያላት ተባይ በሰውነት ውስጥ ቦርቡራ ከገባች በኋላ እንቁላሏን ግን ወደ መግቢያው አዙራ ነው የምትጥለው፡፡ ብዙ ጊዜ የአገሬው ሰዎች እግራቸው ላይ ነው የምትገባው፡፡ አቢሲኒያኖች ተባዩን በመርፌ በማውጣት የተካኑ ናቸው፡፡ ችግሩ ግን ሌላ አይነት ልከፍት (ኢንፌክሽን) እየተከተለ ያሰቸግር ነበር፡፡ እግር ያብጥና ህመም ስሜት ሰላለው አንድ ሰው መራመድ ያቅተዋል፡፡ እኔ ራሴ እንኳን በዚሁ ችግር ለአንድ ሳምንት የአልጋ ቁራኛ ሆኜ ነበር፡፡ እኔ ግን ውጭም ሆነ ዋሻው ውስጥ በባዶ እግሬ ሄጄ አላውቅም ነበር፡፡ ጦርነቱ በትንሽ ወራት ቢራዘም ኖሮ አንድ ሶስተኛው የሚሆነው ሠራዊት በዚህ በቡጀሌ ምክንያት መዋጋት አይችልም ብዬ እፈራ ነበር፡፡

---

*ስለ ቡጀሌ ከተነሳ በአንድ አካባቢ ስለዚች ተባይ የሚገጠም ግጥም እናካፍል፡፡
ሰሟን አማከለች ድንቁ ብለው ነው የሚጠሯት፡፡

አማከለች ድንቁ ነብሰሽን አይማረው
እግሬ ቆሞ ቀረ መሄድ እያማረው

ቡጀሌን በደንብ ፈርፍሮ ማውጣት ሳይቻል ሲቀር የሚገጠመው ደግሞ የሚከተለው ነበር

በዱማ መርፌ ቁልፍ ሲገፉኝ ሲገፉኝ
ባለ ደረባ ቤት ባለፎቅ አረጉኝ፡፡



በገና ዋዜማ ከተጣለብን የመርዝ ጋዝ ቦምብ በተጨማሪ በጥር አሥራ አራትና ሀያ ሰድሰት የመርዝ ጋዝ ቦምብ ተጣለብን፡፡ በመጨረሻው ቀን አርባ ሰዎች ቆሰሉ፤ አንድ ሰው ብቻ ሞተ፡፡ መርዝ በወደቀበት ቦታ ሳር ሊለቅሙ ስለነበር ብዙ የጭነት ከብቶች ሞቱ፡፡

አፍንጫቸው ምላሳቸው እና ጉሮሮአቸው ያብጥና ትንፋሽ ይዘጋቸዋል፡፡ ለአንዳንዶቹና ቀለል ያለ ሁኔታ ለነበራቸው ሎሳንቲን በተባለው መድሃኒት አፋቸውን መለቃለቅ ይረዳ ነበር እለዚያ ግን ተሰፋ ያለው ነገርም አልነበረም፡፡

በጥር ሀያ ስባት ሌሊቱን በዘጠኝ ሰአት አዛዡ ታመዋል ብዬ ተጠራሁ፡፡ ወደ እሳቸው ዋሻ እየሄድኩ መንገዱ ላይ እኔ ራሴም የማዞር ስሜት ተሰማኝ ብርድ ብርድም አለኝ ጉሮሮዬም የማቃጠል ስሜት ነበረው፡፡ ሰደርስ ተጋድመው ሀይለኛ ትውከት ላይ ነበሩ፡፡ ሆዴንና ጉሮሮዬን ያቃጥለኛል አሉ፡፡ ራሴን ያዞረኛል፤ አይኔም ውስጥ የብርሃን ብልጭታ ይታየኛል ብለው ህምማቸውን ገለጡ፡፡

የተበላሸ ምግብ መሆን አለበት (ፉድ ፖይዝኒንግ) ግን ምን አይነት እና እንዴትስ?

አዛዡ አዲስ ከታረደ ከብት ጥሬ ሥጋ መብላት ይወዳሉ፡፡ ይህን በሽታ የሚያስከትል ሌላ ነገር መኖሩን ማለብ አልቻልኩም፡፡ የደጃዝማቹን ሆድ እያጠብኩ እያለ አንድ ሰው እየሮጠ መጣና ቄሱ ፊታውራሪ ሙላውና ወጥቤታቸው በተመሳሳይ ህመም እንደሚሰቃዩ ተናገረ፡፡ ቄሱና ፊታውራሪው ማምሻውን አራት አብረውን ነው የበሉት፡፡ ዋና ምግብ የነበረው አዲስ ከታረደው ፍየል ጉበትና ጨጓራ (ዱለት) ነበር፡፡

ወዲያውኑ የወጥ ቤት ሀላፊውን አሰጠራሁና ለዚህ ምግብ መመረዝ ምክንያቱን እንዲያብራራልኝ ጠየቅሁት፡፡ እሱም ምንም ማብራሪያ የለውም እንዳው ፍየሎቹ እራሳቸው ካልሆኑ በስተቀር፡፡ ሰናሰተውል አሥራ እንዱ ፍየሎች ያን ቀን ማታ ሞተው አድረዋል፡፡ ከዚያ በፊት ግን ሁሉም ደህና ነበሩ፡፡ የመለታርድ ጋዝ መመረዝ ይሆናል የሚል ጥርጣሬ አደረብኝ፡፡ ፍየሎቹ ጋዝ ያረፈበትን ቅጠል በልተው ሊሆኑ ይችላል፡፡

በኋላ ባደረግነው ምርመራ ጥርጣሬየ ትክክል ሆኖ ተገኘ፡፡ በመድሃኒት ሀይል፤ ትውኪያና፤ ባይካርቦኔት በተባለ መድሃኒት ሆድን ማጠብ የነበረኝና ማድረግ የምችለው ነገር ነበር ከዚህ በተጨማሪ ሰውነታችን በማላብ ተሸሎን በእግራችን ተመልሰን መቆም ቻልን፡፡ አዛዡ ግን የሚወዱትን ምግብ በጣም በልተው ሰለነበር ለአምሰት ቀናት ያህል ታመሙ፡፡

በየካቲት አስራ እራት መቶ ሀምሳ የሚሆኑ የኢጣልያ ቃኝ ወታደሮች ወደ አዲያቦ አካባቢ መጥተው ነበር፡፡ በእንድ የራስ አምሩ ጦር ክፍል ተከበው አንዳስ ተደመሰሱ፡፡ ከዚህ የተረፉት ሁለት ፖሊሶች(ካረቢኔር) በአሥራ ሰባት ወደ ዳባት እንዲሄዱ በኛ በኩል ተላኩ፡፡ ደጃች እያሌው ደግሞ በጠላት በኩል ያለውን ወይም የሚካሄደውን ማወቅ ፈለጉና ወደ ራሴ መኖርያ አካባቢ ወስጄ ወሬ እንዳውጣጣቸው ጠየቁኝ፡፡

ደስ የሚሉ ወጣቶች ነበሩ ወዲያም ተግባባንና ወዳጆች ሆንን፡፡ በነሱ በኩልም ብዙ ወሬ አገኘሁ፡፡ ራስ ሙሉጌታ በየካቲት አሥራ አንድና እሥራ ሁለት በአምባ እራዶም እንደማይንሰራሩ ሆነው በጣልያን መሸነፋቸውን ሰማሁ፡፡ ራስ ደስታም ቢሆን በዶሎ አካባቢ ተመሳሳይ ዕጣ አጋጥሟቸዋል፡፡ በተጨማሪም እንድ የስዊድን ዶክተር መቁሰሉንና የስውዲን ህክምና እባል የሆነ ሰው መሞቱን ሰማሁ፡፡

ማርሻል ባዶሊዮ በሚቀጥለው ወር ማሰቂያ በሁሉም ግንባሮች ከፍተኛ ማጥቃት ለማድረግ መዘጋጀት ማሰቡን ሰማሁ፡፡ ራስ አምሩንና ደጃች እያሌውን ደግሞ ወደ ሰሰህሰሀ አፍ ጋጋ በር አካባቢ እንዲወጡ አድርጎ ማሰፈያውን ዘግቶ በሀይል ለመድመሰስ መታሰቡን ሰማሁ፡፡



ማርሻል ባዶሊዮ ወረራውን አላፋጠንከም ተብሎ በተመለሰው በማርሻል ዲ ቦኖ ምትክ ወደ ኢትዮጵያ የመጣ ነው፡፡ በኋላ ግን ሞሶሎኒ ከሥልጣን እንዲወርድ ከአደራጁት አንዱ ሲሆን ከዚያም የኢጣልያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ነበር

አንደ ጓደኞቻው ሰላዩኝ ወደዛ አካባቢ እንዳልሄድ መከሩኝ፡፡ በተቻለ መጠን በርቀት ለመቆየት አንድሞክር ነገሩኝ፡፡ አለዚያ ግን በሀይወት የማልመለስ ለመሆኑ ፍራቻቸውን ገለጡልኝ፡፡

ምንኛ ደስ የሚል ዜና ነው! ከአዲስ አበባና ከአምባ እራዶም በሚመጣልን የሰላም ወሬ ጭምጭምታና የውሸት ሪፖርት እኛ በነበረን የልጅ



አይነት ግዴለሽነት ስናንቀላፋ ከርመናል፡፡ ውነት ነው ለአምስት ቀናት የመድፍ ድምፅ በምሥራቅ አቅጣጫ ስንሰማ ነበር፡፡ አንዳንድም ጊዜም መሬቱ ይንቀጠቀጥ ነበር፡፡ እኛ ግን ያሰብነው ራስ ሙሉጌታ መቀሌን መልሰው ለመያዝ የሚያደርጉት ዝግጅት ነው ብለን ነበር፡፡

ደጃች አያሌው ይህንን ሁሉ መረጃ እንደሰሙ ወደ ራስ አምሩ ሰው ላኩና ለብርቱ ውይይት ራሳቸው ስለሚመጡ አመሻሽ ላይ እንዲጠብቋቸወ ጠየቁ፡፡ ለደህንነት ሊባልም ሀያ አምስት ቀላል አውቶማቲክ መሳሪያና ሁለት ከባድ እውቶማቲክ መሳሪያ በያዙ እምስት መቶ ዘቦች ታጀቡ፡፡ ራሳቸውን ለመጠበቅም አጃቢዎችን በግማሽ ከብ እሰልፈው ከራስ እምሩ ካምፕ ውጭ ቦታ ይዘው ጠበቁ፡፡

የጎጃም ወታደሮች ደግሞ በደጃች አያሌው ዘቦች ረጋ ማለትና በራስ መተማመን ስሜት በጣም ተገርመው እንደነበር ይነገራል፡፡ ዘቦቹ እስከ ሕይወታቸው መጨረሻ ድረስ አያሌውን ለመጠበቅ መዘጋጀታቸው ያስታውቅ ነበር፡፡

ራስ አምሩ በዚያን ጊዜ ከፉ ሀሳብ ነበራቸው ብዬ አላስብም፡፡ ነገር ግን የአቢሲኒያዊን ልብ ማን ያውቃል?

ማታ ስንጠብቅ አመሸን አያሌው እልተመለሱም፡፡ አንግዲህ መጥፎ ነገር ሆኗል ማለት ነው፡፡

በየት አቅጣጫ እንደምሄድ ራሴን ለመጠበቅ ምን ማድረግ እለብኝ የሚል ሃሳብ መምጣቱ ራሱ ያሳሳብኝ ጀመር፡፡ እያሌው በራስ አምሩ ከታሰሩ አመፅና ግርግር አንደሚነሳ ጦሩም እርስ በርሱ መዋጋት እንደሚጀምር ግልፅ ነበር፡፡

ነገር ግን በጠዋት ትዛዝ የያዘ ፈጣን መልከተኛ ከተፍ አለ፡፡ ትዛዙም አመሻሽ ላይ ጠቅላላው ጦር አንቅስቃሴ አንዲጀምርና በእንዳ ስላሴ በዋሻ ከሚቆዩት ከደጃች አያሌው ጋራ አንዲገናኝ የሚል ነው፡፡ የጣልያን ዲቪዚዮን ከአክሱም ተነስቶ ሰሰህሰሀን ለመያዝ ማቀዱን ወሬ ስምተዋል፡፡ ደጃዝማች ደግሞ ከጠላት ተጠግቶ ሁኔታዎችን መከታተል ይበጃል ብለው እስበዋል፡፡

በየካቲት ሀያ ሁለት አንድ ወር ከቆየንበት ካምፕ ለቀን ተንቀሳቀስን፡፡ በጨረቃ ብርሃንና በሰፊው መንገድ ስንገሰግስ አምሽተን ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰአት ሲሆን ከአዛዡ ጎን ቁጭ ብያለሁ፡፡ ሲነግሩኝም ራስ እምሩ የወዳጅ ባህሪ ነው ያሳዩት ነገር ግን እኔ ያገኘሁት መረጃ በጭራሹ የገባቸው አይመስልም፡፡ ስለ

ራስ ደስታ መሸነፍ ያለጥርጥር ያውቁ ነበር ስለሌሎቹ ሰዎች ግን ምንም አይነት ቃል መስማት አልፈለጉም።

በሀያ አንድ የበለሳው ፊታውራሪ ነጋሽ የጣልያን ወታደሮች እየመጡ እንደሆነና በሚቀጥለው ቀን ውጊያ መጀመሩ የማይቀር መሆኑን አስታወቁን ሆኖም ግን ቀዳሚው ጦር በቂ የሆነ መከላከል ማድረግ ይችላል ብለው ማሰባቸውንም ነገሩን።

ከኛ ጋራ ከተቀላቀሉት ከራስ እምሩ ጋራ በመሆን አመሻሽ ላይ ለውጊያ ጠጋ ማለት እንድንችል ወደፊት መንገድ ትንሽ ገፋ አደረግን። በዚያ ቦታ የነበረውን ያህል የዋሻዎች ብዛት አይቼ አላውቅም። በስአታት ውስጥ ወደ ሰላሳ ሺ የሚጠጋውን ጦር እንዳለ ዋጥ አደረገው።

ያን ቀን ማታ ምንም አይነት የማበረታታት ሁኔታ የማይሠጥ አንድ ነገር አየን። ከሀያ አራት ሰአት በፊት ሰፍረንበት በነበሩት ተራሮችና ኮረብታዎች ላይ ወደ አስር የሚሆኑ ቦታዎች ላይ እሳት ይነድ ነበር። እሳቶቹ ይፈጉና ይጠፉ ነበር ሃበሾቹ እንደሚሉት ርችት መሆኑ ነው።

ያካባቢው ሰዎች አታለውናል። አሁን ደግሞ ለጣልያኖቹ ስለ መንገዳችን ምልክት እየሰጡ ነበር። ገበሬዎች በተዘረፈው ቤታቸው ምክንያት ተናደዋል እና በቀላቸውን ግን በጥሩ ሁኔታ በያዝናቸው በኛ ላይ ሊወጡ ነው ምክንያቱም ከበደላቸው ጦር ጋር አብረን ስለምንጓዝ ነው። ስለዚህ ሌላ ጠላት ደግሞ አፍርተናል። ወዮ በነዚህ በተናደዱ ገበሬዎች እጅ ለወደቀ ሰው ሀይወቱ የሁለት የምግብ ፍሬ ያክል እንኳን ዋጋ አይኖረውም።

በየካቲት ሀያ ሁለት እሳቱ ምልክት ለመሆኑ አረጋገጥን የጣልያን አውሮፕላኖች የት ቦታ እንዳለን በትክክል አውቀዋል። በዋሻዎች መግቢያ ላይ ብዛት ያለው ቦምብ ጣሉ። የአውቶማቲክ መሳሪያ ጥይቶች የዋሻዎች ግድግዳ ላይ ይነጥሩ ነበር። የእሳት በምቦች ደግሞ ሜዳው ላይና በሸለቆው ያለውን የደረቀ ሳር ያጋዩት ነበር። እንስሳቶች ሳይቀር በዋሻው ውስጥ መጠለያ አግኝተው ስለነበር በዚያን ቀን የደረሰው ጉዳት መጠነኛ ነበር። እንደሌላው ጦር ሁሉ እኔም እነዚህ ዋሻዎች ለኛ ሲባል ነው የተፈጠሩት ለማለት ከጅሎኝ ነበር። ለማንኛው አስገራሚ ነበር ደግሞም በሚመች ቦታ ነው ያሉት።

በሀያ ሁለት ከሰአት በኋላ ከኛ ቀዳሚ ጦር ጋራ የሚደረገውን ውጊያ መስማት እንችል ነበር። ረዳት ጦር ስላልተጠየቀ ቀለል ያለ ግጭት ነበር የመሰለን።



ፀሀይ ስትጠልቅ ከአክሱም ውጭ ያሉትን የጣልያኖቹን የመብራት ምልክቶች ማየት እንችል ነበር። ቀይ፣ አረንጓዴ፣ ነጭና ቢጫ መብራቶች ወደ ማይሉ በሚጠጋ ቦታ ላይ ጠቆር ባለ ደመና መሀል ከዚህም ከዚያም ይብለጨለጩ ነበር። አስደሳች ትዕይንት!

ወደኋላ ማምሻውን የበለላው ፊታውራሪ ነጋሽ የመጨረሻቸውን ውጊያ ማድረጋቸውን ዜና ሰማን። ግጭቱ የተጀመረው ከቀኑ ስምንት ሰአት ነበር። ነጋሽ እንደተራ ወታደር በግንባር ሆነው ጥይት ይተኩሱ ነበር። ከሶስት ሰኣታት ተኩስ ልውውጥ በኋላ ጨበጣ ውጊያ ተጀመረ። በተኩስ ብዛት ሞቆና ቀልቶ ስለነበር የነጋሽ መውዜር ጠመንጃ ደግሞ ነከሰ። ለወታደሮቻቸው የሚሆን ጥይትም እያለቀ ነበር።

ከዚያም ፊታውራሪ በጩኸት "ልጆች! ከዛፉ ስር የቆመውን ያን ከፍተኛ መኮንን ታያላችሁ? የኔ ነው! እንዳትነኩት"

ጠመንጃቸውን ወርውረው ጎራዴያቸውን መዘው ከወታደሮቻቸው ፊት ለፊት ወደ መኮንኑ ገሰገሱ። ጥይት በዙሪያቸው ይከንፋል ግን ከጉዳይ አልቆጠሩትም፤ አይናቸው የተተከለው ዛፉ ስር የቆመው ጣልያናዊ ላይ ነበር።

ነጋሽ ለራሳቸው ምንም ሳያስቡ በጠላት ወታደሮች መሀል ሮጡ። አስር ሜትር ብቻ ይቀራቸው ነበር። የጦርነት ጥማቸውን በተመረጠው ሰውየ ደም ሊያረኩ ይሆን? የራላቸው ወታደሮች ተስፋ የለውም ብለው አሰቡ። ነገር ግን ነጋሽ የነበረውን ችግር አልተቀበሉትም። በዚያች ወቅት ለሳቸው የጠላት ወታደር ሆነ የጠላት ጥይት አልነበረም ሰውየው ብቻ ነው የታያቸው። ጥይቶችም ሊነኳቸው የፈለጉ አይመስልም ነበር። ተልኳቸውን እስኪፈፅሙ ድረስ ሕይወታቸውን ሊጠብቁ የፈለጉ ይመስል ነበር።

ከኢላማቸው ትንሽ እርምጃዎች እስኪቀሩ ድረስ ባለ ጉልበታቸው ወደፊት ተወረወሩ

አሁን ግን ዛፉ ስር ያለው ሰው ወደሱ የመጣውን ጥቃት ተመልክቷል። ወዲያውኑ ሽጉጡን መዘዘ። ነገር ግን ዘግይቷል። ቢድንጋጤ የፈዘዙት ጣቶቹ የሽጉጡን ምላጭ ሙሉ በሙሉ ከመላባቸው በፊት በጀግና እጅ የሚወዛወዝ ደም የጠማው ጎረዴ አንገቱ ላይ ወረደበት። የመኮንኑ ሰውነት ከመውደቁ በፊት ጭንቅላቱ እግሩ ስር ዘፍ አለ።

ነገር ግን ሽጉጡ ደግሞ ጥይት ተኩሶ ስለነበር የተተኮሰው ጥይት የነጋሽ ልብ ውስጥ ተቀረቀረ። በዚያን ሰአት ግን ሌሎች አስር ጥይቶች በጎናቸው መቷቸው። ለዚህ ጊዜ ነበር ወይ ጥይቶቹ የቆዩት? ግን ለምን?

የበለሳው ፊታውራሪ ነጋሽ ስማቸውን አደሱ:: ከመውደቃቸው በፊት እስከመጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ አሌ የማይባል ጀግና መሆናቸውን አስመስክሩ:: ለሁልጊዜም ጀግና እንደሆኑ ይኖራሉ::

ጣልያኖች በቁጥር እጥፍ ቢሆኑም የኢትዮጵያውያኑ ቀዳሚ ጦር ያሉበት ቦታ እንዳይንቀሳቀሱ አድርጓቸዋል:: ጠላት ወደፊት መጓዝ አልቻለም እንዲያውም ስትንሽ ርቀት ወደኋላ ለማፈግፈግ ተገዷል::

አመሻሽ ላይ ወደፊት ተጓዝንና ከአፍ ጋጋ ማለፊያ አራት ኪሎ ሜትር ርቀት ቦታ ደረስን:: በዚያ አካባቢ ያሉ ዋሻዎች ብዛት አልነበራቸውም ግን ሰፋፊ ነበሩ:: ከመሬት በታች የሆነ አንድ ክፍል ውስጥ መጠለያ አደረግን የዚህ መጠለያ መግቢያው መሀል ሜዳ ላይ ከትልቅ ዛፍ ስር ነበር:: ሁለተኛው መግቢያ ደግሞ ወደ ገደል ነው የሚወስደው:: ቦታው ውስጥ የነበርነው ወደ ሁለት ሺ ሰዎች እንሆናለን ግን ክርን ለክርን አልተገፋፋንም:: ፊታውራሪ ሙላውና የራስ እምሩ ፊታውራሪ ከንፌ ፊታውራሪ ነጋሽ የሞቱበትን ቦታ መልሰው እንዲይዙ ታዘዙ::



# ምዕራፍ አሥራ ሰባት

## ቅዱስ ጊዮርጊስ አልጠበቀንም

የካቲት ሀያ ሶስት ነጋ:: የአድዋ ድል አርባኛ አመት ነበር:: እንደዛን ጊዜም ዛሬ እሁድ ነው:: ጨለማን ተገን አድርገው የጠላት ወታደሮች ወደፊት በመጓዝ ጋራውን አቃበ ሰአት፣ አዲ ሀመልማል እና ሰለህለሀን ይዘዋል:: እነዚህ ቦታዎች ደግሞ ጎን ለጎን ነው ያሉት:: ከመጨረሻው ቦታ በምሥራቅ በኩል ደግሞ አዲስ ሬጅመንት በጥዋት ቦታውን ያዘ:: አሁን ከአክሱም በረድፍ የሚመጡ የጭነት መኪኖችን እናያለን:: ተጨማሪ ወታደር ስንቅና ትጥቅ ነው ይዘው የሚመጡት:: እሁኑኑ ለማጥቃት እንዳሰቡ ምንም ምልክት አይታይም::

ከቀኑ ወደ መሀል ላይ በመጣ ዜና ደግሞ ሞተረኛ የሆነ የጣልያን ጦር በመረብ በኩል አድርጎ አዲ አዞ ተሻግሮ እየተጓዘ እንደሆነ ሰማን:: ግልፅ ሆኖ እንደሚታየው ከኋላችን ሆነው ሊያጠቁን ፈልገዋል:: ወይም ደግሞ መሸሻ መንገዳችን ከኋላ በኩል በምዕራብ አድርገው በቆየሳ ተራራ ዙሪያ መዝጋት ፈልገዋል:: ሁለቱ የጣልያን እስረኞች ሳያጋንኑ ለመናገራቸው ይህ በቂ መረጃ ነበር:: እኛን ወደ ወጥመድ ስበው በመክበብ ሙሉ በሙሉ ለመደምሰስ ፈልገዋል::

በሚያስተማምን መልከተኛ በኩል ራስ እምሩና ደጃች አያሌው ሙሉ ቀን መልከት ሲለዋወጡ ዋሉ:: ደጃች አያሌው ጠላት ሳይጠናከር እሁኑኑ ማጥቃት ፈልገዋል:: ውነት ነው ቀኑ ሁለት በእል ነበረው እሁድም እና ቅዱስ ጊየርጊስም ነበር:: ግን ደጃዝማች “በችግር ምክንያት መደረግ ያለበት ነገር ሲኖር ህግና ልምድ አይከበርም” አሉ::

ነገር ግን ራስ እምሩ እርግጠኛ አልነበሩም እና በማታ መንቀሳቀስ ነው የሚሻለው ብለው ነው ያሰቡት:: አለዚያ እንዴት ተብሎስ የአየር ጥቃቱን ማምለጥ ይቻላል? በዚህ እንኳን ውነት ነው ትክክል ነበሩ::

የበለሳው ፊታውራሪ ነጋሽ ስማቸውን አደሱ። ከመውደቃቸው በፊት እስከመጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ እሌ የማይባል ጀግና መሆናቸውን አስመሰከሩ። ለሁልጊዜም ጀግና እንደሆኑ ይኖራሉ።

ጣልያኖች በቁጥር እጥፍ ቢሆኑም የኢትዮጵያውያኑ ቀዳሚ ጦር ያሉበት ቦታ እንዳይንቀሳቀሱ አድርጓቸዋል። ጠላት ወደፊት መጓዝ አልቻለም እንዲያውም ለትንሽ ርቀት ወደኋላ ለማፈግፍግ ተገዷል።

አመሻሽ ላይ ወደፊት ተጓዝንና ከእፍ ጋጋ ማለፊያ አራት ኪሎ ሜትር ርቀት ቦታ ደረስን። በዚያ አካባቢ ያሉ ዋሻዎች ብዛት አልነበራቸውም ግን ሰፋፊ ነበሩ። ከመሬት በታች የሆነ አንድ ክፍል ውስጥ መጠለያ አደረግን የዚህ መጠለያ መግቢያው መሀል ሜዳ ላይ ከትልቅ ዛፍ ስር ነበር። ሁለተኛው መግቢያ ደግሞ ወደ ገደል ነው የሚወስደው። ቦታው ውስጥ የነበርነው ወደ ሁለት ሺ ሰዎች እንሆናለን ግን ከርን ለከርን አልተገፋፋንም። ፊታውራሪ ሙላውና የራስ እምሩ ፊታውራሪ ከነፊ ፊታውራሪ ነጋሽ የሞቱበትን ቦታ መልሰው እንዲይዙ ታዘዙ።



# ምዕራፍ አሥራ ሰባት

## ቅዱስ ጊዮርጊስ አልጠበቀንም

የካቲት ሀያ ሰለት ነጋ። የአድዋ ድል አርባኛ አመት ነበር። እንደዛን ጊዜም ዛሬ እሁድ ነው። ጨለማን ተገን አድርገው የጠላት ወታደሮች ወደፊት በመጓዝ ጋራውን አቃብ ሰእት፣ እዲ ሀመልማል እና ሰለህለሀን ይዘዋል። እነዚህ ቦታዎች ደግሞ ጎን ለጎን ነው ያሉት። ከመጨረሻው ቦታ በምሥራቅ በኩል ደግሞ አዲስ ሬጅመንት በጥዋት ቦታውን ያዘ። አሁን ከእከሱም በረድፍ የሚመጡ የጭነት መኪኖችን እናያለን። ተጨማሪ ወታደር ሰንቅና ትጥቅ ነው ይዘው የሚመጡት። እሁኑኑ ለማጥቃት እንዳሰቡ ምንም ምልክት አይታይም።

ከቀኑ ወደ መሀል ላይ በመጣ ዜና ደግሞ ሞተረኛ የሆነ የጣልያን ጦር በመረብ በኩል አድርጎ አዲ እዞ ተሻግሮ እየተጓዘ እንደሆነ ሰማን። ግልፅ ሆኖ እንደሚታየው ከኋላችን ሆነው ሊያጠቁን ፈልገዋል። ወይም ደግሞ መሸሻ መንገዳችን ከኋላ በኩል በምዕራብ አድርገው በቆየሳ ተራራ ዙሪያ መዝጋት ፈልገዋል። ሁለቱ የጣልያን አሰረኞች ሳያጋኑ ለመናገራቸው ይህ በቂ መረጃ ነበር። እኛን ወደ ወጥመድ ስበው በመከበብ ሙሉ በሙሉ ለመደምሰስ ፈልገዋል።

በሚያስተማምን መልከተኛ በኩል ራስ እምሩና ደጃች አያሌው ሙሉ ቀን መልከት ሲለዋወጡ ዋሉ። ደጃች አያሌው ጠላት ሳይጠናከር እሁኑኑ ማጥቃት ፈልገዋል። ውነት ነው ቀኑ ሁለት በእል ነበረው እሁድም እና ቅዱስ ጊዮርጊስም ነበር። ግን ደጃዝማች "በችግር ምክንያት መደረግ ያለበት ነገር ሲኖር ህግና ልምድ አይከበርም" አሉ።

ነገር ግን ራስ እምሩ እርግጠኛ አልነበሩም እና በማታ መንቀሳቀስ ነው የሚሻለው ብለው ነው ያሰቡት። እለዚያ እንዴት ተብሎስ የአየር ጥቃቱን ማምለጥ ይቻላል? በዚህ እንኳን ውነት ነው ትክክል ነበሩ።

የደጃች አያሌው ልጅ ፊታውራሪ ዘውዱ በምሥራቅ በኩል የሚገኝ ማለፊያ በር እንዲጠብቁ ተልከው ወደ ማለፊያው ሲጓዙ የአየር በምብ ጥቃት ደረሰባቸው:: አራት መኮንኖችና ሃምሳ ወታደሮቻቸው በገደል ውስጥ ገብተው ተሰውረዋል:: አነሰ ያለ ጉድጓድ ውስጥ ዘለው በመግባት ማምለጣቸው ፊታውራሪው እራሳቸው ዕድለኛ ነበሩ:: በተአምር ነው የዳኑት:: ወታደሮቹም ሰለተበታተኑ ማታ ነው ማሰባሰብ የተቻለው::

በዚያን እለት ጣልያኖቹ ትልልቅ በምብ ጣይ እውሮፕላኖቻቸውን በሙሉ ነው ያሰለፉት:: እንስሶች እንደ መጀመሪያው ቀን ሰላልተጠበቁ በገፍ ነው ያለቁት:: ሜዳው ዳገቱ ሁሉም ቦታ ይነድ ሰለነበር ሙቀቱ የሚቻል አልነበረም:: ያልበንም ነበር፤ ጭሱ ደግሞ አይናችንን ያቃጥለን ጀመር:: ዋሻችን በሴቶቹ ግጥም ብሎ ሞልቶአል:: ሴቶች ፍርሃታቸው ከቁጥጥር ውጭና ከመጠን በላይ ነበር:: የኛ ዋሻ ከሌሎች ይሻላል ብለው ሰላሰቡ ሁሉም ተገፋፍተው ነው የገቡት:: በዚህ ሙቀትና መተፋፈግ መሀል እኔና ድሬሰሮቹ የሚመጡልንን ቁሰለኞች እናከም ነበር::

ከብዙ ውይይት በኋላ ከቀኑ ወደ አስር ሰአት ሲሆን ደጃች አያሌው ራስ እምሩን በሌሊት ወደ ማለፊያ በሩ ሄደው ለማጥቃት ያሰቡትን ዕቅድ አስቀየሯቸው:: ቀኑን ሙሉ ጠላት ያለበትን ቦታ አያጠናከረ ስለዋለ ማጥቃትና መውረር የማይቻል ነው:: ስለዚህ ደጃች አያሌው የተሻለ ነው ብለው ያሰቡት ታኩቲከ ጠላትን በማለፊያው እንዳይወጣ መዝጋት ነው:: በዚህ መንገድ ከጀርባ የሚደርስብን ጥቃትም ይቀራል ጠላት ያሰበውን እቅድም ማከሸፍ እንችላለን::

ጨለማው እየገፋ ሲመጣ ፈጣን መልከተኛ መጥቶ ራስ እምሩ ከአምስት ሺ ሰዎች ጋራ በመሆን መንገድ መጀመራቸውን ነገረን:: ወዲያውኑ ደጃች አያሌው ፀሀፊያቸውን ልከው የተሰማማነው ስምምነት ምን ደረጃ ደረሰ ብሎ እንዲጠይቅ አደረጉ:: መልስ የተሠጠው በሚቁነጠነጥ ፈረስ ላይ በተቀመጠው በዮሐንስ ነበር:: ስምምነት ኖረም አልኖረም ወደ ሰለሀለሀ እየተጓዙ መሆናቸውን ተናገረ:: ደጃች አያሌው ማድረግ የሚችሉት የተሻለ ነው የሚሉትን ነገር ነው:: ተከትለው ለመሄድ ወይም ወደኋላ ለመቅረት ነፃ ነበሩ::

ወዲያውኑ በቦታው የነበሩትን የጦር መኮንኖቻቸውን በሙሉ አሰጠሩ:: የጣልያኖችን ዕቅድ ጨምሮ ሁኔታውን ካብራሩ በኋላ እንዴት ማድረግ እንዳለብን ያለምንም ማወላወል ሀሳባቸውን እንዲሰጡ ጠየቁ:: አብዛኛዎቹ



ባለንበት ቦታ እንድንቆይ ነው ድምፅ የሰጡት ግን ድንገት ራስ እምሩ ርዳታ ከፈለጉ ወይም ከጀርባቸው የሚጠቁ ከሆነ ለመርዳት ተዘጋጅተን እንጠብቅ የሚል ሀሳብ ነበር::

ይህ ስብሰባ እየተካሄደ እያለ የጣልያን አውቶማቲከ መሣሪያዎች መንጣጣት ጀመሩ:: የነጎድጓድ ድምፅ እያሰሙ እየደጋገሙ መድፎች ሲተኮሱ በጨረቃው ብርሃን የሚወረወር ብርሃን ያሳዩ ነበር:: እልፎ እልፎ ጋብ ከማለት በስተቀር ሙሉ ማምሻውን በዚህ ሁኔታ ቀጠለ:: ጣልያኖቹ ድንገተኛ ጥቃት እንዳይፈጠር ለመከላከል ያሰቡት ነገር ነበር:: ምንም ኢላማ ወይ ግብ አልነበራቸውም ጥይቶቹ በዘፈቀደ በየቦታው ነበር የሚወድቁት::

በጨረቃ ብርሀን ራታችን ለመብላት ተቀመጥን:: ከፊት ለፊታችን ጥቂት ኪሎሜትሮች ርቀት ያለማቋረጥ የሚተኮሰውን የአውቶማቲከ መሳሪያ እና እልፎ አልፎም የመድፎቹን ተኩስ እናያለን:: አዛዡ በዝምታ ቁጭ ብለዋል:: ምግቡም ጣዕም አልሰጠም በደረቅ ጉሮሮ ላይ የሚወርድ ይመስላል:: አልፎ እልፎ ብርድ ብርድ እያለኝ ሰውነቴን ያንቀጠቅጠኝ ነበር:: የሚቀጥለው ቀን በእቅፉ ምን ይዞ ይመጣ ይሆን?

ትንሽ ጉርሻዎች ከጎረስኩ በኋላ ደህና እደሩ ብዬ ወደ ድንኳኔ ሄድኩኝ:: ድንኳኔ መረብ ያለበት ነበር ከዋሻ መግቢያ በኩል ካለ ዛፍ ስር ተወጥሮ ተዘጋጅቷል::

ድፍን ያለ ፀጥታ በመላው ካምፕ ውስጥ ሰፍኗል:: የሚነድ እሳትም እልነበረም:: ሁሉም በወዲያኛው ወገን ባለው ትዕይንት ተመሰጠዋል:: በኋላ ያ ምሽት በጨረቃ ብርሃን ፂሜን ለመላጨትና ገላዬን ለመታጠብ ለምን እንደገፋፋኝ ይገርመኝ ነበር:: በኔ በኩል ያለምንም ሀሳብ በድንገት ነበር ያደረግሁት:: በዚህ ወቅትም የሚተኮሱ እውቶማቲከ መሳሪያዎችን አይነት ለመለየት ምን ያህል ርቀት ላይ እንዳሉ ለመገመት እየሞከርኩ ነበር::

የታጠቡ ልብሶች ለብሼ በድንብ የተወለወለውን ጫማዬን አድርጌ ንፁህ ሆኜ ሰቆም ልገልፀው የማልችለው የደሰታ ሰሜት ተሰማኝ:: የማደርገው ነገር በሙሉ አስቤበት ሳይሆን ዝም ብየ ነበር የማደርገው:: አሁን ደግሞ ሣጥኔ ውስጥ ያለውን ነገር አደራጀሁና ደጃች አያሌው በአደራ የሰጡኝን አሰር ሺ ሊሬ በኪሴ ያዝኩኝ:: በንግድ የሰበሰብኩት የራሴ ሀያ ሺ ሊሬ ግን ሳጥኑ ውስጥ ተቀምጧል:: ከዚያ በኋላ በሙሉ ሰውነቴ አልጋዬ ላይ ተጋደምኩና ራስ እምሩ ስላደረጉት ነገር ማሰብ ጀመርኩ::

የሚያወራጭ አንቅልፍ ይዞኝ ነበር ማለት ነው የጥሩምባ ድምፅ ሰሰማ ነቃሁኝ። ሰአቱ ከሌሊቱ ስድሰት ክአሰር ነው የሚያሳየው። ወደ አዛዡ ሰጣደፍ ሄድኩ ልብሳቸውን ለብሰው በዘቦቻቸው ተከበዋል።

"ምንድን ነው ነገሩ?"

"አትሰማም እንዴ?" አሉ ወደ ሰሜን አቅጣጫ እያመላከቱ

አሁን የጆሮ ታምቡር የሚበጥስ ድምፅ ተሰማኝ። መድፎቹና አውቶማቲክ መሳሪያዎቹ በነበራቸው አተኳኮስ ፍጥነት አልነበሩም። እርስ በራስ እየተፎካከሩ ተኩሱን ያቀልጡታል። ቆየሳ ተራራ በሶሰት ባውዛ መብረቶች ደምቆአል። ባሻጋሪ ግን ተወርዋሪ ኮከብ የሚመስሉ በአሳት በራሪዎች ይነዳል። ቦምቦች ከኛ ኪሎሜትሮች ርቀት በአፍ ጋጋ ማለፊያ ሲፈነዱ እንሰማለን።

ጦሩን ለማሰባሰብ ጥሩምባው ያለ ማቋረጥ ይነፋ ነበር። ራስ አምሩ በሌሊት ማጥቃት ሰለጀመሩ ረዳት ጦር ይፈልጋሉ። እዚህ ሆነን ቆመን ማየት ወይም መጠበቅ አንችልም። ይቅርታ የማይድረግለት ከህደት ነው።

ከግማሽ ሰአት በኋላ የሚበቃ ሰው ቁጥር ሰለተሰበሰበ መንገድ መጀመር ነበረብን ጓዝ ያዢዎች ግን ወደኋላ እንዲቀሩ ታዘዙ። በጨረቃ ብርሃን የሰዎችን ቁጥር መገመት አሰቸጋሪ ነበር። ነገር ግን አሁን የሚንቀሳቀሰው የጠቅላላው ጦር ቁጥር አራት ሺ አይሞላም። ሌሎቹ የት ቦታ እንዳሉ ለመናገር ቀላል ነገር አልነበረም።

ከማለፊያ በሩ ምዕራብ በኩል ከተራራው ግርጌ ተጠለልን። ራስ አምሩም እዛው ቦታ ነው ያሉት። ቦታው የጣልያኖቹ ባውዛ መብራት ሰለበራበት የራስ አምሩ ሰዎች ለመንቀሳቀስ አልደፈሩም።

ከአጭር ውይይት በኋላ የሁለቱ ጦር አዛዦች አንድ ላይ ሆነው ለመዋጋት ተሰማሙ። ደጃች አያሌው የጥምር ጦሩን ሀላፊነት እንዲወሰዱ ተደረገ።

ደጃዝማች አሁን በችሎታቸው ወይም በሙያቸው ላይ ነው ያሉት። ለመጀመሪያ ጊዜም የራሳቸውን ሙሉ ሀይልና የመምራት ችሎታቸውን ሊያጠናከሩ ነው። ለመጀመሪያ ጊዜም ነፃ ሆኑ የሁሉም ነገር አሰተዳዳሪ እሳቸው መሆናቸው ተሰምቷቸዋል። በሚያሰገርም ፍጥነት የሁለቱን ጦር በየከፍሉ ከፋፍለው የሚደባለቀውን አደባልቀው አደራጁት። ሰንት ቦታ መመራት እንዳለበት የትኛው የጦር ክፍል ደግሞ የሚለማማው ቦታ የትኛው



እንደሆነ በትክክል አውቀውታል። ከዚህ በፊት የአካባቢውን ገበሬዎች ጠይቀው ሰለነበር የእያንዳንዱን ቦታ ጋራውን ወንዙን ሸለቆውን የአርሻ ቦታውን ሰም አቀማመጡን አውቀዋል። አያሌው ከሳምንታት በፊት አሰቀድመው ወሳኝ ጦርነት በዚህ ማለፊያ በር ላይ እንደሚደረግ ደርሰውበታል።

ሁሉም ነገር ተደራጅቶ ሲያልቅ የተለያዩት የጦሩ ክፍሎች በጨለማው እየተሳቡ ወደፊት በመሄድ ቦታ ቦታቸውን ያዙ። ሁለቱ የጥንት መድፎች ጋራው ላይ በማለፊያው በቀኝ በኩል እንደማይታዩ ተደርገው ተጠምደዋል። ለመሸፈን መሞከሩ እንኳን ጥቅም የሌለው ድርጊት ነው ምክንያቱም ባሩዳቸው ሲጨስ ያሉበትን ቦታ ሰለሚያጋልጥ ነው።

ሰአቱ ከንጋቱ አሰር ሰአት መሆኑን ያሳያል። የምሥራቁ አድማሰ ደግሞ ንጋት መምጣቱን ለማብሰር ፈጋ እያለ ነው።

ያለንበት ቦታ እንደቆምን ቆየን የደጃዝማች አምሰት መቶ ዘቦችና የራሰ አምሩ ተመሳሳይ ቁጥር ዘቦች በዙሪያችን አሉ። ሁለቱም የጦር አዛዦች ለረዥም ጊዜ በዝምታ ቆመው ነበር። አያሌው ቀና ብለው "የለም አሁን በዚህ በጋራው አካባቢ የሚገኝ ዋሻ መፈለግ አለብን" አሉ።

ይህንንም ቢሆን አሰቀድመው አሰበውበትና አቅደውት ነበር

ያለምንም ችግር ዋሻውን አገኙ ግን መጠኑ ትንሽ ሆነ። ቢበዛ ሀያ ሰዎች ብቻ ነው ሊያሰጠልል የሚችለው ሰለዚህ ወታደሮቹ ተበታትነው ከዛፎች ስር ወይም ከድንጋዮች ጀርባ መጠለያ እንዲፈልጉ ታዘዙ።

የዋሻው መግቢያ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ነበር። ፊልገን የምሥራቁን አቅጣጫ አገኘን። ቦታው የጋራው አናት ላይ ሆኖ በትልልቅ ድንጋዮች የተከበበ ነበር። ክዚህ ሆኖ አንድ ሰው ሳይታይ ሰለሀለሀን ማየት ይችላል።

ከጋራው ወደታች ግማሽ ኪሎሜትር ሰፋት ያለው ሜዳ አለ። ትንሽ ወንዝ በዘምባባ ዛፎች ተሸፍኖ ከሜዳው በሰተቀኝ በኩል ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ይወርድና ከሌላ ከሰሜን ምሥራቅ ከሚመጣ ወንዝ ጋር ይገናኛል። በቀጥታ ከፊት ለፊታችን የአቃቢ ሰአት የአዲ ሀይማነል እና የሰለሀለሀ ጋራዎች ወደ ላይ ቆመዋል። የሰለሀለሀ ጋራ የአፍ ጋጋ ማለፊያን አልፎ በግራ በኩል እኛ ካለንበት ዝቅ ብሎ ነው የሚገኘው።

ብርሃን እየጨመረ ሲሄድ ጣልያኖች ያሉበትን ቦታ ማየት እንችል ነበር። የተቆፈሩ ጉድቦች መከለያ ግንቦች የጋራው ወገብ ላይ በተራ ተሰርተውና




*የሰለከለካ ግንባር ከጣልያኖች በኩል የተነሳ ፎቶግራፍ በሚገርም ሁኔታ ፀሃፊው እንደገለፁት የጭነት መኪኖች አቧራ ማስነሳትና ስለ ታንኮች አሰላለፍ በትክክል ያሳያል (በሰባስቲያን ኦኬሊ Sebastian O'Kelly) መልካም ፈቃድ*



ተዘጋጅተዋል:: ስላሳ ታንኮች ወደኛ ዞረው ዝቅ ብለው የሚዳው ጫፍ ላይ ቆመዋል::

ተኩሱ ለረዥም ጊዜ ቆሞ ስለነበር የሚሰማ ድምፅ አልነበረም:: በዚያች ውብ የንጋት ሰአት ላይ ሁሉም ነገር ሰላም ይተነፍስ ነበር:: ማዕበል ከመምጣቱ በፊት እንደሚሰፍነው ፀጥታ ነው:: ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት ማለቂያ የሌለው የሚመስል የጭነት መኪኖች ሰልፍ ከአከሱም በኩል እያጉረመረመና የአቧራ ጉም እያቦነነ ሲመጣ አየን:: መኪኖቹ ጉድቦቹ የተቆፈሩበት ቦታ ሲደርሱ ያቆሙና ወታደሮችን ያለማቋረጥ ያራግፉ ነበር:: ሥርአት ያለው አደረጃጀት ነበር:: የጭነት መኪኖቹ እንደአመጣጣቸው ወዲያው ተመልሰው ይሄዳሉ:: ወታደሮቹ ይሰበሰቡና በሥርአት በሰልፍ እየሆኑ ወደ ምድብ ቦታቸው ይሄዳሉ:: አልፎ አልፎ ጩኸት ይሰማል:: ሁሉም ነገር እንደ ሞተር መኪና ነው የሆነው ያለምንም ውዥንብር በፍጥነት ነበር የሚካሄደው::

ደጃዝማች ተመስጠዋል:: የጠላትን እንቅስቃሴ ትንፋሻቸው የሚቆም እስከሚመስል ድረስ በከፍተኛ ትኩረት ሲከታተሉ ነበር:: ፊታቸውን ሳያዞሩ እጄን ይዘው እስከሚያመኝ ድረስ ጨበጡኝ:: አዎ አኔም በሚገባ ተረድቻቸዋለሁ:: በተፈጥሮአቸው የጦር አዛዥ የሆኑ አኝህ ሰው በቅናት ይንገበገቡ ነበር:: እንደዚህ አይነት የተደራጀ ጦር የመምራት አጋጣሚ አልነበራቸውም:: ቢሆንማ ኖሮ ለንጉሡም ሆነ ለአባት አገራቸው ችሎታቸውን ያሳዩ ነበር:: በተቃራኒው ያልተደራጁና ያልሠለጠኑ ሰዎችን መምራት ነበረባቸው:: እነዚህ ወታደሮች ደግሞ አግራቸው ላይ እንደ ጭነት ነበሩ:: ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ትልቁ ሸክም አገሩን ከድቷል ተብለው መጠርጠራቸው ነው::

በመሀሉ ጣልያኖቹ በዘምባባ ዛፎች ውስጥ በወንዙ አካባቢ የኛ ግንባር ጦር ተደብቆ ባለበት ቦታ እንቅስቃሴ ያዩ ይመስላሉ:: ሁሉም ታንኮች አውቶማቲክ መሳሪያቸውን መተኮስ ጀመሩ:: ወደ አርባ የሚሆን ፈጣን አሩምታ ተኩስ እኛ ወዳለንበት ጋራ ዳገት ላይ ተኮሱ::

ማዕበሉ ጀመረ:: ገና ቃል ሳንተነፍስ ከኛ መጠለያ ፊት ለፊት ብዙት ያለው ፍንዳታ ጀመረ:: የሚያስነሳው ጠጠርና አቧራም እንደዝናብ ላያችን ላይ ይወርድ ጀመር::

ቡም! ቡም! ከኛ መድፎች የመጣ ድምፅ ነበር:: ሁለቱ በደንብ የተነጣጠሩ ተኩሶች ስለነበሩ እያንዳንዳቸው ታንክ ሰባበሩ:: ቀጥሎም ፈጠን ያለ አፀፋ እጠገብ በነበሩ አስር ቦታዎች ተሰማ::

ፀሀይ በዝግታ ወደላይ እየወጣች ነበር፡፡ ከጥዋቱ ሶስት ለአት ሲሆን የኛ መድፎች በተርታ የተሰለፉንትን ታንኮች ወደ ምዕራብ እንዲያፈገፍጉ አስገደደዷቸው፡፡ የመሀል ጦራችን ጠላትን ከመሀል ጋራው እንዲሸሽ አድርጎታል ሆኖም ተደራቢ ረዳት ጦራቸው ተጨምሮ ከአንድ ሰአት ሀይለኛ ውጊያ በኋላ መልቀቅ ነበረብን ነገር ግን እስከጋራው ግርጌ ድረስ ብቻ ነበር፡፡ በግራ በኩል ያለው የጎጃም ጦር ደግሞ ጠላትን ብዙ መቶ ሜትሮች እንዲያፈግፍግ አለደርጎ ቦታውን ተቆጣጥሮ መከቶ ይዟል፡፡ ጠላት ብዙ ወታደሮች ማምጣት ጀምሮ ስለነበር ተጨማሪ ሀይልም ይፈለግ ነበር ፡፡ ተጨማሪ ሀይል ከየት ይመጣል? ዳገቱን የያዘው የደጀን ጦራችን ሜዳው ተኩሰ በተኩስ ስለሆነ ለቆ መውጣት አልቻለም፡፡ ሞከረው ነበር ነገር ግን በየጊዜው ወደኋላ መመለስ ነበረባቸው፡፡

ከቀኑ እምስት ሰአት ሲሆን ጣልያኖቹ ውጊያውን ወደ ምዕራብ በኩል ወደተራራው ግርጌ ለመግፋት ሲሞከሩ አስተዋልኩኝ፡፡ አቅዳቸውን ለመረዳት ቀላል ነበር፡፡ ከሰአት በኋላ ሲሆን ማለፊያውን ዘግተው መሸሸ እንዳንችል ለማድረግ ነው፡፡ ከዚያ ደግሞ ዙርያውን የከበበው ጦር ከምዕራብ አቅጣጫ መጥቶ ሌሎችን እንዲቀላቀል ነው፡፡

ምንም ያህል ጉዳት ይድረሰ ፊታውራሪ ዘውዱ ጎጃሞችን እንዲረዱ ታዘዙ፡፡ ከሁለት ሺ ሰዎች ጋር በመሆን እየጋለቡ ቁልቁል ወደ ሜዳው ወረዱ፡፡ ያለ ምንም ፍራቻ በተኩሱ መሀል ወደ ፊት ገሰገሱ ማዶ ሲሻገሩ ግን ግማሽ ሰዎቻቸው እልቀዋል፡፡ ብዙዎቹ ሞተዋል ሌሎቹም ወደኋላ ተመልሰዋል፡፡ ዘውዱ ሲጋልቡት የነበረው በቅሎ በጥይት ጭንቅላቱን ተመቶ ወዲያው ሞተ።

ዘውዱ በሚያጠቁበት ወቅት ደግሞ የራስ እምሩ ጠባቂ ጦር የጠላትን የምዕራብ ጎን እንዲያጠቃ ታዘዘ፡፡ የራስ እምሩ ጠባቂዎች የንጉሡ የክብር ዘበኛ አባሎች ናቸው በአዲስ አበባ ዘመናዊ የአውሮፓ ወታደራዊ ሥልጠና የተሰጣቸው ነበሩ፡፡ ወታደሮቹ በተማሩት መሰረት ምሰጋና በሚገባው ሁኔታ መዋጋት ጀመሩ፡፡ የቦታውን አቀማመጥ በመጠቀም የጣልያኖችን ሬጅምንት ማጥቃት ጀመሩ፡፡ በመጀመሪያው ድንጋጤ ጠላት የነበረበትን የመጀመሪያውን ጉድብ ሲለቅ ጠቅላላ ለቆ የሚሄድ መሰሎ ነበር፡፡

ከቀኑ ሰድስት ለአት ሲሆን ከዋሻችን መግቢያ ቁጭ ብለን ምግብ ቢጤ ለመቅመስ እየሞከርን ነበር፡፡ ምን መሆኑን አስከምንለይ ድረስ ያለምንም



ማስጠንቀቂያ ለላይ አውሮፕላን እንደ ጭልፊት ቁልቁል ወደኛ ተወረወረ፡፡ ከንሮቹ ለጥቂት እለቱን ነከተውት ነበር፡፡ አውሮፕላኑ ተመልሶ ሲመጣ ገና ወደ ዋሻው ተመልሰን እየገባን ነበር በዚህ ጊዜ ግን አውቶማቲከ መላሪያ እየተኮለብን ነበር፡፡ ብዙ ጥይቶች እየነጡሩ የዋሻውን ጣሪያ መቱት፡፡ አውሮፕላኑም ተመልሶ አልመጣም ግን ተገኘን እነሱም እዛ ዋሻ ውሰጥ ማን እንደተደበቀ አውቀዋል፡፡

ብዙም አልቆየም ምናልባትም እንድ ለአት ተኩል ይሆናል እያፏጨ ቦምብ ሲወርድ መሬቱ እንደምድር መንቀጠቀጥ ይርድ ነበር፡፡ በጥንቃቄ ወደ ውጭ ተለመለከትኩ፡፡ ከኛ ሀያ ሜትር ርቀት የነበረ ዛፍ በቁሙ ተሠንጥቋል፡፡ ከስሩ ግን ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የሚተነፍስ ለው የነበረ ወድቋል፡፡ ከጭንቅላቱ አገጬ ብቻ ነው ጥርስ እልባ ሆኖ አንገቱ ላይ ተንጠልጥሎ የሚታየው፡፡ የግራ እጅና የግራ እግሩ እስከ ጭኑ ድረስ የሉም፡፡ በግራ ጎን ደረቱ ተከፍቶ አንጀቱ ይታያል፡፡ የጎራዴው ግማሽ እንኳን ሳየቀር የለም፡፡

ማን እንደነበረ እውቄአለሁ፡፡ ከአጭር ጊዜ በፊት በፈገግታ ተለያይተናል፡፡ እሱም ልጅ ይሻል ነበር ከእድዋ የነጋዴ ልጅ ነው፡፡ ከልጅነት ጓደኞቼ አንዱ ሲሆን የደጃች አያሌው ጦር ውሰጥ ተሰልፎ እያገለገለ ነበር፡፡

አውሮፕላኖቹ ግን ለትዝታ ጊዜ የሚሰጡ አልነበሩም፡፡ እንደ መጥፎ የዝናብ ነጎድጓድ እያጓሩብን የሚወረወር የእሳት ነበልባል በአይናችን እያየን መሬቱም እየተንቀጠቀጠ ጥቅጥቅ ባለ አቧራ ጉም ታፈን፡፡ የነበረንን የጋዝ ጭምብል አድርገን ነበር ግን መልሰን ማውለቅ ነበረብን፡፡ በጣም ይሞቅም ነበር፡፡ እንደገናም የጭምብሎቹ አየር መዘዋወሪያዎች በአቧራ ተደፍነው ነበር፡፡

መቼ እንዳቆመም አላውቅም ለብዙ ደቂቃዎች ፋታ አግኝተን ነበር እንደገና ተመላሳይ አስፈሪ ድብደባ ሲጀመር፡፡ ድብደባው በዋሻው ጣራ ላይና በጀርባው በኩል ነበር አውሮፕላኖቹ እንደገና ቦምብ ለመጫን ሲመለሱ መድፈኛው እንዲደበድብን ታዞ ነበር፡፡ የነበርንበትን ቦታ አውቀዋል፡፡ ቶሎ ቶሎ አሁንም አሁንም ቦምብ ሲወርድብን ጠቅላላው ዋሻ ይንቀጠቀጣል እኔም እለቱ የተሠነጠቀ መሰሎኝ ነበር፡፡ እለቱ ችሎ ይቋቋመው ይሆን? ወይስ ተደርምሶ ይቀብረን ይሆን? እሰቃቂ ስሜት ነበር!

ነገር ግን ያ ብቻ አልነበረም፡፡ ጠላት ጣራው ላይ መድፍ ይተኩስ ጀመር እርላሶችም መግቢያው ላይ ይፈነዱ ጀመር መውጫውን ለመዝጋት ነው ሀሳባቸው፡፡

ያን ቀን ዋሻውም ሆነ እኛ ራሳችን ያን ሁሉ ነገር እንዴት እንደቻልነው አይገባኝም:: ድምፁን በደንብ እልሰማም ነበር ከባድ ራስ ምታትም ተከትሎ መጣ:: በቦምብ ውርጅብኙ የተናወጠው እንጎላችን በደንብ መሥራት ያቆመ ይመስላል ምናልባትም ለዚያ ይሆናል ከእብደት የተረፍነው:: እኔም ምንም አይነት ስሜት በጭራሽ አልነበረኝም ኩርምትምት ብዬ ያለምንም መንቀሳቀስ ቁጭ አልኩኝ:: እንደፈለገው ይሁን:: ከዚህ የባሰ አይመጣም:: ሞት አረፍት ነው ብዬ አሰብኩ:: ሁላችንም ብንሆን ሞትን የተመኘን መሰለኝ::

ራስ አምሩ እግራቸውን አጣምረው አገጫቸውን በእጆቻቸው ደግፈው ጎላ ያሉ አይኖቻቸው አንድ ቦታ ተተክለው ቁጭ ብለዋል:: ፈገግም ያሉ ይመስላል:: ጨለማና ጭንቅ ያለ ነገር ቢሆንም እርጋታ ነበር:: አልፎ አልፎ አግር አቀማመጣቸውን አየቀየሩ ድምፅም ያሰሙ ነበር:: የሚያሰቡትን ነገር ለማወቅ አስቸጋሪ ነበር:: ምናልባትም የዮሐንስን ምክር መስማታቸው ፀፀቷቸው ይሆናል:: ሁላችንም አየመሩ ወጥመድ ውስጥ እንዳስገቡን እያሰቡ ይሆን?

ደጃች አያሌው ጠንካራ ከሆነው ከወገብ በላይ ሰውነታቸው ጋር በሃሳብ ተውጠው ተቀምጠዋል:: የውጊያውን ሁኔታ መረጃ ለመስማት እየጠበቁ ያለትግሰት ጣቶቻቸውን እያጠፉ ይዘረጉ ነበር:: ረዳቶቻቸው ሳይታከቱ እየሾለኩ ይመጡና ዜና ያቀርባሉ ጥያቄም ይጠየቃሉ አንደገና ደግሞ ከደጃዝማቹ አዲስ ትዛዝ ይቀበላሉ:: ምንም እንኳን ራሳቸው ማየት ባይችሉም የመላው ጦሩን እንቅስቃሴ የት አንዳለ ርዳታ ይፈልጉ አንደሆን መረጃ ያገኛሉ:: እኔ እንደማስበው ከሆነ ራሳቸውን እንዳመማቸው ቢናገሩም ከመሀከላችን አሳቸው ብቻ ነበሩ ከማሰብ ችሎታቸው ጋር የነበሩ::

የንስሐ አባትየውና ሁለት የጦር አዛዦች ደግሞ አጠገቤ ተቀምጠው ሲፀልዩ ይሰሙ ነበር:: ከሁሉም ቅዱሳኖች ቅዱስ ጊዮርጊስ ነበር በብዛት የሚጠራው:: *ቅዱስ ጊዮርጊስ የአቢሲኒያ የጦር ጠባቂ ነው:: በ1888 አመተ ምህረት በሱ ቀን ነበር የአድዋ ጦርነት የተካሄደው አናም በሱ እርዳታ በውጊያው ድል ተገኝቷል:: አሁን ደግሞ ያንን ቀን በማስታወስ ቅዱስ ጊዮርጊስ አየተነሳ ነው:: በፀሎት አሁን በተከታዮቹ ጎን እንዲቆም ጥሎ አንዳይጥላቸው አየተጠየቀ ነበር::

---

** የቅዱስ ጊዮርጊስ ምስል የተጠለፈበት ጨርቅ እንደ ጦር አርማ ይወሰድ እንደነበርና በ1927 አም መሐል ሠፋሪ ተብሎ ለሚጠራው ጦር በስጦታ መልክ እንደተሠጠ ተዘግቧል:: ይህንን የሚሳይ ፎቶግራፍ በመፅሐፍ ይገኛል*

*1935 Invasion of Abysinia, David Nicole*



ከቀኑ አስር ሰአት ሲሆን አልፎ አልፎ ከተናጠል አውሮፕላኖች ከሚጣለው ቦምብ ፍንዳታ ድምፅ በስተቀር ከዋሻው ድብደባ ለአንድ ሰአት የሚሆን ፋታ አግኝተን ነበር :: እሁን ጠላት በግራ በኩል በብዙ ወታደሮች እያጠናከረ ከመሆኑ በስተቀር አሰላለፉ ያው እኩለ ቀን ላይ እንደነበረው ሆኖ አናያለን:: ከፍተኛ ግፊት ቢኖርም የራስ አምሩ ጠባቂዎች ተቋቁመው ነበር ነገር ግን ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ስለሞቱ በቅርቡ የመጨረሻ ሀይላቸው እንደሚሟጠጥ ነው ስለዚህ የደጃማች አያሌው ጠባቂዎች ለርዳታ መላክ ነበረባቸው::

የኛ መሀል ጦር ደግሞ ወደ ምዕራብ በኩል ተንቀሳቅሶ ከግራ ከንፍ ካለው ጦር ጋራ ጎን ለጎን ሆኖ አየተዋጋ ነው:: አንደ መረጃው ከሆነ ሁሉም ወታደሮች የሚያኮራ ጀግንነት አሳይተዋል::

የጠላት የቀበሮ ጉድጓዶች በተያዙበት ጊዜ ብዛት ያለው ንብረት እንደ ጠመንጃ፣ አውቶማቲክ መሳሪያና ጥይቶች ተማርከው ነበር:: ችግሩ በእጅ ቦምቦቹ ምክንያት ሰዎቹ ቦታ ለመልቀቅ ይገደዱ ነበር:: የእጅ ቦምቦችም ቢሆን በብዛት ተማርከው ስለነበር መልሰው ወደ ጠላት ይወረወሩ ነበር:: በርግጥ የሠይጣን ሥራ ናቸው ምክንያቱም የሚፈነዱት ጣልያኖቹ ሲወረውሯቸው ብቻ ነበር:: ከመወርወሩ በፊት ቀለበቱን መመንጨቅ እንዳለባቸው አቢሲኒያውያኖቹ ገና አልደረሱበትም ነበር::

በወንዙ በኩል የነበሩ ሰዎች ከሚታመን መጥን በላይ እንደሞቱም ተነገረን:: እኔም ወደ ጫካው ዞር ብዬ ከተመለከትኩ በኋላ ብዙ ሰው ስለመሞቱ ምንም ጥርጣሬ አልነበረኝም:: ያን ቀን ጠዋት ለምለምና አረንጓዴ የነበረው ጫካ የተሰባበሩ ግንዶች ብቻ ቀርተውበት ይታያል::

በአሥራ አንድ ሰአት እየዳህን መውጣት ነበረብን:: እሰቃቂው ድብደባ እንደገና ጀምሮአል:: በአሥራ ሁለት ሰአት በቀኝ ከንፍ ያለው የኛ ጦር ረጅም ጊዜ መከቶ መቆየት አንደማይችል የሚገልፅ መልከት ደረሰን:: ጣልያኖች ከነበራቸው ሀይል በእስር እጥፍ ጨምረው አያጠቁ ነው:: ደጃዝማች አንዳሉት እሁን መውጫ መግቢያውን ሊዘጉት ነው::

ለርዳታ የሚላክ የደጅን ጦር የለም ስለዚህ በመሀል የተሰለፉት ፈታውራሪ ዘውዱና ሙላው ቦታቸውን ለቀው የቀኝ ከንፉን እንዲያግዙ ታዘዙ:: ወደኋላ ለማፈግፈግ አንዲረዳ እስኪጨልም ድረስ መከቶ መያዝ አስፈላጊ ነበር:: ዙርያውን ከበባ ለማድረግ የሞከረው የጣልያን ጦር ወሬ የለም:: የት ቦታ

እንደሆኑም ማንም አያውቅም፡፡ ፊትለፊት እናገኛቸው ይሆን? ወይስ ከነሱ መራቅ እንችላለን? አውሮፕላኖች እንደ ጉድ በአየር ላይ እያንዣባቡ ባሉበት ሰአት ወጥቶ ለመሄድ መሞከር የማይታሰብ ነው፡፡ ጨለማ እስኪገባ የቀኝ ከንፉ ያለበትን ቦታ ተከላከሎ ይጠብቅ ይሆን?



በራስ ካሳ ግንባር የእጅ በምብ ሲወረወር በጣልያኖች የተሣለ (ምስጋና ፋሲል ጊዮርጊስ)

እንደኔ ከሆነ ያን ቀን ፀሀይዋ እንደዚህ ተዝናንታ ዝግ ብላ ወርዳ አታውቅም፡፡ ሌላ ጊዜ አጭር የነበረው የቀን ብርሃን ለዕድሜ ልክ ረዥም መሰለ፡፡ አውሮፕላኖችም ቢሆን ሲመሽ ጨለማው ሳይገባ ወደ ቤታቸው መሄድ ያለባቸው መሆኑን የዘነጉት ይመስላሉ፡፡



ቢሆንም ሁለም ቀን ማቆሚያ እንዳለው ሁሉ ይህ ቀንም አቆመ፡፡ ወደኋላ የማፈግፈግ ትዛዝ ሲሰጥ ገና መጨለም አልጀመረም፡፡ መድፎቹ ከሌላ ጊዜ በላይ እንደነጎድጓድ ይጮሃሉ፡፡ የጣልያን ባውዛ መብራቶችም ሥራቸውን ጀምረዋል፡፡ ያ ሁሉ መድፍ እየተተኮሰ ከዋሻው ሾልከን ወጣን ጋራውን ቁልቁል ወርደን ሜዳው ላይ ወደሚጠብቁን ፈረሶቻችን ሄድን፡፡ ቃኝ ጦር ፊት ለፊት ተልኮ ስለነበር እነሱን መከተል ጀመርን፡፡

ጨረቃዋ ጥርት ባለው ለማይ ላይ ታበራለች፤ ሁሉም ነገር ሰላም የሚያበስር ይመስላል፤ እኛም ግልቢያችን ቀጠልን፡፡ ከኋላችን የሚጮኸው የመድፍ ድምፅ ብቻ የቀኑን ውሎ ያስታውሰን ነበር፡፡

ወዲያውኑ ወታደሮች እየሮጡ እኛን ማለፍ ጀመሩ፡፡ ማንም ሰው ሊያስቆማቸው አይችልም ነበር፡፡ ሁሉም ወደ ማረፊያ ቦታቸው ነበር የሚሮጡት፡፡ ቀን መከተው በመዋላቸው ረከተዋል ደግሞም ደከመዋል፡፡

ከምሽቱ አንድ ሰአት ተኩል ሲሆን ትልቅ ዋሻ ያለበት ቦታ ደረሰን፡፡ ተቀመጥን ግን በሀሳብ ተውጠናል፡፡ በየቦታው ጩኸትና ትዛዝ ነው የሚሰማው፡፡ "ጫን!" የማፈግፈጉ ትዛዝ ጭንቀት ፈጥሯል፡፡ ሁሉም የሚሮጠው የሚይዘውን ይዞ ወደ ቤቱ ለመሄድ ነው፡፡ ለነሱ ጦርነቱ አብቅቷል፡፡ ሙሉ ቀን በዋለው ውጊያ ጠላት አላፈገፈገም እና ባለድል የሆነ ይመስላል፡፡ በሚመጡት ቀናት ከእንደዚህ አይነት አስደንጋጭና አስከፊ ሁኔታ ለማምለጥ ወታደሮቹ ከማድረግ የሚቆጠቡት ነገር የለም፡፡ ወደ ደቡብ የሚጎርፈወን ሰው ለማስቆም የተደረገ ሙከራ ሁሉ አልሰራም፡፡ መንገደኛውን ለመመለስ የተላኩ ወታደሮች ችግር ላይ ወደቁ እንዲያውም ሁለቱ በጥይተ ተመተው ወደቁ፡፡ በብዛት ለሚጎርፈው ሰው መንገድ መልቀቅ ነበረባቸው፡፡

ሴቶቹ የባሱ ነበሩ፡፡ "ሩብላ" የሚባል ነገርና "ጥልያን" የሚባል ነገር የሚበቃቸውን አይተዋል፡፡ ለነሱ በረሀ ሲጓዝ ውሃ ያለበት ቦታ እንደሚጠራው መንገደኛ ቤታቸው ጠርቷቸዋል ፡፡

ሁለቱ የጦር አዛዦች አማራጭ አልነበራቸውም፡፡ ወታደሮቻቸውን ካልተከተሉ ሁለት ሰአታት በማይሞላ ጊዜ አስር ከማይሞሉ ታማኝ አሽከሮቻቸው ጋራ ብቻቸውን ወደኋላ እንደሚቀሩ ነው፡፡

ያን ቀን ማምሻውን ደጃዝማች አያሌው (ራስ እምሩም ሳይደርሳቸው አይቀርም) ከንጉሡ የተላከ ደብዳቤ ይደርሳቸዋል፡፡ በደብዳቤውም ጣልያኖች በሚቀጥሉት ቀናት ትልቅና መጠነ ሰፋት ያለው ጥቃት ለማድረግ እያሰቡ

መሆኑን ይገልፃል፡፡ አያሌው ያሰቡት እንዲህ አይነቱን ጥቃት ለመቋቋም አስቸጋሪ ስለሆነ የሰው ሕይወት በከንቱ ከሚጠፋ ወደኋላ ወደ ተከዜ ወንዝ እንመለስ ነበር፡፡ ደብዳቤው ደግሞ የተፃፈው ከአንድ ሳምንት በፊት በደሴ ከተማ ስለነበር ጉዳዩ ግልፅ ሆነ፡፡

በየካቲት ሀያ ሶስት በሰለህለህ በተካሄደው ውጊያ አቢሲኒያኖች ተሸንፈዋል ወይ? የዚህ ጥያቄ መልስ ሁለት ነው፡፡ ሽንፈት ነውም አየደለምም ነው፡፡ እስኪጨልም ድረስ ጣልያኖቹ መግፋትና አዲስ ቦታ መያዝ አልቻሉም ነበር፡፡ ስለዚህ ዕቅዳቸውን አላሟሉም ነበር ምንም እንኳን የመሳሪያ ጥራትና የአደረጃጀት ልዩነትን ሳይጨምር በቁጥር ከአቢሲኒያውያን ቢበልጡም፡፡ የደጃዝማች አያሌውና የራስ እምሩ ጦር ተጣምሮ ከአስር ሺ አይበልጥም ነበር፡፡ የተረፈው ጦር ወይም ሸሽቷል አለበለዚያም በአውሮፕላን ድብደባ ምክንያት በውጊያው ሳይደባለቅ ቀርቷል፡፡ እነዚህን ያልተደባለቁትን በጠዋት ማሰባሰብ ቢቻል ኖሮ ጣልያኖቹ እስከ ሃያ ሺ የሚደርስ ወታደር ይጋረጣቸው ነበር፡፡

ነገር ግን አቢሲኒያኖች ደግሞ የመድፉን፤ አውቶማቲክ መሳሪያውን፤ የእጅ በምቡን ከሁሉም በላይ የአየር ድብደባውን ተቋቁመው ለሁለት ሶስት ቀን መቆየት ይችሉ ነበር? በፍፁም የማይቻል ነገር ነው፡፡ የእጅ በምቦች "የሙሶሎኒ ወንበዴዎች" ተብለው ይጠሩ ነበር፡፡ እናም በአቢሲኒያውያን ላይ ትልቅ ሽብር ነበር የፈጠሩት፡፡ በዛው ልክ ደግሞ የነሱ ጎራዴ ጣልያኖቹ ላይ ተመሳሳይ ሽብር ይፈጥር ነበረ፡፡ በተጨማሪም ወታደሮቹ የነበራቸው የውጊያ ፍላጎት የተዳከመ ነበር፡፡ ምክንያቱም ለአንድ ወር ያለምንም ነገር ዝም ብለው መቀመጣቸውና፤ በተከታታይ ከሚደረገው የአየር ድብደባ ተጨማሪም ጣልያኖቹ በአውሮፕላን በሚበትኑት ፕሮፓጋንዳ ወረቀቶች ጭምር ነው፡፡

በኛ በኩል የደረሰውን ጉዳት ለመናገር አስቸጋሪ ነበር፡፡ የሞቱና የቆሰሉ ቁጥር ሶስት ሺ ሊደርስ ይችላል፡፡ በጣም የተጎዳው ደግሞ የራስ እምሩ ጠባቂ ክፍል ነው ከአምስት መቶ ወስጥ ከሁለት መቶ በላይ የሆኑ ብቻ ነበር የተረፉት፡፡

በጣልያኖቹ በኩል የደረሰው ጉዳት ደግሞ በራሳቸው ዘገባ መሰረት ዘጠኝ መኮንኖች፤ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ነጭ ወታደሮችና ሁለት መቶ ሃምሳ አስካሪሶች ነበረ፡፡ የቆሰሉትን ቁጥር ማግኘት አልቻልኩም ቢያንስ ቢያንስ ወደ አንድ ሺ ይጠጋ ነበር፡፡



በየካቲት ሃያ ሁለትና ሀያ ሶስት በተደረገው ጥቃት ስለ ጣልያኖች ቁጥር ከጣልያኖች ያገኘሁት መረጃ በቀላሉ ይህን ይመስል ነበር፡፡ ጦሩ የሁለተኛውና የአራተኛውን ኮር የያዘ ነበር፡፡ መሳሪያ አርባ በፍጥነት የሚተኩሱ መድፎች ከሀምሳ ሺ አርሳሶች ጋራ፤ ሀያ አምስት ሺ ጠመንጃና አውቶማቲክ መሳሪያዎች፤ ከአሥራ ሁለት ሚሊዮን ጥይቶች ጋራ፤ ሁለት መቶ ሺ የእጅ በምቦች፤ ሶስት መቶ ስላሳ የጭነት መኪናዎችን ያካትት ነበር



*የሠለጠኑ አስካሪስ ወታደሮች ከአካባቢው ተወላጆች የሚመለመሉ የኢታሊያ የቅኝ ግዛት የንጉሣዊ ጦር አባሎች ናቸው፡፡ በኤርትራ ብቻ ሳይሆን በሶማሊያም ተመሳሳይ የተወላጅ ወታደሮች ነበሩ፡፡*

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ሁለት መቶ ሺ የሚሆን የአሸዋ ከረጢት፤ ሶስት መቶ ሺ ኪሎ ጥምዝ ባለ ሾህ ሽቦ፤ ሀያ አምስት ሺ አካፋዎች፤ አሥራ አምስት ሺ መጥረቢያዎች፤ ስልሳ ሺ ኪሎ ዳይናሚት ከስማንያ ሬዲዮች ጋራ ነበራቸው፡፡

የደጃዝማች አያሌው መድፎች ስልሳ ጊዜ ከተኮሱ በኋላ አኩለ ቀን ላይ ድምፃቸው ጠፍቷል፡፡ የአየር ድብደባው የመድፎቹን ተሸካሚ ተሽከርካሪዎቻቸውን ሰብሮታል የአንደኛው አንዱን ሲሆን የሌላኛውን ሁለቱንም ነበር፡፡ መድፎቹ ማራኪዎቻቸውን ለአርባ አመት በታማኝነት ካገለገሉ በኋላ ጣልያኖቹ የመድፎቹን ከሃዲነት ያን ቀን በመበቀል ለእድሜ ልክ ፀጥ እንዲሉ አድርገዋቸዋል፡፡

የመድፎቹ ስባሪ ተይዞ ከኛ ጋራ እንዲጓዝ ተደርጓል፡፡ ምክንያቱ አልገባኝም፡፡

# ምዕራፍ አሥራ ስምንት

## ማፈግፈጉ ተጀመረ

የኛን ወደኋላ መመለስ ቆርጦ ለማስቀረት ከመረብ ተነስቶ ስለሚመጣው የጣልያን መካናይዝድ ክፍል ምንም አይነት መረጃ አልደረሰንም:: (ከአራተኛው የጣልያን ኮር የተውጣጣ ነበር) መልከአ ምድሩ እንዳስቸገራቸው አላወቅንም:: መንገድ ለመጥረግም አንድ ሺ ሁለት መቶ ነጭ መንገድ ሰሪዎች ይዘው ነበር፡፡ በመንገዱ ምክንያት አንድ ሙሉ ቀን ሳይንቀሳቀሱ ውለዋል:: እኛም ያሉበት አካባቢ እንዳ ሰላሴ ሊሆን ስለሚችል ደህንነት ያለው መንገድ በደቡብ በአዲ ረሲ በኩል መሆን አለበት ብለን ወሰንን:: መንገዱ ጠባብ ነበር:: አስቸጋሪ ቁልቁለቶችም ነበሩት ቢሆንም ግን ጠላት እኛን ለመከተል አስቸጋሪ ይሆንበታል::

የጭነት ከብቶች እጥረት ጉዟችን አዘገየው:: በመጨረሻዎቹ ሁለት ቀናት የአየር ቦምብ ድብደባ ከጠበቅነው በላይ ብዙ ሞቱብን:: ህክምና ቡድኑ ከነበረው ዘጠኝ አህዮች አራት ብቻ ነበር የተረፉት::

በደጃዝማቹ ጥረት ችግሩ ወዲያውኑ በቀላሉ እንዲስተካከል ሆነ:: ማንኛውም ትርፍ እቃ ወይም ንብረት እንዲቀር ተወሰነ:: እኔ ራሴ ከነበረኝ ንብረት ከጦር ምርኮ በገንዘብ የገዛሁዋቸው ታይፕ መፃፊያና የሙዚቃ ማጫወቻ ፎኖግራፌን መተው ነበረብኝ:: የቆዩ ሞዴል ጠመንጃዎች ጥይቶች በሙሉ በምስጢር መሬት ውስጥ እንዲደበቁ ተደረገ:: የአካባቢው ገበሬዎች የተደበቀውን ንብረት ምናልባት አግኝተው ተከፋፍለውት ይሆናል ጣልያኖቹ ግን አላገኟቸውም::

በሶስት ሰአት ኮርቻችን ጫንን:: አይን ማየት እስከሚችለው ድረስም ከፊትና ከኋላችን ሰዎችና ከብቶቻ በመስመር ይጓዙ ነበር:: ብዙዎቹ ወታደሮች በውጊያው ያልተካፈሉ መሆናቸውን በቀላሉ ማየት እንችል ነበር:: በደንብ ያረፉና ደህና ናቸው የተዝናኑ ይመስላሉ:: ዝናራቸው ሙሉ ነው:: ጠመንጃቸውም አዲስና እንደተወለወለ ነው:: ጓደኞቻቻው ከጉልበተኛ ጠላት



ጋር ሀይለኛ ውጊያ ሲያደርጉ የት ነበሩ? ይህ በማያቋርጥ ሰልፍ የሚጓዘው ሰው በሙሉ ከሽንፈት የተረፈ ጦር ነው ብሎ ተመልካች ያስብ ይሆን?

አይደለም! በአስር ሺ የሚቆጠሩ አባት ሀገራቸው የጣለባቸውን እምነት የከዱ ወታደሮች ነበሩ:: ጉልበታቸው ሳይደክም፤ የታጠቁትን ጥይት ሳይጠቀሙ ያስቡ የነበረው እስከ አሁን ድረስ ካልተሸነፈ ጠላት ፊት ሸሽቶ መሄድ ብቻ ነበር:: ማንም ያዘነ አይመስልም:: ማንም ቢሆን ይህ ወደኋላ ማፈግፈግ ወይመ መሸሸት ለአቢሲኒያና ለህዝቦችዋ ምን ማለት እንደሆነ ያስተዋለ የለም:: ይዘፍናሉ:: ይቀላለዳሉ:: ወሬ እያወሩ ሰላመለጡ ብቻ እርስ በርሳቸው እንኳን አወጣህ ,ይባባላሉ::

አልፎ አልፎ እነዚያ ውጊያው ላይ የነበሩ ሰዎች ሰላደረጉት ነገር ወይም ጓደኞቻቻው  ሰላደረጉት ነገር ይፎከራሉ ጉራም ይነዛሉ:: "ታውቃለህ ጣልያኖች ተጋድመው ከመሸጉበት ጉድጓድ ላይ ለማጥቃት ከመጀመሪያዎቹ አንዱ እንደሆንኩ"

"አንድ ሰላቶ የሙሶሎኒ ቦምብ ወረወረብኝ:: ከነዚያ ቀይ ኳሶች አንዱን፤ ሲወራ ሰምታችሁ ይሆናል፤ ጎንበስ ብዬ በላዬ አልፎ እንዲሄድ አደረግሁት፤ ዘልዬ የዚያን የተረገመ አንገት ቀላሁት! ደሙን ከጎራዴዬ መጥረጌ ነው እንጂ ታዩት ነበር:: ካላመናችሁኝ ጓዴን በቀለን ጠይቁ:: አሰቡት ብቻ የጣልያን አንገቱ ሲቆረጥ ሁል ጊዜ 'ማማ ሚያ' ብሎ ይጮሃል"

ሳቅና እንኳን ደስ ያለህ

ለመረዳት እንኳን የማያስቸግር የአእምሮ ለውጥ በነዚህ ሰዎች ላይ ሰፍኗል:: ግዴታቸውን ባይፈፅሙ እንኳን እንዳው አጠገብ በሆኑም ይበቃ ነበር:: አሁን ሁሉም ነገር አልቆለታል:: የነበረባቸው ሸክም ተነስቷል እና ዕድለኞች ነን ብለውም ያስባሉ:: እውነቱ ቢነገር እኛም ብንሆን በእንደዚህ አይነቱ አእምሮ አስተሳሰብ ተለክፈናል::

በአብዛኞች ሌሊቶቹ መድፎች ሲተኮስ የተተኮሰው እርሳስ ተራራው ላይ ሲያርፍ እንሰማለን:: ብርሃን የሚያበሩ የምልከት ሮኬቶች በአድማሱ ላይ በተከታታይ ይበራሉ:: የአፍ ጋጋ ማለፊያ በር እስከአሁን ክፍት ነው:: ወታደሮች የቆሰሉትን ይዘው ይመጣሉ:: ሌሎች ደግሞ በጨረቃ ብርሃን ተመልሰው የሞቱትን ይቀብራሉ::

ከአክሱም የሚመጣ መንገድ እኛ ካለንበት አንድ ማይል ርቀት ነው ያለው:: ነገር ግን የኛን መመለስ ለመቁረጥ በተዘጋጁ የጣልያን ወታደሮች የተሞላ ነው:: ወደ አንድ ሺ የሚሆኑ የኛ ወታደሮች ተሰብስበው  ከሰላሳ

አውቶማቲክ መሳሪያ ጋራ ቀድመው ተላኩ፡፡ አጋጣሚ ሆኖ ፍራቻችን ትክክል አልነበረም ሁሉም ነገር ፀጥ ያለ ነበር፡፡ ያ ሁሉ ሰው አያለፈ እኛም ለብዙ ሰአታት ተኛን፡፡

ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት አንድ ቦታ ደረስን፡፡ ደጃዝማች እዚህ ቦታ ዋሻ አንዳለ ያውቃሉ፡፡ ስለዋሻው አንድ ገበሬ ሲጠየቅ ስለዚህ ነገር የማውቀው የለም ብሎ መሰሰ ነገር ግን በአነጋገሩና ለኛ ጥሩ አመለካከት ሰላልነበረው ውነቱን እንዳልተናገረ ግልፅ ነበር፡፡ በቀላሉ ምንም አይነት የሚጠቅም መረጃ መስጠት አልፈለገም፡፡ ስለዚህ ለማናገር ክበድ ያሰ ዘዴ መጠቀም ነበረብን፡፡

ተያዘና በሽጉጥ አሰፈራራነው፤ በአግሮቹ መሀል ሲተኮስበት የምር መሆኑ ገባው፡፡ ከሁለት ደቂቃዎች በኋላም በሸለቆው ገደል በኩል ባለ ጠባብ መንገድ ተጉዘን ሰፊ የሆነ ሶስት መቶ ሰዎች መያዝ የሚችል ዋሻ ያለበት ቦታ ደረስን፡፡ ከድንገተኛ ጥቃት ራሳችን ለመጠበቅ ወደ አንድ ሺ የሚሆኑ ወታደሮች ከዋሻው በላይ ባለ ቦታ ላይ አንዲጠብቁ ተደረገ፡፡ ግን አራሳቸውን በድንጋዮች ጀርባና በቁጥቋጦች መሀከል መደበቅ ነበረባቸው፡፡

ዋሻው ግን በአንድ በኩል ክፍት ሰለነበር በችኮላ መጠለያ የሚሆን ግንብ ተሠራ፡፡ የመጨረሻ ረድፍ ድንጋዮች አየደረደርን ነበር ልክ አውሮፕላኖቹ መተው የተለመደውን ሥራቸውን ሲጀምሩ፡፡ በሺ ኪሎዎች የሚቆጠሩ የብረት ቁራጮችና ዳይናሚት ያለ ርህራሄ በመሰመር የሚጓዘው መንገደኛ ላይ ያወርዱ ነበር፡፡

ሰዎች ክአውሮፕላኖቹ ጋራ ድብብቆሹ ሰልችቷቸዋል ደንዝዘዋልም፡፡ ምንም የተለየ ነገር አላደረጉም፡፡ ወደየቤታቸው መንገድ ሰለጀመሩ አነዚህ የሰማይ ላይ አውሬዎች እንደፈለጉ ያድርጉ፡፡ ያንድ ሰው ቀኑ ካልደረሰ አልደረሰም ማለት ነው፡፡ ቀኑ ደርሶ ከሆነ ደግሞ መሮጥና መደበቁ ዋጋ የለውም፡፡ አሁን ያለው አማራጭ በሚቻለው ፍጥነት ወደፊት ቀጥ ብሎ መጓዝ ብቻ ነው፡፡ ወደፊት ወደ ሰላማዊ ጎጆ ቤት፡፡

ጦርነቱ ካለፈ በኋላ  አንድ የኢጣልያ አየር ሀይል መኮንን ጋራ ተገናኝቼ ነበር፡፡ መኮንኑ ያን ቀንና ተከዜን ስናቋርጥ በቦታው የነበረ ነው፡፡ እንደሱ አባባል ምንም ሳያሰቀሩ ሁሉንም እንዲደመስሱ ትዛዝ ተሰጥቷቸው ነበር፡፡ ለነዚህ ያልሠለጡኑ ሰዎች ምንም አይነት ምህረት እንዳይደረግ፡፡ ሰለዚህ መኮንኖቹ ሀላፊነታቸውን ለመወጣት በሙሉ ስሜት ነበር የወጡት፡፡ የሙሶሎኒን ሀይል ለመቃወም የደፈሩ ሰዎች የሙሶሎኒን ክባድ አጅ መቅመሰ ነበረባቸው፡፡



ነገር ግን በነዚህ ሀይለኛ ቦምቦች ምክንያት የሚደርሰውን ጥፋት በተሰይ ምንም መከላከያ በሌላቸው ሰዎች ላይ የደረሰውን የብዙሃን ሕይወት መጥፋት ሲመሰከቱ በሚቆፍ ሰሜት ከመጀመሪያው ተውጠው ነበር፡፡ መኮንኑም አኔም በራሴ

“አቁም! አሁንስ ይበቃል ብዬ” ጮኼ ነበር፡፡

ነገር ግን ትዛዝ ትዛዝ ነው መፈፀም ነበረበት፡፡ አነዚህ ምስኪን ሰዎች እንዳው ለመሮጥ ወይም ለመደበቅ ቢሞክሩ ምን ነበረበት፡፡ ነገር ግን ዝም ብለው መንገዳቸውን ቀጠሉ እንደ ታዛዥ ልጅም ራሳቸውን ለመጣባቸው ነገር ሁሉ ሰጡ፡፡

ብዙ ቦምቦች ከመንገዱ ዳር ራቅ ብለው መውደቃቸው በአብራሪዎቹ የሰብአዊነት ሰሜት ምክንያት ይሆን? አቢሲኒያውኖቹ ቦምቦቹን አርቆ ስላሰጣለላቸው ቅዱሰ ጊዮርጊስን አመሰገኑ አኔ ግን ያመንኩት የምህረት አምላክ ምህረት የሚያሳዩትን ይከሳል ብዬ ነው፡፡

ያን ቀን ዘግየት ብሎ አብራሪዎቹ የአሳት ቦምቦች በመጣል ራሳቸውን ሰላረኩ በመንገዱ ዙርያ የነበረው ሳር ለብዙ ኪሎሜትሮች ርቀት በአሳት ይነድ ነበር፡፡ ለክብቶቹ የሚሆን ግጦሽ ሰሰሌለ ወታደሮቹ መንገዳቸውን ያለማቋረጥ ዝም ብለው ለመቀጠል ተገደዋል፡፡ በተጨማሪም ለመከላከል የነበረውን ስሜትና ችሎታንም ቀንሶታል፡፡

ከጠዋቱ አራት ሰአት ሲሆን ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ አያለ አንድ ወታደር ሲሮጥ መጣና ጣልያኖቹ ለማጥቃት መንገድ ላይ መሆናቸውን ተናገረ፡፡ ጣልያኖቹ በመኪናዎች ላይ ነው የነበሩት ምክንያቱም ሰፋት ያለው የአቧራ ጉም በፍጥነት ሲጓዝ ታይቶአል፡፡ ጭንቀት ተፈጠረ፡፡ ሁሉም ወደ ውጭ ይሮጥ ጀመር፡፡ ማንም ሰው ዋሻው ውሰጥ አንደሆን መያዝ አልፈሰገም ነገር ግን ወደ የት ወይም በየት አቅጣጫ ነው የሚኬደው?

በጠባቡ መንገድ በአንድ ጎኑ መቶ ሜትር ከፍታ ያለው ገደል በሌላ ጎኑ ደግሞ ተመሳሳይ ቀጥ ያሰ ገደል ባለበት መቶ የሚሆኑ የተደናገጡ አርስ በራሳቸው የሚጮሁ ሰዎች ቆመዋል፡፡ አጃቸውን ያወዛውዛሉ አይተገፋፉ ይጨናነቁ ነበር፡፡ ሁሉም ሀሳብና ምክር ሰጪ ነበር፡፡ ግን የሚረባ አልነበረም፡፡ አንግዲህ አውሮፕላኖቹ ቢኖሩም አራሳችን ወደ ሜዳው ወጥተን ጠላትን በመቋቋም የቀረውን ጦር ማዳን እንችል ይሆን? ወይስ በነበልባሉና

በሚነደው እሳት መሀከል እየተሳብን ቁልቁል ሄደን ከሸለቆው ስር ደርሰን ተከዜን እንሻገር ወይ? ሌላ አማራጭ በፍፁም አልነበረም።

የሰማንያ አመት ሽማግሌ የሆኑት ፊታውራሪ አሉላ ጎራዴያቸውን መዘው "ዘራፍ አድዋ ! ትዝ ይበልህ አድዋ" እያሉ ጮሁ። ትውልድ ቦታቸውን ትተው የመጡት በዚህ በተቀደሰ ጦርነት ተካፍለው በመሞት ገነት ለመግባት ነው። ትናንትናም ቢሆን አፍ ጋጋ ላይ ፊት መሰመር ሆነው ተዋግተው ነበር። ነገር ግን ሞት ሊወስዳቸው የተፀየፈ ይመስላል። ዛሬ ቀናቸው ደርሷል። አብረዋቸው የሚዋጉ አንድ መቶ ሰዎች ቢያገኙ ደጃዝማችና ራስ እምሩ በደህና እስከሚያመልጡ ጠላትን ወጥረው መያዝ ይችላሉ።

ሽማግሌው ኮሰተር ያለ ቁም ነገር ነው የሚናገሩት በሰሜት ሰውነታቸው ሲንቀጠቀጥ ምራቃቸውም በፂማቸው ላይ ይፈናጠር ነበር። ነገር ግን በጣም እየከፋቸውና እያዘኑ በጩኸት እንዲቀመጡ ሆነ። ሀሳባቸው ተቀባይ አላገኘም። በመጨረሻም ጠባቂ ዘቦች ጣልያኖችን ለመከላከል ሲሞከሩ የጦር አዛዦችና እኛ ከሥራችን ባለው ሸለቆ አድርግን ወደ ተከዜ ለመሸሽ እንድንሞክር ተወሰነ።

ሰለዚህ ምክር ዶክተሩ ምንድነው ያሰበው?

"እዎ በርግጥ። ነገር ግን መጀመሪያ ጣልያኖቹ እኛን ሊያጠቁ እንደመጡ ማረጋገጥ የለብንም ወይ? እንደዛም ሆኖ ሾልኮ ለመሄድ በቂ ጊዜ አለን"

ገና ተናግሬ ሳልጨርስ አሳሽ ወይም ቃኝ እውሮፕላን ቀጥታ በሸለቆው በላይ መጣ። በዚህ ግርግር መሀል ሰዎች ወደ ዋሻው መግባትና መውጣት ሲጀምሩ ታየንና የአነጣጥሮ ተኩዋሽ ኢላማ ሆን። ጥይቶቹ አለቶች ላይ በሚያለቅቅ ድምፅ ይነጥራሉ። ሁላችንም አንዱ ባንዱ ላይ እየተደራረብን መሬቱ ላይ ተነጠፍን።. ተነስተንም ሮጥን ወደ ዋሻው ለመግባት ከፊት ለፊታችን የዋሻ መግቢያ መንገዱን የዘጉ ሰዎች እስኪለቁ ድረስ በዛው ሁኔታ መቆየት ነበረብን። የሚገርም ሁኔታ ነበር።

እንደእድል ሆኖ የገደሉ ግድግዳ ሰለሚሸፍነን አውሮፕላኑ በተመላለሰ ቁጥር አንታይም ነበር። ሰለዚህ ጉዳዩ ወደ ዋሻው መግባት መቻል ነው። ሁሉም ገብቶ ሲያበቃ ሁለት ሰዎች ብቻ ቆሰለው ተገኙ።

አውሮፕላኑም ያየውን ሪፖረት ለማድረግ ተመልሶ ጠፋ

የኔ ሃሳብ ተሰሚነት እገኘና አንድ መኮንን ተላከና ከአንድ ሰኣት በኋላ ተመልሶ መጣ። ምንም አይነት የጠላት ጦር አላየም። በግርግሩ ንብረታችን ለመዝረፍ አስበው ይህን ውሸት ወሬ ያሰወሩት ለካስ ገበሬዎች ናቸው።



አውሮፕላኖቹም መጡ ነገር ግን የሚጥሉት ቦምብ ኢላማውን አላገኘም። ቦምቦቹ ወይ ሸለቆው ወሰጥ አለዚያም ከገደሉ አናት ላይ ነበር የሚወድቁት፤ ከገደሉ አናት ላይ ሲወድቁ ግን የአለት ሰባሪ ድንጋዮች ቁልቁል ይወርዱ ነበር።

ተዋጊ አውሮፕላኖቹ ደግሞ የባሱ ነበሩ። አንዳበደ ሰው አውቶማቲክ መሳሪያቸውን እየተኮሱ ወደኛ አቅጣጫ ልክ ወደ ዋሻ ውሰጥ እንደሚገቡ ሆነው ይበራሉ። ከዛ በመጨረሻው ሰከንድ ወደ ላይ ቀጥ ብለው ይበሩና ተገልበጠው በጀርባቸው ለብዙ ሜትሮች ከሄዱ በኋላ እንደገና ተገልብጠው ተመልሰው ይመጣሉ።

እንዳንድ ጊዜ በጎናቸው እንደሆኑ ይመጣሉ። የተለመደ የአክሮባት ትርኢት ነበር። በሰላም ጊዜ ቢሆን እንደዚህ አይነቱን በረራ ለማየት በከፈልኩ ነበር።

ይህ ሁሉ አንድ ሰአት የፈጀ ትዕይንት ሲካሄድ እኛ ወይም እንቀመጣለን ወይም ከግድግዳው ጀርባ ተጠቅልለን እንጋደማለን። የሚተኮሱት ጥይቶች አለቱን ወይም ግንቡን እየመቱ ይፈናጠራሉ። ትልቁ አደጋ ደግሞ እንደዚሁ ከሚነጥሩት ጥይቶች ነበር ከውጭ በኩል አልፎ አልፎ ወደ ውሰጥ ይገቡ ነበር።

ከአሰቃቂው የቦምብ ድብደባ ጋራ ሲወዳደር ይኸኛው ጨዋታ ነበር። አየቀለድንም ነበር። ጓደኞቻችን አጠገባቸው ጥይት የዋሻውን ግድግዳ ወይም ጣራ ሲመታ እንዴት እንደሚሆኑ እያነሳን እንስቅና እንቀልድም ነበር። አራት ሰዎች ብቻ ቀላል ቁስል መቁሰላቸው ራሱ የሚገርም ሁኔታ ነበር።

ከቀኑ አሥራ አንድ ሰአት ሲሆን ጣልያኖቹ እየመጡ እንደሆነ የሚገልፅ አዲስ ዜና መጣ። ተኩስ ድምፅ ይሰማ ጀመር። ወዲያውኑ ከላይ ከሜዳው ላይ ያሉ የኛ አውቶማቲክ መሳሪያዎች መንፈቅፈቅ ጀመሩ። ያለምንም ጥርጥር አንድ ነገር ሊሆን ነው።

አሁን ግን ምንም ግራ የሚጋባ ነገር የለብንም። ቀኑን መንገድ ሰንፈልግ በሜዳው በኩል አደርጎ በዋሻው ደቡብ አቅጣጫ የሚወሰድ ሌላ መንገድ አግኝተናል። እንዴት ያለ መንገድ! ቀጥ ባለው ገደል በድንጋዮች ላይና በከፍተቶች በኩል ወደ ላይ መቶ ሜትር የሚሆን ከፍታ ወደ ሰማይ ይወጣል። በጣም መጠጋጋታችን የሚረዳ ነገር ሆነ። እኔ ራሴ እንኳን ጉልበታቸው በጠነከረ ሰዎች ትከሻ እየተረማመድኩ ነው ወደ ላይ ያወጡኝ። ከታች ከሰር ያሉት እንዴት አድርገው የሰዉን ሁሉ ከብደትና ጭነት ችለው

ከዚያም በመጨረሻ እራሳቸው ተከትለውን እንደወጡ ለመረዳት አሰቸጋሪ ነው፡፡

ወደ ላይ በምንወጣበት ጊዜም የተኩስ መጠን ጨመረ፤ ጥይቶች እያፏጩ በአናታችን ላይ ያልፉ ነበር፡፡ ከላይ ከሜዳው ለመጀመሪያ ጊዜ ላይፈሩ ወደፊት የሚገፉ በርከት ያሉ ሰዎች አየን፡፡ አሁንም አሁንም በጥይት ሲመታ ወዲያው የሚቀመጥ ወይም ደግሞ የሚወድቅ ሰው አያለሁ፡፡ እንደዛም ሆኖ ሰዎቹ ሳያቆሙ የቆሰሉትን ያነሱና በበቅሎ ይጭኑ ነበር፡፡

በሰሜን አቅጣጫ የኛ ወታደሮች ተጋድመው ጠላት ላይ ይተኩላሉ፡፡ ጠላት እኛ ቆመን ከነበርንበት ቦታ አንድ ኪሎሜትር ርቀት ላይ ጠምዶ ተቀምጧል፡፡ አውቶማቲክ መሳሪያ ቢኖረውም በብዙ ምክንያቶች ይህ ጠላት በርግጥ የጣልያኖች ጦር ነው ብዬ አላመንኩም፡፡ ገበሬዎቹ ነበሩ፡፡

በምሥራቅ በኩል መልሰን በማጥቃት ከግማሽ ሰአት በኋላ ወደ አምስት መቶ የሚሆኑ ገበሬዎችን ማባረር ቻልን፡፡ የሞቱባቸውን ሰላሳ ሰዎች ጥለው ሄዱ፡፡ ከእንደዚህ አይነቱ አዲስ ድንገተኛ ጥቃት ለመከላከል የደጀን ወይም የኋላ ጦር ለማዘጋጀት መቆም ነበረብን፡፡ ከምሽቱ ሶስት ሰአት ሳይደርስ የሰላሳ ኪሎሜትር ርዝመት ያለው የተጓዥ ሰዎች መሰመር አልፎ ከሄደ በኋላ ጉዟችን ጀመርን፡፡

ያን ሌሊት በሽሬና በዛና መሀከል ባለው ቀጥ ባለው የገደል ቁልቁለት ብዙ ሰዎችና ከብቶች እየወደቁ አለዚያም እየተረገጡ ሞቱ፡፡ አሁንም አሁንም በአለቶቹ መሀል በደንብ የተደበቁ ገበሬዎች ይተኩሱብን ነበር፡፡ ነገር ግን እንደሚወራባቸው ፈሪነታቸው ምስክርነት ደግሞ አውቶማቲክ መሳሪያ ስናረበርብባቸው ወዲያው ጥለው ይጠፋሉ፡፡

እኩለ ሌሊት ሲሆን በመሀል ዛና የሚገኙ ሁለት ትልልቅ ዋሻዎች ያሉበት ቦታ ደረሰን፡፡ እዚህ ቦታ ላይ ለአንድ ቀን ቢሆን አቁመን ጠላትን ለመከላከል እንድንሞክር ተወሰነ ነገር ግን ወታደሮቹን እንዲቆሙ ማሳመን ብንችል ነበር፡፡

ማረፍ መቻል እንዴት ጥሩ ነገር ነበር፡፡ በሶስት ቀናት ውሰጥ ተደምሮ ሰድሰት ሰአት የሚሆን እንቅልፍ እንኳን አልተኛንም ሰለዚህ ድካም አያሸንፈንም ነበር፡፡ ምግብም ቢሆን ለሃምሳ ሰድስት ሰአታት በሚሆን ጊዜ ውስጥ የቀመሰነው ነገር አልነበረም ወደፊትም ቢሆን የሚበላ ነገር መኖሩ አይታወቅም፡፡ በመንገዱ አቅራቢያ የነበሩ ጥቂት ገበሬዎችም ቢሆኑ የነበራቸውን ምግብ አሸሽተው ጥለው ሄደዋል፡፡ የራሳችን የጭነት ከብቶችም የት እንዳሉ ማወቅም አይቻልም ነበር፡፡ ለኔ ከፋው ነገር ግን ትምባሆዬ ማለቁ ነበር፡፡



# ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ

## በሞት ወጥመድ መሀከል

ከተጠለልንባቸው ከሁሉም ዋሻዎች ሁሉ ሁለቱ የዛና ዋሻዎች በማንኛውም ረገድ የበለጡ ነበር፡፡ ጠባብ የሆነ የሀምሳ ሜትር ማለፊያ ሁለቱንም ያገናኛል፡፡ ውጭ ካለው የአመድ ክምርና ውሰጥ ደግሞ የሚታዩትን ቁፋሮዎች ሳይ ዋሻዎቹ ከጥንት ጀምሮ ሰዎች ይኖሩባቸው እንደነበር ማሰተዋል ይቻላል፡፡ የመቆፈሪያና የመሮ ቅርፆች በተጠረቡት ድንጋዮች ላይ ማየትም ይቻላል፡፡

የትልቁ ዋሻ መግቢያ ከፍ ያለ ጣራ ወዳለው ሰፊ አዳራሽ ክፍል ያመራል፡፡ ውሰጥ ሆኜ ሰናገር የሚነጥረው ድምፅ ትልቅ የድሮ ቤተክርስቲያን አዳራሽ ያለሁ ነው የሚመስል፡፡ በሶስት በኩል ወደ ውጭ የሚወሰዱ ማለፊያዎች አሉ ርዝመታቸው ተደምሮ አንድ ኪሎ ሜትር ይሞላል፡፡ የተቆፈሩ ክፍሎች፤ ኪሰ ቢጤ ቦታዎች እና ጥርቦች ይታያሉ፡፡ ከነዚህም በተጨማሪ ወለሉ ላይ የተቆፈሩ ጉድጓዶችም ነበሩ፡፡ በኋላ በጉድጓዶች ውሰጥ ብዛት ያለው የገብስና የአተር ክምር አገኝተን ወዲያው አውጥተን ቀቅለን በላን፡፡ ዋሻው ውስጥም የምንጭ ውሃ ነበር፡፡ በጥንቃቄ ለተጠቀመበት ለአንድ ሺ የሚሆን ሰው ይበቃ ነበር፡፡ የከብት ማደሪያው እራሱ አስር ከብቶች ማላደር ይችላል ከድንጋይ የተጠረበ የከብት ማብያም ነበረው፡፡

የተናፈቀው እንቅልፍ ረዥም ጊዜ አልቆየም፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ቁንጫችና ትኋኖች በቁማችን ነው የበሉን፡፡ ውጭ መተኛት ደግሞ አልቻልንም ብርዱም ሀይለኛ ነበር ብርድ ልብሰም አልያዝንም፡፡

ፀሀይ እንደወጣች አውሮፕላኖቹ ለተለመደው ሥራቸው መምጣታቸውን አሰታወቁ፡፡ ጥቂት ከጣሉዋቸው የፈንጂ ቦምቦች ውጭ የአላት ቦምቦችን በመጣል ነው ያተኮሩት፡፡ አካባቢው በሙሉ በአላት ይንቦገቦግ ጀመር፡፡ ይህ ዘዴያቸው የሚሠራ ሆኖ ተገኘ፡፡ ማንም ሰው በመቆየት ከብቱ በረሃብ ሲሞት ማየት አልፈለገም ሰለዚህ በዚህ ሁኔታ ብቻ

ጠላትን ለመቋቋም ያሰብነው ዕቅድ በሙሉ ተበላሸ:: ያለን አማራጭ መቀጠል ብቻ ነበር:: ከተቻለ በተከዜ ሸለቆ ማዶ ሆነን ራሳችን መከላከል ነው:: እንግዲህ የትግራይ ክልልን እንዳጣነው አድርገን መቀበል ነበረብን::

ሁኔታዎች እዚህ ደረጃ ሲደርሱ ጣልያኖቹ የትግራይን መሬት በመውሰዳቸው የሰላም ካሳ ነው ብለው ቢረኩና ቢበቃቸው አንድ ነገር ነበር::

ፀሀይ እንደጠለቀች ማምሻውኑ ባለ ብዙ ሞተር ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች ከደቡብ ተነስተው እኛን አልፈው ሲበሩ አየን:: ወዲያውኑ ሁለት ተዋጊ አውሮፕላኖች ጎን ለጎን በሰአት አራት መቶ ኪሎ ሜትር በሚሆን ፍጥነት እየተጣደፉ ከነፉ:: ለምን?

ቆየት ብሎ አመሻሽ ላይ ያን ቀን በእኩለ ቀን ጣልያኖቹ ፊት ፊት በመስመር የሚጓዘውን መንገደኛ የተከዜ መሻገሪያ ላይ እንደበደቡት ሰማን:: ውጤቱም እንደተባለው ከሆነ በጣም አሰቃቂ ነበር::

ለነገ ለብዙሃን ጭፍጨፋና አልቂት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑ ግልፅ ሆነ:: እነዛ ተዋጊ አውሮፕላኖች እየተጣደፉ የሄዱበት ምክንያትም ግልፅ ሆነልን:: በጊዜ ሪፖርት አቅርበው ወድያውኑ ትዛዝ እንዲሰጥና አውሮፕላኖቹ በነጋታው ቦምብ እንዲጫኑ ነበር:: በነሱ ቤት እነዚህ የጫካ ሰዎች እንደ አይጥ በየቦታው ተደበቀው ስለነበር ያ የተጣለው ሁሉ ቦምብና የጠፋው ነዳጅ እስካሁን ድረስ በከንቱ ነበር:: አሁን ግን ያለምንም መከላከያ ወጥመድ ውስጥ ገብተዋል:: ከዚህ የበለጠ ጥሩ አጋጣሚስ ይኖራል ብሎ የሚመኝ አለ? በሚቀጥለው ቀን ቦምቦች በከንቱ አይወድቁም ምክንያቱም መረጃ አቀባዮቻችን እንደነገሩን ከሆነ ከዛና ጀምሮ ተከዜ ሸለቆ ማዶ ድርስ ያለው መንገድ መላወሻ በሌለው የሰዎችና የእንስሳት መንገደኞች ተጨናንቋል::

በሌሊት እያንዳንዱ ሰው በሚቻል ፍጥነት ወንዙን መሻገር ይፈልጋል:: እኛም ብንሆን ተመሳሳይ ፍላጎት ስለነበረን ማለፍ የማይቻለውን ዋና ቀጥተኛ መንገድ ትተን ወደ ተከዜ የሚወስድ ዙሪያ ጥምዝ መንገድ እንድንወስደ ሆነ:: በፈጣን እርምጃ ከተጓዝን ቦታው ላይ ልክ እኩለ ሌሊት እንዳለፈ እንደምንደርስ ገምተናል::

የሚያታልል ተስፋ

አስቤው ከማውቀው በላይ በጣም አስቸጋሪ መንገድ መሆኑን መግለፅ ብቻ አይበቃም:: መንገዱ ከአንድ ከደረቀ ወንዝ ዳርቻ አሸዋማ ቦታ ሲደርስ አለቀ ተሰወረ:: ያገኘነው ገበሬ መንገድ አመላከተን ግን ወዲያው ሲሰውር



አሳስቶ ወዳልሆነ ቦታ እንደመራን ገባን:: ወደኋላ ተመልሰን ትክክለኛውን መንገድ ማግኘት አማራጭ የሌለው ነገር ነበር:: ያን ቀን ማታ የዚያ መንገድ የጠቆመን ገበሬ ቤት በእሳት ሲጋይ ቂም በቀላቸውን በመወጣታቸው ደስ ያላቸው ሰዎች ነበሩ::

ቁሸሽ ብለን በላብና ከዛፎችና ከቁጥቋጦች ጋራ እየተጋፋን ስንመጣ ከለበስነውን ጥላሸት ጋራ ከጥዋቱ አሥራ አንድ ሰአት ሲሆን ተከዜ ሸለቆ ደረስን:: ሸለቆው የ ላቲን ፊደል ቪ "V" ቅርፅ ያለው ሆኖ ወደ ታች አንድ ሺ ሜትር ጥልቀት አለው ከታች ደግሞ የወለሉ የጎን ስፋት ከአስር ሜትር አይበልጥም ነበር:: መንገዱ ቁልቁለታማ በሆነ የተሸረሸረ አለት ላይ በጎንና በጎን ቀጥ ባለ ገደል ግድግዳ ታጅቦ ወዲያው ይታጠፍና ሰላሳ ሜትር ስፋት ወዳለውና አንድ ሜትር ጥልቀት ወዳለው ወንዝ ውሀ ይወርዳል:: በዚህ ቦታ ላይ የደከማቸው ሰዎችና እንስሳት ተጨናንቀው በፍጥነት ይጓዛሉ:: መንገዱም ቁልቁል ነው:: ከወንዙ ማዶ ደግሞ ቀጠን ባለ መስመር አነስ ያለ የሰው ቁጥር እየተንፏቀቀ በገደሉና በጠባብና በተጠማዘዘው መንገድ ወደ ላይ ሲወጣ ይታያል::

ከታች ከወንዙ ዳርቻ ከጩኸት ጋራ የተኩስ ድምፅ ይሰማል:: ከመሻገሪያው ቦታ አካባቢ ያሉ አዞዎችን ለማስፈራራትና ለማሸሽ ነበር:: ፊዘዝ ባለው በጥዋት ብርሃን የሚታየው አስፈሪና አሰቃቂ ትዕይንት ከዳንቴ ዲቫይን ኮሜዲ (Dante's Divine Comedy) መፅሀፍ ውስጥ ከተፃፈው የገሃነም ትዕይንት ጋራ ይመሳሰላል::

ለጥቂት ጊዜም የስንፍናና የመሸነፍ ስሜት ተሰማኝ:: ያለኝ ጉልበት በወንዙ ማዶ ያለውን ገደል ለመውጣት ያስችለኝ ይሆን? እንደያው ትንሽ አረፍ ማለት ብችል

"ሀኪም! እዛው አትቁም ና አብረህ ሂድ! የምናባክነው ጊዜ የለንም! " ጥሪው ከደጃዝማች ስለነበር ወዲያውኑ አነቃቃኝ:: ደጃዝማች ከአንድ የጭነት ከብት ኮርቻ በጎራዲያቸው ማንገቻ የሚሆን ቀበቶ በጥንቃቄ ከቆረጡ በኋላ ቅርጫቶችን አነሱና ለወታደሮች እንዲሸከሙ ሠጡ:: ወደ ኔ ዞር ብለውም "ቢያንስ ቢያንስ ለዛሬ የምንበላው ምግብ አለን:: ና! " አሉ::

ከጭነት በቅሎአችን አንዱ ተገኘ:: ረሃባችን ለማስታገስ እድል መገኘቱ ሁሉንም ነገር ብሩህ ተስፋ ሰጠው:: ነገር ግን የደጃዝማችን ትዛዝ መከተል ማለት ደግሞ ሌላ ጣጣ ነበር:: የኔ የግል ሠራተኛ ስለጠፋብኝ የራሴን በቅሎ እራሴ መምራት ነበረብኝ:: ቀጥ ባለው የቁልቁለት መንገድ መጋለብ አይቻልም

ነበር፡፡ በቅሎዋን በልጓሙ እየጎተትኩ ስሄድ በቀጠነው ሰውነትዋ እንኳን ሰትስበኝ የምንትትበት ከንዴ ከመታጠፊያው ወልቆ የወጣ ነበር የመሰለኝ፡፡ በቅሎዋን እየጎተትኩ ደግሞ ባለኝ ሀይል በሙሉ ፊት ለፊቴ ያሉ ሰዎችንና አመፀኛ እንስሳቶችን እየተጋፋሁ ማለፍ ነበረብኝ፡፡

ሳስተውል ከጓደኞቼ ተነጥዬ ብቻየን ቀርቻለሁ፡፡ ቀስ ብዬ እየተሳብኩ ከወንዙ ለመድረስ ኢጋማሽ መንገድ ላይ ደረስኩኝ፡፡ እዛ ስደርስ ደግሞ መንገዱ ሙሉ በሙሉ በራስ አምሩ ሰዎች ተዘግቷል፡፡ ሰዎቹም ሊያሳልፉኝ አልፈቀዱም፡፡ የኛ ሰዎች ቢሆኑ ኖሮ ያሳልፉኝ ነበር፡፡ አመፀኛዋ በቅሎ ወደኋላ እየሳበችኝ ደጃች አያሌውንና እሽከሮቻቸውን ልደርስባቸው እንደማልችል ግልፅ ሆነለኝ፡፡ ፀሀይ መውጫም እየተቃረበ ነበር፡፡ በዛ ሰአት ውስጥ ከጓደኞቼ ጋራ ካልተደባለቅሁ በአደጋ ጊዜ የሚደርስልኝ ሰው የለም፡፡ ስለዚህ በቅሎዋን እንደ ዕድሏ ትሁን ብዬ ለቀቅኳት፡፡

በጠመዝማዛው መንገድ ከአንዱ መታጠፊያ ወደ ሌላው መታጠፊያ እየዘለልኩ ቁልቁል ወረድኩ፡፡ ቀስ እያልኩም ብዙ መንገድ ሸፈንኩ፡፡ በላብና በአቧራ ተሸፍኜ የሚያስቅ ፊት ሳላሳይ አልቀረሁም ምክንያቱም ባለፍኩ ቁጥር ሰዎች እየሳቁ "ተመልከቱት" ይሉ ነበር፡፡ አንድ ቦታ ላይ ስደርስ ዘጠኝ ሜትር ከፍታ ያለው ጉብታ ላይ ስዘል ድንገት ጠመንጃውን እያቀባበለ የሚጮህ ሰው ድምፅ ሰማሁ

"ያውና! ነጭ ሰው እየዘለለ ነው! እንዳያመልጥህ!"

ገና ሸጉጤን መዝገቤ ዞር ከማለቴ በፊት ወዳጄ እቶ ማሞ ሊረዳኝ ሲጣደፍ መጣ፡፡ መጀመሪያ ሰውየው ላይ ድንጋይ ወረወረበት፡፡ ከዛም ነጎድጓድ በመሰለ ድምፅ "ትነካውና መሞቻህ ነው!"

ሕይወቴን አተረፈልኝ አለበለዚያ በምንም መንገድ ራሴን መከላከል አልችልም ነበር

ራሰና ደጃዝማች በየበቅሏቸው ልክ ውሀውን ሊያቋርጡ ሲሉ ደረስኩባቸውና ለደጃች አያሌው የምጋልበው ከብት እንደሌለኝ ተናገርኩ፡፡ በምልከት ከወጣቱ የወንድማቸው ልጅ ኋላ እንድፈናጠጥ አሳዩኝ፡፡

የነበረኝ ጉልበት በሙሉ ተሟጦ ነበር፡፡ ትንፋሽም እያጠረኝ ልቤ በፍጥነት እየመታ የሚንቀጠቀጡ ጉልበቶቼ ሰውነቴን መሸከም እቅቷቸው ነበር፡፡ ጆሮዎቼ ደንቁረዋል አፌና ጉሮሮዬ በአቧራ ተሞልቶአል ከዚህ የባሰ ደግሞ የውሃ ጥሙ ያቃጥለኝ ነበር፡፡ እንደምንም ታግዬ በቅሎዋ ላይ ወጣሁ፡፡



በወንዙ ውሀ መሀል ስንጓዝ ቀዝቃዛውን የወንዙን ውሀ መጠጣት የምችል መሰለኝ፡፡ ደጋግሜ አጎንብሼ በእጄ ውሀውን ለማፈስ ያደረግሁት ሙከራ እልተሳካም፡፡ በፍጥነት የሚወርደው ውሀ ደግሞ ያዞረኝ ጀመር፡፡ ይህንን የተመለከተና ችግሬን ያየ ወታደር የምጠጣው ውሀ በቅል ሰጠኝ፡፡ ሁለት ሆዳቸው የተቀደደ የሞቱ በቅሎዎች ወንዙ ወስጥ ነበሩ ነገር ግን የጠጣሁት ውሀ ጉሮሮዬን ሰላረጠበልኝ ከመጀመሪያው አሰቃቂ ነገር በማየቴ ሰውነቱን ሊያንቀጠቅጠው የነበረውን ሁኔታ አስረሳኝ፡፡

የሞተር ድምፅ መስማት ስንጀምር ገና የወንዙ ማዶ አንኳን አልደረሰንም፡፡ ደጃዝማች ለጥቂት ሰከንዶች ቆም እሉ ዙሪያውን ካዩ በኋላ ተከተሉኝ በሚል ድምፅ ተመለሱ፡፡ ተመልሰው ወደ መጣንበት ሄዱና መቶ ሜትሮች የሚሆን መንገድ ቁልቁል በወንዙ ከሄድን በኋላ  ከበቅሎዎቹ እንድንወርድ ትዛዝ ተሰጠ፡፡

በፍጥነት ሁኔታዎችን በማስተዋል ችሎታቸው ከገደሉ ግድግዳ ወደ ፊት ወጣ ያለ መቶ ሜትሮች ርዝመት ያለው አለት አይተው ነበር፡፡ እኛም በዚህ ወጣ ባለው አለት ስር ተጠለልን፡፡ በፍጥነትም ድንጋዮች ሰበሰብንና ግማሽ ሜትር ከፍታ ያለው መከለያ ሰራን፡፡ መጠለያው ሰፊ አልነበረም ተጨናንቀን ስምንት ሰዎች ብቻ ነው መያዝ የሚችለው፡፡ ሌሎቹ ተበትነው ለየራሳቸው መጠለያ ወይም መደበቂያ መፈለግ ነበረባቸው፡፡ ከፊት ለፊታችንና ከጎን የሰራነው የድንጋይ ካብ መከለያ ስለሆነ ተረጋግተናል፡፡ ዋናው መጠለያ ግን በአናታችን ላይ ወጣ ብሎ እንደ ጣራ የሚሸፍነን አለት ነው፡፡

ወደ የመደበቂያችን ቦታ ለመግባት እንኳን በቂ ጊዜ ሳናገኝ አሥራ አራት ባለ ሶስት ሞተር አውሮፕላኖች ተቃረቡ፡፡ ቀስ እያሉ በሸለቆው ላይ ይበሩ ጀመር፡፡

ጭልፊቶች፡፡ ለመሰየም አንኳን ጆፌ እሞራ ሳይሻል አይቀርም የሚያድኑትን በደንብ ያውቃሉ

ምንም ማምለጫ አልነበረም

ለምንስ ግዳዮቻችው ገና በሞት ፍርሀት ሲጠማዘዙ ማየቱን እንኳን አያስደስታቸውም?

በመጨረሻም ከደቡብ በኩል በመሀከላቸው የሚበቃ ከፍተት ፈጥረው በመስመር መጡ፡፡ መሪያቸው አንድ ቦምብ በደቡብ ከፍታ ላይ ሌላ ደግሞ መሀከል ላይ እንደገናም ሶስተኛ በሰሜን አቅጣጫ ከፍታ ላይ ጣለ፡፡ ሁሉም መንገዱ ላይ ወደቁ አላማውም እሱ ነበር፡፡ መንገዱ ለመተላለፊያ እንደማይሆን ማድረግ፡፡

ያ መግቢያ ወይም መተዋወቂያ ነበር

ከዚያ በኋላ ሁሉም በየተራ ይመጡ ጀመር:: ቦምብ በቦምብ እየተከተታለ ከእሥራ እራቱ እውፕላኖች ይወርድ ጀመር:: ሁለት ኪሎሜትር ርዝመት በማይሞላ ቦታና በሰዎችና በእንስሳት በተጨናነቀ መንገድ ላይ በሚያስፈራ ሁኔታ ኢላማው ትክክል ነበር የሚያርፈው::

በሽሰቆው ከሚነጥረው የገደል ማሚቶ ጋራ ጆሮ የሚያደነቁር ድምፅ ነበር

ልብ የሚያሰጨንቅ የህፃናትና የሴቶች ጩኸት ከዚያም በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ድምፅ ወደ ላይ ወደ መንግስተ ሰማይ ሲማፀኑ ይሰማል "በክርስቶስ ፈጣሪ እባክህ ምህረቱን አውርድልን!"

እሰቃቂ ኢሰብእዊ "ሥልጣኔ"

እኛም በሠራነው ግንብ ጀርባ ስር ተንቆራጠን መደበቅ ነበረብን:: ድንጋይና የቦምብ ፍንጣሪዎች በሚያስገርም ፍጥነት እያፏጩ ወደ መጠለያችን ይመጡ ነበር:: ጭስና አቧራ መተንፈሻችን ስለዘጋው ያደረግነውን ጭምብል ለማውለቅ ተገደድን:: የማይቻል ድካም ይሰማን ጀመር:: በነበረን የሰውነት እቀማማጥ ምክንያት መጋጠሚያዎቻችን ላይ ቁርጥማት ጀመረን::

ወዲያውኑ የሸለቆው ግማሹ በጨለማ ተዋጠ:: ፀሐይዋ ጥቅጥቅ ባለ አቧራና ጭስ ተጋርዳለች:: የወንዙ ውሃ ከተራራ የወጣ ፍል ውሃ ይመስል መጨስ ጀመረ:: ሙቀቱ የሚቻል አልነበረም ሁሉም ነገር የቃጠሎ ሽታ ነበረው::

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አውሎ ነፋስ ተነሳ:: በፍጥነት እየጋለ የመጣው የአካባቢ ሙቀት የአየር ማዕበል መፍጠር ጀምሮ ስለነበረ እውሮፕላኖቹ ተመልሰው ጠፉ:: .

ለሰዎቹ ፀሎታቸው መልስ አገኘ::

በተረፈው ቀን የሚመጡት እውሮፕላኖች ተመልካቾች ብቻ ነበሩ:: መንገደኛው ህሳቡን ሳይቀይር ቀጥታ ወደ ቤቱ ብቻ የሚጓዝ መሆኑን ማረጋገጥ ፈልገዋል::

"እልቂት" በዛን ቀን ለደረሰው የቦምብ ድብደባ ምናልባትም የሚስማማው ቃል መሆን እሰበት:: ግማሽ ሰአት ያክል እንኳን አልቆየም ነገር ግን ጦሩ የሞት እይቀጡ ቅጣት ነው የደረሰበት:: ከዚህ በኋላ ማንም በጭራሽ ጣልያኖች ላይ ሙከራ እያደርግም:: የባዶሊዮ ስሌት ነበር::



እሰቃቂና ኢሰብእዊ ያም ሆኖ ምህረት የለሽ በሆነ ሁኔታ ስሌቱ ትክክለኛ ነበር:: የደከመው ወኔና ስሜት በጠቅላላ በነዚህ የነጎድጓድና የመብረቅ አምላኮች ፍራቻና አክብሮት ተተካ::

የራስ እምሩና የደጃዝማች አያሌው ጦር ያለ ምንም ጥርጥረ ተሸነፈ::

በግድያው ቦታ የሚታየውን መግለፅ የሚያዳግት እሳዛኝ ነገር ነው:: የቆሰሉ ሰዎች ውሃ ውስጥ ወይም ዳርቻው ላይ ተቀምጠዋል:: እንዳንዶቹ ጥማቸውን ለመቁረጥ ይሞክራሉ:: ሌሎች ደግሞ በእፈርና በረጋ ደም የተሸፈነውን ቁስላቸውን ያጥባሉ:: በዚህም በዚያም የተበጣጠሰ የሰው እስከሬን ይታያል:: ውሀ ውስጥ ደግሞ የሞቱ በቅሎዎች ከነሸክማቸው ወይም ያለሸክማቸው ወድቀው ይታያሉ::

በጠቅላላው መንገዱ ላይም ተመሳሳይ ሁኔታ ነው የሚታየው ልብ የሚያሰጨንቅ የእርዳታ ፀሎትም ይሰማል:: የጦሩ ሙሉ ስንቅ ተደምሰሷል:: በየመንገዱ የዱቄት ክምር፤ ማር፤ ቅቤ፤ እህል የማብሰያ እቃዎች ልብሶች በየቦታው ተበትነው ይታያል ባዶ ሳጥኖችም ቢሆን በእሳት እየነደዱ አብረው ተበትነዋል:: የሞቱ በቅሎዎች፤ ፈረሶች እና እህዮች ከምር አልፎ እልፎ ከሚታይ የሰዎች እስከሬን ጋር ተደባልቆ ከገደሉ ስር ይታያል:: አንዳንድ እንስሶች መንከባለል ሲጀምሩ ሌሎችንም ይዘው ሲወርዱ እንደ ናዳ ፈጥረው ታች ዝቅ ያለው ቦታ ላይ ሲደርስ ነው የቆመው::

እንድ የበታች መኮንንና ጥቂቶች ወታደሮቹ ፊታቸው በሸማ ተሸፍኖ ከዛፍ ግንድ ተጠግተው ተደግፈዋል:: ሁሉም የሞቱ ነበሩ::

ቆንጆ የሆነች ሴት ድንጋይ ተደግፋ ተቀምጣለች:: ያደረገቻው ጥቁር ባርኔጣ የትልቅ ሰው ቤተሰብ መሆኗን ያሰታውቃል:: እንደ እመድ የገረጣው ፊቷና የጎደጎዱ አይኖቿ ያሳለፈቻውን መከራ ይገልፃሉ:: ምን ሆነሽ ነው ተብላ ስትጠየቅ ቀሚሷን ነበር የምትገልበው:: ግራ እግርዋ ከጉልበቷ በታች ተገንጥሎ የለም ደም እንዳይፈስ ጭኗ በመቀነት ጥብቅ ብሎ ታስሯል:: ጓደኞቿ የሉም:: ምናልባትም እነሱም ሞተው ይሆናል:: በእባቷ አስከሬን እጠገብ ተቀምጣ ታነባለች::

እይን የሚያየውን ይህን ሁሉ አሰቃቂ እይታ ማነው መግለፅ የሚችለው? ብዙ ባለጌዎች እጋጣሚውን በመጠቀም ቦምብ በሚጣልበት ጊዜ ከሚበተኑ ጭነቶች ላይ ውድ እቃዎችን ይሰርቁ ነበር:: ገንዘብ የሆነ ወይም ገንዘብ ነክ

የሆነ ነገር መጀመሪያ ይወሰዳል። እንደሚባለው ከሆነ ብዙዎቹ ለመሰረቅ ሲሻሙ እርስ በርስ ይተኳኮሱ ነበር።

ራስ እምሩ የነበራቸውን ሁሉንም ነገር ነው ያጡት። ልብሳቸው፤ ቀለባቸው ሌላውን ጨምሮ የተረፉቸው ሀያ ሁለት ሺ ብር የለም። ደጃች አያሌው ደግሞ አምስት ሺ ማር ትሬዛ ብርና ሌሎችም ነገሮች ጠፍተውባቸዋል።

እኔም ብሆን የራስ እምሩ ዕጣ ነው የደረሰብኝ። የነበረኝ ሁሉ ነገር መድሃኒቶችን ጨምሮ በእሳት ነው የተቃጠለብኝ። የነበረኝ ሀያ ሺ ሊሬም ሄዷል። በተጨማሪ ምትክ የሌላቸው ሰማንያ ስድስት የፎቶ ፊልሞች (ነጋቲቭስ)፤ ትልቅ ማስታወሻ መፃፊያ፤ የመንገድና የመኝታ ልብሶቼ ሌሎችንም ጨምሮ። አሁን ያለኝ የለበስኩት ልብስ ብቻ ነው። ከዚህ ሁሉ ግን ትንሽ ማስታወሻዬንና መፅሐፍ ቅዱሴን ማዳን ችያለሁ።



# ምዕራፍ ሀያ

## በሰሜን ተራሮች ላይ

ወደ ላይ ፀጥ ወዳሉት በደመና በተሸፈኑት ወደሰሜን ተራሮች እናቶች ሽሽቱ ቀጠለ። አሁን ትዛዙን የሚሰጡት ተራዎቹ ሰዎች ናቸው። የጦሩ አዛዦች ያለምንም ሥልጣን መከተል ብቻ ነው የነበረባቸው። ለደህንነትም ሲባል አዛዦቹ በማታ ብቻ ነበር የሚጓዙት።

አውሮፕላኖቹ የቅስቀሳ ወረቀቶች በተከታታይ ይበትኑ ነበር በወረቀቱም ጣልያኖቹ ከተራው ህዝብ ጋራ ምንም አይነት ጠብ እንደሌላቸው ይገልፁ ነበር። መቅጣት የሚፈልጉት የንጉሡ ተከታዮች የሆኑትንና ገበሬውን የሚያሰቃዩትን የጦር መኮንኖችን ብቻ ነው። ስለዚህ ተራው ሰው ወደየቤቱ በእስቸኳይ እንዲመለስ ተማሳፅም ይሰጡ ነበር። ይህንን ትዛዝ ከተቀበሉም ከድብደባ ይድኑ ነበር።

ከዚያ በኋላ የቦምብ ድብደባው በጣም እልፎ አልፎ ነበር የሚካሄደው። በምብም የሚጣለው እንድ ካምፕ ከአንድ ቀን በላይ የሚቆይ ከሆነ ጥርጣሬ ካለ ነው። ያም ሆኖ ግን አውሮፕላኖቹ ከፊት ለፊት ከሚሸሸው ሰው መንገድ ዳርና ዳር የሚገኘውን ሳር በሙሉ በእሳት ያቃጥሉት ነበር። መንገዳችንም በረሃብና በድካም ምክንያት የሞቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ፈረሶች ይታይበታል።

ከአበር ተራራ ስር ለሁለት ቀናት እቆምን። ማምሻውን በመጣ ዜና የጣልያኖች ሬጅመንት እኛ ያቋረጥን ቀን ተከዜን ማቋረጡን ሰማን። ነገር ግን ከኛ ዝቅ ብሎ ነው የተሻገሩት። አሁን ደግሞ ወደ ዳባት እየተጓዙ መሆናቸውን ሰማን። ራስ እምሩ ወደ ግንባር ሲመጡ ይዘው የመጡትን መንገድ ይዘው ነው ወደ ዳባት የሚሄዱት። የካምፕ እሳታቸውን ከታች ከረባዳው መሬት በምእራብ በኩል እሥራ እምስት ኪሎ ሜትር በማይሞላ ርቀት ማየት እንችል ነበር።

በጣም ተዝናንተዋል ምንም እንግዳ በሆነ በጠላት ቦታ ቢሆኑም ማን ቀድሞ ዳባት ይደርሳል በሚል አይተፎካከሩ ነበር።

ራስ እምሩ ጣልያኖችን ለማዘግየት ማጥቃት ፈልገው ነበር ነገር ግን ወታደሮቻቸው ፊት ለፊት ትዛዙን እንደማይቀበሉ አሰታወቁ:: እንደ ወታደሮቹ ግዛቱ የዳጃማች አያሌው ስለሆነ የመከላከል ሀላፊነቱም የሳቸው እንጂ የነሱ አይደለም:: ወደ ቤታቸው በተቻለ መጠን በፍጥነት መመለስ ሰለወሰኑ ራስ እምሩ ከፊለጉ መከተል አለዚያም መቅረት ይችላሉ::

በሌላ በኩል ደጃች አያሌው በሶስት ፊታውራሪዎች የሚመራ አምስት መቶ ወታደሮች ማሰባሰብ ችለው ነበር:: ትዛዙም በማታ ጠላትን በማጥቃትና በመረበሽ ወደኋላ መመለስ እንዲያስብ ለማድረግ ነበር:: በተጨማሪም ወታደሮቹ ገበሬዎች ጠላት እንዲራብ ለማድረግ ቤታቸውን ባዶ እንዲያደረጉ ይገፋፉ ነበር:: እንደ ሰማነው ከሆነ ጠላት ስንቅ ሳይዝ ነው የተንቀሳቀሰው፤ የሚፈልገውን ነገርም ከገበሬዎች አየገዛ ነበር::

አንድ ቀንም አለፈ በሁለተኛው ቀን ከሰአት በኋላ አንደኛው ፊታውራሪ ከሰላሳ ሰዎች ጋራ ተመለሱ:: ወኔያቸው የወደቀ ይመስላሉ:: ምን ተፈጠረ?

ሁለቱ ፊታውራሪዎች የኛ ማጥቃት ተስፋ የሌለው ነገር ነው ብለው ከቀረው ጦር ጋር ከጣልያኖቹ ጋራ ተደባልቀዋል::

ይህ የመጀመሪያው ከዳት ነበር:: ደጃዝማች አያሌው ላይ ከፍተኛ የሀዘን ስሜት ነው የፈጠረው:: የዚህ ላይበቃ ደግሞ በደረሳቸው ደብዳቤ በዳባት የገበያ ቦታውና የገብርኤል ቤተከርሰቲያን በአየር ድብደባ ወድመዋል::



በዳባት ከተማ ተመልሶ የተሰራው የቅዱስ ገብርኤል ቤተከርስቲያን





በዳባት አሁንም የሚገኝ ቤተከርሰቲያኑ ላይ ከተጣሉ ቦምቦች የአንዱ ክፍል

ከዚያን ቀን በኋላ ደጃች አያሌው እንደድሯቸው አልሆኑም:: ከዚህ ቀደም ተጫዋችና ተደባላቂ የነበሩት ሰው ዝምተኛና ቀስተኛ ሆነዋል:: ፀጉራቸው አልፎ አልፎ ሽበት የነበረበት በጥቂት ቀናት ውስጥ ተቀየረ:: በሙሉ ነጭ ሆነ::

ይህ ሁሉ ችግር አያለ ሁሉም ነገር አለቀለት የሚለውን አሰተሳሰብ ግን አልተቀበሉትም::

ውሳኔውም በተቻለ ፍጥነት ከዳባት ሰላሳ ኪሎሜትር ርቀት ወደሚገኘው የደጋው ከተማ ወደ ደባርቅ እንድንሄድ መንገዱም ለማለፍ አስቸጋሪ በሆነው በሊማሊሞ ገደል በኩል እንዲሆን ምክንያቱም ጣልያኖቹም ማለፍ የፈለጉት በዚሁ በሊማሊም በኩል ሰለሆነ ነበር:: የዚህ ማለፊያ ለሀምሳ ሜትር የሚሆን ቦታ ላይ በጣም ጠባብ ሰለነበር የተጫነ አህያ ማለፍ አይችልም ነበር:: እዛ ቦታ ላይ በጥቂቱ በመቶ የሚቆጠሩ ሰዎች ቦታ ይዘው ለማለፍ የሚሞከረውን ማንኛውም ጠላት እንዲያሰቆሙ ታሰበ::

ትዛዙም ለፊታውራሪ ተሻገር ተሰጠና ወታደሮች ይዘው በአስቸኳይ ወደ ሊማሊሞ ማለፊያ እንዲሄዱ ነበር:: ከአየር ድብደባ የሚከላከሉበት መጠለያ እንዲያዘጋጁ በተጨማሪም ጠመንጃ መደገኛ ጉድቦች እንዲቆፈሩና ወደ ረባዳው መሬት አቅጣጫ ሁለት ቦታ ላይ ግንብ እንዲገነባ ተወሰነ::




በዳባት ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ የሚገኝ
ደጃዝማች አያሌው ራሳቸው ያሰሩት የመቃብር ቤታቸው

በዚህ ጊዜ አኛም በአሰቸጋሪ ሁኔታ ወደ ላይ ወደ ተራሮች መውጣት ቀጠልን፡፡ ሁልጊዜ ወደ ላይ መውጣት ነው፡፡ አየሩም በየቀኑ እየቀዘቀዘና እየቀሰሰ ይሄዳል፡፡ መያዝ የቻልነውን ወሰድን ከነልብሳችንም እንተኛ ነበር፡፡ ምንም ነገር አልነበረንም፡፡






የደጃች አያሌው መቃብር ቤት በሌላ ጎን ሲታይ

የቅማል ነገር እንዴት ነው ብሎ ሰው ሊጠይቅ ይችላል፡፡ አዎ ቅማል ነበር፡፡ እነዚህ ትንንሽ ተባዮች ሰዎችን እንደዚህ ያስቃያሉ ብዬ ገምቼ አላውቅም፡፡ የሚገርም ነው በአንድ ወቅት በአውሮፓ የነበሩ መርማሪዎች (ኢንኩዊዝተርስ) ቅማሎችን ሰው ለማስቃየት አለመጠቀማቸው፡፡ ስንት አንቅልፍ ያጣሁባቸው ማታዎች ነበሩ በበሉኝ ቁጥር እንደ ህፃን ልጅ ያስለቅሱኝ ነበር፡፡ በማከክ ብዛት ቆዳዬ ተልጦና ቆስሎም ነበር፡፡ በመጋቢት ሶስት በማስታወሻዬ የሚቀጥሉትን ቃላት ስፅፍ ስለቅማሎቹ እያስብኩ ነበር፡፡

ከየካቲት ሀያ ሶስት ውጊያ በኋላ ከፍተኛ ስቃይ ነው የደረሰብኝ፡፡ አሁንስ ሁሉም ነገር ደከሞኛል፡ ምናለ ማቆሚያ ቢኖረው

አንድ ቀን አቶ ማሞ ወደ ዋሻችን መጣ በጣም የተጨነቀ ይመስላል፡፡ ልጁ አፀደ ለሁለት ቀናት አልታየችም፡፡ የራስ አምሩ ሰዎች ሰርቀዋታል ብሎ አርግጠኛ ነበር፡፡ ምክንያቱም በዚያ በመበታተኑ ጊዜ በአንዳንድ የራስ አምሩ ወታደሮች ዘንድ ፈረስ በቅሎና አገልጋዮች መሰረቅ የተለመደ ነገር ሆኗል፡፡ ሀሳባቸውም በየትውልድ በታቸው ተመልሰው ሲገቡ ሰመሸጥ ነው፡፡

አሷን አንዴት እንደምንፈልግ እየተነጋገርን እያለን አንድ ወታደር ይዟት መጣ፡፡ አንደ ወታደሩ አገላለፅ አንደ ቀን በንጋቱ ገና ጨለማ አንደሆነ አፀደን በአንቅልፍ ልቧ ወደሱ ሰትመጣ ያያታል፡፡ ከንድዋን ሲጨብጥ ነቃች ደንግጣም ነበር ነገር ግን የማስታወስ ቾሎታዋ አንደጠፋ ይረዳል፡፡ ልጅቷ የራሷን ሰም ሆነ የወላጇቿን ሰም ማስታወስ አልቻለችም፡፡ ያን ቀን ብቻ የሚያውቃት ሰው መጥቶ የአባቷን ሰም ሲጠራ ማስታወስ ጀመረች፡፡

መልካም ያ ጥሩ ነገር ነበር!! ከዚያ ውጭ ግን በዚህ በማይረሳ መከራ ቀን አንድ ጣጣ በሌላ ጣጣ ይተካ ነበር፡፡

ፈጠነ በጣም ታመመ የያዘው በሽታ ደግሞ የሚያገረሽ ተስቦ (Relapsing fever) መሰለኝ፡፡ መድሐኒት አልነበረኝም በዚህ ያልሆነ ቦታ ደግሞ ጥዬው አልሄድም፡፡ ደጃዝማች አንድ ከተከዜ ጭፍጨፋ የተረፈች በካምፑ ውስጥ ያለችዋን ብቸኛ በቅሎ ሳኩልኝ እኔም ፈጠነን አሳፈርኩባት፡፡ መንገድ በጀመርን ቁጥር የትኩሳት ቅዝት ውስጥ ሰለነበር አንዳይወድቅ ከኮርቻው ጋር በደንብ መታሰር ነበረበት፡፡

መንገዱ ቀጥታ በሰሜን ተራሮች በኩል ነው የሚወስደው፡፡ ሲያደናቅፈኝ በአይኔ ብልጭታ ማየት ጀመርኩ ጉልበቶቼም ሊከዱኝ ያሰቡ ይመስላል፡፡ የምግብ ዕጥረት ከቅማሎቹ ደም መምጠጥ ጋራ ያሰኝን አቅም በሙሉ አዳከሞታል፡፡

ከብዙ ቀናት በኋላ ከታች ከተከዜ ሸለቆ ከባህር ወለል ዘጠኝ መቶ ሜትር ከሆነ ቦታ ጀምረን ወደ ላይ ከባህር ወሰል አራት ሽ ሜትር ከፍታ በላይ ወጥተናል፡፡ እዚህ ላይ ባሰግርማ ሞገሱ ቡዋሂት በአራት ሺ ስድስት መቶ ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል፡፡ ከብዙ አመታት በፊት ይህ ተራራ በወንድሜ በዋልደማርና በጂኦሎጂስቱ ዶክተር ኤሪክ ኔልሰን ድል ተደርጓል፡፡



ሁለቱ በአቢሲኒያ ከፍተኛው ተራራ ላይ እግራቸውን ለማሳረፍ የመጀመሪያዎቹ አውሮፓውያን ነበሩ፡፡ ኩርምትምት ብዬ ቁጭ ስልና በበረዶ የተሸፈነውን የተራራውን ነጭ አናት ስመለከት የቫይኪንግ ትውልድ ያላቸው ስውዲናውያኑ እንደወንድሜና ዶክተሩ ያሉ ጠንካራ ሰዎች ናቸው እንዲህ ያለውን ነገር መፈፀም የሚችሉት አልኩኝ፡፡ ሌላ ሰው ተራራው ጫፍ ድረስ ለመውጣት ገና መቆየት አለበት ብዬ አሰብኩ፡፡ ስዊድን ስዘላለም ትኑር!

ይህ ግርማ ሞገስ ያለው አስደናቂ አይታ መንፈስን የማደስ ስሜትም ይፈጥራል፡፡ ላፍታ ያክል የወንድሜን አግር የመከተል ስሜት ተፈታተነኝ፡፡ አቢሲኒያኖችን ስውዲናዊ ማድረግ የሚችለውን ነገር ባሳያቸው ደስ ባለኝ፡፡ የዋልደማር ወንደምስ አይደለሁም ወይ? አያሌውና ሰዎቻቸው በደምብ የሚያውቁት ዋልደማር! ሙሉ አድናቆታቸውን ያገኘው ዋልደማር፡፡

ነገር ግን በታው በጣም ቀዝቃዛና የሚቆረጥም ብርድ አለው፡፡ መሬቱ እንደበረዶ ቀዝቅዞአል እዚህ እዚያም የበረዶ ክምር ይታያል፡፡ ስሳ ያለው አየር ትንፋሼን ቁርጥ ነው ያሰደረገኝ ብሰበው ብሰበው የሚበቃ አየር የማገኝ አልመስለኝ አለ፡፡ ከጂባራውና(ጅብራ) እጅብ ብሎ ከሚታያው ከርዳዳ ሳር ውጭ ሌላ አይነት ተክል አይታይም፡፡ ጅባራ የሚገኘው ከባህር ወለል ሶስት ሺ ስምንት መቶ ሜትር ከፍታ ብቻ ነው፡፡ ቁመቱ እስከ ሶስት ሜትር ድረስ ይሆናል ከሩቅ ሲታይም ልክ የዘንባባ ዛፍ ይመስላል፡፡ ከስር በኩል ግንዱ የሀያ አምስት ሴንቲ ሜትር ውፍረት አለው ወደ ላይ እያደገ ሲሄድ ግን መቅጠን ይጀምራል፡፡ ተከሉ ሲደርቅ እንደ ግንድ ነው የሚነደው ነገር ግን ሙቀት አይሰጥም፡፡

በቡዋሂት ምአራብ ጎን በኩል ባለ ዋሻ ሰሶስት ቀናት ሰነበትን፡፡ በዚህ ቦታ ብዙ በጎች ይረባሉ፡፡ አንድ በግ በርካሽ በሀምሳ አር (ግማሽ ክራውን - የስዊድን ገንዘብ) ይገዛል፡፡ ጉልበታችን ማገገም የሚችልበት ቦታ ነው ብሰን አሰበናል፡፡

ከጥዋት እስከ ማታ በግ በየተራ እያታረደ ይቀቀላል፡፡ እንደዚህ ጊዜ ስጋ በብዛት በልቼም አላውቅም ይህን ያህልም ቡቡኝ ጠጥቼ አላውቅም፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ምን ያህል ተርበን እንደነበር ተገነዘብን፡፡ ጨጓራና አንጀታችንም አልተጣሉንም፡፡ ምን ያህል ብዛት ቢኖረውም የበላነውን ሁሉ ተቀበሉ፡፡

የሰሜን ገበሬዎች እነዚህ ትሁትና የደጋ ተራ ሰዎች በግልፅ ወዳጅ መስለው ነበር የሚታዩት፡፡ ሲመጡም እንጨት ጠላ ዳቦ ወተትና እህል ስጦታ ይዘው ነበር፡፡ እልፎ አልፎም እንቁላል ይሰጡን ነበር፡፡ አገሩ ግን የዶሮ ሀብት የለውም፡፡

ካምፑን ለቀን በምንሄድበት ቀን በጥዋቱ ገላየን ታጥቤ በፈላ ውሃ የተቀቀለ አዲስ ልብስ ከለበስኩ በኋላ በጣም ደስታ ተሰማኝና ከደጃዝማች ልጅ ጋራ በመሆን ዋልያ ለማደን ወጣን፡፡ ዋልያ በሰሜን ብቻ ነው የሚገኘው፡፡ ብዙ ዋልያዎችን ቀጥ ባለው ገደል ላይ አየን፡፡ ጠጋ ብለን ለመተኮስ የጠመንጃ ተኩስ ርቀት ያህል የሚያስጠጉን አይነት አልነበሩም፡፡ በተጠጋን ቁጥር ስለሚሸሹ አፋራምነታቸውን አስመሰከሩ፡፡ ለማንኛውም እንዲህ አይነት ያልተለመደ አደን ለማድረግ ወጥተን ነበር፡፡

በሳንቃ በር በኩል አድርገን ወደ ደባርቅ መንገድ ቀጠልን፡፡ ሳንቃ በር በዚህ ቀጥ ባሉ አለትና መጋጠሚያዎች በተከበበው ሰሜን ክልል ካሉት ሶስት ማለፊያዎች አንዱ ነው፡፡ የጣልያን ወታደሮች ከታች ከደልዳላው ቦታ ስለተቀመጡ እኛ የሚሻለን በዳባትና በደባርቅ መሀከል ግማሽ መንገድ ላይ በሚገኙ ዋሻዎች ቆይተን የሚመጣውን ማየት ነው ብለን ወሰነናል፡፡

አሁን የደረስንበት ዋሻ ትልቅ ነበር በቀላሉ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ማስተናገድ ይችላል ነገር ግን በእርጥበቱ ምክንያት ውስጡ መቆየት የማይቻልበት ሁኔታ ደረጃ ሊደርስ ይችል ነበር፡፡ ሰፊና ጠመዝማዛ መንገድ በተራራው መሀል ለመሃል ይወስዳል፡፡ ለደቂቃዎች ከተጓዝን በኋላ ሰፊ ውሀ የተከማቸበት ኩሬ ደረስን፡፡ ውሀው ከላይ እንደነጎድጓድ እይጮኸ በሚወርደ ፏፏቴ ይሞላል፡፡ በፏፏቴው ጩኸት ንግግሬ መሰማትም አይችልም ነበር፡፡ ኩሬው ከስር በኩል የውሀ መውጫ ቢኖረው ነው እንጂ ከላይ በኩል የሚታይ የውሀ መውረጃ አይታይም ነበር፡፡

ከሳንቃ በር ወዲህ ከአቶ ማሞና ቤተሰቦቹ ጋራ በጣም ተቀራርቤያለሁ፡፡ ከነሱ ጋራ ሆኜ የሚቻለውን ቦታው የሚፈቅደውን እንክብካቤ አግኝቼአለሁ፡፡ በቀሩት ወራቶች አብረን ነው ያሳለፍነው፡፡ ከደጃዝማች በየቀኑ የሚላከልንን ዳቦ እንደወንድማማች እንከፋፈል ነበር፡፡

ደጃች አያሌው በቆየ ቁጥር ዝምታቸው እየጨመረ ነበር የሄደው፡፡ ጨዋታቸው ምንም አልተሻለም ያ ግን የራስ ካሳ ልጅ የሆኑት ባለቤታቸው ከዳባት ተነስተው እኛን ለመከተል እስኪመጡ ድረስ ነበር፡፡



ባለቤታቸው ስማቸው ማናህሎሽ ነበር ሲመጡም የውጭውን አለም ጭልፍታ ይዘው ነበር የመጡት፡፡ በጣም ንፁህ ናቸው ለብዙ ጊዜ አዲስ አበባ ሲኖሩ እንደ አውሮፓዊ ባላባት ሴቶች ነበር የኖሩት ያም በባህሪም በአለባበስም ጭምር ነበር፡፡ በጣም መልከኛና አስደሳችም ነበሩ ነገር ግን ራስ ወዳድ በመሆናቸው የተነሳ ተወዳጅነት አልነበራቸውም፡፡ ይህ ባህሪ ደግሞ የተወረሰ ነው ተብሎ ይወራ ነበር፡፡ በሳቸው እርዳታ ነበር አስቀያሚና የማይመቸውን ፂሜን ማስወገድ የቻልኩት፡፡ ፂም መላጫዬንና ሌሎች ንብረቶቼ ተከዜ ላይ ስለጠፉብኝ ፂሜን ከማላደግ በስተቀር አማራጭ አልነበረኝም፡፡ ከነበራቸው የመዋቢያ ነገሮች ጋራ ፀጉር የሚያስወግድ ወይም የሚነቅል ፓውደርም ይዘው ነበር፡፡ በወፍራሙ ፂሜ ላይ አደረግሁበት ከሶስት ደቂቃ በኋላ ፂሜ እንደ ህልም ድራሹ ጠፋ፡፡ ደስተኛ ነበርኩ፡፡ ከዚህ በኋላ ግን ደግሜ ተጠቅሜ አላውቅም፡፡




ደጃች አያሌውና ባለቤታቸው ወይዘሮ ማናህሎሽ ካሳ (Agenore Frangipani)

በዚህ ትልቅ ዋሻ ሶስት ቀናት እንዳሳለፍን ፊታውራሪ ተሻገር በላብ ተጠምቀው ፈረሳቸውን እየጋለቡ መጡ፡፡ ሰዎቹ ከድተዋቸዋል እናም ብቻቸውን የሊማሊሞን ማለፊያ መከላከል አልቻሉም፡፡

ጣልያኖቹ በደባርቅ ከተማ ዙሪያ ካምፕ መስርተዋል፡፡ የአካባቢው ገበሬዎች በሙሉ ለኛ ግልፅ የሆነ ጥላቻ እያሳዩ ነው፡፡ ለጣልያኖቹ

ወዳጅነታቸውን ለመግለፅ ሁሉም ነጭ ባንዴራ በየጎጆአቸው ላይ ያውለበልቡ ነበር፡፡ በገበሬዎችና በወታደሮች መሀከል ተኩስ ልውውጥ ማድረግ የተለመደ ነገር አየሆነ መቷል፡፡ ፊታውራሪ ደግሞ የነበራቸውን ጥሩ ዜናም ማካፈሉን አልረሱም ነበር፡፡ የጣልያን አውሮፕላኖች በስህተት የራሳቸውን ሰዎች በቦምብ ደብደው በራሳቸው ዜጎች ላይ ሞትና ሽብር ፈጥረዋል፡፡

ወዲያውኑ የተወሰነው ውሳኔ ደጃች አያሌው ራሳቸው ብቻቸውን ወይም ከኛ አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ከሚገኙት ራስ አምሩ ጋራ በመሆን ጣልያኖቹን ለመመከት ነበር፡፡ አቶ ማሞ እና እኔ ራሴ ከሌሎች ሰዎች ጋራ በመሆን የተሰጠን ሀላፊነት ወይዘሮ ማናህሎሽን እጅብን በቀጥታ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ እንድንሄድ ነው፡፡ ሀሳቡ በሱዳን በኩል አድርገን ሄደን ከአንግሊዞች መጠለያ ለማግኘት ነው፡፡ ደጃዝማችም በሙከራቸው ካልተላካለቸው አኛን ሊደርሱብን እንደሚሞከሩ ነበር፡፡

ከሰአት በኋላ ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ላይ ደጃዝማች ከብዙ መቶ ሰዎች ጋር በመሆን ተለይተውን ሄዱ፡፡ እኛ ግን መንገድ ለመጀመር የጨረቃ ብርሃን እስኪወጣ ድረስ መጠበቅ ነበረብን፡፡ ልክ እንደ ሌሎቹ ሴቶች ሁሉ ወይዘሮ ማናህሎሽ በፍፁም ተዘጋጅተው አልጨረሱም፡፡ ይሄ ጎድሏል፤ ልብሱ በደንብ ስከት አላለም፤ ጫማው ይቆነጥጣል ወይ ደግሞ የፀሐይ ባርኔጣው ቀለም ከሌላው ጋራ የሚለማማ አይደለም፡፡

እንደ ተለመደው መንገዱ በጣም አለቸጋሪ ነበር ዕጣችን በሙሉ በአስቸጋሪ መንገዶች እንድንጓዝ የተወሰነበት ይመስላል፡፡ አንድ ሰባት የሚሆኑ አላዛኝ ሁኔታዎች ወደ ሰምንት አስቸጋሪ ሁኔታዎች (ከሌሎች ሁኔታዎች ጋራ የአቶ ማሞ ፈረስ ከነጭነቱ በገደሉ ወድቆ ቀርቷል) በኋላ የሚያምርና አስደናቂ ወደ ሆነው ̈ የቦዛ አካባቢ ደረስን፡፡ አዚሀ ቦታ ላይ ሆነን በስምምነታችን መሰረት የደጃዝማቾ አያሌውን ወሬ ልንጠብቅ ነው፡፡

አኩለ ቀን ሲሆን ዜና መጣልንና ከነበረን መዳከምም እንድንነቃ አደረገን፡፡ በዙሪያው በነበሩ ሰዎች ግን ከፍተኛ ጩኸት ነበር፡፡ የደጃች አያሌው ሁሉም ንብረት ዳባት አጠገብ ባሉ ዋሻዎች ተደብቀው ነበር ነገር ግን በአካባቢው ሰዎች አንዳለ ተዘርፈዋል፡፡ ሁሉም አርስ ባርሱ አየተራኮተ ነበር፡፡ እቅም ያነሰው ለባለጉልበተኛው መልቀቅ ነበረበት፡፡ ይህ ሁኔታም በየቦታው የሚታይ ነገር ሆኗል፡፡



ራስና ደጃዝማች ለኛ የሚበጀው ወደ ጎንደር መሄድ ነው ብለው አስበዋል ለለዚህ እኛም ከኋላቸው ወደ ረባዳው በሚወስደው መንገድ ላይ እንድንደርስባቸው ተወሰኖአል፡፡ ሰባት ሰአት ሲሆን መንገድ ጀመርን መንገዳችንም ለሶስት ቀናት ቀጠለ በመሀል የዘጠኝ ሰአታት አረፈት ብቻ ነው ያደረግነው፡፡

በመጨረሻም ደንቀዝ የሚባል ከተማ ደረስን፡፡ ፀሀዩ ያቃጥላል እስኪመሽ ድረሰና ከአምስት ወራት በፊት ወደ ጠገዴ ስሄድ የመጣሁበትን መንገድ እስከምናቋርጥ ድረሰ የሚጠጣ ውሀም አላገኘንም፡፡ ሌሊቱ እንዳለፈ ፀሀይ ስትወጣ ወደ ሰማይ ቀጥ ብሎ የወጣ የመቶ ሜትር ከፍታ ያለው ዳገት መውጣት ነበረብን፡፡



በዳባት የሚገኝ የደጃች አያሌው ግብር ማብያ ቤት የነበረ (ደሳለኝና ገበየሁ)



በዳባት የደጃች አያሌው ፍርድ መስጫ ሥፍራ የነበረ

ደጋማው ቦታ ላይ እያለን በቡድን በተደራጁ ገበሬዎች ጥቃት ደረሰብን ሆኖም ከሀያ ደቂቃዎች ውጊያ በኋላ በነበሩን ሶስት አውቶማቲክ መሳሪያዎች እርዳታ ልናባርራቸው ቻልን፡፡

ከሰአት በኋላ ሲሆን ራሰና ደጃዝማች ይጠብቁን ስለነበር ደረስንባቸው፡፡ የማውቃቸው ጓደኞቼንም አገኘሁ፡፡ ከአዲስ አበባ ከመጡ ሁለት የአቢሲኒያ ፓይለቶች ጋራ ተዋወቅሁ፡፡ አውሮፕላናቸው ዳባት ላይ ስለተመታ ከእጀቡ ጋራ በመሆን ወደ አዲስ አበባ ለመመለስ ወስነዋል፡፡

ከምሽቱ ሶስት ሰአት ሲሆን በፀጥታና በተረጋጋ ሁኔታ በጣም ደስ በሚል ጨረቃ ብርሃን ስር ወደፊት እንጓዝ ነበረ፡፡ ድንገት ተኩስ ከሁሉም አቅጣጫ ይተኮሰብን ነበር ጥይቶችም እያፏጩ በአናታችን ላይ ይበሩ ጀመር፡፡ ግራ እንደገባው ዶሮ በየቦታው በጭንቀት የሚሮጡት ህፃናት ለመከላከልና ለመደራጀት አሰቸጋሪ ሁኔታ ፈጠሩብን፡፡ እንስሶችም ፈርተው ስለነበር ችግሩን አባባሱት፡፡

ተኩሱ ቀስ እያለ እየጨመረ ሄደ የኛም አውቶማቲክ መሳሪያዎቻችን ተጠመዱና መንጣጣት ጀመሩ ወታደሮቻችን በጨለማው ወደማይታይ የጠላት አቅጣጫ ነበር የሚተኩሱት፡፡

"እሃ! ተመልከት!" ከመትረየስ ተኳሾቹ አንዱ መሳሪያውን ወደኛ አዞረብን፡፡ ጥይቶቹ በአናታችን ላይ ነው የሚሄዱት ግን ይሄ ከሀዲ መትረየሱን ወደ ታች ማነጣጠር መቼ እንደሚጀምር ማንስ ያውቃል?

"አበራ! እንዳትለቀው!"

ደጃማች ነበሩ ለአነጣጥሮ ተኳሻቸው ትዛዝ የሰጡት፡፡ አበራም በርከክ አለና ጠመንጃውን ከጉንጩ አስጠግቶ ተኮሰ፡፡ ኢላማ! መትረየሱም ፀጥ አለ ተኳሹም ወደ መሬት አጥፍ አለ፡፡ ከግማሽ ሰአት ተኩስ በኋላ አጥቂዎቻችን ሙትና የቆሰሉ አስር ሰዎቻቸውን ትተው ተበተኑ፡፡ እኛ ግን በአጥፍ የሚሆን ነበር ያጣነው፡፡

መንገድ እንደገና ለመጀመር ስንዘጋጅ እንደኛው የኢጣልያ እስረኛ የለም፡፡ በየቦታው ተፈልጎ በመጨረሻ ዋሻው ውስጥ ተገኘ፡፡ በዚያው እንደተደበቀ እንቅልፍ ወስዶታል፡፡ ሙሉ ቀን ያሳለፈው ጉዞ አድክሞትም ነበር፡፡

በመንገዳችን ላይ የሚደረሰብንን ብዛት ያለው ጥቃት መቋቋም ነበረብን። ጉልበታችንን ጨርሰን በመጋቢት ሀያ ሁለት እንድ ጥንታዊ ፍርሥራሽ ያለበት ደንቀዝ ከተማ ገባን፡፡ እዚህ እያለን የሚገርም ዜና ሰማን፡፡ ጣልያኖች ከአንድ



ቀን በፊት ጎንደር ከተማ ገብተዋል፡፡ እኛም ያለነው ከጎንደር አርባ ኪሎሜትር ርቀት ነበር፡፡ እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ?

ጄኔራል ሰታራቼ በሰምንት ቀናት ውስጥ ከሰቲት ተነሰቶ መንገድ እየሰራ መካናይዝድ የሆነውን ጦሩን ይዞ ጎንደር ሲገባ የምናውቀውም ነገር አልነበረም፡፡



በሰቲት በኩል ጎንደር ገሰግሶ የገባው ጀኔራል ሰታራቼ
ከሰር የሚታየው ጣልያኖች ጎንደር ከተማ ሲገቡ ነው



# ምዕራፍ ሀያ አንድ

## የገማ አሣ

ጎንደር በጣልያኖች መያዙ ለራስ እምሩም ሆነ ለደጃዝማች ትልቅ ውድቀት ነበር። ጠላት ጠቅላላውን የሰሜን ድንበር ስለሚቆጣጠር ወደ ሱዳን የሚወስደው መንገድ ተዘግቷል። ራስ እምሩም ወደ ጎጃም የመመለሻ መንገዳቸው የተዘጋ መሆኑን አወቁ ስለዚህ የራሳቸውን ግዛት እንኳን ለመከላከል ማድረግ የሚችሉት ነገር አልነበረም።

ከብዙ ቀናቶች በፊት ራስ እምሩ ከንጉሡ የተላከ ደብዳቤ ደርሷቸው ነበር። በደብደቤውም ከወታደሮችና ከገበሬዎች ጋራ የተባበረ ግንባር ፈጥረው የጠላትን ግስግሳ ለመግታት እንዲሞከሩ ያን ማድረግ የሚቻል ካልሆነ ደግሞ እራሳቸው ራስ እምሩና ደጃዝማች አያሌው ከንጉሡ ጋር እንዲገናኙና ለመጨረሻ ጊዜ ተስፋ በሌለው ጦርነት ለሀገራቸው እንዲሞቱ ጥሪ ነበር። መልሳቸውን በስልክ እንዲያስታውቋቸው ንጉሡ ጠይቀው ነበር።

ንጉሡ ባሉበት ግንባር በሰሜን ምሥራቅ በኩል ስላሉት ሁኔታዎች ምንም ፍንጭ ሳይኖረን ነበር የከረምነው። ይህ ደብዳቤ ብዙ ነገር ነው ያስረዳን። እያንዳንዱን መስመር በፅሞና ላነበበው ሰው ደብዳቤው ንጉሡ ጦርነቱ ያለቀለት እንደሆነ አድርገው እንዳሰቡ ያስረዳል። የደብዳቤው መጨረሻ ራሱ ንጉሡ ጥርጣሬና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት እንዳላቸውም ያስረዳል። የመጀመሪያና የመጨረሻ የሆነው የንጉሡ ተስፋ ሞቷል።

ከዳባት እስከ ይፋግ(ጣና ሀይቅ አጠገብ ያለ ከተማ) ድረስ የነበረው የቴሌፎን መስመር ጠቅላላ በአካባቢው ሰው ወድሟል። ስለዚህ አዲስ አበባ የሚሆነውን ነገር ለማወቅና በየግንባሩ ያለውን ሁኔታ ለመረዳት ከፈለግን በተቻለ ፍጥነት ወደ ይፋግ ከተማ መሄድ ነበረብን። በደንቀዝ ከተማ ካደረግነው የሀያ ሰአታት እረፈት በኋላ ልክ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቀን የመጨረሻ ጦርነት ባደረግንበት በወሩ መንገድ ጀመርን። የመከራ ጉዟችንም ቀጠልን። አሁንም እንደገና ቅዱስ ጊዮርጊስ ለኛ እንዳልታደገን ለማየት ቢቃን።



ከከተማው ስንወጣ ከቀኑ አስር ሰአት ነበር ሰማዩን ከባድ ጥቁር ደመና ጋርዶት ነበር። ፈጠነ ተሸሎት በእግሩ መራመድ ይችላል። እኔም ከሶስት ሳምንት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በቅሎ ላይ በመውጣቴ ደስ ብሎኛል። የጉዟችን የመጨረሻዎቹ ቀናት በጣም አስቸጋሪዎች ነበሩ። እርቃኔን ለመሸፈን ስል የዝናብ ልብሴን በየቀኑ መልበስ ነበረብኝ። ሱሪዎቼ ተበጣጥሰው የተንጠለጠሉ ነበሩ። መከራ ቻይ የሆነውን ጫማዬን ለመቆጠብ ሥራመድ በጥንቃቄ ነበር።

መንገድ ከጀመርን አንድ ሰአትም አልሞላም ነበር ድንገት የዝናብ ማዕበል ጀመረ። በህይወቴ እንደዚህ አይነት አይቼም አላውቅም ወደፊትም እንደማላይ ተስፋ አደርጋለሁ። ልክ የማታ ያህል ጨለመ። ቁጥር የሌለው የመብረቅ ብዛት በአጠገባችን መሬት ከሚያንቀጠቅጥ ነጎድጓድ ጋር ይወርዳል። እንደበረዶ የሚቀዘቅዝ ማዕበልም መንፈስ ጀመረ። ፊታችን ሲመታን የነበረው ዝናብ ወደ በረዶ ተቀየረ ያለማቋረጥ ከሁለት ሰአታት በላይ ወረደ።

እንስሶቹ ጭራቸውን ወደ ነፋሱ አዙረው የሚንቀሳቀሱ አልሆኑም። በዚህ ሁኔታ በሜዳ ላይ ያለምንም መጠለያ በግራና በቀኛችን ጎርፍ እየወረደ መቆየት ነበረብን። ከቆምንበት ቦታ በረዶና ውሀ እስከጉልበታችን ድረስ ውጦን በብርድ እየተንቀጠቀጥን ነበር። "ቅዱስ ጊዮርጊስ! ምን በድለን ነው እንደዚህ የፈረድከብን" የሚሉ ንግግሮችም ይሰሙ ነበር ያም ሆኖ ትግሰት ያጠረው ማማረር አልነበረም። እልፎ አልፎ በረኸም መተንፈስ ብቻ ነው። ሰዎቹ ይህንንም ቢሆን እንደታዛዥ ልጅ ነው የተቀበሉት።

ቀጥሎም በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ሁልጊዜ እንደሚሆነው ሁሉ ጤነኛ ያልሆነ የመፅናናት ስሜት መታየት ተጀመረ። ከልክ በላይ የሆነ እንደሰካርም የሚመስል ሁኔታ ነው። ግን አንድ ሰው ከመጠን ወይም ከአቅም በላይ በሆነ የአእምሮ ጭንቀት ሲወጠር ለማረሳሳትና ለማሳለፍ ይረዳል። አንድ የጅል ቀልድም ተጀመረ። ቀልዱም በአቶ ማሞ ቤተሰ፣ በኢትዮጵያውያን ፓይለቶች፣ በጣልያን ምርኮኞችና በኔ በቀረው ድሬሰር በፈጠነ (ምክንያቱም ሌሎቹ ሁለቱ ስለጠፉ) መሀከል ነበር። ሁሉም በአንድ ጊዜ ይናገራሉ፤ ለመቀለድም ይሞክራሉ፤ እንደገናም በሆነው ባልሆነውም ከልባቸው ከት ብለው ይስቃሉ። የጅል አይነት ቀልድም ነበረ። አንድ ሰው አድጦት ሲወድቅ፤ ወይ ደግሞ አህያ ጭንቅላቱን ከዝናብ ለማስጣል ከሌላው አህያ ሆድ ስር ሲደብቅ፤ ወይ ደግሞ በቅሎ በብርድ እየተንቀጠቀጠ እየር

ሲያመልጠው ነበሩ። እንደዚህ አይነት ነገሮች ሳቅ ያስጀምራሉ ወዲያውኑ ሁሉም የተሰበሰበው ሰው እንደተለከፈ ሰው መሳቅ ይጀምራል።

ወኔያችም ተመለሰልንና ያ ሁሉ መአት እየወረደብን በጉልበት እንስሶችን ወደፊት ገፋናቸው። ሽባ እንደሆነ ሰው እዚህ መቆየቱ ምን ይጠቅማል? እንደምንም ታግለን ወደ ታች ወደ ረባዳው መሬት መውረድ አለብን ቢያንስ ቢያንስ ለአሳት የሚሆን እንጨት ይኖራል።

እየተገፋፋንም እየተሻሸንም ነበር። ሰዎች እየተደናቀፉ ጭቃ በጭቃ ሆነው ውሀ በሞላው ጉድጓድ ውስጥ ይወድቁ ነበር። ምን ይመጣል? በነዚህ ነገሮች መሳቅ ብቻ ነበር።

በሌላ በኩል ግን በጣም ደካማ የሆኑ ይህን ለመቋቋም እቅም የሌላቸው ሰዎች ነበሩ እነሱም መረዳት ነበረባቸው። ከነዚህ እንዱ ትንሿ አፀደ ነበረች በሚያሰገርም ጥንካሬ በረዶውን ተቀበለችው። ባዶ በነበረው በኔ በቅሎ ላይም እሳፈርኳት ነገር ግን በጣም ደከማ ስለነበር እንቅልፍ ወሰዷት ጭቃው ላይ በጭንቅላቷ ወደቀች። ከዚያ በኋላ  እኔና እንደኛው ፓይለት በየተራ እንሸከማት ነበር።

ከምሽቱ ሶስት ሰአት ብሰብሰ እንዳልን ሰውነታችን በሙሉ በጭቃ እስከ ጆሮአችን ድረሰ ተለቅልቆ ግራኝ በር ደረሰን። ወዲያውኑ ለእሳት የሚሆን እንጨት ለመልቀም እሽቅድድም ተጀመረ።

"እባባ ቶሎ ናልኝ" ተመልሳ ነቃ ያለችው አፀደ ነበረች እኔን ስትጠራ የሰማሁት።

እየሮጥኩ ሰደርሰ ከእቅሟ በላይ እሰር እጥፍ የሚሆን ግንድ ላይ ተጋድማ ባለ ጉልበቷ ግዙፍ ከሆነ አገልጋይ ትከላከላለች።

"ግንዱ የኔ ነው! መጀመሪያ ያየሁት እኔ ነኝ" እያለች በመጮህ እንደ እነር እየዘለለች የግዙፉን አገልጋይ እግር ትደበድብና ትናከሰ ነበር።

ሶሰት ቦታ በሚነድ ትልልቅ አሳት ዙሪያ ተቀመጠን ልብሳችንም ወዲያው ደረቀ ቡናም እፈላን ከደንቀዝ ያመጣነውን አንጀራና ወጥም በላን። እሁን የነበረን ሰሜት ቀዝቀዝ ማለት ጀመረ ደግነቱ ደከሞን ሰለነበር የማገገሚያው መልእከ እንቅልፍ በትክከለኛው ጊዜ ደረሰልን።

ማዕበሉ ከነበረዶው በጣም ሀይለኛ ቢሆንም ለኛ ጠቀሜታ ነበረው። ነግቶ በጣም ወሳኝ በሆነና በቀላሉ በማይታለፈው በግራኝ በር ማለፊያ ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያን የወረረው ግራኝ መሀመድን ያስቆሙበትና የተገደለበት ቦታ ለናልፍ ያየነው ነገር ነበር። ማለፊያው በጉድብና በግንብ የተዘጋጁ መተኮሻ



ምሽጎች ተሰርተውበታል። ለካሰ የእካባቢው ገበሬዎች እኛን ላለማሳለፍ ቆርጠው ተዘጋጅተው ነበር። ነገር ግን ማታውኑ ማዕበሉ በመምጣቱ ዕቅዳቸውን አፈረሰባቸው። እዛ ቦታ ላይ ከመጠን በላይ በረዶ የወረደ ይመሰላል ምክንያቱም ግዙፍ የሆኑ የበረዶ ከምሮች በየቦታው እናይ ነበር፡

በማለፊያው ደግሞ ግራኝ በፅኑ ሲቆሰል በንዴት በጎራዴው መትቶ ሊቆርጠው ነበረ የተባለውን የተጠማዘዘ የወይራ ዛፍ እየን። ይህ ዛፍ ራሱ ይሁን እርግጠኛ እልነበርንም ግን ይመሰላል ምክንያቱም ዛፉ በዘጠና ዲግሪ የተጣመመበት ቦታ ላይ የጠባሳ ምልክት ይታይ ነበር።



አሁንም በጎንደር ግራኝ በር በሚባል ቦታ (ፀሐፊው እለፍንበት ባሉበት) የሚገኝ ግራኝ መሀመድ ሲቆስል ተበሣጭቶ በጎራዴ የከተከተው የሚባለው የወይራ ዛፍ በተለያየ አቅጣጫ የተነሳ ፎቶ (ከላይና ከስር) (2007ዓ.ም.)

---

*ግራኝ አህመድ በዚህ ሰፍራ አድፍጦ በተኮሰ ሰው ጥይት የተመታ ሲሆን ተኳሹ ደግሞ የፖርቱጋል ወታደሮች አዛዥ የነበረው የከርሰቶፎር ደጋማ የግል ዘብ ነው። ከርሰቶፎር ደጋማ የታዋቂው አሳሽ የቫሰኮ ደጋማ ወንድም ነው ወደ ኢትዮጵያ ለእርዳታ አራት መቶ ወታደሮች ይዞ መምጣቱ ይታወቃል። ከርሰቶፎር ደጋማ ተማርኮ በግራኝ እጅ ሰለተገደለ ተኳሹ የአለቃውን ደም ተበቀለ ተብሏል። ግራኝ አህመድ በዚህ ቦታ ሲሞት ተከታዮቹ ሸሽተው ወደ ሐረር በመመለሰ በከተማው ግንብ እንደሠሩ ተዘግቧል። ከተለያዩ መረጃዎች የተሰበሰበ። (ተክለፃድቅ መኩሪያ ፣ ሪቻርድ ፓንክረሰት፣ ኢንሳይክሎፔዲያ ኢትዮፒካ)*



በቀን ብዛት ያላቸው አውሮፕላኖች ይመጡብን ነበር ግን ምንም አይነት የመተናኮል ሁኔታ አላሳዩም:: በጣም ዝቅ ብለው በላያችን ላይ ደጋግመው ይበሩ ነበር ምንም ነገር አልጣሉብንም:: የኛ ሰዎችም ቢሆኑ ወደ አውሮፕላኖቹ የመተኮስ ፍላጎት አልነበራቸውም::

ማታውን በእጠገቡ የጥንት ቤተመንግስት ፍርሥራሽ በሚታይበት በአሰደላቹ የአርኖጋርኖ ወንዝ ዳርቻ አሳለፍን:: በሚቀጥለው ቀን ተጉዘን በመጋቢት ሀያ ሰድሰት እኩለ ቀን ላይ ይፋግ ከተማ ገባን::

የጦር አዛዦቹ ወዲያውኑ ከአዲስ አበባ ጋራ ግንኙነት አደረጉ:: የቴሌፎን ሠራተኛው የጎንደሩ መስመር ተቋርጧል አለ በኋላ ሰናጣራ ግን ውሸት ነበር:: ሰውየው ከጣልያኖች ጋራ ሲገናኝ ነበር አሁንም ይገናኛል::

ከሁለት ሰአታት ደወልና ጩኸት "ሀሎ!" በኋላ ከአዲስ አበባ ጋራ ግንኙነት ተጀመረ:: ግንኙነቱም በመሀል መቀባበያ ጣቢያዎች በደብረታቦር፣ አጋት፣ በሸሎ፣ መቅደላና ወረኢሉ በኩል አደርጎ ነበር::

ራስ እምሩ የመጀመሪያውን እድል ስለወሰዱ ከሁለት ሰአት በላይ ለሚሆን ጊዜ ማውራት ቀጠሉ ደጃች አያሌው በትግስት ውጭ ሆነው አየተጠባበቁ ነበር:: ከዛም የደጃዝማች ተራ ደረሰና አሳቸውም ተመሳሳይ ረጅም ንግግር



አደረጉ:: ከዛ በኋላ ሁለቱም በአየጃቸው መገናኛውን ይዘው ተቀመጡና ከአዲስ አበባ ጋራ ከአንድ ሰአት በላይ ተነጋገሩ::

በመሀሉ አንደነሱ ብዙም ጭንቀት የሌለብን እኛ ደግሞ ጊዜያችን ደስ በሚል ሁኔታ ለማሳለፍ አሰበናል:: መልከተኛ ከምሽቱ አራት ሰአት ላይ ወደኛ ሲመጣ በከተማው ውስጥ ባለ አንድ የመኖርያ ቤት ደምበኛ አራት ግብዣ አዘጋጅተን አየተደሰትን ነበር:: መልከቱም አዛዦቹ ንግግራቸውን ስለጨረሱ ከከተማው ብዙ ኪሎ ሜትሮች ራቅ ባለ የካምፕ ቦታ አንድንሄድ ነበር::

ለብዙ ሰአታት አዲስ አበባ ካሉ ገዥዎች ጋራ ንግግር ቢያደርጉም ደጃች አያሌው ስለ አቢሲኒያ ምን አንደተደረገና ምን አየሆነ አንደሆነ ያገኙት ዕውቀት የለም:: በኦፊሲያል አቴጌይቱ ሀላፊ አንደሆኑ ነው የተነገረው ነገር ግን በርግጥ ሀላፊ የነበሩት የንግድ ሚኒስትሩ አቶ መኮንን አንደሆኑ ነው የተረዳነው::

"እንዲህ ከሆነ ነገሮች በሙሉ መጥፎ ደረጃ ደርሰዋል" አሉ ደጃዝማች የሰሙትን ነገር ሲነግሩኝ:: እኔ አንኳን ገብቶኛል ምክንያቱም የተከበሩ ሚኒስትሩን በደንብ አውቃቸው ነበር:: በትልቁ ምንም አይነት የሚረባ ነገር የሌላቸውና ከዚህ በፊት ታይቶም ተፈጥሮም የማያውቅ በጣም የገማ አሳ ማለት ነበሩ::

ትንሽ ዘግይቶም የጦር ሚኒስትሩ ልጅ የራስ ካሳ እና የራስ ሰዩም ሠራዊት የተሸነፈ መሆኑ ታወቀ:: ሆኖም አንደሚኒስትሩ አቶ መኮንን አገላለፅ ይህ አደገኛም አልመሰለም ምክንያቱም ንጉሡ ብዛት ያለው ሠራዊት ይዘው ወደ ጦር ግንባር አየሄዱ ሰለሆነ ጣልያኖችን በመጡበት መመለስ ይችላሉ:: አንደዚያ ከሆነ ደግሞ ሠላም ተመልሶ ይመጣል:: በአጋጄን በኩል ደግሞ ኢትዮጵያውያኑ የግራዚያኒን ሠራዊት ሙሉ በሙሉ ሲደመስሱት ምንም አልቀራቸውም ነበር:: ራስ እምሩና ደጃች አያሌውን በተመለከተ እርሰ በርሳቸው ከተመካከሩ በኋላ ይበጃል ብለው ያሰቡትን ነገር ሲያደርጉ ነው:: እንግዲህ በቆራጥነትና በአገር ወዳድነት ሰለተዋጉ በንጉሣውያን ቤተሰቦች መታመንና መልካም ፈቃድን አግኝተዋል::

በኋላ አንኳን ሰለዚህ ቅጥፈት ሳስብ በንዴት ብዛት ያጥወለውለኝ ነበር:: እንግዲህ ይህን ያደረጉት ቀበሮው አቶ መኮንን ናቸው:: ያን ሁሉ ሰአት በሰልክ ንግግር ሲለዋወጡ አነዚህን ሁለት የተከበሩ ሰለ አባት አገራቸው ሁኔታ የተጨነቁ ሰዎችን በውሸት ሲደልሉዋቸው ነው የቆዩት:: ራስ እምሩና

ደጃች አያሌውን:: ምንም አይነት መረጃም የላቸውም እናም ሀይልም አልነበራቸውም ስለዚህ በሙሉ እምነት ከአዲስ አበባ ገዥዎች ባለው ሁኔታና ወደ ፊት ስለሚሆነው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ምክር ጠየቁ:: በዚህ ሁኔታ አያሉ ነው ሚኒስትር ተብየው አዲስ አበባ ቁጭ ብለው ሰዎቹን ጆሯቸው እስኪሞላ ድርስ ምንም አደጋ የለም አያሉ ሲነግሯቸው የነበር:: ሚኒስትሩ ግን ንጉሡ ሽሽት እንደጀመሩ ያውቁ ነበር::

በሚቀጥለው ቀን ወደ ጎጃም ለመሄድ ከወሰኑት ከራስ እምሩ ጋራ ተለያዬን:: ለኛ የነበረን እማራጭ ወደ ደብረ ታቦር መሄድ ነው:: ደብረ ታቦር የደጃዝማች አያሌው አማች ደጃዝማች እስፋወሰን ነበሩ አዛዡ:: ከአምስት መቶ ከማይበልጡ ወታደሮች ጋራ በመሆን በመጋቢት ሰላሳ በጠዋቱ ደብረታቦር ገባን:: ከተማው ዙርያው ያምር ነበር::

እኔና ፓይለቶቹ ጓደኞቼ መጀመሪያ ያደረግነው ነገር ቢኖር አውሮፕላን እንዲላክልን ወደ አዲስ አበባ ቴሌግራም ማድረግ ነበር:: መልሱም ከጥቂት ቀናት በኋላ በቴሌግራም ተላከልን:: ከእቴጌዋ ነበር የተላከው:: አውሮፕላን መላክ እንደማይቻል ነው የተገለፀልን:: ለደህንነታችን ሲባል ከደጃዝማች አያሌው ጋራ እንድንቆይ ተነገረን::

ቴሌግራሙን ከላኩ በኋላ ወደ እድቬንቲስት ሚሲዮን ማዕከል ሄድኩኝ በሶስቱ አውሮፓውያን ታላቅ የወዳጅነት አቀባበል ተደረገልኝ:: ሚስተር ፓልም ስዊድናዊ፤ ሚስስ ፓልም ኖርዌይ እና በእንግድነት የመጣው ጀርመናዊው ሚስተር ሄስ ነበሩ:: በደብረታቦር ለአንድ ሳምንት በቆየሁበት ጊዜ በሚስተርና ሚስስ ፓልም ቤት ነበር በእንግድነት ያረፍኩት ሚስትር ሄስም እዛው ቤት ነው ያለው:: ገላ ለመታጠብና ፂሜን ለመላጨትም እድል አገኘሁ:: የራሴ ፀጉር ትከሻዬ ላይ ይደርስ ነበር:: ሄስ ፀጉሬን ቆረጠልኝ:: ሚስትር ፓልም ደግሞ ሱሪ ሰጠኝ::

---

*አጼ ሀይለ ሥላሤ በስደት በነበሩበት ጊዜ ራስ እምሩ በሀገር ውስጥ የንጉሡ ተወካይ ወይም እንደራሴ ነበሩ:: በዚህ ምክንያት ይኖሩበት የነበረው ከተማ ጎሬ ለተወሰነ ጊዜ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ነበረ:: ከከባድና ከፍተኛ ውጊያዎች በሁዋላ ራስ እምሩ በታሕሣሥ ዘጠኝ ለጣልያኖች እጃቸውን ሠጥተዋል:: ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ወደ ግራዚያኒ ተልከው ነበር ቀጥሎም ወደ ሞሶሎኒ ወደ ሮማ ከተላኩ በሁዋላ ፖንዛ በሚባል ደሴት የቁም እስር ሆነው ነበር:: የሚገርመው ነገር ከሰባት አመታት በሁዋላ ሞሶሎኒ ራሱ በዚህ ቦታ ታስሮ ነበር::*
*Haile Selassie's War by Anthony Mockler*
*በተመሳሳይ ሁኔታም ደጃዝማች አያሌው ጣልያን ውስጥ አሲናራ የሚባል ደሴት በቁም እስር እንዲቆዩ ተደርገዋል:: ከተመለሱ በሁዋላም ለሁለተኛ ጊዜ ተዋግተው እንደገና እንደተማረኩ ተዘግቧል::*
*(ኢንሳይክሎፔዲያ ኢትዮፒካ)(ጎንደሬ ቢጋሻው በገሪማ ታፈረ)*



ለአምስት ወራት በየጫካው ከርታታ ኑሮ ስኖር ከርሜ አሁን ግን ንፁህና ደስ የሚል በስዊድን ባህል የተዘጋጀ ጠረጴዛ አጠገብ ስቀመጥ የተሰማኝ ስሜት መግለጫ የለውም:: የውነት አልጋ ላይ ንፁህና ጥሩ ሽታ ያለው ነጭ አንሶላ ውስጥ ገብቼ መተኛት ደግሞ የነበረኝን ስሜት ከፍ ነው ያደረገው:: በአራት ማዕዘን ግድግዳ ያለው ቤት ውስጥ መተኛት መቻልስ የሚሰጠው የደህንነት ስሜትስ! ምስጋናዬ ለእነዚህ ለረዱኝና ለተንከባከቡኝ ጓደኞች ልክ የለውም ወደፊትም ቢሆን ሳመሰግናቸው እኖራለሁ::

የሚያምረው የሚሲዮን ማዕከል ከከተማው ጠርዝ ነው የሚገኘው:: የጠቅላላው የሚሲዮኑ ቅጥር ግቢ ወደ 35 ሄክታር ይሆናል ዙሪያውንም በአጋም ተክል ታጥሮአል:: ግቢው ውስጥ ደግሞ በጣም ጥሩ ከሀያ አምስት እስከ ሰላሳ ሰዎች መያዝ የሚችል ሆስፒታል፣ የኦፕሬሽን ክፍልና ክሊኒክ ፤ ሶስት የመኖርያ ቤቶች፤ ትምህርት ቤትና ቤተክርስቲያን አሉበት:: በደንብ በእንክብካቤ የተያዘ የአትክልት ቦታና ብዙ ሺ ለአይን የሚያስደስቱ የባህር ዛፎች ያሉበት መናፈሻ ቦታም አለው:: ሁሉም ነገር በደንብ በሥነሥርአት ነው:: እኔም ምቾት አልጎደለኝም:: ከራሳቸው ጄኔሬተር የኤሌክትሪክ መብራትም ነበር::

በጦርነቱ ምክንያት ስለተዘጋ ትምህርት ቤቱ በዚያን ጊዜ ለአቢሲኒያ ባንክ የደብረታቦር ቅርንጫፍ በኪራይ ተሰጥቶአል:: ባንኩም ወስጥ የሚሰሩ አሜሪካ የተማሩ ሁለት ወጣት አቢሲኒያውያን ጋራ ተዋወቅሁ::

ፓልም ቤት ውስጥ የተሠራ የሚገርም ሬዲዮ ማዳመጫ ስለነበረው በውጭው አለም የሚደረገውን ነገር መከታተል እንችል ነበር:: ያው ፀጉር የሚያቆም ዜና ተራ በተራ ቢያሰማንም ለኔ ደግሞ ትልቅ ዜና የሆነው አቢሲኒያ ውስጥ የሚደረገው ነገር ነበር ::

ጠቅላላው የሰሜን ግንባር እልቆለታል ንጉሡም እየሸሹ ነበር:: የት እንዳሉ ግን ማንም አያውቅም::

የአዘቦና የወሎ አሮሞዎች ድሮ የደረሰባቸውን በደል ለመበቀል ከግንባር የሚመለሰውን ጦር ይዘርፉትና ይወጉት ነበር::

ራስ ሙሉጌታና ልጃቸው ተገድለዋል

ጣልያኖቹ ጉዟቸውን ወደ ደሴ እየቀጠሉ ነበር:: አረንጓዴ ነጭና ቀይ ቀለም ያለው የጣልያኖች ባንዴራም በጣና ሀይቅ ዳርቻ ለሀያ አራት ሰአታት ይወለበለብ ነበር:: በአጋዴን ግንባር አቢሲኒያውያኑ መከተው እንደያዙ ነው ነገር ግን የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ መስመሩ መሰበሩ አይቀርም::

አቅም የሰሹ ሊግ ኦፍ ኔሽንስ ስብሰባ በመጥራትና አስተያዬት በመደርደር ጊዜ እያጠፋ ነው::

የንጉሡ ሀይለኛ ተናጋሪ የነጭ አማካሪዎች በሙሉ አገሩን ለመልቀቅ የተገኘውን አጋጣሚ እየተጠቀሙ ነው ምክንያቱም ሁኔታው ደካማና አደገኛ ነው ብለው አስበዋል::

በግልፅ አጠቃላይ የሆን ድምዳሜ እለ ነገር ግን ገና በጦርነት ያልተሸነፈው የአሊጋ ወራሹ ጦር በቦታው እያለ ጠላት እንዴት ብሎ ነው ደሴ ድረስ የዘለቀው? እንዲህ ብለን ነበር እኛም አስበን የነበረው::

ፋሲካን በደብረታቦር ከአከበርን በኋላ ወዲያውኑ በኃይንትና በመቅደላ አድርገን ወደ ደሴ መጓዝ ነበረብን::

በየቀኑ የሚሸሹ የራስ ካሳ ሰዎች ይመጡ ነበር:: እነዚህን የተጎዱ ወታደሮች ማየት በጣም ያሳዝን ነበር:: አቅም ያነሳቸው ዕራፊ የለበሱ በተቅማጥና በፈንጣጣ የደከሙ ነበሩ:: በየቀኑ በአስሮች ቤት የሚቆጠሩት እየሞቱ ነበር የቤተከርሰቲያን ቅጥርም በቂና ሰፊ ስላልነበረ በየሜዳው ነበር የሚቀበሩት::

አንድ ቀን አንድ ትልቅ ባለሥልጣን ከብዙ መቶ ወታደሮች ጋራ ሸሽቶ መጣ ወዲያውኑ ወደ አዲስ አበባ ሊሄድ ነው:: የባንክ ሠራተኞቹ ፓይለቶቹ እና እኔም ልንከተለው ወሰንና ተዘጋጀን:: ደጃች አያሌው ግን እኔን እንዳልሄድ ከለከሉኝ:: አያሌው ሁኔታው በጣም አደገኛ ነው ያሰቡት ቦታም አይደርሱም እሉ:: ለመንኩ ፀለይኩ ቢከለከሉኝም እሄዳለሁ ብዬ አስፈራራሁ:: "የራሴ አሰቃ ራሴ አይደለሁም እንዴ?" አይሆንም!:: እሄዳስሁ ብዬ ከሞከርኩ እንደሚያስሩኝ ነገሩኝ ምክንያቱም በመንገድ ላይ እንድገደል አልፈለጉም::

ስለዚህ ሌሎቹ ጥለውኝ ሄዱ:: በመቅረቴ ተፀፅቼ አላውቅም:: በአንድ ሳምንት ውስጥ ሁሉም ተገደሉ::



# ምዕራፍ ሀያ ሁለት

## መከበብ

በበጌምድር በራስ ካሳና በልጆቻቸው በአስፋወሰንና በወንድ ወሰን ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ነበር:: ምክንያቱም በራሰ ወዳድነት የመሠረቱት የግብር ሥርአት ገበሬውን የሚበዘብዝ ነበር::

እያንዳንዱ ገበሬ ካመረተው ሰብል አንድ አሥረኛውን ዋጋ
ስእያንዳንዱ በሬ ሁለት ማር ተሬዛ
ለበግ አንድ አስረኛ
አንድ ማር ትሪዛ በጭስ (በጎጆ ማስት ነው)
ከዶሮ አንድ አሥረኛውን
ለሠራዊቱ የሚሆን አራት ማር ትሬዛ
ሁስት ማር ትሬዛ ለፍርድ ቤት
ገበያ ላይ ስተሸጡ ማንኛውም እቃዎች አንድ አስረኛውን ዋጋ
በተጨማሪም ደግሞ ለአገረ ገዥው በድምሩ የሰላሳ ቀን የጉልበት ሥራም ነበረበት::

ከዚህ በተጨማሪ ከጠቅላላ ገቢ አንድ አስረኛውን ለቤተከርስቲያን ብዙ ጊዜ ደግሞ ተጨማሪ ግብር ስማዕከላዊ መንግስት ይሰበሰብ ነበር:: በድምሩ የበጌምድር ገበሬ ከአመት ገቢው ከሀምሳ እስከ ስልሳ በመቶ (ፐርሰንት) ድረስ ይገብር ነበር::

በዚህ ሁኔታ እንግዲህ ያሁኑ ገዥ አስፋወሰን ደብረታቦር ላለመቆየት ቢወስኑ እንግዳ ነገር አይሆንም:: ከኛ ጋራ በመሆን አዲስ አበባ ስመሄድ ወስነዋል:: ያገሩ ሰዎች በምስጢር ወደ ጣልያኖች ወደ ጎንደር ተወካይ ልከው ጣልያኖቹን የተቀበሉ መሆኑን ለማረጋገጥ እንደሞከሩ አሰፋወሰን ያወቃሉ:: ከሌሎች ከተሞች ተለይቶ ደብረ ታቦር በቦምብ ያልተደበደበበት ምክንያትም ይህ የምስጢር መልከት መሆኑን መረዳት ይቻላል::

በሚያዝያ ስድስት በጠዋቱ የኔ አለቃ ደጃች አያሌው ከአማቻቸው ጋር በመሆን ከተማውን ጥለው በመውጣት በምሥራቅ በኩል የአንድ ማይል ርቀት ላይ ካምፕ መሰረቱ። እኔ ራሴ ምሽት እስከሚሆን ዘገየሁኝ ምክንያቱም ከጓደኞቼ ከሚሲዮናውያኑ ጋር እስከተቻለ ድረስ አብሬ መቆየት ፈልጌአለሁ። የነሱን ምክር መቀበል ግን አልፈለግሁም። ምክራቸውም ጣልያኖቹ እስከሚመጡ ድረስ ከነሱ ጋር ሆኜ እንድጠብቅ ነበር። የአቢሲኒያ መንግስት ሠራተኛ ስለሆንኩ ራሴን አሳልፌ ለመስጠት አልወሰንኩም።

ከዚህ በተጨማሪ እንዲህ አይነት ነገር ማድረግ ደጃዝማችን መክዳት ነው ብዬ አምናለሁ። ምንም አንኳን ወደፊት ምንም የምረዳቸው ነገር ባይኖር በክፉ ጊዜ ከጎናቸው መቆም የኔ ሀላፊነት ነው ብዬ አስቤያለሁ።

ማታው በችኮላ ነው የደረሰው ስለዚህ ጓደኞቼን ትቼ መሄድ ነበረብኝ። ልቤ እየተንተተ በቅሎዬ ላይ ተሳፍርኩና ጀርባየን ለአስደሳቹ የሚሲዮን ጣቢያ ሰጠሁኝ። ለአጭር ጊዜ በሚሲዮኑ ጣቢያ ባሳለፍኩበት ጊዜ የለመድኩትን አኗኗር ጭልፍታ አይቼ ነበር አሁን ግን እንደገና እየተዘጋብኝ ነው። እንደገና ደረቁ መሬት መኝታዬ ሊሆን ነው። እንደገና አምስት ጣቶቼን እንደ ሹካ ልጠቀም ነው። እንደገናም ከቅማል ጋራ ልንገናኝ ነው እንግዲህ ይህን መድረሻው ያልታወቀ ያልተቋረጠ የመከራ መንገድ ልቀጥል ነው።

ለአንደ አፍታም ቢሆን አይታው ብሩህ ነበር። የማስታውሰው ትዝታ አግኝቻለሁ። ወዳጅነት የሚያሳዩ ሰዎች ትዝታ፤ በሰላም ያሳለፍኳቸው ሰአቶች፤ ሰላማዊ የነበሩ የማንበቢያ ቀኖች፤ ከሰዎች ጋራ ያደረግሁት ተሀድሶ የሚሠጥ ንግግር። ይህ ትዝታ እንግዲህ የሚመጣውን አዲስ ማዕበል ለማሳለፍ ይረዳኛል።

ግማሽ መንገድ በጀርባዬ ትቼ ነበር ጨለማው መስፈን ሲጀምር። በአካባቢያችንና በተለያዩ አቅጣጫ የተኩስ ድምፅ መሰማት ጀመርኩ። የውሻ ጥርስ የሚባል ማለፊያ ቦታ ላይ ነበር። ከፍታው ላይ ባሉ ሰዎች እንድንቆም ታዘዝን።

በቅሎውን ሲመራ ከነበረው ወታደር ጋራ በመሆን ከኮርቻ ወርጄ ጥይቶች በጎናችን እያፏጩ በታቻለ ፍጥነት መሮጥ ጀመርን። ትንሽ መቶ ሜትሮች ወደፊት እንደሮጥን ወንዝ አጠገብ ስንደርስ ደጃች አያሌው የሰጡኝን አውቶማቲክ መሳሪያ ጠመድን።

የተኩስ ልውውጡ ለደቂቃዎች ቀጠለ ቆይቶም የተፋጠጡት ከአውቶማቲክ መሳሪያ ጋራ ስለነበር ወንበዴዎች ተኩስ በማቆማቸው ደስተኛ



ሳይሆኑ አይቀሩም። ከዚያ በኋላ መንገዳችን ያለምንም ረብሻ መቀጠል ቻልን።

በሚቀጥለው ቀን በበጌምድር አረንጓዴና ለምለም ነገር ግን ቀዝቀዛና ደጋማ በሆነው ክፍል አቋርጠን መጓዝ ቀጠልን። በየቦታው ብዙት ያለው የቀንድ ከብት የበግ የፈረስና የበቅሎ መንጋ አየን። ለመጀመሪያ ጊዜ በአቢሲኒያ በፈረስ የሚያርሱ ገበሬዎች አየሁ ሌላ ጊዜ በበሬ ነው የሚታረሰው።

አመሻሽ ላይ ደጃዝማች አያሌው ከአካባቢው ሰዎች በጣም ቁምነገር ያለው መልክት ይዘናል የሚሉ ተወካዮችን ተቀበሉ። በዚያን ጊዜም ግልፅ የሆነው ገበሬዎቹ ደጃች አያሌው በመካከላቸው አልፈው ቢሄዱ ችግር እንደሌለባቸው ነው። ደጃማቹ ችግር ላይ እንደሆኑና ንጉሡን ለመገናኘት እንደሚሄዱ አውቀዋል። ነገር ግን ደጃማች ከራስ ካሳ ልጅ ከአስፋወሰን ጋር አብረው እንዳይጓዙ ጠየቁ ምክንያቱም የራስ ካሳ ልጅ በመሬታቸው አልፈው እንዲሄዱ አልፈለጉም። ሲጨቁኗቸው ስለኖሩ የነሱ አንባ ሲፈስ እንደኖረው ሁሉ ደማቸውን ካላዩ እንደማይረኩ ገለፁ።

"በጥያቄያችሁ ባልስማማስ?" ብለው ጠየቁ ደጃዝማች ምንም አይነት የሰውነት ምልክት ሳያሳዩ

"መልካም፤ ህዝቡ አማራጭ የለውም ስለዚህ አያሌውም ቢሆኑ የበዳዮቹን ዕጣ ይካፈላሉ"

የደጃዝማች ደማቸው ነው የፈላው። ቀጥሎም

"አስፋወሰን እኔ እስከፈቀድኩ ድረስ አብሮኝ ይሄዳል። አናጠቃለን ብላችሁ ከደፈራችሁ መላኩ ገብርኤል ይርዳኝ ቤታችሁንና እናንተን አቃጥላችኋለሁ የመትረየሴ ሳት ራት ትሆናላችሁ" አሉ።

ቅዱስ ገብርኤል የአያሌው ጠባቂ መልአክ ነው። አያሌው በገብርኤል ከማሉ አለቀለት ማለት ነው ይህንንም ድፍን አቢሲኒያ ያውቀዋል።

ከገበሬዎችም የመጣ ጥቃት አልነበረም። ከፍታው አራት ሺ ሁለት መቶ ሜትር የሆነው ጉና ተራራ ለንደርስ በብርድ ሰውነታችን ሲረጋ ምንም አልቀረውም። አስፋወሰንም የመረጋጋት ስሜት ተሰማቸው። አዲስ አበባ ቶሎ ለመድረስ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ከኛ ተለይተው ሄዱ። ከሳቸውም ጋራ

አምስት መቶ ወንዶችና ሴቶች ነበሩ በተጨማሪም የኛ የጣልያን ምርኮኞችና ሌሎች ሶስት በራስ ካሳ የተማረኩ ወደ ደብረታቦር የተላኩ ጣልያኖችም ነበሩ፡፡

እኛ ደግሞ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ወደ ደሴ የሚወስደውን መንገድ ያዝን፡፡ መጀመሪያ ደጃች አያሌው የትውልድ ቦታቸውን በጋይንት የሚገኘውን ሌፍራታን ማየት ፈለጉ፡፡ እናታቸውንና ወንድማቸውን መጠየቅ ፈልገዋል፡፡ ልጃቸው ሳይሰሙ እናትየዋ ከሞቱ መንፈቅ አልፏል፡፡

ጋይንት ስንደርስ የደጃዝማች አድማሱ እንግዶች ነበርን፡፡ አድማሱ ከወንድማቸው ከአያሌው ጋራ የሚያመሳስላቸው ነገር የሰም፡፡ ተጫዋቾች ናቸው ወፍራምም ነበሩ፡፡ አድማሱን በሕይወታቸው በጣም የሚያስደስታቸው ነገር ጥሩ ምግብ ከጨዋታና ከሳቅ ጋር ተበልቶ የሚመች አረፍት ማድረግና ቀኑን ሙሉ መተኛት ነው፡፡ ሌላ የተሰየ ባህሪ ካላቸው ደግሞ በቆይታ የሚታይ ነገር ነበር፡፡

ለማደሪያ የተሠጠኝ ትልቅ ድንኳን ነበር በጣራው ላይ ትልቅ ቀይ መስቀል ተስሎበታል፡፡ አድማሱን ምን ማለት ነው ብዬ ስጠይቅ ቀይ መስቀል ያስቀባሁት ጣልያኖቹ እንዳይደበድቡት ለማታሰል ነው በማለት የጮሌ መልስ ሰጡኝ፡፡ ይህንን ማታሰል የጀመሩት ራስ ካሳ ናቸው እሳቸውን ተከትሎ ጦሩም ቀጥሎበታል፡፡ “ስለዚህ” አሉ አድማስ በረዥሙ እየተነፈሱ “ብዙ ሳይቆይ ጣልያኖቹ ማታሰል መሆኑን ማወቅ ይጀምራሉ”

በርቀት የመቅደሳ ተራራ ይታየናል ወደ ትልቁ የበሸሎ ወንዝ ለመሄድ እየተዘጋጀን እያለን ደሴ በጣልያኖች መያዙን የሚገልፅ ዜና ደረሰን፡፡ የማይታመን ነገር ነው የመሰለው ደጃዝማችም እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ሁለት ሰዎች ላኩ፡፡

ከአምስት ቀናት በኋላ መልከተኞቹ ተመለሱ የተወራው ነገር እውነት መሆኑንም አረጋገጡ እንዲያውም ብዙ ተጨማሪ ወሬ ይዘው መጡ፡፡ ጣልያኖቹ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ወስነው ወደፊት እየገሰገሱ ነው፡፡ የያዟቸው መኪናዎች ብዛት ስላላቸው መቁጠርም አስቸጋሪ ነበር፡፡

አሁን ያለን አማራጭ ሁለት ብቻ ነው፡፡ ወይ ወደ ምዕራብ በኩል ወደ ጎጃም መሄድ አለዚያም ወደ አዲስ አበባ መቀጠል ነው፡፡ ወደ አዲስ አበባ መሄዱ ጥሩ ሀሳብ መስሎ ለማንኛውም ለደህንነት ሲባል ሁለት መልከተኞች ወደ አዲስ አበባ ሄደው ሁኔታውን እንዲያጣሩ ተደረገ፡፡



በዚህ ሁኔታ እያለን ውሎ አድሮ መከበባችን ግልፅ ሆኖ ታወቀ፡፡ የሰማዳ ገበሬዎች በምዕራብ እና በደቡብ በኩል ተሰባስበዋል፡፡ ደፍሮ በመሬታቸው በኩል የሚያልፈውን ማንም ሰው ለመግደል ወስነዋል፡፡ አስፋወሰን በብልጠት ሾልከው አምልጠዋል፡፡ ገበሬዎችም እንዲህ ያለ ነገር አይደገምም ብለዋል፡፡ ሁለቱ የአቢሲኒያ ፓይለቶች የባንኩ ሠራተኞችና አብሮ የነበረው ጦር ለአራት ቀናት አራሳቸውን ተከላከለው ነበር ሆኖም በመጨረሻው ተገድለዋል፡፡

በሚያዝያ ሀያ አንድ ጣልያኖቹ ደብረ ታቦር ከተማ ገብተዋል፡፡ ከሳምንት በኋላ ደግሞ ያ የምናውቀው *መሀመድ ኢማም የኤርትራው ገዢ የጋስፓሪኒ መልከተኛ ሆኖ መጣ፡፡ ሀሳቡ እንግዲህ ይህን የሚያህል ትልቅ ሰው ደብረ ታቦር ድረስ በድካም መምጣቱ ለአያሌው ወዳጅነት ተብሎ ስለሆነ መሀመድ ኢማም አያሌው እጃቸውን እንዲሠጡ ሊያሳምናቸው ይችላል ነው፡፡ ደጃዝማች ምንም አይነት ተቃውሞ እንዳያደረጉ ምክር ተሠጣቸው፡፡ ቢያደርጉ የሚጎዱት እሳቸው ናቸው ምክንያቱም የኃይለ ሥላሴ መንግሥት የሚባል ነገር የለም፡፡

ጋስፓሪኒ ፊርማው ያለበትና ማህተም በተደረገበት ደብዳቤ አያሌው መልካም አመሰካከት ካሳዩ ምንም እንደማይደረጉ ዋስትና ሰጥቷል፡፡ የተከበረው የኤርትራው ገዢ ለአያሌው የራስ ማዕረግ ከነሙሉ ጥቅሙ እንዲሠጣቸው ከጣልያን መንግስት ሊጠይቅላቸው አስቧል፡፡

ደብዳቤውን ከሳረከበ በኋላ የተከበረው አስታራቂ ማስታወቅ የፈለገው በግሉ በራሱ በወዳጅነት እንደመጣ እንጂ በጣልያን መንግሥት እንዳልተላከ ነው፡፡

መሀመድ ኢማም በመጣ በሁለተኛው ቀን ወደ አዲስ አበባ ተልከው የነበሩት ሁለቱ ፈጣን መልከተኞች ተመለሱ፡፡ እንዴት አድርገው የሶስት መቶ ኪሎሜትር ርቀት በሶስት ቀን ተኩል እንደሸፈኑ ለመግለፅ አስቸጋሪ ነው፡፡ እንጦጦ ጋራ ላይ ሆነው አዲስ አበባ በእሳት ሲቃጠል አይተዋል፡፡ ዲያብሎስ ከተማውን እያመሰው ነበር፡፡ ንጉሡ ወደ ጅቡቲ ሸሽተዋል፡፡ ጣልያኖችም እየተቃረቡ ነበር፡፡ መላው አገሩ ቅጥ ያጣ ስለመሆኑ በመልከተኞቹ ይታወቃል፡፡ ከለበሱት ሱሪ በስተቀር ሁሉም ነገር ተወስዶባቸዋል፡፡ ሕይወታቸውም የተረፈው ጠመንጃ ባለመያዛቸውና የነበራቸውን በፍቃደኝነት በመስጠታቸው ነበር፡፡

---

*ስለዚህ ሰውየ ወደ ደብረ ታቦር መምጣት ገሪማ ታፈረ ጎንደሬ ቢጋሻው በሚባለው መፅሐፋቸው ዘግበዋል፡፡ ገሪማ መሐመድ ኢማምን ካባለሬ ኢማም ብለው ነው የሚጠሩት

በዚህ ሁኔታ እያለን ጣልያኖቹ በሚስጥር ገበሬዎቹን የሚያስፈራራ ቅስቀሳ ያሰደርጉ ነበር፡፡ እያሌው እጁን ካልሠጠ አውሮፕላኖች እሱ ያለበትን ቦታና አካባቢውን በሙሉ እንደሚደበድቡ ነው፡፡ አውሮፕላኖቹ አንድ ቀን ብቅ እሉ ነገር ግን በምብ ሳይሆን ፓምፍሌት ነበር የሚጥሉት፡፡ አዲስ እበባ መያዙን፤ ጠቅላላው አገሩ እጅ መሰጠቱንና፤ የጣልያኑ ንጉሥ የአቢሲኒያ ንጉሥ መሆኑን የሚገልፅ ነበር፡፡

በመጨረሻም ደጃዝማች እያሌው ሰጣልያኖች እጃቸውን ለመስጠት ወሰኑ፡፡ የወሰኑት ውሳኔ ትክክል ወይም ስህተት ይሆን እኔ ፍርድ መስጠት የምችልበት ሁኔታ እይደ.ሰም፡፡ ውሳኔው የራሳቸው ነው፡፡ እኔ የማውቀው ነገር ቢኖር ደጃዝማቹ ያንን ርምጃ ባይወሰዱ ኖሮ እንደኛችንም በሕይወት አንገኝም ነበር፡፡ ሌላ አማራጭ እልነበረም፡፡

በግንቦት ሰባት ደጃዝማች በፍጥነት ወደ ደብረታቦር ተመለሱ ምክንያቱም ጋስፓሪኒ ለመልስ ከሁለት ቀን በላይ መጠበቅ እንደማይችል እሰታውቆ ሰለነበር ነው፡፡ እኔ ለጊዜው ከወይዘሮ ማናህሎሽ ጋራ በመሆን ኤፍራታ ቆየሁ፡፡ ከሳምንት በኋላ ወይዘሮዋ ባላቸውን ሊከተሉ ነው፡፡ ከእኔ ምንም ግፊት ሳይኖር ደጃዝማች ጣልያኖቹ እኔን እንዳይነኩኝ ከጣልያኑ እገረ ገዥ ቃል ማግኘት ፈልገዋል፡፡ ደጃዝማች እኔ በጥይት ተረሽኜ የምገደል ወይም ደግሞ እሰር ቤት ውሰጥ የሚወረውሩኝ ወይም ሌላ እይነት ሰቃይ ያደርሱብኛል ብሰው ፈርተዋል፡፡ እኔ ዶክተር ነኝ እና ያደረግሁት ነገር የለም ሰለዚህ መጨነቅ አያሰፈልግም ብዬ ብከራከርም ሊሰሙኝ እልፈለጉም፡፡ ምናልባትም ትክከል ነበሩ፡፡

በግንቦት እሰራ ሰድሰት ሁሉም ነገር በጥሩ ሁኔታ ተሰተካክሏል የሚል መልከት ከደጃዝማች ከሰማን በኋላ ወደ ደብረ ታቦር መመሰስ ጀመርን፡፡ የጣልያኑ እገረ ገዥ ሰአያሌው የከብር ቃሉን ሠጥቷል፡፡ የእያሌው ሀኪም በምንም እይነት ምንም ነገር አይደርሰበትም እንዲያውም ድንበር ተሻግሮ እንዲሄድ እንደሚረዱ ነው የተነገረው፡፡

በግንቦት በደብረ ታቦር ከተማ በየቦታው በብዛት ቆመውና እየተንቀሳቀሱ ከሚታዩ የኢጣልያ ወታደሮች በሰተቀር ከተማው ከዚህ በፊት እንዳየነው ሌላ ሰውጥ እልነበረውም፡፡ አዲሰ ነገር ያየሁት ቢኖር መንገዶችና ገበያዎች በሚሰቁና በሚያውካኩ የተሰያየ ቀለም ያሰው የሀር ቀሚሰ በሰበሱ ደሰተኛ ወጣት ሴቶች ተሞልቷል፡፡ "ሥልጣኔ" የጣልያኖችን አግር ተከትሎ መጥቷል፡፡



በተጨማሪም ሰዎች ከዚህ በፊት ያልታየ እፍረት የለሽና ወራዳ ባህሪ ማሳየት ጀምረዋል፡፡

በሚቀጥሰው ቀን የሁሰቱ ጦር ከፍሎች ሀላፊ ወደ ነበረው ሜጀር ኡጎሊኒ ቢሮ ተጠራሁ፡፡ የመጀመሪያ ግንኙነታችን የተፋጠጠ አይነትና ከሜጀሩም በኩል ወዳጅነት የጎደለው ነበር፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ በተለይም በማሰተርጎም ከረዳሁት በኋላ በመካከላችን የነበረው ሁኔታ ተሻሻለ፡፡ የሱ አሰተርጓሚ የሚረባ እልነበረም፡፡ ወደ ቤት ደብዳቤ እንድልክ ረዳኝ በተጨማሪም ሰነበሩት ባለሥልጣኖች ወደ አዲስ እበባ እንድጓዋዝ ሰለሚያሰፈልገኝ ፈቃድ ቴሌግራም እንድልክ ረዳኝ፡፡ ሲጋራዎችም ሰጠኝ፡፡ የሲጋራው ነገር የወዳጅነት ይሁን እጠራጠራለሁ፡፡ ሰሶሰት ወራት ማጨሰ አቁሜ ሰለነበር በጣም ጥሩ ሰሜት ነበረኝ፡፡ ለማንኛውም በደብረታቦር የመጀመሪያው ሲጋራ ጥሩ ጣዕም ነበረው፡፡

የጉዞ ፈቃድ አስኪሰጠኝ በደብረታቦር ያሳለፍኩት ሶሰት ሳምንት የሚሆን እሰልቺ ጊዜ የሜጀር ኡጎሊኒ ጥፋት እልነበረም፡፡ ወዳጅና የሚከበር የሰሜናዊ ኢጣልያ ተወላጅ የሆነው ሰውዬ በሚቻሰው አቅም እኔን ሰመርዳት ሞከሯል፡፡ በሰሩ ካሉ መኮንኖች ጋራም ወዳጅነት መሰርቼ ነበር ሁልጊዜ ከኔ ከሚርቀው ከወጣቱ ዶከተር በሰተቀር፡፡

ሚሲዮናውያን ጓደኞቼ ከተማው እንደተያዘ በዚያኑ ቀን ሰቀው ሄደዋል፡፡ ሁሉንም ነገር ጥሰው እንዲሄዱ ተገደው በፍጥነት ወደ ጎንደር ተወሰደዋል፡፡ ለዚህ ፈጣንና አሰገዳጅ ለቆ መሄድ በዚያን ጊዜ የተሠጣቸው ምክንያት እያሌው ከተማውን ሰለሚያጠቁ ሰደህንነታቸው ሲባል ጎንደር መሄድ ነበረባቸው ነው፡፡ ነገር ግን እያሌው እጃቸውን ከሰጡ በኋላ ሚሲዮናውያኑ አልተመለሱም የሚሲዮኑ ማእከሉም ሰወታደራዊ ሥራ ተወሰዷል፡፡

# ምዕራፍ ሀያ ሶስት

## መበታተን

ደብረ ታቦር እያለሁ በመሃልና በምሥራቁ የሰሜን ግንባር ክፍል የነበሩ እስተማማኝ ሰዎች አገኝሁ ያም ማለት ራሰ ካሳና ራስ ሙሉጌታ በነበሩባቸው ግንባሮች ነው። ከሰማሁት ሁሉም ነገር የተረዳሁት የሆነውና የተደረገው ነገር በሙሉ እኛ ላይም እንደሆነው ነበር ለውጥ ቢኖር አሰላለፍና ትብብር እንደኔ ሰዎች ደረጃ አልነበረም።

በመጀመሪያ በህዳር ማለት ነው በአቢሲኒያውያን ዘንድ ትኩስ ሰሜትና ፍላጎት ስለነበር በመጀመሪያዎቹ ውጊያዎች አስደናቂ ድሎችን ተጎናፅፈው ነበር። ወደ ሀያ መድፎች ብዛት ያለው የአውቶማቲክ መሳሪያዎች ቁጥር፤ ጠመንጃዎችና ጥይቶች በኢትያጵያውያን እጅ ወድቋል። በራስ ካለ በኩል አድዋን መልሶ መውሰድና በራስ ሙሉጌታ በኩል ደግሞ መቀሌን ማስመለስ የጊዜ ጉዳይ ብቻ መስሎ ነበር። በጦሩም በኩል ጣልያኖች የያዟቸውን ቦታዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ለቀው እንደሚሄዱ ጥርጣሬ አልነበረም።

ነገር ግን የጦር ሚኒስትሩ ራሰ ሙሉጌታ ለሥራው ብቁ አልነበሩም ታማሚና ሽማግሌም ነበሩ። የመምራት ችሎታም አልነበራቸውም ስለ ዘመናዊ ጦርነትና ውጊያ አውቀቱም አልነበራቸውም። እንደላቸው ከሆን ሥራውን ለሌላ ሰው ሠጥተው ወደ ገዳም ቢሄዱ ይቀላቸው ነበር። ግን ሥራው በግድ ነው የተሠጣቸው። ለምን የሀገሩ ሰዎች ይህን አንዴት ሲረዱ አልቻሉም በተለይም ለሥራው ብቁ የሆኑ ሌሎች አዛዦች እያሉ?

ከአዲስ አበባ የሚመጣው ጥቃት እንዳትፈፅሙ ዝምብላችሁ ጠብቁ የሚለው ትዛዝ ተሰማምቷቸዋል። ለሽማግሌው የሚመች አልጋ ላይ ተኝቶ ማደሩ ጥሩ ነገር ነበር። የነበሩት ደህንነቱ የተጠበቀ በእምባ እራዶም በሚገኝ ዋሻ ነበር። ዋሻው እንደ መኖሪያ ቤት ተደራጅቶ ስለነበር የጎደላቸውም ነገር አልነበረም። ይህ አይነቱ ሰላም ለረዥም ጊዜ በቆየ ቁጥር ለራስ ሙሉጌታ ጥሩ ነበር ያ ግን ከብዙ ወራቶች በኋላ ጣልያኖቹ እረፍትና ምቾቱ በቃ እስኪሉ ድረስ ነበር።



ከዚያ ግን ተረለቶና ተንቆ የነበረ አንድ ነገር መታወቅ ጀመረ። የወታደሮቹን ስሜት ለመጠበቅ የተደረገ ምንም ነገር አልነበረም። የጠላትን ፕሮፖጋንዳ በተጋነነ ሁኔታ መቀበል ጀምረዋል። ለጦሩ የሚበቃ ቀለብም አልተዘጋጀም። የጦሩ የጤንነት ሁኔታ ጦርነት ለመዋጋትና ለማሸነፍ ወሳኝ ነገር መሆኑም ተረስቷል።

በተጨማሪ ደግም ውነተኛ ባልሆነ ተስፋና መረጋጋት ስሜት ራሳቸውን ሞልተዋል። "ጣልያኖች እንደዚህ ያለ ጠንካራ የአቢሲኒያ ጦር ማጥቃት አይችሉም። ጀኔቫ የሚካሄደው ውይይት ደግሞ ውጤታማ የሆነ ኢጣልያን የማግለል ውሳኔ ይሰጣል ስለዚህ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ አውሮፕላኖቹ ጭጭ ይላሉ ጠላትም ለሰላም ይደራደራል" የሚሉ ተስፋዎች ነበሩ።

የዚህ ሁሉ ምክንያት ውጤት የማይቀር መከራና ውድቀት አስከተለ

እንግዲህ አንድ ለው ሽማግሌው ሙሉጌታ ላይ ፍርድ ከሚሰጥ ዝም ብሎ ቢያማርር ይሻለዋል። በርግጥም በራሳቸው ሰዎች በችኩሎቹ ኦሮሞዎች እጅ ወድቀው ሰቃይ ከሚደርስባቸው የደረሳቸው ዕጣ የተሻለ ነበር።

የራስ ካሳ ጉዳይ እንደ አቢሲኒያውያን ፍርድ እሰጣጥ በጦር አዛዥነት ከመጣ ዜሮ ነበሩ። ወታደር ከመሆን ይልቅ ቄስ ሆነው ቢያገለግሉ ይሻላቸዋል ይሉ ነበር። በአጠገባቸው ግንባር እንደነበሩት እንደ ራስ ሙሉጌታ የራስ እነሳሽነት የላቸውም ነበር። በጠቅላላው ጦርነት ጊዜ ምንም አይነት ውሳኔ በግላቸው ወሰነው አያውቁም ይባላል። በሳቸው ፋንታ ወይም ንጉሡ አለዚያም ራስ ስዩም ነበር ውሳኔ የሚሰጡት። ከንጋቱ ጀምሮ አስከ እኩለ ቀን ድረስ ራስ ካሳ ቁጭ ብለው ዳዊት ነበር የሚደግሙት። በጣም አሰፈላጊና ወሳኝ ጉዳዮች ቢኖሩ እንኳን ዳዊት በሚደግሙበት ጊዜ መረበሽ የለባቸውም። በቅዱሳን በአላት ቀኖች ምንም አይነት ጠቃሚ ሥራ አይሰራም ነበር። በየወሩ ደግሞ እነዚህ በአላት በተከታታይ ነበር የሚመጡት በአምስተኛው ቀን፡ በሰባተኛው፤ በአሥራ ሁለተኛው፤ በአሥራ ዘጠኝ፤ በሀያ አንድ፤ በሀያ አራት፤ በሀያ ሰባት እና በሀያ ዘጠኝ ይውላሉ።

ለባ ሺ የሚሞላው የራስ ካሳ ሠራዊት ስነ ስርአት አልነበረውም። የአካባቢው ገበሬዎች ይዘረፉሉ ቤታቸው ፈርሶ ለማገዶም ይሆን ነበር። የማጥቃት ርምጃ እንዳይወሰዱ ቢታዘዙም ብዛት ያለው የጦር ክፍል መሪዎች በራሳቸው እነሳሽነት እጠገብ ወዳሉ ሰፈሮች ይሄዱ ነበር። ብዙ ጊዜም ከጠላት ጋራ ይጋጩ ነበር።

ሌላው የሚባለው ደግሞ ራስ ካሳ አንድ ወይም ሁለት ብር ከሚያወጡ ወታደር በረሃብ ቢሞት ማየት ይቀላቸው ነበር፡፡ የጦርነቱ ካዝና በመቶ ሺ የሚቆጠር ብር የያዘ ነው፡፡ ካዝናው በሰምንት ፀሀፊዎች ነበር የሚጠበቀው፡፡ ፀሀፊዎቹ ለየግላቸው ሆነው ነው የሚሠሩት ያ ማለት ቀላል ወይም ትልቅ ግምት የማይሠጠው ወጭ እንኳን በሰምንት የተለያዩ መዝገቦች ላይ መሰፈር ነበረበት፡፡ አንድ ፀሀፊ ከጎደለ ደግሞ ምንም አይነት ከፍያ አይደረግም ነበር፡፡

ረሃብ በሽታ በተለይም ፈንጣጣና ተቅማጥ የራስ ካሳን ሠራዊት ከማንም ሠራዊት በላይ ከራስ ደስታ ሠራዊት በስተቀር በጣም ነበር የወረረው፡፡ እንደዚህ ሆኖ በሺ የሚቆጠር ብር በራስ ወዳዱ ሰውዬ እልጋ ስር ተቀምጦ ነበር፡፡ ብሩ ብዙ የተራቡ ሰዎችን በመመገብ ለታመሙ ሰዎችም እርዳታ መስጠት በቻለ ነበር፡፡ ውድም ቢሆን የሚሸጥ ምግብ ነበረ፡፡

በርግጥ የራስ ካሳ ሠራዊት ውደቀት እንደ ራስ ስዮም ያስ ብልህ አማካሪ ባይኖር ኖሮ ቀደም ብሎ ነበር የሚመጣው፡፡ ራስ ስዩም ራሳቸው ዋና አዛዥ እለመሆናቸው የሚያሳዝን ነገር ነው፡፡ ስዮም ልምድ ያላቸው ፈጣን ከማሰብ ችሎታ ጋራ ቆራጥ የሚከበሩና ተወዳጅ የጦር መሪ ነበሩ፡፡ ስዩም መሪ ቢሆኑ ኖሮ ከግድ የለሹ ቄስ ቢጤ ራስ ካሳ የተሻለ ውጤት ያመጡ እንደነበር ግልፅ ነበር፡፡ ራስ ካሳ በነበራቸው የመንገብገብ ባህሪ ወላዋይ የሚርበተበቱና እና ግድየለሽ በመሆናቸው ይጠሉ ነበር፡፡

ያልተጠበቀ የጠላት ማጥቃት በሀይለኛ ግፊትና በተቀናጀ ከበባ በምሥራቅ በኩል ሲመጣ የራስ ካሳ ሠራዊት በጀግንነት ነበር የተዋጋው ግን ሙሉ ስሜት አልነበረውም፡፡ መከበባቸው መቃረቡን ሲያውቁ ደግሞ የማይቀረው መበታተን ተጀመረ፡፡ ከዚያም እንደ ራስ እምሩና እንደ ደጃች እያሌው ሠራዊት በተከዜ በኩል ሽሽት ተጀመረ መጠኑ ግን ተሰምቶ የማይታወቅ አይነት ነበር፡፡ ረሀብ በሽታና ድካም ከውሰጥ በኩል፤ የሠለጠነው ሠቆቃ ከአየር ላይ፤ የተናደዱ ገበሬዎች በጎን በጎን፤ አሰቸጋሪው ምድር ከእግር ስር እንዲህ አይነቱ የመከራ ብዛት በአንድ ቦታ በአንድ ላይ ሲከሰት የሚያስከትለውን ውጤት ማን ነው መገመት የሚችለው?

ጥቂት ወታደሮች አስከትለው ራስ ካሳ በሌሊት ጋልበው ማምለጥ ችለዋል፡፡ ነገር ግን ሲንገበገቡለት የነበረው ሰንት የተራቡና የተቸገሩ ወታደሮች መርዳት የሚችለው ያ ሁሉ ገንዘብ በየመንገዱ ተበትኖ የገበሬዎች ሲሳይ ሆኗል፡፡



በንጉሡ የመጨረሻው ውጊያ ጊዜ በሚታየው ድራማ ተሰፋ የቆረጡት ሁኔታውን በትክክል ይሁን በስህተት አሳዛኝ ነው ያሉት ራስ ስዩም በጦርነቱ ከመሳተፍ እምቢ ብለው እንደነበር ይነገራል፡፡ ውጊያውን ከፍታ ያለው ቦታ ላይ ሆነው መመልከት ብቻ በቅቷቸዋል፡፡

ጦሩ ወደኋላ እንዲመለስ ሲደረግ የገበሬዎች ማጥቃትና ሽብር ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ፡፡ ፊታውራሪ እዮ የተባሉ ሰው ንጉሡ በነበሩበት ውጊያ ከተካፈሉ በኋላ ከደብረ ታቦር የሁለት ቀን መንገድ ወደሚሆነው ወደ ትውልድ ቦታቸው ወደ ሰማዳ ሽሽት ጀመሩ፡፡ ሰውዬውና ሶስት መቶ የሚሆኑት ወታደሮቻቸው እየተዋጉ ነበር ማለፍ የቻሉት ግን የሰማዳ ደንበር ላይ ሲደርሱ ወደ አንድ ሺ የሚሆኑ ገበሬዎች ፊታውራሪውንና ወታደሮቹን ለመዝረፍ ይጠብቁ ነበር፡፡ ከቤተከርሰቲያን ጀርባ መሽገው ከተቀመጡ በኋላ ፊታውራሪ ለገበሬዎቹ መልከት ላኩ፤ ማንነታቸውን ገልፀው ወደ ትውልድ ቦታቸው ያለምንም ችግር እንዲያልፉ ጠየቁ፡፡ የተሠጠው መልስ ግን ፊታውራሪውና ወታደሮቹ ከለበሱት ሱሪና ሸማ በሰተቀር ጠመንጃና ጥይት ሆነ ሁሉንም ነገር እንዲያስረከቡ ነበር፡፡ እዮ ለማስረከብ ሳይስማሙ ሲቀሩ ገበሬዎቹ ማጥቃት ጀመሩ፡፡ ፊታውራሪው በያዟቸው ጠመንጃዎችና ከውጊያው በማረኩት ሁለት አውቶማቲክ መሳሪያዎች መልሰ መስጠት ጀመሩ፡፡ ከቤተ ከርሰቲያኑ ፊት ለፊት በሜዳው ላይ ሀይለኛ ውጊያ ከተካሄደ በኋላ ገበሬዎቹ መንገድ መልቀቅ ጀመሩ፡፡ ሰድሰት መቶ የሚሆኑ ሰዎቻቸው ከሞቱ በኋላ የሀገራቸውን ሰዎች ለመርዳት ፍቃደኛ ሆኑ፡፡

ጦሩ ከተበተነ በኋላ እንደዚህ አይነቱ አጋጣሚ እንግዳም አልነበረም፡፡ ስለ አቢሲኒያውያን የሰማሁትን የጀግንነት፤ የድፍረትና ሞት አይፈሬነት ብፅፍ በብዙ አስገራሚ ይዘቶች ብዙ መፅሀፍቶች ይሞላሉ፡፡ በጣም አስተማማኝ የሆኑ ጥቂት ምሳሌዎችን መጥቀስ አፈልጋለሁ፡፡

በራስ ሙሉጌታ ሠራዊት ሥር የነበሩ የከምባታ ተወላጅ ወታደሮች ቡድን በመቀሌ ባለው የጣልያኖች ካምፕ ጎን በሚገኝ ዋሻ ብዙ ቀለብና ሌላም ንብረት ጨምሮ እንደሚገኝ ይሰማሉ፡፡ ከአዛዦቻቸው ፈቃድ ሳይጠይቁ በሌሊት ሾልከው በመውጣት የማይል ርቀት ያለውን ሜዳ ያቋርጣሉ፡፡ ሜዳው በጣልያኖች ባውዛ መብራት በየጊዜው ይፈተሻል፡፡ ሆኖም መብራቱ ሲመጣ ወደ መሬት ተወርውረው ልጥፍ በማለት ሳይንቀሳቀሱ መብራቱን ማሳለፍ ለነዚህ ሰውነታቸው ቀላል ለሆኑ ሰዎች እንደጨዋታ ነበር፡፡

መጥፎው ነገር ሌሊቱ ባለበት አልቆየም:: የከምባታ ወታደሮች ከጦር ካምፑ ስር ሲደርሱ የንጋት ኮከብ መውጣት ጀመረች:: ሲያዳምጡ ምንም ድምፅ የለም:: ከፊት ለፊታቸው ግን ባለ ሾህ የሽቦ አጥር ነበር:: ምንም የያዙት መቁረጫ መሳሪያ ስላልነበራቸው አጥሩ ለነሱ የሚጣለ ሆኖ አልተገኘም:: ለትንሽ ሰከንዶች ግራ መጋባት ተፈጠረ ከዛም በሹክሹክታ ለአጭር ጊዜ ውይይት ከተደረገ በኋላ  ድምፅ የሌለው በመቶዎች የሚቆጠሩ እጆች መሬቱን መጫር ጀመሩ በአጋጣሚ መሬቱም ቀለል ያለ ነበር::

ብዙ ጊዜ ሳይወስድ ሁሉም ከሽቦው አጥር ስር በቆፈሩት መሬት በኩል እየተሳቡ አለፉ:: ጠመንጃቸውን ትከሻቸው ላይ አድርገው ጩቤዎቻቸውን በጥርሶቻቸው ነክሰው ይዘው እየተሳቡ ጋራውን መውጣት ቀጠሉ:: ጋራው ላይ ዋሻዎች በረድፍ ሜትሮች ከፍታ ባለው ጉብታ ላይ ይታያሉ:: አንዱ በአንዱ ላይ እየተረማመዱ የሰው መሰላል ላይ በመውጣት በያዟቸው ጩቤዎች ጠባቂዎችን ጭጭ አደረጉ::

ዋሻዎች ውስጥ ያለውን ለማየትና የሚመረጠውን ለመምረጥ እሳት አበሩ:: በመጨረሻም ከባድ ከረጢቶችን ይዘው ወጡ:: ዱቄት፤ ስኳር፤ ዘይት በጠርሙስ፤ ጥይቶች ካኪ ዩኒፎርም ሌሎችም ብዙ ነገሮች ይዘዋል:: በትከሻቸው ደግሞ ሶስት ወይ አራት ጠመንጃዎችን ተሸከመዋል:: ነገር ግን የቀን ብርሃን ወጥቷል የተዘረፈው ንብረት ቀርቶ ራስን ማዳን ከተፈለገ ወጥቶ በሜዳው በኩል መሄድ የማይታሰብ ነገር ነው:: ያሰው አማራጭ ሌሊቱ እስኪመጣ መጠበቅ ነው:: ከዋሻዎቹ ወደ ጦር ካምፑ የሚወስደውን ትንሽ መንገድ ለአንድ ቀን ዘግተው መያዝ ይችላሉ:: ውሀ ለማግኘት ግን ምንም እድል የለም ነገር ግን ስለዛ ምን አሰጨነቃቸው?

ውሎውን ብዙ የጠላት ጥቃቶችን መቋቋም ነበረባቸው ከአውሮፕላኖቹ የሚተኮሰው አውቶማቲክ መሳሪያ ጥይቶችን አረበረበባቸው እነሱ ግን በከረጢት ከተሞሉት ዱቄት ጀርባ ስለመሸጉ ግድም አልሠጣቸውም::

መምሸት ሲጀመር ጋራው በነጭ ዱቄት ተሞልቷል::

ከሰአት በኋላ  ሲሆን አጥቂዎቹ አቆሙ:: የታሰበው ሰዎቹን በረሃብና በውሃ ጥም የግድ እንዲወጡ ማድረግ ነው:: በመጨረሻም የከምባታ ተወላጆቹ የናፈቁት ሌሊት ሲመጣ የጣልያኖች ባውዛ መብራት ሰዎቹ በመጡበት መንገድ በኩል ያለማቋረጥ ይበራ ጀመር:: እንደዛም ሆኖ እጃቸውን አልሰጡም::



በፀጥታ መሬት ለመሬት እየተሳቡ በመጡበት ሳይሆን በጋራው በሌላ በኩል መብራት እልፎ እልፎ በሚበራበት ቦታ መሄድ ጀመሩ:: ትላንትና ማታ እንዳደረጉት ሁሉ በአጥሩ ስር ቆፍረው መሹለክ ጀመሩ:: የመጨረሻው ሰው በአጥሩ ስር ሾልኮ እንደጨረሰ ተነቃባቸው:: ወዲያውኑ ሜካው በእንቅስቃሴዎቸ ተሞላ:: ጠመንጃዎች አውቶማቲክ መሳሪያዎች ይተኩሱባቸው ጀመር መድፉም አልቀረም:: ነገር ግን ድምፅ እንጂ ትንሽ ጉዳት ነው የሚያደርሰው:: ሰዎችም ነብሴን አውጭኝ ብለው በሜዳው ተበታትነው መሮጥ ቀጠሉ::

ወዲያውኑ ከጠምንጃ ተኩስ ርቀት ውጭ ሆኑ እራሳቸውንና የዘረፉትን ማዳን ቻሉ:: ለነሱ የተዘረፈው ነገር የህይወት ያህል ጠቃሚ ነበር:: አስር ሰዎች ወደኋላ  ቀርተዋል:: ስንት ሰው ይቁሰል ስንት ሰው ይሙት ማንም የሚያውቅ ሰው የለም::

ጦርነቱ እንደተጀመረ የደጃዝማቾ አያሌው ወንድም ደጃዝማች አድማሱ የጣልያኖች ጓደኛ ናቸው አገራቸውንም ለመክዳት ከጣልያኖች ጋራ አቅድ አላቸው ተብለው ተከሰው በንጉሡ ትዕዛዝ ለብዙ ሳምንታት እንዲታሰሩ ተደርገው ነበር ሆኖም ምንም ማስረጃ ስላልተገኘ በነፃ ተለቀቁ:: ይህንን የሐሰት ክስ መሆኑን ለማስመስከር አድማሱ ለአባት አገራቸውና ለንጉሡ ታማኝነታቸውን የሚያሳዩበት አጋጣሚ እየጠበቁ ነበር:: ነገር ግን ከመጀመሪያውም ለክሱ ምክንያት የሆኑት ራስ ካሳ የአድማሱን የየጁ ግዛት ይመኙ ስለነበር አድማሱ ስማቸውን ለማደስ የሚፈልጉበትን አጋጣሚ ሁሉ ይከለክሏቸው ነበር::

እንዲህም ሆነ:: አንድ ትንሽ የሆነ የጣልያኖች ካምፕ ሁልጊዜ አቢሲኒያዊያን ላይ በርቀት እየተኮሰ ያስቸግር ነበር:: ይህን የመድፍ ተኩስ በብዛት የሚቀበለውም የአድማሱ ሠራዊት ነበር ስለዚህ አድማሱ የጣልያኑን ምሽግ ጥሰው ለመግባት ራስ ካሳን ደጋግመው ፈቃድ ጠይቀው ነበር:: ራስ ካሳ ግን የሰው ሕይወት ቢጠፋ የሚሰጠው ጥቅም የለም በማለት ከለከሏቸው::

ደጃዝማች አድማሱ ራሳቸው ወሰኑና አንደ ቀን በንጋቱ ላይ አንድ ሺ የሚሆነውን ሠራዊታቸውን እንዲያጠቃ ትዛዝ ሠጡ:: እራሳቸውም ቢሆን በጣልያን የተሰራ አውቶማቲክ መሳሪያ ሲተኩሱ ዋሉ:: እኩለ ቀን ሲሆን ተራ በተራ ያደረጉት የማጥቃት ሙከራ አልሰራም ራሳቸው እድማሱ በመሳሪያው ግለት ምክንያት እጃቸው ውሃ መቋጠር ሲጀምር አጥቂዎቹ ጥቃቱን የማቆም አዝማሚያ ላይ ነበሩ::

ራስ ካሳ ውጊያው ትርፍ የሰውም ብሰው ነው ያሰቡት ያውም አጠገባቸው ያሉ ሰዎቻቸው ተጨማሪ ሀይል ሰርዳታ እንዲላከ ቢወተውቷቸውም:: ሰዎቹ በሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖቻቸውን ለመርዳት ዝግጁ ነበሩ:: "አይሆንም!" ራስ የፈለጉት ጠቅላላው አጥቂ ጦር ከአዛገፉ ጋር እንዲደመሰሱ ነው:: አድማሱ የራስ ካሳን ትዛዝ መጣስ ማሰት ምን ማሰት እንደሆነ ማወቅ አለበት::

ያም ሆኖ ደጃዝማች አድማሱ ማቆም አልፈለጉም:: ተስፋ በሌሰው ሁኔታ ይመጣል ተብሎ ሲጠበቅ የነበረው ተጨማሪ ሀይል አሰመምጣቱን ሲያዩ የየጁ ጎበዞች ሰዎቻቸውን ለመጨረሻ ጊዜ ለማጥቃት እንዲሞከሩ ያበረታቱ ጀመር::

ተሳካላቸው:: ልክ ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት ከመሆኑ በፊት የመጀመሪያው የአቢሲኒያ ሠራዊት የካምፑን አጥር ጥሶ ገባ:: የጨበጣ ውጊያ ነበር:: አንድ የበታች መኮንን ሀያ የሚሆኑ ወታደሮችን ይዞ እየተኮሰ ያስቸገረውን አንድ መድፍ ለመውሰድ ወሰኗል:: መድፉ በጥሩ የተጠበቀ ቦታ ነበር:: መኮንኑ ሰዎችን ሰበሰበና ከሁሰት ቦታ ከፍሎ በጎን በጎን ካሰሰፈ በኋላ ራሱን በመሀከል አደረገ::

"አሁን እኔ ፊት ለፊት ወደ መድፉ አፈሙዝ ስሮጥ እናንተ በጎን እንድታጠቁ:: አትፍሩ! የሚተኮሰውን እርሳስ(ጥይት) እኔ አቀበሰዋለሁ!!"

ያን ትዛዝ ከሰጠ በኋላ ቀጥታ ወደ መድፉ አፈሙዝ ፊት ሰፊት ሮጠ መድፉም ሰተኩስ ተዘጋጅቶ ስለነበር ተተኮሰ ሌሎቹ ወታደሮች እየጮሁ ወደፊት በመሮጥ መድፉን ሲተኩሱ የነበሩትን ስድስት የጣልያን ወታደሮች ጭጭ አደረጓቸው ነገር ግን አቢሲኒያዊው መኮንን አዛዣቸው ሳይመሰስ ለዘላለም ሄደ::



# ምዕራፍ ሀያ አራት

## በመጨረሻም ሥልጣኔ
## ድንገተኛ አውሮፕላን ማረፊያ ያለመኖር

ግንቦት አሥራ ሁሰት የተከበሩ ፒሪዞ ቢሮሊን ተቀበልን:: ቢሮሊ የምድር ጦር ጀኔራል ነው የባዶሊዮ ቀኝ እጅ ሲሆን በቅርቡ ደግሞ የአማራ ገዢ ተብሎ ተሰይሞ መኖሪያውን በጎንደር አድርጓል:: የደብረ ታቦሩ ጉዞው ጦሩን ሰመጎብኘት ነው::




ጀኔራል ፒሪዞ ቢሮሊ
የኤሪትራ ጦር አዛዥ

በጀኔራሉ አዝ ስር ከነበሩት
የኤሪትራ ተወላጆች ጦር
ግማሹ ጦር በመጀመሪያዎቹ
ቀናት በመከዳት ወደ
ኢትጵያውያን ወገኖቻቸው
ተደባልቀዋል ተብሎ ተዘግቧል

በሚቀጥለው ቀን ሰውየው ተቀብሎኝ የሚያስፈልጉኝን ነገሮች መናገር እንድችል ተፈቀደልኝ:: ጀኔራሉ ያለሁበትን ሁኔታ በመገንዘብ ዕርዳታ እንደሚያደርግልኝ ቃል ገባልኝ:: በሚቀጥሰው ቀን ወደ ጎንደር አብሬው በመሄድ ከዚያ በኋላ በወታደራዊ አውሮፕላን ወደ አዲስ አበባ እንደምሄድ ነው የታሰበው::

ለአንድ ሰአት የሚሆንም ሰሰ ጦርነቱ ቁጭ ብሰን ተወያየን:: ጀኔራሉ ማወቅ የፈሰገው በአቢሲኒያውያ በኩል ሁኔታው ምን እንደነበር ነው:: በተጨማሪም አዲስ አበባ ከተማ የደረሰውን ውድመት ነገረኝ:: ፒሪዞ ቢሮሊ አዲስ አበባ ከገቡት የመጀመሪያው ነው በተሠረቀ በንጉሡ መኪና ሆኖ ነው

የገባው:: ከአየር ላይ የተነሳ ፎቶግራፍም አሳየኝና ስመለከት ቤቴ አንዳልፈረሰ ማየት ቻልኩኝ::

እንግዲህ ነፃ የምሆንበት ሰአት እየመጣ ነው:: አጭር ቀን ብቻ:: ከተኩስ ልውውጥ ከልል ውጭ አሆናለሁ እና ህይወቴን መጠበቅ እችላለሁ:: ጄኔራሉን ትቼ ስወጣ በጣም ደስተኛ ነበርኩ:: ሁሉም ነገር በትክክል ከሄደ በአሥራ ስድስት በሰቀቅኩ ከሰባት ወራት በኋላ ተመልሼ አዲስ አበባ እንደምገባ ተስፋ አድርጌያለሁ::

በሰኔ አሥራ አምስት ገና ፀሐይ ሳትወጣ ተዘጋጅቼእስሁ:: ሻንጣዬ የያዘው ነገር ቢኖር ሶስት የፂም መላጫ ከሶስት ምላጮች ጋራ፣ ሳሙና፣ የአጅ ፎጣና የተጠቀሰለ ብርድ ልብስ ነበር::

ስንብቴ ከደጃዝማች አያሌውና ከሁሉም ወዳጆቼና የጦርነት ጓደኞቼ ጋራ ከጠበቅሁት በላይ ከባድ ነበር:: እይናቼ እያነቡ ቃላቶቼም ጉሮሮዬ ውስጥ እየተሰነቀሩ ነበር:: አብረን ደስታውን ቁጥር ስፍር የሌለውን መከራና ችግር ያሳለፍን ሰዎች አንደገና እንገናኝ ይሆን? በዚህ በከፉ ቀን መልሶ መገናኘቱ የማይታመን ነገር ነው::

ደጃች አያሌው መሄዴን ሲገነዘቡ ተመልሼ መጥቼ የላቸው ሀኪም እንደሆን ቃል አስገቡኝ:: እሱም እኔ የምመለስበትን ሁኔታ ደጃዝማቸ ካዘጋጁ ነው:: ልክ ስንለያይ ብዙ መቶ የማር ተሪዛዎች ለመንገድ አንዲሆን ብለው ሰጡኝ:: እንደማፈር ብለው ገንዘቡን ሲሰጡኝ ሀዘኔታ ተሰማኝ:: ቢችሉ ከዚህ እጥፍ ሊሰጡኝ እንደሚችሉ አውቃለሁ::

የደጃዝማች ሚስት ወይዘሮ ማናህሎሽ የጣታቸውን የወርቅ ቀለበት አውልቀው ለማስታወሻ እንዲሆን ብለው ሠጡኝ::

እቶ ማሞና ባለቤቱ እንደ ሕፃን ልጅ ያነቡ ነበር:: ትንሿ አፀደ ከእግሬ ላይ ተጠምጥማ

"አባባ ጥሎን አይሄድም!!" እያለጭ ትጮሀለች::

ከዚያ ቀጥሎ ሃምሳ የሚሆኑት የደጃዝማች የቀሩት የግል ዘቦች በአከብሮትና በፀጥታ እየመጡ ጉልበቴን ወይ እግሬን ይስማሉ:: በዚህ ሁሉ መሀል የከዳኋቸው መስሎ ተሰማኝ ነገር ግን መሄድ ነበረብኝ ግዴታዬ ነበር::

ጄኔራሉና ተከታዮቹ ስንብቱን ትቼ ከመልቀቄ በፊት ተነስተው ሄደዋል:: የጭነት መኪና ከአስር ወታደሮች ጋራ ሆኖ ይጠብቀኝ ነበር:: ሾፌሩ ባለበት ጋቢና በኩል ዘልዬ ገባሁ ማርሽ ተቀየረ መኪናው ማጓራት ጀመረ ከዚያም ጓደኞቼና ከተማው ከጋራው ጀርባ ተሰወሩ::



ጉዞው ከመጀመሪያው አስቸጋሪ ነበር:: ለብዙ ቀን ሲዘንብ ሰንብቷል:: እየደጋገምን በጭቃ እየተያዝን ሁላችንም እየወረደን አንረዳ ነበር:: ትልቁን የርብ ወንዝ በአፄ ፋሲል ድልድያ ላይ ከተሻገርን በኋላ  መንገዱ ደረቅና ለስላሳ ሆነ:: ጉዟችንም ይፋግን እልፎ በአሰልቺው የደምቢያ ሜዳ በኩል ቀጠለ:: ለምሳ በጣና ሀይቅ ዳርቻ አጭር አረፍት ካደረግን በኋላ  አንደገና ጉዟችን ቀጠልን::

አሁን ደግሞ የመንገዱ ችግር አንደገና መጣ:: ዳገታማ ነው:: ዝናብ መጣል ጀመረ:: መኪናው ይንሸራተታል ወይም ጭቃ ውስጥ ይቀረቀራል:: ጎማ በየተራ እየተነፈሰ ጉዟችን አራዘመው:: ከሌሊቱ ሰባት ሰአት ሲሆን በጎንደር የወታደር ካምፕ ግቢ ውስጥ ገባን:: አብረውኝ የተጓዙት ሰዎች መኖርያ ቦታቸው ስለሆነ  አያንዳንዳቸው ድንኳን አግኝተዋል:: ሌሊት ስለሆነ ሁሉም ሰለተኛ ለኔ ማደሪያ ሆቴል አልተገኘም ሰለዚህ ብቻዬን የቀረውን ሌሊት ከጭነት መኪናው ጀርባ አሳለፍኩ:: ጭቃ በጭቃ ሆኛለሁ በድካም ሙትት ብያለሁ ለማንኛውም ጎንደር ገብቻለሁ:: ቀስ በቀስ ወደ ግቤ እየተጠጋሁ ሰለሆነ ደስተኛም በመሆኔ እንቅልፍ እንዲወስደኝም አደረግሁና እንደወደቀ ግንድ ተኛሁ::

ቀረብ ያለው የአውሮፕላን ማረፊያ ከጣና ሀይቅ አጠገብ የሚገኝ ጎርጎራ የሚባል ቦታ ነው:: በአሥራ ስድሰት ማምሻውን ወደ ጎርጎራ ልንሄድ ነው:: በተመደበልኝ አስጎብኝ እርዳታ ቀኑን የፈረሱትን በመሀከለኛው ከፍለ ዘመን የተሠሩ የጎንደር ቤተመንግስት ግንቦች ስጎበኝ ዋልኩኝ አለዚያ ከተማው አንኳን ምንም የሚታይ ነገር የለውም ነበር::

በጊዜ ብዛት የግንቡ ቅስቶች ጡቦችና ሲሚንቶው ተጎድቷል:: የፈራረሱት ግንቦች ብዙ ጊዜ ሳይቆዩ አንዳለ እንደሚናዱ ነው:: እንደተረዳሁት ከሆነ ደግሞ ጣልያኖቹ ግንቦቹን ሰማደስ ምንም ፍላጎት የላቸውም::

በመሀከለኛው ከፍለ ዘመን የአቢሲኒያ መናገሻ ከተማ ስለነበረው ጎንደር ያን ሁሉ ከሰማሁ በኋላ  ከተማውን ላየው እንደጠበቅሁት ሰላላገኘሁት በጣም ነው ያዘንኩት:: ጠቅላላው ጎንደር ያልፀዳና ያረጀ ሆኖ ነው የታየኝ:: ጣልያኖቹም ከተማውን ከጎንደር አርባ ኪሎሜትር ርቀት ወደሚገኘው ወደ ጎርጎራ ለመውሰድ ያቀዱ ይመስላል::



የጎንደር ግዛቱ ከጦርነቱ ከጥቂት አመታት በፊት የተነሣ ፎቶግራፍ (Agenore Frangipani, l'equivoco Abissino)



ለምሳ የተጋበዝኩበት የጄኔራሉ ፅሕፈት ቤት በሚገርም ማረፊያና መናፈሻ ቦታ አድሜ ባላቸው የወይራና የፅድ ዛፎች ባሉበት ነው ያረፈው፡፡ በመሀሉም የፈራረሰው የመዝናኛው ግንብ አለበት፡፡ ባለሁለት ፎቅ የሆነው የመዝናኛው ግንብ በየወለሉ አዳራሽ ያለው ሲሆን በድሮ ጊዜ ለመዋኛ የሚያገለግል የውሃ ፊስስ ላይ ነበር የተሰራው፡፡ አሁን ድረስ የሚያገለግል መሻገሪያ ድልድይ ወደ ግንቡ ያስገባል፡፡ በመሀከለኛው የአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን በዳግማዊ አፄ አያሱ ዘመነ መንግስት ወግ የሌለው የግብረ ሥጋ ግንኙነት በዚህ ግንብ ውስጥ ይካሄድ ነበር ይባላል፡፡

ከንጋቱ አሥራ አንድ ሰአት ሲሆን ዱቄትና ሌላም ቀለብ የተጫኑ ሁለት የጭነት መኪናዎች ይዘን ወደ ጎርጎራ መንገድ ጀመርን፡፡ ከብዙ ድካም በኋላ በዝናብና በሚያንሸራትት መንገድ ጎማዎች እየተነፈሱብን ከጠዋቱ ሶስት ሰአት ጎርጎራ ደረስን፡፡ እዛ እንደደረስኩ በአንድ ሻለቃና አስር ወታደሮቹ ወዳጅነት የሌለበት አቀባበል ነበር የገጠመኝ፡፡ ሆኖም በጦርነቱ ጊዜ አቢሲኒያኖቹ እንዴት እንደተዋጉ ለማወቅ ታላቅ ጉጉት ስለነበራቸው ንግግር ተጀመረና በመሀከላችን የነበረው ቀዝቀዛ ግንኙነት ቆመ፡፡

በየጊዜው ግን እየደጋገሙ ለውዲኖች ጥሩ ሰዎች አይደሉም እያሉ ያስታውሱኝ ነበር፡፡ እንደ ጣልያኖቹ ከሆነ እያንዳንዱን የሚያገኙትን የስዊድን ዜጋ መስቀል ነበረባቸው፡፡ ያም ሆኖ ጥሩ ምግብና ጥሩ መኝታ ከማግኘት አልተከለከልኩም፡፡ በኋላ እንደተረዳሁት ስዊዲኖችን መስቀል በሌላ መንገድም ሊደረግ ይቻላል ልክ እንደ[1] ግሬታ ጋርቦን የመሰለ ሰው ፎቶግራፍ ከምሽግ ግድግዳ ጀርባ እንደመሰቀል ማለት ነው፡፡

ጎርጎራ አውሮፕላን እንደሌለ ተነገረኝ፡፡ በዝናቡም ምክንያት ወደ አዲስ አበባ የሚሄድ አውሮፕላን የለም፡፡ ግን በነጋታው ከጎጃም የሚመጣ ካፕሮኒ የሚባል አውሮፕላን ይጠብቁ ነበር፡፡ አውሮፕላኑ ከጥቂት ቆይታዎች በኋላ ወደ አስመራ ይሄዳል፡፡ ሜጀሩ ወደ አስመራ እንዲሄድ ለለተፈቀደለት አውሮፕላኑ ለሱ ሲባል ነው ጎርጎራ የሚያርፈው ለኔም እንግዲህ ቦታ አይጠፋም፡፡ አጋጣሚ ሆኖ እኔም የጉዞ ፈቃድ አለኝ፡፡ ሆኖም ማለፊያ ወረቀት አልነበረኝም፡፡ ጀኔራል ቢሮሊ ለኔ ወደ አስመራ ለመሄድ ከፍት ነው ከዛ በኋላ ወደ አዲስ አበባ መሄድ እንደምችልም ነግሮኝ ነበር፡፡

---

1 ግሬታ ጋርቦ በስዊድን ሀገር የተወለደች በዘመኑ ታዋቂ የሲኒማ ተዋናይ ነበረች

ሌሊቱን በሙሉ ሲዘንብ አደረ ጠዋት አስቀያሚና ቀዝቃዛ ነበር፡፡ ከጥዋቱ ሶስት ሰአት ሲሆን ባለአንድ ሞተር ቦምብ ጣይ አውሮፕላኑ ሲመጣ እኛ በዝናብ የራሰው ማረፊያ ላይ ወጥተን እየጠበቅን ነበረ፡፡

መንገደኞቹ የአየር ሀይል ጄኔራልና ሁለቱ ረዳቶቹ ፓይለቱና መካኒኩ ከአውሮፕላኑ ወረዱ፡፡ የነበረንን ሃሳብ ነገርናቸው፡፡ ጄኔራሉም ሁለት ሰዎች መውሰድ የሚችልበት ሁኔታ የለም ብሎ መለሰልን፡፡ አንድ ሰው እንኳን ተጨምሮ ተንደርድሮ ለመነሳት አስቸጋሪ ነው አለ፡፡ ሜጀሩ በደግነት ቦታውን ለቀቀለኝ፡፡ ምድሩ በጣም ረጥቦ ስለነበር አውሮፕላኑ የተነሳው በሁለተኛው ሙከራ ነበር፡፡

የጣና ሐይቅ እንደመስታውት ተዘርግቶ ይታያል ከዚያ ውጭ ግን የቀረውን መሬት ከባድ ደመና ሸፍኖታል፡፡ ምንም ማየትም አንችልም ነበር ነፋሱ ደግሞ አንደማዕበል ነው፡፡ አሰቀያሚ የአየር ጉዞ ነበር፡፡ ቀዝቃዛው አየር በቦምብ መጣያ ስድስት ከፍተቶች በኩል ሰለሚገባ በብርድ ተንሰፈሰፍን፡፡ ወደ ሰሜን ተራሮች አካባቢ ስንደርስ ከደመናው በላይ አምስት ሺ ሁለት መቶ ሜትር ከፍታ መውጣት ነበረብን፡፡ አሰቃቂ ነበር፡፡

ወደ ተከዜ ረባዳ መሬቶች ስንደርስ ደመናው ቀለል ማለት ስለጀመረ ወንዞችንና በጦርነቱ ጊዜ በደንብ የማውቃቸውን የትግራይ መሬቶች ማየት ቻልን፡፡ ነገር ግን እንደገና የኤርትራ ከፍታማ ቦታዎች አስከንደርስ ድረስ ደመና መልሶ ሸፈነ፡፡

በዚህ ጊዜ የአውሮፕላኑ ነዳጅ መጠን በፍጥነት እየቀነሰ እንደሆነ መጠቆሚያው ያሳያል፡፡ በደመናዎቹ አልፈን ከአስመራ ሰማንያ ኪሎ ሜትር ርቀት የሚገኘው አዲ ቋላ ከተማ ስንደርስ ሁለት መቶ ሊትር ብቻ ነው የቀረን፡፡ አውሮፕላኑን እያበረረ የነበረው ጄኔራሉ ያለው ነዳጅ ያሰብንበት ቦታ ያደርሰናል ብሎ ነው ያሰበው፡፡

እንዴት እና ለምን አቅጣጫው እንደጠፋብን አልገባኝም፡፡ ያውቅሁት ተመልሰን አድዋን አንደገና በሩቁ ስናይ ነው፡፡ የሚታመን ነገር አልነበረም፡፡ በቀጥታ ወደ መጣንበት እዞረን ተመልሰናል፡፡ ካፒቴን ፓይለቱ ደጋግሞ ስለ አቅጣጫው ተናግሮ ነበር ነገር ጄኔራሉ ሊሰማው አልፈለገም፡፡

አድዋ መታየት ሲጀምር በመቶ ሰማንያ ዲግሪ ተመልሰን ዞርን፡፡ መጠቆሚያው በዚህ ጊዜ አንድ መቶ ሊትር ነዳጅ ብቻ መቅረቱን ነው የሚያሳየው፡፡ ያ እንግዲህ አዲ ቋላ የሚገኘው አውሮፕላን ማረፊያ ሊያደርስን ይችላል፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን የሆነ ነገር ተበላሸ፡፡

*ፑፍ! ፑፍ! ፑፍ!* ከዚያ በኋላ ፍፁም ፀጥታ፡፡



የምንሰማው ነገር ቢኖር የአውሮፕላኑ ክንፍ አየሩን እየቀዘፈ ሲሄድ የሚሰማው ፉጨት ነው፡፡ ሞተሩ ቆሟል፡፡

ነዳጁ አልቋል፡፡ ሀምሳ ሊትር የሚሆን በነዳጅ መያዣው ውስጥ ቢኖርም፤ እኛም አንድ ሺ ሜትር ከፍታ በአየር ላይ ነበርን፡፡

"በፍጥነት እየዘለላችሁ ውጡ!" አለ ጄኔራሉ በጩኸት መሪውን ለካፒቴኑ እየለቀቀ፡፡ በደንቡ መሠረት ሁላችንም ፓራቹት አስረናል፡፡

ቁልቁል ተመለከትኩ በሕይወቴ ከአየር ላይ ዘልዬ ለመውረድ ደፍሬ አላውቅም፡፡ አስቡት እንግዲህ ፓራቹቱ ባይከፈትስ! በፍጥነት ወደ ምድር ወርጄ ብፈጠፈጥ ምን አይነት ሰውነት ነው የሚቀረኝ? አንድ ሰው መሞት ካለበት ምናልባትም ይህ የተሻለ አሟሟት ይሆናል፡፡

"ባላችሁበት ቆዩ፡፡ ይህን ነገር ልቆጣጠረው እችላለሁ" የሚያረጋጋ የፓይለቱ ድምፅ ነበር፡፡

አውሮፕላኑ እየተሽከረከረ ቁልቁል ወረደ፡፡ መሬቱ እየተቃረበ ይመጣል፤ ተከሎቹና ምድሩም እየተለቁ መታየት ጀመሩ፡፡ እኛ ባለንበት ቆመን መሬቱ በኛ ዙሪያ የሚሽከረከር ነበር የሚመስለው፡፡ ከጥቂት ሰከንዶች በኋላ ሜዳ መታየት ጀመረ፡፡

"ወለሉ ላይ ተኙና አጥብቃችሁ ያዙ አውሮፕላኑን ላሳርፍ ነው"

ሀይለኛ መንጠርና መርገብገብ ነበረ እኔም የሚሽከረከር አውሎ ነፋስ እዙሪት ውስጥ ያለሁ መስሎ ነው የተሰማኝ፡፡ እርስ በራሳችን እስከንላጋ ድረስ ደጋግሞ መንጠር ቀጥሎም ድንገተኛ መርገብገብ ካደረግን በኋላ ቆምን፡፡

ፓይለቱ ላማሳረፍ ሲዘጋጅ ፍጥነቱን ለመቀነስ ልጓሙን ተረግጦ ነበር ነገር ግን ከፊት ለፊቱ ትልቅ ዛፍ ሲያይ በድንጋጤ ልጓሙን እንደያዘ መሬቱ ላይ አረፍን፡፡ አውሮፕላኑ በቀኝ በኩል ዛፉን መቶ ሰብሮታል በዚህ ምክንያት በቀኝ በኩል የሚገኘው የማቆሚያ ልጓም ተሰብሮአል፡፡ በግራ በኩል ያለው ብቻ ስለሚሰራ አውሮፕላኑ ተሽከርክሮ ካፒቴኑ ወዳልፈለገበት ወደ መጣበት አቅጣጫ በኩል ዞሯል፡፡ ወደፊትም በቁጥቋጦና በትንንሽ ዛፎች ላይ በመሄድ ጉድባ ውስጥ ሲደርስ ብቻ ቆመ፡፡

ነገር ግን መጨረሻው ጥሩ የሆነ ነገር ጥሩ ነው ከመጥፎ አደጋም ተርፈናል፡፡ ከያዝነው ስንቅም ጥሩ ምግብ አዘጋጅን፡፡ በአውሮፕላኑ ጥላ ስር ተጠግተን ምግቡን በላን፡፡ ሁሉም የምመኘው ነገር ነበር ፡፡የጎደለኝም አልነበረም፡፡

ወደ አድዋ ከሚወስደው ዋናው ጎዳና ስድስት ኪሎ ሜትር ርቀት የአውሮፕላን ድንገተኛ ማረፊያ ከመረብ ወንዝ አጠገብ መሠራቱን አወቅን:: አልፎ አልፎም አልፈው ከመሄዱ መኪኖች ድምፅ እንሰማ ነበር:: ያካባቢው ተወላጆች መጡ:: የኢጣልያ የመንገድ ሠራተኞችም መጡ:: ከአውሮፕላኑ ሲዘል የተጎዳውን ካፒቴን ተሸከመው መንገዱን በማሳየት ረዱን::

በተጠራው አምቡላንስም ሆነን መጀመሪያ ወደ አዲ ቋላ ከዚያም ወደ ጎራ ቀጠልን:: ጎራ ትልቁ የጣልያኖች የአየር ጣቢያ ነው ከአስመራ በደቡብ አርባ ኪሎ ሜትር ርቀት ቦታ ላይ ነው የሚገኘው:: በዚህ ቦታ ወደ አዲስ አበባ የሚሄድ አውሮፕላን እየጠበቅሁ የአብራሪ መኮንኖች እንግዳ ሆኜ ሰሁለት ቀናት ቆየሁ:: የዝናቡ ወራት ስለጀመረ የአውሮፕላን በረራዎች ይሰረዙ ነበር:: መጥፎ አጋጣሚ ነበር:: ሰኔ የነበረኝ የቀረኝ አማራጭ በአስመራ በኩል ሄጄ ከምፅዋ ጀልባ ይዤ ወደ ጅቡቲ መሄድ ነው:: ነገር ግን እንዴት ብዬ ነው ለጉዞው ይለፍስ ሆነ ገንዘብ የማገኘው?

ምንም ቢሆን ለአንድ ነገር መውጫ አሰው:: አስመራ ውስጥ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ፈቃድ እስካገኝ ድረስ ለሶስት ሳምንታት መቆየት ነበረብኝ:: በመጨረሻ ይለፍ ወረቀት ማግኘቴ ከታላቅ ዕድል ነው የሚቆጠረው:: "Nulla Osta" "ይህን ይለፍ ለያዘው ሰው ምንም አከል እንዳያጋጥመው" የሚል ፅሁፍ ያለው ይለፍ አዲስ አበባ ከተያዘች ወዲህ ለሲቪል ሰው ሲሰጥ አምስተኛው ነው:: ሌላ ከፍ ያለ ችግር ሳይፈጠር የምፅዋን ሞቃታ አየር ከተቀበልኩ በሐምሌ አስራ ሰባት አዲስ አበባ እገባለሁ:: ቀናቱን ሳሰብ ዘጠኝ ወራቶች አልፈዋል::

በመጨረሻም አዲስ አበባ:: የደረስኩ እለት እየዞርኩ ያየሁት ውድመት የፈጠረብኝን የሀዘን ስሜት ምንም ጊዜ አልረሳውም:: ስለዚህ ጉዳይ ግን ብዙ ሰዎች ስለፃፉ በዚህ ውስጥ መጥቀስ አያስፈልገኝም:: በየመንገዱና በገበያ ቦታ ይርመሰመስ የነበረው ሰው ፤ ባለባቶች ከአጃቢዎቻቸው ጋራ በፍፁም አይታዩም:: የአውሮፓውያን ሠራተኞች ከሆኑት በስተቀር ሁሉም አቢሲኒያኖች የሸሹ ይመስላል::

ቤቴ ውስጥ የቀረ አንድ ነገር የለም:: ሁሉም ነገር ተዘርፏል::

በደቡብ በኩል ከአዲስ አበባ መቶ ሃምሳ ኪሎ ሜትር ርቀት ከሚገኘው እርሻ ቦታዬ ጋራ ግንኙነት ማድረግ አልተቻለም:: እስካሁን ራቅ ካለው ከእርሻ ቦታው ነው አለ ከሚባለው ከወንድሜ ከዋልደማር ጋራም መገናኘት አልተቻለም:: ጣልያኖቹ ሰዎች እንዲልኩም ሞከሬ ነበር:: በፈቃዳቸው ከሚጓዙ ጀርመኖች ጋራም አብሬ እንድሄደ ብለምንና ብማፀነም ትከሻቸውን



እየገፉ "አይሆንም" ነው የሚሉት:: ሌላ አይነት ሙከራ አደገኛ ነበር:: ያገሬው ሰዎች አውሮፓውያንን እንዳይነኩ የሚል ፅሁፍ ያለባቸው ሊፍሌቶች በአውሮፕላን ተበትነዋል ብለው ሊያፅናኑኝም ሞከሩ::

አዲስ አበባ በቆየሁበት ጊዜ ሁል ጊዜ ማታ ማለት ይቻላል ጣልያኖቹ በጣም በሚፈሩዋቸው ሽፍቶች ከተማው ጥቃት ይደርስበት ነበር:: በነዚህ የአባት አገር ተዋጊዎች እጅ የወደቁ ጣልያኖች አስከሬን ካየሁ በኋላ የጣልያኖቹ ፍርሀት አላስደነቀኝም::

አዲስ አበባ በመጣሁ ከጥቂት ቀናት በኋላ  የኢጣልያ ሆስፒታል ወደሚባለው ቦታ ሔድኩኝ:: በዚያም ለብዙ አመታት የሆስፒታሉ ሀላፊ የነበረ ጓደኛዬን ለመገናኘት ነበር:: በአምቦ መንገድ ላይ በሚገኘው አሁን በጣልያኖች እጅ በሆነው የስዊድን ሚሲዮን ማአከል አጠገብ ደርሼ ነበር:: ማአከሉ ከሆስፒታሉ ጎን ነው የተሰራው::

በድንገት በግራ በኩል ካለው ጉድጓዳ ስፍራ ጥይቶች እያፏጨ ይመጡ ጀመር:: በማአከሉ ግንብ ጀርባ የጣልያኖቹ አውቶማቲክ መሳሪያም መልስ ይሰጥ ጀመር:: ለማሰብ እንኳን ጊዜ ሳለገኝ በሁለቱ ተኩስ ልውውጥ መሀል መሆኔን አወቅሁ:: ከአንድ ጦርነት ወደ ሌላ ተሸጋገርኩኝ:: ያ ሁሉ ተብሎና ተደርጎ በመጨረሻው ህይወቴም ሊያልፍ ነው ማለት ነው::

በኋላ  አንድ የኢጣልያ መኮንን እየተሳበ መጥቶ አፌን ከፍቼ አዛው ባልቆም እንደሚሻለኝ ይልቁኑ ተከትየው ከሚሸኑ ግንብ ጀርባ እንድጠለል ጮኸብኝ:: ለሶስት ሰአታት ቁጭ ብዬ የተኩስ ድምፅና የጥይቶችን ፉጨት ሳዳምጥ ቆየሁ:: የጣልያኖቹ ካምፓኒ ወጥቶ ለማጥቃት ዝንባሌም አላሳየም ምክንያቱም ከተኩሱ በመገመት የሽፍቶቹ ቁጥር ከሀምሳ በላይ ይሆን ነበር::

በአዲስ አበባ ውስጥ ምቾት ባይኖረውም ለአምስት ሳምንታት ቆይታ ካደረግሁ በኋላ  ከተማውን እንድለቅ ተገደድኩ:: ጣልያኖቹ በግልፅ ስዊድናዊ የሚባል ሰው ማየት እንደማይፈልጉ ነው የነገሩኝ::

ያለኝን ነገር በሙሉ በሁስት ሻንጣዎች አሽጌ ለዘጠኝ አመት የሰራሁበትን ከተማ ለቀቅኩ:: በዚህ ከተማ የተዳርኩበት ቤት የሠራሁበት እና ሁለት ልጆች ያፈራሁበት ነበር:: ተመልሼ የማላያቸው ብዙ ጓደኞችም ነበሩኝ:: በጣም የለመድኩት ሀገር ቋንቋቸውን እንደራሴ አድርጌ የምናገረውና እየወደድኩዋቸው የመጣሁት ተወላጆቸ ለአድሜ ልክ ላጣቸው ነው:: የነበረኝን ገንዘብ በሙሉ ያፈሰስኩበት የእርሻ ቦታዬም ስነፋስና ሰውሀ ሊቀር ነው::

በጣም ያሸበረኝ ነገር ግን የወንድሜ ጉዳይ ነበር ምንም ላደርግለት የምችለው ነገር አልነበረም፡፡ በዚያን ጊዜ ያላውቅሁት ነገር ከሁለት ወራት በኋላ በርግጠኛነት እንደተረዳሁት ለዘላለም እንደማላየው ነው፡፡ ከወንበዴዎች በተተኮሰ ጥይት ህይወቱ አልፏል፡፡ ምናልባትም በግንቦት ወር መጨረሻ አካባቢ ነበር፡፡ ብቻውን ተረሰቶ ቀርቶ ቁጭ ባለበት ሰርአትና ህግ በሌለበት በአርሲ ያለምንም ማምለጫ እርስ በእርስ በሚዋጉ ጎሳዎችና በጨካኝ ወንበዴዎች ተከቦ ነበር፡፡

እኔ ለንት ጊዜ ነው የሞትን ነጭ አይኑን ያየሁት ግን ሕይወቴን እጅና እግሬን ይዤ ያመለጥኩት? ነገር ግን ዋልደማር መሞት ነበረበት ወይ? አጋጣሚ?

እይሆንም! በፍፁም፡፡ በአጋጣሚ ለማለፍ የሰው ህይወት በጣም ውድ ነው፡፡ ለሁሉም ለሚሆነው ነገር ሁሉ ትርጉም ይኖረዋል፡፡ ይህ አመለካከትና በቅፅበት መሞቱ ለኛ ለምንወደው ለሀዘናችን ማፅናኛና ብሩህ የሆነ የሱ ትዝታ እንዲኖረን ይረዳናል፡፡

በግብፅ በፖርት ሰይድ በአንድ ካፌ ቁጭ ብዬ ወደ ሀገሬ የሚወስደኝን ኮምፒየኝ የተባለ ጀልባ ስጠብቅ አንድ ሰው በአማርኛ ሲያናግረኝ ሰማሁ፡፡ ጀልባው አንደነዳጅ ሀይል የሚጠቀምበትን የድንጋይ ከሰል እየሞላ ነበር፡፡ በአማርኛ ያናገረኝ ሰው የንጉሡ ሾፌር መሆኑን ሳውቅ በጣም ነው የተገረምኩት፡፡

የተላከው ከአቴጌዋ ነው፡፡ አቴጌዋ ከእየሩሳሌም ተመልሰው ወደ ኢንግላንድ እየሄዱ ነበር፡፡ በሚገርም ሁኔታ የኔን መምጣት ሰምተዋል እና መንገዴን እንዴት ብየ እንደምቀጥል ማወቅ ይፈልጋሉ፡፡ እኔም በምሄድበት ጀልባ ስለሚሄዱ ጀልባው ውስጥ መገናኘት የምንችል ከሆነ ብለው ጠይቀዋል፡፡

በተከተሉት አምስት ቀናት ከአቴጌዋ ጋራ በየቀኑ እንገናኝ ነበር፡፡ በጣም የወዳጅነት ስሜት ያሳያሉ በርግጥም አቢሲኒያ ውስጥ ስላለው ሁኔታ ደግሞ ማወቅ ይፈልጋሉ፡፡ ከብደት ከመቀነሳቸውና ከሚታይባቸው የሀዘን ስሜት በመነሳት በቅርቡ ያሳለፉት ወራት ከባድ እንደሆነባቸው ያስታውቃል፡፡



# ምዕራፍ ሀያ አምስት

## የውድቀቱ መንስኤዎች

የአቢሲኒያዋ አዲስ አበባ ለአቷ እየተቃረበ ነበር፡፡ በአለም ውስጥ የመጨረሻዋ የፊውዳልና ያልሠለጠነው ሀገር ዋና ከተማ ውስጥ ቅጥ ያጣ የውጭ ሰዎች ጥላቻ አንደ ድንገተኛ ጎርፍ ይገነፍል ነበር፡፡ በያሉበት ሆነው የውጭ ሰዎች ጣልያኖች ላይ ርግማንና ጥላቻ ያወርዱ ነበር በጎን ደግሞ በሽብር ተውጠው ጣልያኖቹ መጥተው እነዚህ ራሳቸው ያስታጠቋቸው የአቢሲኒያ ሰዎች ካደረጉባቸው ከበባ እንዲያድኗቸው ይፈልጋሉ፡፡

በመስከረም ሀያ ሶስት የኢጣልያው መሪ ሙሶሎኒ በሚያዝያ ሀያ ሰባት ለመላው የኢጣልያ ህዝብ አዋጅ እንዲነገር ትዕዛዝ ሠጥቷል፡፡ ለላሳ ሚሊዮን የሚሆኑት ጥሪው የተደረገላቸው ጣልያኖች የሚከተለውን ታሪካዊ ንግግር አዳምጠዋል፡፡

“የአብዮቱ ጥቁር ሸሚዝ ለባሾች፤ መላው የኢጣልያ ወንዶችና ሴቶች፤ ከተራሮችና ከውቅያኖስ አድማሰ የምትገኙ ኢጣልያውያንና የኢጣልያ ወዳጆች፡፡ ስሙ፡፡ ማርሻል ባዶሊዮ የሚከተለውን የቴሌግራም መልከት አስተላልፎልኛል፡፡

‘ሚያዝያ 27 በአለር ሰአት እኔ በድል አድራጊው የኢጣልያ ሠራዊት ግንባር በመሆን አዲስ አበባ ገብቻለሁ’

ለኢጣልያ ህዝብና ለመላው አለም ጦርነቱ እንደላቀለት አስታውቃለሁ፡፡ ለኢጣልያ ህዝብና ለመላው አለም ሰላም እንደተመለረተ አስታውቃለሁ፡፡ አቢሲኒያ ኢጣልያ ነች፡፡ ብዛት ያላቸው የቀድሞው የይሁዳ አንበሳ ስርወ መንግስት ጎሳዎች በኢጣልያ ሶስት ቀለም ባንዴራ ስር በሰላም ለመኖርና ለመሥራት ፍላጎታቸውን በግልፅ አሳይተዋል፡፡ ያለቀላቸውና በሽሽት ላይ ያሉት

ባለባቶችና ራሶች ከዚህ በኋላ ምንም ሥልጣን የላቸውም፡፡ ወደ ቦታቸው የሚመልሳቸው ምንም አይነት ህይል በአለም ውስጥ የለም፡፡"

የሺ አመታት ዕድሜ ያለው ሀገርና መንግስት በፍጥነት ሊወድቅበት የቻለበት ምክንያት ምንድነው? ባለው የተራሮች አቀማመጥ፤ በተዋጊ ሰዎቹ ምክንያት እስከዛሬ ድረስ ከውጭ ከሚመጣ ጥቃት የተጠበቀ የሚመስል በተጨማሪም እስካሁን ድረስ ከውጭ ወራሪ ነፃነቱን ጠብቆ የኖረ አገር እንዴት በዚህ ባጭር ጊዜ በሰባት ወራት ውስጥ ይሸነፋል? ጄኔራል ስታራቼ ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ ወታደሮቹ ፊት ለፊት በመሆን እና ከአንድ ሜጀር ጋር በድምሩ ከአንድ ሺ አምስት መቶ ወታደሮች ጋራ አንድ ጥይት እንኳን ሳይተኮስባቸው ገና የንጉሡ ጦር ሳይሸነፍ ሁለቱም ከተለያዩ አቅጣጫ የአቢሲኒያ ጥንታዊ ከተማ የሆነችው ጎንደር እንዴት ይገባሉ? ማንስ ነው ይህንን ማስረዳት የሚችለው? ወይም ደግሞ ማርሻል ባዶሊዮ እንዴት አድርጎ ነው በመንገዱ ላይ መዋጋት የሚችሉ በአስር ሺ የሚቆጠሩ የአቢሲኒያ ወታደሮች በየጫካውና በየቁጥቋጦው ተደብቀው ምንም ተቃዋሚ ሳያጋጥመው ከአሸንጌ ሀይቅ ተነስቶ አዲስ አበባ የገባው?

ለዚህ ውድቀት መንስኤ መልሱ ጠላት ለረዥም አመት በጥንቃቄ መደራጀቱ ወይም በአደረጃጀትና በጦር መሳሪያ የባለይነት ስለነበረው ብቻ አይደለም፡፡ ለምክንያቱ ደግሞ የአቢሲኒያ ውስጣዊ ሁኔታ በተጨማሪ መመርመር አለበት፡፡

ታላቋ ኢጣልያ የቅኝ ግዛቶቹዋ እንጀራ እናት እንደሆነች አድርጋ ነው የምትቆጥረው፡፡ ድሃና በህዝብ ብዛት የተወጠረችው ኢጣልያ ከቁጥር በላይ ላደገው ህዝቧና ለምታመርተው ቁሳቁስ ገበያ ቅኝ ግዛት በጣም ያስፈልጋት ነበር፡፡ አቢሲኒያ እስከአሁን ድረስ በቅኝ ገዥዎች ሳትወረር የቆየች አገር ባላት የተፈጥሮ ሀብት የተነሳ ምክንያት ኖረም አልኖረም ኢላማ ትሆናለች፡፡ በድከመት የታቀደ ጥቃት በ1888 በአድዋ ተሞክሮ ከሽፏል፡፡ የሚቀጥለው ጥቃት በደንብ የታቀደና የተዘጋጀ መሆን ነበረበት፡፡ በአድዋ የደረሰው ሀፍረት መታጠብ ነበረበት፡፡

ስለዚህ ለአርባ አመት በሙሉ ጉልበት የተጠናከረና በደንብ የተደራጀ ዝግጅት ተጀመረ፡፡ ጣልያኖች በመላው አቢሲኒያ የተሠራጩ የንግድ ወኪሎች መሰረቱ፡፡ በወኪሉ ውስጥ የነበሩ ሰዎች ሰላይ፤ ሀኪምና የቴሌግራም ሠራተኛ ይጨምራል፡፡ የወኪሉ ዋና አላማ ከሰዎች ጋር ግንኙነት መመስረት፤



አሰተሳሰባቸውን መማር፤ ለወደፊት የሚጠቅሙ መረጃዎችን መሰብሰብ፤ ኢጣልያን ተወዳጅ ለማድረግ ስጦታ በአልኮሆል፤ የሚያብረቀርቁ የታደሱ የድሮ ጠመንጃዎችንና ገንዘብም በመስጠት ነበር፡፡ ሀኪሙ የታመሙ ድሆችን የነፃ ህክምና መስጠትም ከላይ ከተጠቀሰው ግብ ጋራ አብሮ የሚሄድ ነበር፡፡ ቴሌግራም ሠራተኛው በተራው የታየውንና ውጤታማ የሆኑ ሥራዎችን ሪፖረት መላክ ነበረ ሥራው፡፡

ለሰላማዊ ሥራ ነው ተብሎ አቢሲኒያ ውስጥ የሰዎች ቡድን በዚህ በዚያም ይላኩ ነበር፡፡ ነገር ግን ዋናው አላማቸው በጣም ጠቃሚ የሆኑ የአገሪቱን ቦታዎች ማወቅና ካርታ ማንሳት ነበር፡፡

ይህ በሙሉ ጉልበት የተደረገው የአቢሲኒያ ጥናት ውጤታማ ነበር ምክንያቱም ስለአቢ.ሲኒያ በጣም አዋቂ ኤክስፐርቶች ኢጣልያውያን ነበሩ እንደ ባሮን ፍራንቸቲ እንደ ፖላራ እንደ ታላሞንቲ ና ደ ካስትሮ የመሳሰሉት ሰዎችና ሌሎችን ጨምሮ፡፡

በተከተሉት እመታት ኤርትራና ሶማሊ በቁጥጥራቸው ስር ሆኑ ለከባድ ወይም ብዛት ላለው መጓጓዣ የሚሆኑ መንገዶች ተሠሩ፡፡

"ኢጣልያ ያገገመ በሽተኛ ነች" የአንድ ዲፕሎማት ንግግር ነበር በአዲስ አበባ፡፡ በካፖሬቶ ጊዜ የነበሩ ጣልያኖቹ አሁን ካሉት ጋራ ተመሳሳይ አይደሉም፡፡ የአለም ጦርነት ትምህርት ሰጥቷቸዋል የቀረውን ደግሞ ከሙሶሎኒ ተምረዋል፡፡

የቅኝ ግዛት ጦርነት በዚህ በጣም በተደራጀ ሁኔታ ተዘጋጅቶ አያውቅም፡፡ ሁሉም ነገር ተዘጋጅቷል፡፡ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ የኢጣልያ ወታደሮች መርከብ ላይ መውጣት ብቻ ነው ከዚያም ከኔፐልስና ከጀኖአ ተነስቶ በጥቂት ቀናት ውስጥ ደጋማው የኤርትራ ቦታዎች ድንኳንና አልጋ ተዘጋጅቶ የበሰለ ምግብ ወደ ሚጠብቃቸው ቦታ መውረድ ነው፡፡ ከጠመንጃና ከሁለት መቶ ጥይቶች በስተቀር ወታደሮቹ ሌላ ሸክም እንዳይዙ ተደርጓል፡፡ ሁሉም የሚያስፈልጋቸው ነገር በጭነት መኪና ይከተላቸዋል፡፡ የጎደለ ነገር የለም፡፡ በተቃራኒው ሁሉም ነገር ከሚገባው በላይ ነበር በተለይ በጦርነቱ የመጀመሪያ አጋማሽ ድረስ፡፡ በዚህ ግዙፍ በሆነ ድርጅት ምንም አይነት ስህተት አልነበረም፡፡

ምናልባትም በነሐሴና በመስከረም ወራቶች ከምፅዋ ወደብ በስተቀር፡፡ ለዚህ ትንሽ ወደብ ከመጠን በላይ ነው የሆነበት፡፡ በቀን ወደ ዘጠና መርከቦች ከጫኑት የጦር መሳሪያ ጋር የወደቡን እቃ ማራገፊያ ያጣብቡ ነበር፡፡ በዚህ

ጊዜ የሚፈለገውን ነገር በቀላሉ ማግኘት ወይም በሰርአት መጠበቅ አስቸጋሪ ነበር:: ጣልያኖቹ እራሳቸው አቢሲኒያ በዚያን ጊዜ ጥቂት ቦምቦች መጣል ብትችል ጥቂት ጀልባዎች ማስመጥ ብትችል ወደቡ ጠቅላላውን ዝግትግት ብሎ ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ያልቅ ነበር ይሉ ነበር::

ነገር ግን የአየር ሀይሉ የኢጣልያ ግንባር ቀደምና ውጤታማ መሳሪያ ነበር:: ለዚህ ምንም ጥርጣሬ የለም:: በአየር ላይ የሚወርደውን ቦምብ ነበረ አቢሲኒያኖች በጣም የሚፈሩት:: ጆሮ የሚበጥሰው ድምፅና የቦምብ ፍንጣሪው ከዚህ በፊት እንዲህ አይነት ነገር አይተው ለማያውቁ ሰዎች አሸባሪ የሆነ የሚያስፈራ ስሜት ነው የፈጠረባቸው:: ምንም አይነት መከላከያ መንገድ ባለመኖሩ ሽብሩ ደግሞ በዛው ልክ ይጨምራል::

በርግጥም የሠራዊቱ ወኔና ስሜት በዚህ መንገድ እንዲሰበር ሆኗል ለነገሩ በዝግታ ቢሆንም:: መሀል አገር ያለ ሰው እንኳን ማምለጥ የማይችልበት ሁኔታ ውስጥ እንደሆነ አድርጎ ነበር የሚሰማው:: በድንገት አውሮፕላን ይመጣና በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ቤቱ በሳት ይጋያል ሴቶችና ልጆች ይሞታሉ ወይም ይቆስላሉ:: እነዚህን ጭራቆች መከላከያ የለም:: ታዲያ ሰዎች ዘመድና ልጆች ራሳቸውን ለአደጋ አጋልጠው ወደ ጦር ሜዳ በመሄድ የጠላትን እንቅስቃሴ መግታት ካልቻሉ መታገሉ ጥቅሙ ምንድን ነው? ስለዚህ የልጆቻቸውንና የሚስቶቻቸውን ህይወት ለማዳን ንብረታቸውንም ለመጠበቅ እቅም ከሌለው ንጉሥ ስር ከመሆን በጉልበቱ ለላቀው ሀይል እጃቸውን ሰጡ::

ጣልያኖቹ ሰላይ አውሮፕላኖቻቸውንም በደንብ ነበር የተጠቀሙባቸው:: የአቢሲኒያችን ካምፕ በማግኘት የወታደሩን ቁጥር መገመትና የጉዞ አቅጣጫውን ማወቅ ይችሉ ነበር::

ያም ሆነ ይህ ጣልያኖቹ አብራሪዎቻቸው የጀግንነት ሥራ ሰሩ ብሉ ጉራ ለመንዛት በቂ ምክንያት የላቸውም:: እንዴት ነው በአየር ላይ የሚቃወማቸው አንድ ጠላት እንኳን ሳይኖር ስለ ጀግንነት የሚወራው? ፓይለቶቻቸው ልምድ የሌላቸው ለመሆኑ ኢላማቸውን የሚስቱት ቦምቦች ወይም ያለምንም ስሌት ዝምብለው የሚጣሉት ቦምቦች ምስክር ናቸው::

አንድ ጊዜ ዳባት ውስጥ ቆሞ የነበረ የአቢሲኒያ አውሮፕላን በሁለት የኢጣልያ ቦምብ ጣዮች ይታያል:: ከአጭር ከፍታ ሆነው ሰላሳ ቦምቦች ቢጥሉም ይስቱታል:: ከዚያ ወደ ምድር ዝቅ ብለው ያን ምስኪን የፈረንሳይ ፖቴዝ አውሮፕላን አውቶማቲክ መሳሪያ ያረበርቡበታል:: ያ አልሰራ ሲላቸው የእሳት ቦምብ በመጣል በመጨረሻ በእሳት ሲያነዱት ችለዋል::



የመርዝ ጋዝ በጣም ወሳኝ በሆነ ጊዜ እንደ መጨረሻ አማራጭ አድረገው ነበር ጣልያኖቹ የሚጠቀሙት:: እዝነው ሳይሆን የመርዝ ጋዝ ውድ ስለሆነ በነዚህ ያልሠለጠኑ ሰዎች ላይ በከንቱ እንዳይባክን ነው:: ምናልባትም ለተሻለ አጋጣሚ በአውሮፓ ለሚደረግ ውጊያ እየቆጠቡ ነበር:: አቢሲኒያውያን ደግሞ በአዲስ አበባ ገና አስቀድሞ ጋዝ ስለተባለ ነገር ትልቅ ፍራቻ ነበራቸው በተለይም አንድ የአዎሮፓ የጥርስ ሀኪም ስለ ጋዝ ፅሁፍ ከፃፈች በኋላ "ጋዝ" የሚለው ቃል ብቻ ሲጠራ ያንቀጠቅጣቸው ነበር::

ጣልያኖቹ ደግሞ በአውሮፕላን በመላው አገሪቱ ወረቀት በትነዋል:: በወረቀቱም የሚታወቁ የጋዝ አይነቶች፤ በውስጣቸው ስለሚገኙ ኬሚካሎች አሰቃቂ የሆነ ውጤታቸውና አንድ ሰው ደግሞ የጋዝ ማስክ በማድረግ ብቻ ራሱን መጠበቅ እንደሚችል የሚገልፁ ነበሩ:: ነገር ግን ለእያንዳንዱ አይነት ጋዝ በፅሁፉ ውስጥ የመጨረሻው ቃል የሚለው ለነዚህ ጋዞች የተጋለጠ ሰው ምንም አይነት የመዳን ተስፋ የለውም ነው::

እነዚህ በራሪ ወረቀቶችም ደጃዝማች አያሌው ባሉበት ግንባር መጥተው ነበር በዚያን ጊዜም ለመርዙ መፈወሻ የመሆኑ እምነት ሳጥን ሙሉ የሎሳንቲን መድሃኒት የመጣልን ጊዜ ነበር::

በወረቀቱ ውስጥ የተፃፈውን ነገር ወታደሮቹ ማወቅ ሲጀምሩ የነበራቸው ወኔ ሟሸሸ:: በግልፅ ምንም አይነት ጋዙን የሚቋቋም ነገር አለመኖሩን የተረዱት:: በጣም የተናደዱት ደጃዝማች ፅሁፉን የፃፈው ሰው መሰቀል አለበት አሉ እንደሳቸው አባባል የአማርኛው ፅሁፍ እንኳን ራሱ አስቀያሚ ነው የነበረው::

ስለ ፕሮፖጋንዳ ጥቂት ቃላት ለመጨመር:: ጣልያኖቹ የአቢሲኒያውያን ስነልቦናና አስተሳሰብ አስቀድመው በደንብ አጥንተውታል እና እንዴት አድርገው እንደሚያዳክሙትም ያውቃሉ:: በጦርነቱ ጊዜ ፓምፍሌት ወይም በራሪ ወረቀቶችን በየጊዜው ይበትኑ ነበር ሁልጊዜም በመሀል አገር ስለ ጦሩና ስለ ሕዝቡ ትክክለኛ ጊዜና ቦታ ጠብቀው ነበር የሚያደርጉት::

ጦርነቱ በተጀመረበት ሳምንት ውስጥ አቢሲኒያውያን የሚከተለው ወሬ ደርሷቸው ነበር::

በሀገራችሁ የሚኖር ባህታዊ ከአመት በፊት የሚከተለውን ትንቢት ተናግሮ ነበር "በ1928 በዘመነ ዮሀንስ ታላቋ ኢጣልያ የበለጠ ታላቅ ትሆናለች"

በአቢሲኒያ ዘመን አቆጣጠር እራት አመታት በተራ በተራ በአራቱ ወንጌላውያን ስም ይጠራሉ:: ማቲዎስ ማርቆስ ሉቃስ ዮሐንስ ተብለው::

ጳጉሜ ስድስት ቀን የሚሆነው ሁልጊዜ በዘመነ ዮሐንስ ጊዜ ነው፡፡ ይህ የባይዛንቲን አቆጣጠር ነው 1928 አመት ምህረት በአውሮፓውያን 1936 ነው፡፡

ብዙ ሰዎች ይህን ትንቢት የማይረባ ትርጉም የሌለው ጨዋታ ነው የሚሉት ነገር ግን አቢሲኒያውያን በባህታዊያን ያላቸውን ሙሉ እምነት ለተረዳ ሰው ጣልያኖች አቢሲኒያኖችን በደንብ አድረገው እንደሚያውቁ መገንዘብ ይችላል

እንግዲህ ጣልያኖች የአቢሲኒያውያንን ወኔ ለመሰበር የተጠቀሙባቸው እነዚህ ሁሉ ዘዴዎች ለአቢሲኒያ በፍጥነት መወድቅ በቂ ምክንያት ናቸው ካልተባሉ ታዲያ ትክክለኛው አገሪቱን ለውድቀት የዳረጋት በሀገሪቱ ውስጥ የነበረው ሁኔታ ምን ነበር?

## 1. በራስ መተማመንና ስንፍና

የአቢሲኒያ የራሳቸው ታሪክ ፀሀፊዎች ህዝቡን ከጥንት ጀምሮ ነፃ የሆነች አገር ነች እያሉ ሲነግሩ ነበር፡፡ ከነጮች ጋራ በተደረገው አንድ ጦርነት በ1896 (እኤአ) አስደናቂ ድል ተጎናፅፈዋል፡፡ እንግሊዝና ፈረንሳይ መሬታቸውን እንደሚመኙ ግን ደፍረው እንዳላጠቁ ያውቃሉ፡፡ ይህ ደግሞ በአለም ውስጥ ጥሩ ተዋጊዎች እንደሆኑና የማይሸነፉ እንደሆኑ አድርገው ራሳቸውን እንዲቆጥሩ አድርጎአቸዋል፡፡ ከአቢሲኒያውያን ጋራ ጥቂት ጊዜ ያሰላፈ ሰው አቢሲኒያውያን ኩሩና በራሳቸው የሚተማመኑ መሆናቸውን ማወቅ ይችላል፡፡

የዚህ ውጤት ደግሞ ስንፍና ነበር ለረዥም ጊዜ ሥር የሰደደም ነበር፡፡ ማን ነው የሚያጠቃቸው? እንደዛ ከሆነ ደግሞ አገርን ለመከላከል ምን አስጨነቃቸው ወይም በአውሮፓውያን ሞዴል ሠራዊት መገንባት ለምን ያሰፈልጋል? እያንዳንዱ አቢሲኒያዊ ከትውልዱ ተዋጊ ነው ጠመንጃውንም ሆነ ጎራዴውን ያለምንም ችግር በደንብ መጠቀም ያውቅበታል፡፡ ሥልጠና? ያ ምን ጥቅም አለው በተለይ ጣልያኖች በሰአታት ወስጥ ከፍተኛ ሽንፈት ሲደርሰባቸው ካዩ በኋላ ?

የነበራቸው በራስ መተማመን ሰሜት ደግሞ ከፍተኛ ደረጃ ደርሷል በተለይም ለአመታት ወደ ሀገሪቱ በሚመጡት አውሮፓውያን ሽንገላና አስመሳይ ሙገሳ በየጊዜው ሲደርግላቸውም ስለነበር፡፡



ይህንን አደጋ በደንብ ተረድተው የነበሩት የመጨረሻው ንጉሥ ነበሩ፡፡ ሠዎቻቸውን ለማስረዳትና ለማሰገንዘብ እና የነበረውን ሁኔታም ለማሻሻል ሞክረው ነበር፡፡ ነገር ግን አንድ ብቸኛ በሰውነት ደቀቅ ያለ ሰው ከአሥራ አምሰት ሚሊዮን ስንፍና የተሞላበት እንጎል ጋራ ምን ፋይዳ ማምጣት ይችላል? ከዚህ በላይ ንጉሡ ዘግይተው ነው የደረሱት፡፡ ወደኋላ በታዩት አመታት ሙከራቸው በሙሉ ተስፋ አስቆራጭ ነው የሚል ደረጃ እንደደረሱ ያሰታውቅ ነበር፡፡ ከአቅማቸው በላይ ነበር፡፡ ለማሻሻል የነበራቸውን ብርቱ ምኞትና ፍላጎት አጡ፡፡

## 2. የውስጥ እርስ በርስ ባላንጣነትና ደስተኛ አስመሆን

ሌላ ሰው ደስ የሚለውን መናገር ይችላል ነገር ግን አፄው በዚያን ጊዜ ተወዳጅ አልነበሩም፡፡ ለአብዛኛው ህዝብ የህገሪቱ መሥራች የሆኑትን የሚኒሊክን ዙፋን በጉልበቱ የወሰደ ሰው ነበሩ፡፡ የኦሮሞ ተወላጆች በሙሉ እፄ ምኒሊክ በነሱ ላይ የሾሚቸውን ልጅ ኢያሱን አልረሱም፡፡

በየአመቱ ግብር እየተጨመረ በገበሬዎች በኩል መማረርን አስከተለ፡፡ እንደ አውነቱ ከሆነ ንጉሡ የተለያዩ ግብሮች እንዲቆሙ ትዛዝ ቢሰጡም በየአቅራቢያው በሚገኙ ሹማምንቶች ትዛዙ ተቀባይነት ሰላልነበረው በአጅ እዙር ደካማ ማእከላዊ መንግስት ሆኖ በመታየቱ የመከፋትን ስሜት ፈጠረ፡፡ በእካባቢ ገዥዎች መሀከል የባላንጣ ስሜት በየጊዜውና አሁንም ድረሰ በአቢሲኒያ ይታያል፡፡ ከንጉሡ ፊት አንዱ ሌላውን ይኮንናል፡፡ ሰው ሆኖ መሳሳት ያለ ነገር ነው ንጉሡም ደጋግመው በስህተት ትክከለኛውን ወገን አልያዙም፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ እሳቸው ሲያደርጉት እንደነበረው በሥራቸው ባሉ ሰዎች መሀከል በነበረው ጠብ ውሰጥ ገብተው በችኮላ ውሳኔ ለአንዱ ወይ ለሌላው ወገን መሰጠት አልነበረባቸውም፡፡ ጉዳዩን በውል ለመመርመር በቂ ጊዜ አልነበራቸውም፡፡ ሰለዚህ በአማካሪዎቻቸው አማካኝነት ወደ ተሳሳተ እቅጣጫ ይሄዱ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ በየከልሉ ባሉ ሹማምንቶች ላይ የመከፋት ሰሜትን ቀሰቀሰ፡፡

## 3. ንግርትና ቅስና

ንግርት ለኢትዮጵያ ውድቀት ምክንያቶች ከሆኑት አንዱ ነው ብሎ መናገር ትንሽ አንግዳ ነገር ይመስላል፡፡ ያለውን ተፅእኖ ከመጠን በላይ ሳያጋንኑ ግን ተፅዕኖ አንዳለው ማመን ተገቢ ነው፡፡ አቢሲኒያውያን በንግርት የሚያምኑ ሰዎች ናቸው፡፡ በጊዜው በመላው ሀገሪቱ የተሠራጩ ንግርት ተናጋሪዎች የሚሉትን በቀላሉ የሚቀበሉና የሚፈሩ ነበሩ፡፡ *ትንቢት ወይም ንግርት ተናገሪዎች ደግሞ የተለያዩ ነበሩ አንደ የኦሮሞ ቃልቻ፣ ሼኮች፤ ደብተራና ጠንቋዮችን ጨምሮ፡፡

በቅርብ ጊዜ የተለያዩ ትንቢቶች በየጊዜው ይነገሩ ነበር ሁሉም ግን ተመሳሳይ አባባል ነበረባቸው፡፡

"ከውቅያኖስ ማዶ በሚመጡ ሰዎች ትልቅ ጦርነት ይመጣል፡፡ ቁጥራቸው እንደ አንበጣ ብዙ ነው፡፡ በአፍንጫቸው እሳት የሚረጩ ክንፍ ያላቸው ፈረሶች ሀገሪቱን በመላ ይወሩና ይወስዷታል፡፡ ረሃብና በሽታም ይከተላል፡፡ የወራሪዎቹ ዙፋንም የመጡበት ጎዳናም ከፍት ይሆናል፡፡ ይህ ሁኔታ ግን ብዙም አይቆይም ቢበዛ ሶስት ወር ወይም ሶስት አመት ብቻ ነው፡፡ አዲስ ንጉሥ የእውነተኛው እምነት ጠባቂና ድሃን የሚወድ ወደ ዙፋኑ ይወጣል ምክንያቱም ከውቅያኖስ ማዶ የመጣው ሀይል በጎረቤቱ ይሸነፋል"

ጦርነቱ እንደተጀመረ በመሃል አገር የሚኖረው የአቢሲኒያ ሰው ጦርነቱን አቢሲኒያኖች ያሸንፋት ይሆን ብሎ ራሱን እየጠየቀ ነበር፡፡ መልሶ መላልሶ የሚሰማው ደግሞ "አዎ ግን ይኸኛው ወይም ሌላኛው ትንቢት ተናገሪ በዚህ መንገድ ወይም በሌላ መንገድ ነው ያለው"

ወደ ጦር ሜዳ ሄዶ ጠላትን ለመምታት በነበራቸው ፅኑ ፍላጎት ሠራዊቱ ንግርት ነጋሪዎቹ ያሉትን ነገር አላሰተባቃውም ነበር፡፡ ነገር ግን ጦርነቱ እየተራዘመ ሲሄድና በጦርነት መሸነፍ ሲመጣ ከሰሟቸው ንግርቶቹ ስለመጥፎዎቹ ማሰብ ጀመሩ፡፡

---

*ትንቢት ተናጋሪዎችን በተመለከተ ገሪማ ታፈረ በመፅሐፋቸው (ጎንደሬ ቢጋሻው፣ ገፅ 5) በጊዜው በየአውራጃውና በየወረዳው የሚኖሩ ብለው የሃያ ሶስት ሰዎች ሰም ዝረዝር አስቀምጠዋል፡፡ ሰም ዝርዝሩ የእስልምናና የክርስትና እምነት ተከታዮችን ይጨምራል፡፡ እንደ ገሪማ አዘጋገብ ትንቢት ተናጋሪዎች ደግሞ ጣሊያኖቹ ላይ ጉዳት ማስከተሉን ይገልፃሉ ይህም ትንቢቱ አርበኞችን ስለሚያበረታታ ነበር፡፡



ከፍተኛ ስልጣን ያለው እያንዳንዱ ጦር አዛዥ ደግሞ ጦር ሜዳ ተከትሎት የሚሄድ ደብተራ፣ ሼኪ ወይም ቃልቻ ነበረው፡፡ እነዚህም በየጊዜው የሚጠየቁና ለምክር የሚፈለጉ ነበሩ፡፡ አንድ አዛዥ አዋቂ ሳያማክር ወይም ሳይጠይቅ ዘመቻ ወይም ጦርነት መጀመር አለዚያም ጠንከር ያለ እንቅስቃሴ አያደርግም ነበር፡፡ የደጃዝማች አያሌው ጓደኛ አንደመሆኔ ለዚህ ጉዳይ አብሬያቸው እሄድ ነበር፡፡ ትዛዝ ይሰጥና በመጨረሻው ደቂቃ ይሠረዛል፡፡ ለምን? ሲባል ዋናው አዋቂ ዲበኩሉ ይህ ሙከራ ውጤት የለውም ብሏል ነው መልሱ፡፡ ጉዞ እየተደረገ ድንገት መሀል ላይ ይቆማል ምክንያቱም ፊት ለፊት ከሚጓዙት አንዱ ወፍ መንገድ ላይ አይቷል፡፡ የተሠጠ ትዛዝ መልሶ ይሻራል ምክንያቱም የወፍ ጩኸት ወይም የኤሊ ድምፅ ተሰምቷል፡፡

ቄሶችን በተመለከተ በማጠቃለል ንጉሡ ከጠዋቱም ቢሆን የነበራቸውን የደከመ በራስ መተማመን መልሶ አዳከሞታል ማለት ይቻላል፡፡ የሀገሪቱ መሪ ተሃድሶ ለማድረግ በነበራቸው ዕቅድ መሠረትና ተጀምሮም በነበረው ሥራ የቤተክርስቲያንን ሐይል ለመገደብ ሞክረው ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት በቄሶቹ በኩል ተወዳጅነት አልነበራቸውም፡፡ ካቶሊክ ናቸው ወይም ፀረ ማርያም ናቸው እያሉ ሲጠሯቸው ነበር ሲከፋም አገሩን የከዳ ይሏቸውም ነበር፡፡

## 4. ደካማ አደረጃጀት

ከዚህ ቀደም አስቀድሞ እንደተጠቀሰው ለውድቀቱ አንደኛው ምክንያት በግልፅ በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ የነበረው የከፋ አደረጃጀት ነበር፡፡ እስከ መጨረሻው ሰአት ድረስ ይህ ለአንድ ሀገር ህልውና ወሳኝ የሆነ ሥራ ተረስቶና ተንቆ ነበር፡፡ ከወድቀቱ ከብዙ አመታት በፊት ሕዝቡን እየቦጠቦጡ በአውሮፓውያን መልክ የከብር ዘበኛ ጦር ያደራጁ ነበር፡፡ ይህ የሰልፍ ወታደር አዲስ አበባ ተቀምጦ መጠን የሌለው ገንዘብ የሚወጣበት ሲሆን በሌላ በኩል በመሐል አገርና በየዳር ድንበሩ የተሰማራው የመከላከያ ሠራዊት በጣም ተዳከሞ ነበር፡፡

ጣልያኖቹ በድንበራቸው ላይ ምሽጎችን በየተራ ሲገነቡና ወደ አቢሲኒያ ድንበር ውስጥ እየገቡ አስርና ከዚ.ያ በላይ ኪሎሜትር መሬት ሲወስዱ ኢትዮጵያኖቹ እጃቸውን አጣምረው የምፀት ሳቅ እየሳቁ

ይመለከቱ ነበር:: ደንበራቸውን ለመከላከል ሀሳቡ አልነበራቸውም በመሀል አገርም ቢሆን የወታደር ካምፕ መመስረቱ አልታያቸውም:: በመሀል አገር ወታደራዊ ካምፕ ቢኖር ደግሞ የአካባቢ ሹማምንቶችን ታዘዦች አድርጎ ሥርአትም ይፈጥር ነበር::

የተሾሙ አማካሪዎች በየተራ ይሀን ጉዳይ ቢያነሱም ንጉሡም ሆነ ሚኒስትሮቹ ነጮች ላይ ባላቸው የተፈጥሮ ጥርጣሬ ምክንያት ምክሩን አልተቀበሉም:: ምክር ሲሰጥ በደንብ ያዳምጣሉ ከተወያዩም በኋላ ምክሩ ጠቃሚ ነው የተለየ ነው ይላሉ አማካሪውንም ያመሰግናሉ እንዲህ አይነት ብልሃት እነሱ በጭራሽ እንደማያስቡትም ይናገራሉ:: ነገር ግን ደስተኛና የረካው አማካሪ አግሩ ሲወጣ የተናገረውን ነገር ረስተውታል ወይም ልዩ ነው የተባለውን ምክሩን ተቀብለው ርምጃ ላለመውሰድ ይወስናሉ:: አንዳንድ ጊዜ ፊት ለፊት ጮክ ብለው በማዛጋት አማካሪውን ያበሳጫሉ:: ጦርነቱ በር ላይ ሲደርስ ብቻ ነው በቂ ጠመንጃ ጥይትና መድፍ እንደሌላቸው ያወቁት የአየር መከላከያ አለመኖሩንም ጨምሮ:: ከዚያ በኋላ በግራም በቀኝም ማግኘት የሚችሉት ነገር ካለ መደራደር ይጀምራሉ::

የጀርመን የይሁዳዊና ኢትዮጵያዊ ዝርያ ያለበት የትንሽ መሣሪያዎች ሻጭ አውሮፓ ተልኮ ልምድ የሌለውን የጦር መሳሪያ እንዲገዛ ይሆናል:: ውጤቱ ለአቢሲኒያውያን የሚያሳፍር ነበር::

በጦርነቱ ጊዜ ዕቃ ማጓጓዣ ማደራጀት አስቸጋሪ ስለነበር ወታደሮቹ በየጦር ሜዳው ይራቡ ነበር:: አዲስ አበባና ደሴ ግን ከተራው ኢትዮጵያዊ የተዋጣው ሥጦታ መካዝናኖችን ያጣብብ ነበረ:: ምንም አይነት የህክምና እርዳታ የሌላቸው ብዛት ስላላቸው የጦር ክፍሎችስ ምን ይባላል? ለሁሉም ነገር ከውጭ የሚመጣ የቀይ መስቀል አምቡላንስ ይጠብቁ ነበር:: ራስ እምሩ ሀኪምና የህክምና ቁሳቁሶች እንዲላክላቸው ሲጠይቁ መንግስት የሰጠው መልስ በሱዳን በኩል የሚመጣ የእንግሊዝ አምቡላንስ መንገድ ላይ ነው የሚል ነበር:: የተባለው አምቡላንስ ሰላልመጣ ራሳቸው ለአርባ ሺ ሰዎች ሀኪም መሆን ነበረባቸው::

ለእንዲህ አይነቱ አሳዛኝ ደካማ አደረጃጀት ከመጀመሪያው ንጉሡ ራሳቸው ሀላፊነት እንዳለባቸው ነው:: ይህ በሙሉ የሳቸው ጥፋት



ነበር:: ጉዳዩን አቅልለውታል ወይም ከሥራቸው ያሉ ሰዎችን ስለማያምኑ ሀላፊነት መውሰድ እንዲማሩ እንኳን አልፈቀዱላቸውም:: በዙሪያቸው የተሰበሰቡ ባለሥልጣኖች ከጥቂቶቹ በስተቀር ሰነፍና የማይፈይዱ ነበሩ:: የንጉሡ ፍላጎት ምን እንደሆነ ባይታወቅም ይህ ነገር ደግሞ የራሱ ችግር ነበረው:: ለባለስልጣኖቹ ንጉሡ ራሳቸው የረሱት ነገር መሆኑን እንኳን እያወቁ በራሳቸው አነሳሽነት ጉዳዮችን መፈፀም አይታያቸውም:: ለትንሹና ጥቃቅን ነገር በሙሉ ንጉሡን መጠየቅ ነበረባቸው::

## 5. የአቢሲኒያ በፍጥነት መሸነፍ በሊግ ኦፍ ኔሽንስ መተማመናቸው ነው

አቢሲኒያ የሊግ ኦፍ ኔሽንስ አባልነት የፈለገቸው ከጎረቤቶቿ የሚደርስባትን ጥቃት ለመከላከል ነበር:: ያ መከላከያቸው ነበር እናም ተማምነውበት ነበር:: ምክንያቱም ለኢቢሲኒያኖች ይህን ያህል ወጭ የሚፈጅ ማህበር ሀያል ቢሆን ነው ብለው ያስቡ ነበር::

ወራቶች እያለፉ ሲሄዱም መግለጫዎች ከአንድ ኮሚቴ በሌላው ኮሚቴ ቢሰጥም ውጤት አልባ በመሆኑ ለኢትዮጵያውያን ቆይቶ ግልፅ የሆነው ነገር ምንም አቅም የሌለው ድርጅትን እንደጠባቂ አድርገው መተማመናቸው ነው:: ጥርጣሬ በተሰፋ መቁረጥ ተተካ ዘግይተውም ነው ከዚህ ከማያስተማምንና ብዙ ገንዘብ የሚጨርስ ድርጅት ጋራ ልክልክ ባይኖራቸው ራሳቸውን በተሻለ መንገድ መከላከል ይችሉ እንደነበር የተረዱት:: ይህን ድርጅት ባያምኑት ኖሮና ሀጉና ደንቡን ባይቀበሉ የራሳቸው የጦር መሳሪያዎች ራሳቸውን በሚመቻቸው መንገድ ይኖራቸው ነበር ስለዚህም ጣልያኖች ጥቃት ሳይጀምሩ ገና እየተደራጁ እያሉ ማጥቃትም ይችሉ ነበር:: ጠላት ራሱ እንኳን ቢሆን ማለትም ጣልያኖች ራሳቸው አቢሲኒያውያን ማሸነፍ ስላለመቻላቸው የጥርጣሬ ሃሳብ ነበራቸው::

ስለዚህ እንደአቢሲኒያኖች ግንዘቤ ዋናው የሸንፈታቸው ምክንያት ሊግ ኦፍ ኔሽንስ ነው::

ፍፃሜ

## ስለ ፀሐፊው ዶክተር ሃራልድ ናየስተሮም

ከዶክተር ቶማስ ፒ ኮልማን ሰሰ ሀራልድ ናየስተሮም ከፃፉት የአንግሊዘኛ ግጥም የተዘጋጀ



ዶክተር ሀራልድ ናይስተሮም

ሀራልድ ናየሰተሮም በጥር ወር በ1898 (እኤአ) በኤርትራ ውስጥ በለሳ በሚባል ቦታ በጭቃ ቤት ውስጥ ነው የተወለደው፡፡ ወላጆቹ ካርል ናይሰተሮምና አግነስ ናየሰተሮም በዚህ ቦታ ለአሰራ አምስት አመታት ኖረዋል፡፡ ቦታው እርስ በርስ በሚዋጉ ጎሳዎች የተከበበ ስለነበር ሁልጊዜም ፍርሃት ነበረ፡፡

የጭቃ ቤታቸው አንድ ከፍል ብቻ ሲሆን ወለሉም ከጭቃ ነው የተሰራው፡፡ ግድግዳው በጭቃና በአበት የተሰቀሰቀ ነበር፡፡ ፈጣሪን ሲያገሰግሉ ሰሰወጡ ምንም ጊዜ ቢሆን ድሃ ነን ብለው አስበው አያውቁም፡፡

ሃራልድ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ስዊድን ሲሄድ የሀያ ሁለት አመት ወጣት ነበረ፡፡ አናትየዋ ወጣቱን ኮሌጅ መግቢያ ደረጃ አሰኪደርስ ቤት ውስጥ ነበር ያሰተማሩት፡፡ ሰህከምና ትምህርትም ወደ ቤይሩት ሄዶ የሜዲካል ዲግሪ ተቀበሰ፡፡ ከዚያም ለተጨማሪ ሥልጠና ወደ ፈረንሳይ ከሄደ በኋላ  የህከምና ፈቃዱን በኒዮርከ ሰቴት ነበር ያገኘው፡፡ ወደ ስዊድን ሲሄድም ከወደፊት ባሰቤቱ ጋራ ተገናኘ፡፡ ከሳፍል ቫርመላንድ ነበር ሴትዮዋ የመጣቸው ከዚያ በኋላ  በሶስት ጦርነቶች ጊዜ ችግርና መከራም አብረው አይተዋል፡፡



አብረው ሲኖሩም ሁለት ልጆች ወልደዋል የመጀመሪያው ልጅ ወንድ ጋነር ተከታይዋ ደግሞ ሴቷ ብርጊታ ነበረች፡፡ ጋነር አሥራ ዘጠኝ አመት ሲሞላው የትምህርት ቤት ፈተናውን ከጨረሰ በኋላ የባህር ሐይል ውስጥ ተሰልፎ ጎትላንደ በምትባል መርከብ ተመድቦ ነበር፡፡

ሀራልድ ወደ ኢትዮጵያ በሄደበት ጊዜ ባሳቤቱ ማርታ ሳፍል ሰዊድን ውስጥ ነበረች፡፡ በዚያም አያለች የወንድ ልጃቸውን የጋነርን ሞት ትሰማለች፡፡ በመርከቢ ላይ በመድፍ ውስጥ አርሳስ ሲያስገቡ ፈንድቶ ከጋነር ጋራ ሶስት ሰዎች በቅፅበት ሕይወታቸው አልፏል፡፡ ሀራልድ በኢትዮጵያውያን ባህል መሰረት ለሶስት ቀናት በሀዘን ተቀመጠ ከዚያ በኋላ  ስለዚህ አሳዛኝ ቀን አንስቶም አያውቅም፡፡ ማርታ ደግሞ በስዊድን በራሷ መንገድ ነበር ሀዘኗን የገለፀችው በየአመቱ ከጋነር ፎቶ ፊት ሰፊት ሻማ ታበራም ነበር፡፡

በ1928 እኤአ ወደ ኢትዮጵያ ሲመሰስ የከብር ዘበኛ ሀኪም ሆነ፡፡ ከሰባት አመታት አገልግሎት በኋላ ጦርነት መጣ ችግርም ተከተሰ፡፡ ፋሺስቶቹ ምንም ርሀራሄም አልነበራቸውም፡፡ ደሀዋ ኢትዮጵያም እንደዚህ አይነት ሰቃይ ደርሶባት አያውቅም፡፡ በጦርነቱ ጊዜ ሀኪሙ ሀራልድ ከዳጃች አያሌው ብሩ ጦር ጋር በመዝመት ብዙ ፈተና እንደደረሰበት መፅሀፉ ያስረዳል፡፡

በደብረ ታቦር ከተማ ሀራልድ ለጣልያኖች እጁን ከሰጠ በኋላ የኢጣልያው ሜጀር ለሃራልድ ደብዳቤ እንደተሳከሰት ይነግረዋል፡፡ ባሰቤቱ ማርታ ሀራልድ በሕይወት ይኖራል በሚል ተስፋ በስዊድን በጣልያን ኤምባሲ በኩል ነበር የላከችው፡፡ ከዚያም ሜጀሩ በተጫማሪ ነገር ሀራልድን አስገረመው፡፡ ሜጀሩ ሮም ደውሎ ወደ ሰውዲን ከተሳሰፈ በኋላ  ሬድዮውን ሰሀራልድ በመሰጠት ያንተ ነው እንደፈሰግህ ተናገር ብሎ ከባለቤቱ ማርታ ጋር አገናኝቶታል፡፡ ሀራልድ በህይወቱ እንደዚህ ቀን ተደስቶ እንደማያውቅ ይናገር ነበር፡፡

ከጦርነቱ በኋላ  ሰዊዲን እንደተመሰሰ በሰፔይን የእርስ በርስ ጦርነት ተጀመረ፡፡ ሀራልድም በቀይ መስቀል ሥር ስፔይን ሄደ እንደገናም ጦርነት አየ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ፊንላንድ በነበረው ጦርነትም ከስዊድን በቀይ መስቀል ስር እንዲሄድ ሆኗል፡፡

በ1940 በስዊድን የሀኪምነት የሙያ ፈቃድ ተቀበለ እስከ 1945 ድረስ በሰዊዲን የህከምና ሙያ ሲሰራ ቆየ፡፡ በ1945 ወደ ትውልድ ቦታው ተመሰሰና በአድዋ በመንግስት ሥራ ሲሰራ ቆየ በኋላም በ1952 እኤአ በሚሲዮን ስር የሚፈልገውን ሥራ ጀመረ፡፡ ለአሥራ ሁሰት አመታት በአሰላ ሆስፒታል ያገለገለ ሲሆን የአሩሲ ጠቅላይ ግዛት የጤና ጥበቃ ቢሮ ሀላፊም ነበር፡፡

አሥራ ሁለት ቋንቋዎች የመናገር ችሎታው አለም አቀፍ ዝናን ነው ያተረፈለት። አዋሳ ቤት ሰርቶ በዚያው ጡረታ ወጣ። በኋላም በህመም ምክንያት ሴት ልጃቸው ቢርጊታ መጥታ ቤታቸውን ትተው ወደ ስዊድን ተመለሱ። በ1974 በህዳር ወር ስዊድን ሲገቡ አየጠበቋቸው የነበሩ መቶ የሚሆኑ ሰዎች በመዝሙር ነበር የተቀበሏቸው።

የመጨረሻ ቀን ታህሳስ 18 1974 እኤአ ነበር። ሕይወቱ ከማለፉ በፊት በቦታው የነበረ ጓደኛው የሰማው ቃል ነበረ። ቃሉን እንደተናገረም አረፈ።

"አባክህ የዳዊት መዝሙር ቁጥር አንድ መቶ ሰላሳትን አንብብልኝ"



## አስተያየት

መፅሐፍ ከመተርጎም መፅሐፍ መድረስ ይቀላል። በመጀመሪያ ይህን ጠቃሚ መፅሐፍ ለመተርጎም ጊዜያቸውን መስዋዕት ያደረጉትን ማመስገን እወዳለሁ። ከምርመር አንፃር መፅሐፉ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን መጠቆም እፈልጋለሁ። እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ስንወርሰው የቆየነው የሀገራችን ታሪክ ከገዢዎች አንፃር የተፃፈ እየሆነ ትክክለኛውን የህዝብ ተሳትፎ ማወቅ አልተቻለም ነበር። ይህ መፅሐፍ ከዚህ አኳያ ብዙ ለታሪክ ጥናት የሚጠቅሙ ነጥቦችን አስተላልፎልናል። ታሪካቸው እምብዛም ያልታወቀው ደጃዝማች አያሌው ከባዱን የጠላት ጦር ለመመከት የተጠቀሙባቸውን ስልቶች የሰው ነፍስ በከንቱ እንዳይጠፋ ያሳዩትን የአመራር ብቃት እንዲሁም ለተማረኩ የጠላት ወገኖች ያሳዩትን ደግነት አሳምሮ አቅርቦታል። በጣልያኖች በኩል የነበረውን የጦር መሣሪያ ዓይነትና ብዛት፤ ጣልያኖች ለ40 አመታት በተለያየ መልክ ወደ ኢትዮጵያ ሠርገው በመግባት ህዝቡን ባህሉንና የሀገሪቱን መልክአ ምድር በማጥናት ምን ያህል እንደተዘጋጁ፤ የመርዝ በምብ ጥቅም ላይ ማዋላቸውንና የምዕራባውያንን "አስቃቂ ኢሰብአዊ ሥልጣኔ" በሰፊው ዘርዝረውታል። በሌላ አንፃር የኢትዮጵያውያን ጀግንነት ለነፃነት የተከፈለውን የወገን ውድ ዋጋ፤ የአመራሩን ብቃት ማነስና ጦርነቱን ማቸነፍ ያልተቻለበትን ጉዳይ ከነምክንያቱ አቅርቧል። ጥቂት ገፆች በያዘ መፅሐፍ ከዚህ ቀደም ያልተጠቀሱ አዳዲስ የታሪክ ነጥቦች ቀርበውበታል።

ፋንታሁን ጥሩነህ (ዋሽንግተን ዲሲ)

በሞት ጉዞ ከቅዱስ ጊዮርስ ጋር በሚል ርዕስ የተፃፈውን መፅሐፍ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ተርጉመው ለአንባብያን ላቀረቡት ለዶክተር ገበየሁ ተፈሪና ለአቶ ደሳለኝ አለሙ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አገልፃለሁ።

መፅሐፉን በጥሩ አማርኛ መተርጎም ብቻ ሳይሆን፤ በመፅሐፉ መቅድም ላይ የፃፏቸው መግለጫዎችና አስተያየቶች አስተዋይነትና ሐቀኛነት አለባቸው። የመፅሐፉ ደራሲ ሐኪም ሐራልድ ናየስተሮም ከዳጃዝማች አያሌው ብሩ ጋር በመሆን ወደ ሽሬ ጦር ግንባር ሄዶ እንዳባጉናና ሰለህለሐ ላይ በተደረገው ጦርነት በዐይኑ ያየውን በጆሮው የሰማውን በእጁ ዳሶ ሰላከማቸው ቁስለኞች በየቀኑና በሰአቱ መዝግቦ ባቆየው ማስታወሻ መሠረት

የተፃፈ ታሪክ ስለሆነ፣ ለምናነበው ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለታሪክ ተመራማሪዎችም በጣም ጠቃሚ የሆነ የጥናት ምንጭ ሊሆን ይችላል።

ዝነኛው ደጃዝማች አያሌው ብሩ ያሳዩት የጦር አመራር ስልትና ዘዴ አስቀድመው ያዘጋጁት ስንቅና፣ ተዋጊዎቻቸው ለአውሮፕላን በምብ እንዳይጋለጡ ያደረጉት ጥንቃቄ በጣም ሊያስመሰግናቸው ሊያስከብራቸው ይገባል።

የጦር አዋጊዎቻቸው ፊታውራሪ ሽፈራው፣ ፊታውራሪ ነጋሽና ሌሎችም ያሳዩት ጀግንነት ዕፁብ ድንቅ ነው። በዘመናዊ የጦር ስልት የሰለጠነ፣ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ የታጠቀ፣ ብዛት ያለቸው ታንኮችና የወታደር መጓጓዣ፣ በምብ የሚጥሉ አውሮፕላኖች የነበረውን የጣልያን ወታደር የኢትዮጵያ አርበኞች በአልቢንና በምንሽር ግፋ ሲል በመትረየስ ተዋግተው እንዳባጉና ላይ እንዳሸነፉት ያነበበ ሁሉ አንገቱን ቀና ደረቱን ለጠጥ አድርጎ በኢትዮጵያውነቱ ሊኮራ ይገባዋል። በዚያን ጊዜ የተከሰተውን የአርበኞች ጀግንነት የሚገልፅ ፉከራ ሚከተለው ነው።

ትግራይ ላይ ገዳይ እንዳባጉና
የተለየ ለት ፈሪና ጀግና

ትግራይ ላይ ገዳይ ሰለህለሐ
ያ ሁሉ ጣልያን ሲጠማው ውሀ

ይህ መፅሐፍ ደጋግመው ቢያነቡት አይሰለችም። ያለፉት ወገኖቻችን ምን ያህል ጠንካራና አገር ወዳድ እንደነበሩ በግልፅ ያሳያል። በበላይ መሪዎች ሆነ በሕዝቡ በኩል ካለማወቅ የተነሳ ብዙ ድክመቶች እንደነበሩ መፅሐፉ ይጠቁማል።

ዶክተር ጥላሁን እንየው

ይህ መፅሀፍ የ1928ን የፋሺስት ኢጣሊያ ወረራና በሰሜን ምእራብ ግንባር የተፈፀሙትን ድርጊቶች በወፍ በረር ስንሰማ የነበረውን የወረራውን አስከፊነትና ጭፍጨፋ ለማንም ባልወገነ መልኩ የሚተርክ ሲሆን የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት የአመራሩን ደካማ የውጊያ ዝግጅትና ያልተመጣጠነ ትጥቅ በሚገባ ይገልፃል፡፡ ደራሲው የውጭ ዜጋ ቢሆንም ባህላችንን በሚገባ ስለሚያውቅ የብዙ ወራትን ውጊያ፣ መከራና የእለት በእለት ድርጊት በማይሰለችና አጓጊ በሆነ መልኩ ይገልፃል፡፡ ተርጓሚዎችም ይህንን የማይረሳ ታሪክ የኢትዮጵያ ህዝብ በአማርኛ እንዲያነበው ባማረ መልኩ በመተርጎማቸው መፅሀፉን በቀላሉ ተነባቢ እንዲሆን አድርገውታል፡፡

**ፋሲል ጊዮርጊስ**

መፅሐፍ ከመተርጎም መፅሐፍ መድረስ ይቀላል፡፡ በመጀመሪያ ይህን ጠቃሚ መፅሐፍ ለመተርጎም ጊዜያቸውን መስዋዕት ያደረጉትን ማመስገን እወዳለሁ፡፡ ከምርምር አንፃር መፅሐፉ እጅግ ጠቃሚ መሆኑን መጠቆም እፈልጋለሁ፡፡ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ስንወርሰው የቆየነው የሀገራችን ታሪክ ከገዢዎች አንፃር የተፃፈ እየሆነ ትክክለኛውን የህዝብ ተሳትፎ ማወቅ አልተቻለም ነበር፡፡ ይህ መፅሐፍ ከዚህ አኳያ ብዙ ለታሪክ ጥናት የሚጠቅሙ ነጥቦችን አስተላልፎልናል ...

**ፋንታሁን ጥሩነህ (ዋሽንግተን ዲሲ)**

መፅሐፉን በጥሩ አማርኛ መተርጎም ብቻ ሳይሆን በመፅሐፉ መቅድም ላይ የፃፏቸው መግለጫዎችና አስተያየቶች አስተዋይነትና ሐቀኛነት አለባቸው፡፡ ...

**ዶክተር ጥላሁን እንየው**

እውነተኛ ታሪክ፣ ሚዛናዊ ፅሁፍ፣ አገራቸውን ለመጠበቅ የዘመቱ ኢትዮጵያውያን የደረሰባቸውን መከራና ግፍ በስዕላዊ ሁኔታ የዘገበ ፅሁፍ፡፡ ሌሎችም ርዕሶች፣ ስለጥሬ ሥጋ አበላል አጀማመር፣ ስለ "አያሌው ሞኙ ሰው አማኙ" ታሪካዊ ምክንያት፣ አስደናቂ የከምባታ ተወላጆች ጀብድና ሌሎችም፡፡ መፅሐፉን ማንበብ ጀምረው ማቆም ያልቻሉ ዕንቅልፍ አጥተው ማደራቸውን የመሰከሩለት ፅሁፍ፡፡



Chibo Light Book
www.chibolight.com
Info@chibolight.com

ISBN 978-0-692-26893-3 $20.00
52000>
9 780692 268933